የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Education

የተቀናጀ የቅድመ - አንደኛ ደረጃ ትምህርት
መምህር መምሪያ

ደረጃ 2

አዘጋጆች:-

መ/ር ደረጀ ዳቃሞ

መ/ሪት ፌቨን ተመስገን

ወ/ሮ ዘላለም ቦጋለ

አቶ ታዬ ማሞ

አቶ ረሞዚ አብድረህማን

መ/ሪት ቤተልሄም ሀሰን

አስተባባሪ:-

አቶ ዑመር ኢማም

ዲዛይነር:-

መ/ር ደረጀ ዳቃሞ

አርታኢዎች:-

አቶ ያዕቆብ ሀብቴ

አቶ በሃይሉ ኮርማ

የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Education

የባለቤትነት መብት ©

የአዘጋጅው ባለቤትነት መብት የተረጋገጠ ነው። ያለትምህርት ሚኒስቴር ፈቃድ በባለቤትነት መብት ህግ ከተፈቀደው ውጪ የመምህሩን መምሪያ የተወሰነ ክፍል ወይም ሙሉ በሙሉ መልሶ ማሳተም፣ ማባዛት፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸት እና መልሶ በማንኛውም መንገድና ሁኔታ መጠቀም ለሚደርሰው የመንግሰትና የህዝብ ጉዳት በወንጀል ህግ ተጠያቂ ያደርጋል።

የመጀመሪያ ዕትም 2017 ዓ.ም

ትምህርት ሚኒስቴር

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ምስጋና

ይህ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህር መምሪያ ለክልሎች ዝግጅት በናሙናነት እንዲያገለግል ታስቦ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ከክልሎች ጋር በጋራ የተዘጋጀ ነው። በዚህ የመምህር መምሪያ ዝግጅት ላይ ውድ ጊዜያቸውን ለዝግጅቱ ጥራት ትኩረት በመስጠት በአዘጋጅነት፣ በገምጋሚነት፣ በአስተባባሪነት፣ በጥራት አስጠባቂነት እና በዲዛይን ሥራ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ላበረከቱ ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋና እናቀርባለን። በመቀጠል ሥራው በጥራት እና በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛውን ድርሻ ቢወስድም በገንዘብ ድጋፍ እና በማማከር ያላሰለሰ ጥረት ያደረጉ የሁል ጊዜ አጋሮቻችን አለም አቀፍ እና ሀገር በቀል ተቋማት ለሆኑት የአለም አቀፍ የህፃናት ተራድኦ ድርጅት (UNICEF)፣ አለም ባንክ (World Bank)፣ የኢትዮጵያ ስኩል ሬዲነስ ኢኒሼቲቭ (ESRI) እና ኢዱኬሽን ፎር ሰስተኔብል ድቭሎፕመንት (ESD) ያለንን ልባዊ ምስጋና በኢትዮጵያ ህፃናት ስም ማቅረብ እንወዳለን።

ማውጫ

ምስጋና iii
ክፍል 1፦ አጠቃላይ መረጃ 1
1.1. መግቢያ.. 1
1.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነትና አስፈላጊነት 3
1.2.1. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነት 3
1.2.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት አስፈላጊነት 3
1.3. የቅድመ-አንደኛ ትምህርት መርሆዎች 3
1.3.1. ሕጻን-ተኮር አቀራረብ 3
1.3.2. ጨዋታ-ተኮር ትምህርት 3
1.3.3. የተቀናጀ ሥርዓተ-ትምህርት 4
1.3.4. አካቶ ትምህርት 4
1.3.5. ሀገር በቀል ዕውቀት 4
1.3.6. ከዕድገታቸው ጋር ተስማሚ የሆኑ ተግባራት 4
1.3.7. የወላጆች/አሳዳጊዎችና የማህበረሰብ ተሳትፎ 4
1.3.8. ጤናማና ምቹ የትምህርት አካባቢ 5
1.3.9. ሁለንተናዊ ዕድገት 5
1.3.10. የተመጣጠነ አቀራረብ 5
1.3.11. የህጻናት ተከታታይ ምዘና 5
1.4. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ሥርዓተ-ትምህርት አጠቃላይ ዳሰሳ 5
1.5. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ-ትምህርት 6
1.6. የዕድገትና የመማር መስኮች 6
1.6.1. የቋንቋ መዳበርና ተግባቦት 6
1.6.2. የቅድመ-ሂሳብ መዳበር 6
1.6.3. አካባቢ ሳይንስ 7
1.6.4. የግልና ማህበረ-ስሜታዊ መዳበር 7
1.6.5. አካላዊ መዳበርና ጤና 7
1.6.6. የክወናና ዕይታ ጥበባት 7
1.7. የዕድገትና የመማር ብቃቶች 8
1.8. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህጻናት ባህርይ ገጽታ 8

1.9. ሀገር በቀል (አካባቢያዊ) ዕውቀትን መሰረት ያደረገ ትምህርት 9
1.10. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውህደት 10
1.11. የህጻናት ንቁ ተሳትፎ በትምህርት 11
1.12. ህጻን-ተኮርና በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ትምህርት 11
1.13. ህጻናትን ማዕከል ያደረገ ትምህርት ላይ የመምህራን ሚና 13
1.14. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የዕለት ተዕለት ተግባራት 13
1.15. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ባህሪያት 16
1.16. የህጻናት ዕድገትና ትምህርት ምዘና 17
1.17. የወላጅና አሳዳጊ ተሳትፎ በህጻናት ትምህርትና እንክብካቤ 19
1.18. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመምህር መምሪያ አጠቃቀም 19
1.19. የክፍል ጊዜ ድልድል 20
ክፍል 2፡- የመማር አውዶች.................... 21
አውድ 1፡ ማህበረሰብ 21
ሳምንት አንድ 23
ተግባር 1፡ መዝሙር.................... 24
ተግባር 2፡ ተረት 26
ተግባር 3፡ ውይይት 27
ተግባር 4፡ የተግባር ሥራ.................... 28
ተግባር 5፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ.................... 30
ተግባር 6፡ የመስክ ጉብኝት.................... 31
ተግባር 7፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ 32
ሳምንት ሁለት 34
ተግባር 1፡ ተረት 35
ተግባር 2፡ በሥራ መማር 37
ተግባር 3፡ የተግባር ሥራ 38
ተግባር 4፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ.................... 41
ተግባር 5፡ ውይይት.................... 42
ተግባር 6፡ መዝሙር.................... 42
ሳምንት ሶስት 44
ተግባር 1፡ ተረት 45
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ 46

ተግባር 3፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 48
ተግባር 4፡ ውይይት 49
ተግባር 5፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 50
ተግባር 6፡ መዝሙር........ 51
ተግባር 7፡ የመስክ ጉብኝት........ 52
ሳምንት አራት 53
ተግባር 1፡ ተረት 54
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ 55
ተግባር 3፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 58
ተግባር 4፡ ውይይት........ 59
ተግባር 5፡ መዝሙር........ 60
ተግባር 6፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 61
ተግባር 7፡ የመስክ ጉብኝት 62
ሳምንት አምስት 63
ተግባር 1፡ ተረት 64
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ 65
ተግባር 3፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 68
ተግባር 4፡ ውይይት........ 69
ተግባር 5፡ መዝሙር........ 70
ተግባር 6፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 71
ተግባር 7፡ የመስክ ጉብኝት 72
የአውድ 1 ማጠቃለያ ቼክ-ሊስት........ 73
አውድ 2፡ እንስሳት 74
ሳምንት ስድስት........ 76
ተግባር 1፡ መዝሙር........ 77
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ 79
ተግባር 3፡ ውይይት........ 81
ተግባር 4፡ ተረት........ 82
ተግባር 5፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 83
ተግባር 6፡ የመስክ ጉብኝት 86

ሳምንት ሰባት... 87
ተግባር 1፡ የተግባር ሥራ 87
ተግባር 2፡ ውይይት.. 90
ተግባር 3፡ ተረት.. 90
ተግባር 4፡ በሥራ መማር 91
ተግባር 5፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ.. 92
ተግባር 6፡ መዝሙር 92
ሳምንት ስምንት.. 95
ተግባር 1፡ መዝሙር.. 95
ተግባር 2፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ.. 96
ተግባር 3፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ... 98
ተግባር 4፡ ተረት.. 99
ተግባር 5፡ ውይይት.. 100
ተግባር 6፡ በፕሮጀክት መማር 101
ተግባር 7፡ ተረት 101
ሳምንት ዘጠኝ... 103
ተግባር 1፡ መዝሙር.. 104
ተግባር 2፡ በሥራ መማር... 105
ተግባር 3፡ የተግባር ሥራ 107
ተግባር 4፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ.. 108
ተግባር 5፡ ተረት 108
ተግባር 6፡ ውይይት 109
ተግባር 7፡ የመስክ ጉብኝት 110
ሳምንት አስር.. 111
ተግባር 1፡ የተግባር ሥራ 112
ተግባር 2፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ 114
ተግባር 3፡ በሥራ መማር... 114
ተግባር 4፡ ተረት 117
ተግባር 5፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ... 118
ተግባር 6፡ ውይይት 119

ሳምንት አስራ አንድ.. 121
ተግባር 1፡ መዝሙር 122
ተግባር 2፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ 124
ተግባር 3፡ የመስክ ጉብኝት... 126
ተግባር 4፡ ውይይት.. 127
ተግባር 5፡ ተረት.. 128
ተግባር 6፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ... 129
የአውድ 2 ማጠቃለያ ቼክ-ሊስት.. 130
አውድ 3፡ ሥራ 131
ሳምንት አስራ ሁለት.. 133
ተግባር 1፡ መዝሙር.. 133
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ 136
ተግባር 3፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ... 137
ተግባር 4፡ በፕሮጀክት መማር.. 139
ተግባር 5፡ ተረት.. 140
ተግባር 6፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ... 141
ሳምንት አስራ ሶስት.. 142
ተግባር 1፡ የተግባር ሥራ... 142
ተግባር 2፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ 145
ተግባር 3፡ መዝሙር 145
ተግባር 4፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ... 148
ተግባር 5፡ ተረት.. 149
ተግባር 6፡ በሥራ መማር... 151
ተግባር 7፡ ውይይት 151
ሳምንት አስራ አራት.. 152
ተግባር 1፡ መዝሙር.. 153
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ 154
ተግባር 3፡ በሥራ መማር... 156
ተግባር 4፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ... 157
ተግባር 5፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ... 157
ተግባር 6፡ ውይይት.. 158

ሳምንት አስራ አምስት........ 159

ተግባር 1፡ የተግባር ሥራ........ 160

ተግባር 2፡ መዝሙር 162

ተግባር 3፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 163

ተግባር 4፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 164

ተግባር 5፡ በፕሮጀክት መማር........ 165

ተግባር 6፡ የመስክ ጉብኝት........ 165

ተግባር 7፡ ውይይት 166

ተግባር 8፡ ተረት 167

ሳምንት አስራ ስድስት........ 168

ተግባር 1፡ መዝሙር........ 169

ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ 170

ተግባር 3፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 172

ተግባር 4፡ ተረት 174

ተግባር 5፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 175

ተግባር 6፡ በፕሮጀክት መማር........ 176

ተግባር 7፡ የመስክ ጉብኝጥ........ 176

የአውድ 3 ማጠቃለያ ቼክ-ሊስት........ 178

አውድ 4፡ ህዋ........ 179

ሳምንት አስራ ሰባት........ 180

ተግባር 1፡ ውይይት........ 180

ተግባር 2፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 181

ተግባር 3፡ መዝሙር........ 183

ተግባር 4፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 185

ተግባር 5፡ በሥራ መማር........ 186

ተግባር 6፡ ተረት 187

ሳምንት አስራ ስምንት........ 188

ተግባር 1፡ መዝሙር........ 189

ተግባር 2፡ በሥራ መማር........ 190

ተግባር 3፡ ተረት........ 192

ተግባር 4፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ 193

ተግባር 5፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 194
ተግባር 6፡ ውይይት........ 195
ሳምንት አስራ ዘጠኝ........ 196
ተግባር 1፡ መዝሙር........ 197
ተግባር 2፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 198
ተግባር 3፡ በሥራ መማር........ 201
ተግባር 4፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 203
ተግባር 5፡ ተረት........ 204
ተግባር 6፡ ውይይት........ 204
ተግባር 7፡ የተግባር ሥራ 205
ሳምንት ሃያ........ 206
ተግባር 1፡ መዝሙር........ 207
ተግባር 2፡ በሥራ መማር........ 208
ተግባር 3፡ ተረት........ 209
ተግባር 4፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 211
ተግባር 5፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 213
ተግባር 6፡ ውይይት........ 213
ተግባር 7፡ የተግባር ሥራ 214
ሳምንት ሃያ አንድ........ 215
ተግባር 1፡ መዝሙር........ 216
ተግባር 2፡ ተረት........ 219
ተግባር 3፡ የተግባር ሥራ........ 220
ተግባር 4፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 221
ተግባር 5፡ ውይይት........ 223
ተግባር 6፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 224
የአውድ 4 ማጠቃለያ ቼክ-ሊስት........ 225
አውድ 5፡ ውሃ........ 226
ሳምንት ሃያ ሁለት........ 228
ተግባር 1፡ ተረት........ 229
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ........ 230
ተግባር 3፡ ክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 231

ተግባር 4፡ ውይይት.. 232
ተግባር 5፡ መዝሙር.. 232
ተግባር 6፡ የመስክ ጉብኝት.. 233
ሳምንት ሃያ ሶስት.. 234
ተግባር 1፡ ተረት.. 235
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ 235
ተግባር 3፡ በሥራ መማር.. 237
ተግባር 4፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ.. 238
ተግባር 5፡ ውይይት.. 239
ተግባር 6፡ መዝሙር.. 240
ተግባር 7፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ.. 242
ሳምንት ሃያ አራት.. 243
ተግባር 1፡ ተረት.. 244
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ.. 246
ተግባር 3፡ በፕሮጀክት መማር.. 247
ተግባር 4፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ.. 248
ተግባር 5፡ ውይይት.. 248
ተግባር 6፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ.. 249
ተግባር 7፡ መዝሙር 251
ሳምንት ሃያ አምስት.. 252
ተግባር 1፡ ተረት.. 253
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ.. 253
ተግባር 3፡ በፕሮጀክት መማር.. 256
ተግባር 4፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ.. 256
ተግባር 5፡ ውይይት.. 257
ተግባር 6፡ መዝሙር 258
ተግባር 7፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ.. 259
ሳምንት ሃያ ስድስት.. 260
ተግባር 1፡ ተረት.. 261
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ.. 261

ተግባር 3፡ በሥራ መማር........ 263
ተግባር 4፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 264
ተግባር 5፡ ውይይት........ 265
ተግባር 6፡ መዝሙር........ 265
ተግባር 7፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 266
ሳምንት ሃያ ሰባት........ 267
ተግባር 1፡ ተረት........ 268
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ........ 268
ተግባር 3፡ በሥራ መማር........ 270
ተግባር 4፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 271
ተግባር 5፡ ውይይት........ 272
ተግባር 6፡ መዝሙር 272
ተግባር 7፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 274
የአውድ 5 ማጠቃለያ ቼክ-ሊስት........ 275
አውድ 6፡ ወቅቶች........ 276
ሳምንት ሃያ ስምንት........ 278
ተግባር 1፡ ተረት........ 279
ተግባር 2፡ መዝሙር 281
ተግባር 3፡ የተግባር ሥራ........ 284
ተግባር 4፡ ክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 285
ተግባር 5፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ 286
ተግባር 6፡ ውይይት 287
ሳምንት ሃያ ዘጠኝ........ 288
ተግባር 1፡ መዝሙር........ 289
ተግባር 2፡ ውይይት 291
ተግባር 3፡ የመሰክ ጉብኝት........ 291
ተግባር 4፡ የተግባር ሥራ........ 292
ተግባር 5፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ 293
ተግባር 6፡ ተረጥ........ 293
ተግባር 7፡ በፕሮጀክት መማር 294

ሳምንት ሠላሳ........ 295
ተግባር 1፡ መዝሙር........ 296
ተግባር 2፡ ተረት........ 297
ተግባር 3፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 298
ተግባር 4፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 299
ተግባር 5፡ ውይይት........ 300
ሳምንት ሠላሳ አንድ........ 302
ተግባር 1፡ ተረት........ 303
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ........ 303
ተግባር 3፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 305
ተግባር 4፡ ውይይት........ 305
ተግባር 5፡ መዝሙር........ 306
ተግባር 6፡ የመሰክ ጉብኝት........ 308
ሳምንት ሠላሳ ሁለት........ 309
ተግባር 1፡ ተረት........ 310
ተግባር 2፡ የተግባር ሥራ........ 310
ተግባር 3፡ የክፍል ውስጥ ጨዋታ........ 313
ተግባር 4፡ መዝሙር........ 315
ተግባር 5፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ........ 316
የአውድ 6 ማጠቃለያ ቼክ-ሊስት........ 317
አባሪ ገጾች........ 318

ክፍል አንድ

አጠቃላይ መረጃ

1.1 መግቢያ

የቀዳማይ ልጅነት ጊዜ የሰው ልጅ የዕድገት መሰረት የሚጣልበት ወሳኝ ወቅት ነው። የሰው ልጅ የህይወት ዘመን ሰኬት የሚጀመረው በዚህ ጊዜ ነው። የዘርፉ ምሁራን እድሜያቸው ከ4 እስከ 6 ዓመት ክልል ውስጥ ለሚገኙ ህፃናት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መስጠት አጠቃላይ እድገታቸውን ለማጎልበት አስፈላጊ መሆኑን ይስማማሉ። በኢትዮጵያ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ለረጅም ጊዜ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን ዘመናዊው የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ከመምጣቱ በፊትም በአብነት እና ቁርዓን ትምህርት ቤቶች አማካይነት ህፃናት መሰረታዊ የንባብና የህይወት ክህሎቶችን እንዲማሩ ይደረግ እንደነበር ድርሳናት ይነግሩናል። በሀገራችን ዘመናዊ ትምህርት ከመጀመሩ (ከ1908 ዓ.ም) በፊት ለኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ሥራ የመጡ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ዜጎች ህጻናትን የሚያገለግል የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት በድሬዳዋ ከተማ ይሰጥ እንደነበረም ታርክ ያሳያል። በ1960ዎቹም ከአውሮፓ የተቀዱ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት በሀገራችን እንዲተገበሩ የተደረገ ሲሆን ህፃናት የትምህርት እድል እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ይሁን እንጂ አሁንም የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተደራሽነት፣ ተገቢነትና ጥራት ጉዳይ ፈተና ሆኖ ይገኛል።

የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን ችግር ለመፍታት በርካታ እርምጃዎችን ወስዷል። ከእነዚህ እርምጃዎች መካከል ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የኦ-ክፍል (የአንድ ዓመት መርሃ-ግብር)፣ የህፃን ለህፃን ትምህርት፣ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የተፋጠነ የትምህርት ቤት ዝግጁነት እና የሶስት ዓመት ቅድመ መደበኛ የህፃናት ትምህርት ተግባራዊ ተደርጓል።

የትምህርትና ስልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት ግኝትም የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የአጠቃላይ ትምህርት አካል አለመሆኑን፣ ለግልና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት የተተወ መሆኑን፣ መደበኛ ትምህርት ራሱን ችሎ ሳይሆን እንደ ተጨማሪ መርሃ-ግብር መታየቱን፣ በየደረጃው በባለድርሻ አካላት በቂ ትኩረት አለማግኘቱን እና ራሱን የቻለ አስተዳደር የሌለው መሆኑን አመላክቷል።

ከዚህ በተጨማሪ ፕሮግራሙ ከአንደኛ ደረጃ ጋር ያለው ትስስር በግልጽ አለመቀመጡ የተጠያቂነት ችግር ማስከተሉን፣ ሥርዓተ ትምህርቱ አምዳዊና የጎንዮሽ ትስሰሩ በሚገባ የጠበቀ አለመሆኑን፣ በህጻናቱ ሁለተናዊ ዕድገት ላይ ትኩረት ያላደረገ መሆኑን እና ሥርዓተ ትምህርቱ የተቀናጀ ሳይሆን በአብዛኛው ለተወሰኑ የመማር ይዘቶች ማለትም ቁጥርና ቋንቋ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን ጥናቱ በግልጽ አሳይቷል።

ሌላው የመማሪያ ማስተማሪያ ቁሳቁሶችና ተግባራት የህጻናትን የዕድገት ደረጃ እና ባህል ያገናዘቡ አለመሆናቸው፣ በዘርፉ በቂ የሰለጠኑ መምህራን አለመኖራቸው፣ መምህራን በቂ የሆነ ስልጠና አለማግኘታቸው፣ መምህራን በሚያስተምሩበት ቋንቋ ቅድመ ስልጠናው አለመሰጠቱ እንድሁም መምህራን የሚያገኙት ደመወዝ አነስተኛ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ ፍልሰት መታየቱ ተግዳሮት መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል።

አዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ግብረ-ገብን፣ ሀገር በቀል ዕውቀቶችንና የ21ኛ ክፍለ ዘመን ክህሎቶችንና ሀገራዊ ጉዳዮችን የፕሮግራሙ አካል በማድረግ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቷል። በተጨማሪም ህጻናት የሙያ እና የቴክኖሎጂ ትምህርት እንዲተዋወቁ ይጋብዛል። ፖሊሲው የፈጠራ ሥራዎች እንዲበረታቱ፣ ቅንጅታዊ ውህደትና ጨዋታ-መር የማስተማርያ ዘዴ እንዲኖር፣ የመማር ውጤቶች ብቃት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ይደነግጋል። በ2015 ዓ.ም በተከለሰው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ እድሜያቸው ከ5 እስከ 6 ዓመት ለሆናቸው ሕጻናት የ2 ዓመት ትምህርት የነጻና የግዴታ እንዲሆን እና እድሜያቸው 4 ዓመት የሞላቸው ህጻናት ደግሞ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርትን በሌሎች አማራጮች እንደሚማሩ በግልጽ ተደንግጓል።

ይሁን እንጂ እድሜያቸው 4 ዓመት ለሆኑ ሕፃናት አገልግሎት መሰጠት የሚያስችሉ የሥርዓተ- ትምህርት ሰነዶች ባለመኖራቸው ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የ3 ዓመት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ከፍተኛ ፍላጎትና ጥያቄ ቀርበዋል። ከዚህ መነሻ የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመከተል የ4 ዓመት ህፃናትን ያካተተ የ3 ዓመት መርሀ-ግብር መርሀ-ትምህርት ተዘጋጅቷል። ይህንን መርሀ-ትምህርት መሰረት በማድረግ የ5 ዓመት ህፃናትን ታሳቢ ያደረገ፣ ተግባር-ተኮር/ህጻን-ተኮር እና ጨዋታ ላይ የተመሰረተ፣ ስድስቱን የእድገትና የመማር መሰኮችን በአውድ ያቀናጀ፣ ሀገር በቀል እውቀቶችን ያካተተ፣ ንቁ ተሳትፎን የሚያበረታቱ የማስተማርያ ዘዴዎችን እና ህፃን-ተኮር የምዘና ስልቶችን ያካተተ የተቀናጀ የመምህር መምሪያ ተዘጋጅቷል።

ህጻናት እጅግ የተለያዩ የትምህርትና የዕድገት ፍላጎቶች ያሏቸው በመሆናቸው ለዚህ ደረጃ የተቀመጡ የመማርና የዕድገት ውጤቶችን ታሳቢ ያደረገ ትምህርት ያስፈልጋል። ይህ የመምህር መምሪያም ዕድሜያቸው 5 ዓመት ለሆናቸው ህጻናት የተዘጋጅ ስሆን ስያሜውም የተቀናጀ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ደረጃ ሁለት የመምህር መምሪያ ይባላል።

1.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነትና አስፈላጊነት

1.2.1. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ምንነት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ዕድሜያቸው ከ4 እስከ 6 ዓመት ለሚሆናቸው ህጻናት የሚደረግ እንክብካቤንና የሚሰጡ መሰረታዊ እውቀትና ክህሎቶችን ያካተተ የትምህርት እርከን ነው። መርሀ-ግብሩ ጨዋታ ተኮር በሆነ የአቀራረብ ዘዴ የህፃናቱን ሁለተናዊ እድገት (አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜት፣ ስነ-ምግባር) በማጎልበት የተሟላ የሰብዕና እድገት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው። የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህፃናት የህይወት ዘመን ውጤታማነት የሚጀምርበት እና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ የሚሆኑበት ወሳኝ ምዕራፍ ነው።

1.2.2. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት አስፈላጊነት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም የትምህርት እርከን መሰረት ነው። የዚህ እርከን ትምህርት የሚያስፈልግበት ዋነኛ ምክንያት የህፃናትን ሁለንተናዊ (አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ማህበረ-ስሜታዊ፣ የቋንቋና ሞራላዊ) ዕድገት ማረጋገጥ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። በተጨማሪ ህጻናት ዛሬን መኖርና ዓለም የራሳቸው እንደሆነች መገንዘብ መቻል አለባቸው። ይህ ማለት ህጻናት አስፈላጊ እንክብካቤና ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው ማለት ነው። ነገ የተሻለና የበለጸገ ማህበረሰብ እንዲኖር ከተፈለገም ዛሬ ለህጻናት የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤና ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል። ጥራት ያለው የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ሌላይኛው አስፈላጊነት ህጻናትን ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

1.3. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሆዎች

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሕጻናት ዘላቂ ትምህርትና እድገት መሠረት የሚጣልበት ደረጃ ነው። መርሃ-ግብሩ ጥራት ያለውና ተደራሽነትን ያረጋገጠ መሆን ይጠበቅበታል። ጥሩ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚከተሉት ቁልፍ መርሆዎች ይኖሩታል። ህጻናትን በተገቢው ለመንከባከብና ለማስተማር እነዚህን መርሆዎች ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

1.3.1. ሕጻናት-ተኮር አቀራረብ

የሕጻናት ፍላጎትና ችሎታ ሊያሟሉ የሚችሉ ተግባራትን ማደራጀት ያስፈልጋል። ለህጻናት አካባቢያቸውን በማሰስ እንዲሁም በመሞከርና ንቁ ተሳታፊ በመሆን ተግባራትን በግል፣ በጥንድና በቡድን በማከናወን የሚማሩበትን ዕድል መፍጠር ያስፈልጋል። ይህም የፈጠራ ችሎታቸውንና የመማር ፍላጎታቸውን ለማሳደግ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል።

1.3.2. ጨዋታ-ተኮር ትምህርት

ጨዋታ የሕጻናት ቋንቋ ነው፡፡ ህጻናት ካልተጫወቱ በተገቢ ሁኔታ መማርና ማደግ አይችሉም፡፡ በመሆኑም እእምሯዊና ማህበራዊ እድገታቸውን ለማዳበር ያለውን ሚና በመረዳት ነጻ፣ መምህር መርና የተደራጁ/የተዋቀሩ ጨዋታዋችን በመጠቀም የሕጻትን የመማር ፍላጎት ሊያሳካ በሚችል መልኩ መተግበር ያስፈልጋል፡፡

1.3.3. የተቀናጀ ሥርዓተ-ትምህርት

ለቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተመረጡ ስድስት (6) የእድገትና የመማር መስኮችን (ቋንቋና ተግባቦት፣ መሠረታዊ ሂሳብ፣ አካባቢ ሳይንስ፣ ማህበረ-ስሜታዊ ዕድገት፣ ጤናና የአካል መዳበር እና ስነ-ጥበባት) ተቀናጅተው በቀረቡበት አውድ ከነባራዊ የሕይወት ልምድና ተሞክሮ ጋር በማዛመድ የሚማሩበትን እድል መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

1.3.4. አካቶ ትምህርት

ሁሉም ሕጻናት ያለምንም ልዩነት ጥራት ያለው የቅድመ-አንደኛ ትምህርት በእኩል ደረጃ ማግኘታቸውን ማረጋገጥና ብዝሃነት (ከባህል፣ ከቋንቋ፣ ግለሰባዊ ልዩነትና ወዘተ.) በክፍልና ከክፍል ውጪ እንደሚኖር በመረዳት ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

1.3.5. ሀገር በቀል እውቀት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ህጻናት በቋንቋቸውና በባህላቸውና ቅኝት የሚማሩበትና ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ እና ከራስ ወደ ቤት/አካባቢ የሚዘጋጅና የሚቀርብ ሂደትን ይከተላል፡፡ የሚቀርቡ ይዘቶች ህፃናቱ በአካባቢያቸው በሚያውቁት እና ቅርብ በሆኑ ቅድመ እውቀቶች ላይ በመመስረት የተቀመጠውን ብቃት መላበስ እንድችሉ መደረግ አለበት፡፡

1.3.6. ከእድገታቸው ጋር ተስማሚ የሆኑ ተግባራት

ከሕጻናት የእድሜና የእድገት ደረጃ ጋር የሚጣጣሙ ተግባራትን በማዘጋጀት ሁለንተናዊ እድገታቸውን ማለትም እእምሯዊ፣ ስሜታዊ፣ ማህበራዊና አካላዊ እድገታቸውን ሊያዳብሩ በሚችሉ ተግባራት ላይ ትኩረት ማድረግ፡፡

1.3.7. የወላጆች/አሳዳጊዎችና ማህበረሰብ ተሳትፎ

ወላጆች የህጻናት የመጀመሪያዎቹ የህይወት መምህራን በመሆናቸው የዚህ ደረጃ ትምህርት ያለእነርሱ ንቁ ተሳትፎ ዋጋ አይኖረውም፡፡ ስለዚህ በመማር ማስተማር ሂደት ወላጆች/አሳዲጊዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታትና ከማህበረሰቡ ጋር የሕጻናቱን ትምህርትና እድገት ለመደገፍ የሚያስችል ጤናማ ግንኙነትን ከማህበረሰቡ ጋር መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

1.3.8. ጤናማና ምቹ የትምህርት አካባቢ

ለሕጻናት ምቹ፣ ንጹህና ጤናማ የመማር አካባቢ እንዲኖር በማድረግ ደህንነትና ምቾት እንዲሰማቸው የሚያስችል የትምህርት አካባቢ መፍጠር ያስፈልጋል። የክፍል ውስጥ አደረጃጀቱ ጣሪያ፣ ግድግዳዎቹና ወለሉ በመማሪያ መጫዎቻ ቁሳቁሶች የበለጸጉ መሆን አለባቸው። የክፍል ውጭ አደረጃጀትም ለህጻናት አስፈላጊ ሁሉ ሁኔታዎች የተሟሉበት መሆን ያስፈልጋል።

1.3.9. ሁለንተናዊና ቀጣይነት ያለው እድገት

የልጆች ሁለንተናዊ እድገትና ትምህርት የሚጀምረው ከማህፀን ውስጥ ጀምሮ ሲሆን ይህም በሕይወት ዘመናቸውም ቀጣይነት ያለው መሆኑን በመረዳት የልዩ ፍላጎትን ጨምሮ በቀዳማይ የልጅነት ጊዜ ጥሩ የስሜት ማነቃቂያና የቅድመ እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል።

1.3.10. የተመጣጠነ አቀራረብ

በእውቀት፣ በአመለካከት እና በችሎታ እንዲሁም በንድፈ ሀሳብ እና በተግባር መካከል የተመጣጠነ አቀራረብ መከተል እና በተጨማሪም የክፍል ውስጥና የክፍል ውጭ ተግባራትን ለሕጻናቱ መማር በሚጠቀም መልኩ አመጣጥኖ ማቅረብ ያስፈልጋል።

1.3.11. የህፃናት ተከታታይ ምዘና

የሕጻናትን ሁለንተናዊ እድገታቸውንና የመማር ሂደትን በምልከታና መደበኛ ባልሆነ የምዘና ስልት በመጠቀም መከታተል፣ እንደማህደረ-ተግባር፣ የመከታተያ ቅጾችና የመሳሰሉትን በመጠቀም ለውጣቸውን መመዝገብ፣ ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለው-ግብረ-መልስ መስጠት የሚያስችል የግንኙነት ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

1.4. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ሥርዓተ-ትምህርት አጠቃላይ ዳሰሳ

አዲሱ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት በ3 የትምህርት ደረጃዎች የተዋቀረ ነው። ደረጃ አንድ እድሜያቸው 3 ዓመት ከ9 ወር እስከ 4 ዓመት ከ8 ወር ለሆናቸው ህጻናት የተዘጋጀ ሲሆን ይህም ለቀጣይ የልጆች እድገትና የመማር ደረጃዎች መሠረት ሆኖ ያገለግላል። በዚህ ደረጃ “ ስለ እኔ”፣ “ቤቴ እና ቤተሰቦቼ”፣ “ጎረቤቶቼ እና ትምህርት ቤቴ”፣ “ቀለማት”፣ “ጓደኝነት” እና “ጊዜ” የሚሉ የትምህርት አውዶች ተካተዋል። ደረጃ 2 ዕድሜያቸው ከ4 ዓመት ከ9 ወር እስከ 5 ዓመት ከ8 ወር ላሉ ሕፃናት የተዘጋጀ ሲሆን “ማኅበረሰብ”፣ “እንስሳት”፣ “ሥራ”፣ “ውኃ”፣ “ጠፈር” እና “ወቅቶች” በሚባሉ ስድስት የትምህርት አውዶች የተዘጋጀ ነው። ደረጃ 3 ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት ከ9 ወር እስከ 6 ዓመት ከ8 ወር ለሆናቸው ህጻናትን የተዘጋጀ ሲሆን በዚህ ደረጃ “ተክሎች”፣ “ቴክኖሎጂ”፣ “ባህል”፣ “ትራንስፖርት”፣ “ግብርና” እና “ሰላም” የሚባሉ ስድስት አውዶች ተካተዋል።

1.5. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ-ትምህርት

መርሀ-ትምህርት በአንድ የትምህርት ዓይነት ወይም መርሃ-ግብር የሚሰጡ ይዘቶችን፣ ዓላማዎችንና የማስተማር ዘዴዎችን ያካተተ ዝርዝር የይዘት ሠንጠረዥ የያዘ ሰነድ ነው። በዚህ መሠረት በዚህ ደረጃ የተዘጋጀው የቅድመ-አንደኛ ደረጃ መርሃ-ትምህርት ለየደረጃው የተለዩ ስድስት አውዶች፣ ስድስት የትምህርት መስኮችን፣ በየአውዱ መጨረሻ ከህፃናት የሚጠበቁ ውጤቶች፣ በሳምንት የተለዩ የትምህርት ይዘቶች፣ ሳምንታዊ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፣ የተቀናጁ ተግባራት፣ የማስተማሪያ ዘዴዎች፣ የመማሪያና መጫወቻ ቁሳቁሶችና በመጨረሻም የምዘና ስልቶች በዝርዝር የቀረቡበት ሀገራዊ ሰነድ ነው። ሰነዱም የመምህር መምሪያና የህፃናት መለማመጃ ደብተር ለማዘጋጀት መሠረትና መሪ ሆኖ የሚያገለግል ነው።

1.6. የዕድገትና መማር መስኮች

ለቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተቀናጅተው የሚሰጡ ስድስት የእድገትና የመማር መስኮች ተለይተዋል። እነዚህ መስኮች የሕጻናትን ሁለንተናዊ እድገት ለማበልጸግ የሚያስችሉ ሲሆን እንደእድሜ ደረጃቸው ህጻናት አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ የቋንቋ፣ ግብረ-ገባዊ እና ስነ-ጥበባዊ ክህሎታቸውን ለማዳበር በማቀናጀት እንዲቀርቡ ተደርጓል። እነዚህ የዕድገትና የመማር መስኮችን እንደሚከተለው ለመዳሰስ ተሞክሯል።

1.6.1. የቋንቋ መዳበርና ተግባቦት

ህጻናት ቋንቋን በመጠቀም ተሞክሮዎቻቸውንና ስሜቶቻቸውን መግለጽ እንዲሁም እርስ በርስ መግባባት ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪም ህጻናት በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍም የማዳመጥ፣ የመናገር እና የቅድመ ንባብ ክህሎቶቻቸውን ያዳብራሉ። ስለሆነም ይህ የዕድገትና የመማር መስክ በዋናነት የሚያተኩረው ማዳመጥና መናገር፣ ፊደላትን ማወቅ፣ የመጽሐፍ እውቀት፣ የህትመት ግንዛቤ፣ ድምጾችን መለየትና የተግባቦት ሥርዓት የሚሉት ላይ ነው።

1.6.2. የቅድመ-ሂሳብ መዳበር

ህጻናት በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ የሂሳብ ፅንሰ ሐሳቦችን ይማራሉ፤ የሂሳብ ሀሳቦችን እና ሂደቶችን ይመረምራሉ። አካላዊና ማህበራዊ አካባቢያቸውን በመመርመር ከቀዳሚ ልምዶቻቸው አዲስ ዕውቀትን በንቃት ይገነባሉ። ስለዚህ ይህ የመማር መስክ ቁጥሮችን በመቁጠር፣ በመጻፍ፣ በማወዳደር፣ በቅደም ተከተል በመደርደርና በመመደብ እንዲሁም በመለካት፣ ቀላል የማመዛዘን (ጊዜን፣ ገንዘብንና ቅርጾችን) ችሎታዎችን እና ቀላል የሂሳብ ስሌቶችን (መደመርና መቀነስ) ያሉ ክህሎትን ማዳበር ላይ ያተኩራል።

1.6.3. አካባቢ ሳይንስ

ህጻናት በዚህ የዕድገትና የመማር መስክ ስለአምስቱ የስሜት ሕዋሶቻቸውና ስለሰውነት ክፍሎቻቸው መማርና ግንዛቤ ማዳበር ይችላሉ። በተጨማሪም ህፃናት ስለተክሎች፣ እንስሳትና በአካባቢያቸው ስለሚሆኑ ቀላል ክስተቶች በዕይታና በቀላል እንቅስቃሴዎች በመማር አዎንታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩና በዕለት ተዕለት ህይወታቸው የቴክኖሎጂን አስፈላጊነት ለመማር እድል ይሰጣቸዋል። ስለዚህ ይህ የዕድገትና መማር መስክ በሰው አካል ክፍሎች፣ በአካባቢያቸው በሚገኙ እንስሳት፣ እጽዋት፣ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ክስተቶች፣ ራስንና አካባቢን በመንከባከብ፣ በጥንቃቄና ደህንነት ጉዳዮች፣ ቀላል ቴክኖሎጂን በማስገንዘብ ማህበራዊ ግንኙነቶች በመረዳት ዙሪያ ያተኩራል ።

1.6.4. የግልና ማህበረ-ስሜታዊ መዳበር

በዚህ የዕድገትና የመማር መስክ ህጻናት ራስን በመገንዘብ የራስን ማንነት መገንባት፣ ራሳቸው ለመቻል ጥረት ማድረግ እና ስሜቶቻቸውን መቆጣጠር የሚጀምሩ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ከሌሎች ጋር ውጤታማ በሆነ መንገድ መግባባትን፣ ሌሎችን ማክበርና መንከባከብን ይማራሉ። ስለዚህ ይህ የዕድገትና የመማር መስክ የራስ ግንዛቤ፣ የግል ነፃነት፣ የማህበራዊ ግንዛቤ፣ የሞራል እሴቶችን መገንዘብ፣ የተግባቦት ችሎታ፣ ለደንብ መገዛት፣ ውሳኔ የመስጠት ክህሎትና የሀገር ፍቅር ስሜት ለማዳበር የሚረዱ ዕውቀትና ክህሎቶች እንደ የደረጃቸውና እድሜያቸው ተካተው ቀርበዋል።

1.6.5. አካላዊ መዳበርና ጤና

ህጻናት ጥሩ ልማዶችን በማዳበር ንቁና ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን ማዳበር እንዲሁም መሠረታዊ የጤናና የደህንነት ጉዳዮችን በመረዳት ራሳቸውን መጠበቅን ይማራሉ። በተጨማሪም ስለስሜቶቻቸውና አካባቢያቸውን ለመመርመር የስሜት ህዋሳቶቻውን የመጠቀም ችሎታን ያዳብራሉ።ይህ የዕድገትና የመማር መስክ በጤና፣ በአመጋገብ፣ በአካላዊ ቅልጥፍና እድገት፣በቦታ ግንዛቤ፣ በአካል ብቃት እና በአካላዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኩራል።

1.6.6. የክወናና የእይታ ጥበባት

ይህ የዕድገትና የመማር መስክ ህጻናት የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና አካባቢያቸውን እንዲመረምሩና እንዲከታተሉ ይረዳቸዋል። በተጨማሪም ህጻናት በዚህ ደረጃ የተለያዩ የኪነ-ጥበባት፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የሙዚቃ፣ የታሪክ፣ ተረት እና እንቅስቃሴን በመጠቀም ሀሳባቸውንና ስሜታቸውን ለመግለጽ የፈጠራ ችሎታቸውን ይጠቀማሉ፤ እንዲሁም የሥነ-ጥበብ ተሞክሮዎችንና ሰብዓዊ እሴቶችን ያደንቃሉ። ስለሆነም ይህ የዕድገትና መማር መስክ በኪነ-ጥበባዊ ግንዛቤ፣ በፈጠራ አገላለጽ፣ በባህላዊ ቅርስ፣ ውበትን ማድነቅና ተገቢውን ዋጋ መስጠት ላይ ያተኩራል።

1.7. የዕድገትና የመማር ብቃቶች

የእድገትና የመማር ብቃቶች በሰርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንደሚያመላክተው ልጆች በሶስቱም ደረጃዎች በእድገትና የመማር ተግባራት ላይ ማግኘት የሚገባቸውን ተፈላጊ እውቀትን፣ አመለካከትን እና ክህሎቶችን ያመላክታል። እንደየደረጃውና እውዱ በዋና ዋና የብቃት ዘርፎች ሊደራጁ ይገባል። ስኬታማነት፣ ጥልቅ አሳቢነትና ችግር ፈቺነት፣ተግባቦት፣ የመማር ቀጣይነትና የምዘና መሳሪያነት የአጥጋቢ የመማር ብቃቶች መሰረታዊ ባህሪያት ናቸው። በተጨማሪም በዚህ የትምህርት ደረጃ ህጻናት መሠረታዊ የግል ክህሎቶች፣ የመማር ዝግጁነት፣ ችግር የመፍታት ክህሎት፣ በጥልቀት ማሰብና መመራመር፤ ተግባቦት፣ የፈጠራ ክህሎት፣ ትብብርን፣ በጋራ የመማርና የመስራት ክሂል፤ አመራርና ውሳኔ ሰጭነት፣ መሠረታዊ የዲጂታል ዕውቀትና ክህሎት፣ የአመራር እና ውሳኔ አሰጣጥ፣ ባህላዊ ማንነትና ዓለም አቀፋዊ ዜግነት ብቃቶችን ያዳብራሉ።

1.8. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህጻናት የባህርይ ገጽታ

የህጻናት የባህርይ ገጽታ የሶስቱም ዓመታት ቆይታ ውጤት ነው። ይህም ህጻናት ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ መሆናቸውን የሚለኩበት መነጽር ነው። በእያንዳንዱ ደረጃ ህጻናት የሚጠበቅባቸውን ብቃትና የዕድገትና የትምህርት ውጤት በማሟላት የራሳቸውን የባህርይ ገጽታ ይገነባሉ ተብለው ይጠበቃል። ስለሆነም ይህ የ3 ዓመት ቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ሲጠናቀቅ ህፃናት፡-

* የቅድመ ስሌት፣ የቅድመ ንባብና ጽህፈት ክህሎቶችን ማዳበር፣

* መሰረታዊ የቴክኖሎጂ ክህሎቶችን መጠቀም፣

* ከተፈጥሮ እና ከማህበረ-ኢኮኖሚ አካባቢዎች ጋር ጤናማ መስተጋብር መፍጠር፣

* የአካባቢያቸውን ባህላዊ ልምዶችን መገንዘብ፣ ማድነቅ እና መስተጋብር መፍጠር፣

* ከሌሎች ጋር ለመገናኘትና ለመተባበር የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ክህሎትን መጠቀም፣

*መሰረታዊ የሥነ-ምግባር መገለጫዎችን ማለትም ታዛዥነት፣ ታማኝነት (ሀቀኝነት፣ መልካምነት፣ እውነተኝነት)፣ እራሳቸውንና ሌሎችን መንከባከብና አክብሮትን ማሳደግ፣

* ሀሳቦችንና ስሜቶችን በኪነጥበብ፣ በሙዚቃ እና በእንቅስቃሴ መግለፅ፣

* የግል ንጽህና ደህንነት እና የአካባቢ ጽዳት ለመጠበቅ መሰረታዊ የጤና ህግጋትን ማወቅ፣

* በዝቅተኛ ደረጃ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ማከናወን፣

* የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለመማር አስፈላጊ የሆኑ ዕውቀትንና ክህሎትን መጠቀም።

1.9. ሀገር በቀል (አካባቢያዊ) እውቀትን መሠረት ያደረገ ትምህርት

የሀገር በቀል ዕውቀት እንደየአውዱና ደረጃው የተመጠኑ ባህላዊ ዕውቀቶች፣ ክህሎቶች፣ አመለካከቶች፣ ልምዶች እና እሴቶች ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው የሚተላለፉ ናቸው። ይህ እንደ ተረት፣ ባህላዊ ዘፈኖች፣ እንቆቅልሾች፣ የቃል ጨዋታዎች፣ እሴቶች፣ ደንቦች፣ ቁሳዊ ባህሎችና ስለተፈጥሮአዊ አካባቢዎች ዕውቀትን ጨምሮ የአገር በቀል የጨዋታ ልምዶችን ያጠቃልላል። እነዚህ የተዘረዘሩት ሀገር በቀል እውቀቶች በአምስት ሰፋፊ ምድቦች (በቃል የሚተላለፍ የሀገር በቀል ዕውቀት፣ በባህላዊ ልምዶች የሚተላለፍ የሀገር በቀል ዕውቀት፣ ቁሳዊ ባህል፣ የህዝብ ጥበባትና ሙዚቃ እና የአኗኗር ዘይቤ ወይም ትውፊት) ይመደባሉ። እነዚህ ዕውቀቶች ለህጻናት ተመጥነው ከቀረቡ የሚኖራቸው ዋና ዋና ጥቅሞች የሚከተሉትን ይጠቀሳሉ:-

- የሀገር በቀል እውቀት ወጪ ቆጣቢ የመማር ዘዴዎችን ያረጋግጣል፤
- እውቀትን ተደራሽ፣ ተገቢና ውጤታማ ያደርጋል፤
- የልጆችን ማህበራዊና ተፈጥሯዊ አካባቢን በተመለከተ ያላቸውን እውቀት ያሻሽላል፤
- ሕጻናትን ስለልዩነት አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ይረዳል፤
- በአካባቢው ተቀባይነትን ያገኙአዎንታዊ እሴቶችን እንዲያከብሩ ያደርጋል።

ስለሆነም ከላይ የተገለጹትን የተለያዩ የሀገር በቀል ዕውቀት ዓይነቶችን በመጠቀም ተቀናጅተው የቀረቡ የትምህርት መስኮችን በማስተማሪያ ዘዴነት መገልገል ከመምህራን ይጠበቃል። ለአብነት የሚከተሉትን አቀራረቦች ማየት ይቻላል።

- ከወላጆቻቸው ያዩዋቸውን ባህላዊ ጥበቦችንና እደ-ጥበባት ሥራዎችን እንዲሠሩ በማበረታታት፤
- በባህላቸው የሚገኙትንና በንድፍ የተዘጋጁ የእደ-ጥበብ ውጤቶች እንዲያቀርቡ በማድረግ፤
- በአካባቢው በሚከበሩ በዓላት ወቅት የሠሯቸውን በስጦታ መልክ እንዲሰጣጡ በማመቻቸት መከባበርን እንዲማሩ በማድረግ፤
- በአካባቢው ያሉ ታሪኮችን፣ አፈ-ታሪኮችን መምህራን፣ ወላጆች፣ የአካባቢው አርቲስቶች፣ ሽማግሌዎች እንዲነግሩዋቸው በማድረግ፤
- የአካባቢውን መዝሙሮች እንዲዘምሩ በማድረግና፣ቀላል የሆኑ የአካባቢ የሙዚቃ መሳሪያዎችን (ለምሳሌ ከበሮ) እንዲጫወቱ በማድረግ፤
- በአካባቢያው የሚዘወተሩ ልዩ ልዩ ውድድሮችን በጋራ እንዲጫወቱ በማድረግ መምህራን የህፃናቱን ትምህርት ተጨባጭ በማድረግ ማቅረብ ሳቢ እንደሚያደርገውና የክፍል ውስጥና ውጭ ተግባራትን አመጣጥኖ ለማስተማር የሚኖረውን ፋይዳ በመረዳት እንደሚጠቀሙት ይጠበቃል።

1.10. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውህደት (PPE Integration)

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውህደት የተለያዩ ይዘቶችን አንድ ላይ በማቀናጀት የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት የሚደግፍ የተቀናጀ አቀራረብ ነው። ውህደት የህጻናትን አዕምሯዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ እድገትን ጨምሮ የትምህርት ቤት ዝግጁነትን እውን የሚያደርግ ተመራጭ ሂደት ነው። በውህደት የማስተማር ሂደት የትምህርት ይዘቶች በተግባራት ውስጥ ተቀናጅተውና በአቀራረብ ዘዴዎች፣ ግብዓቶችና ምዘናዎች ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥተው ይቀርባሉ። ይህም ህጻናት በመዳሰስ፣ በመሞከር፣ በማብራራት እና በተግባር ልምምዶችን በአንድ ተግባር ውስጥ ልዩ ልዩ እውቀት፣ክህሎትና ልምድ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።

የተቀናጀ አቀራረብ ለህፃናት ሰፊ ክህሎቶችን እና ችሎታን እንዲያዳብሩ ከመርዳት ባሻገር የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ ግብር ብዝሃነትን እንዲያስተናግድ ይረዳል። ህጻናት ይዘቶቹ ተቀናጅተው በሚማሩበት ጊዜ የችግር መፍታት፣ ፈጠራ እና ወሳኝ የማሰብ ችሎታን በቀላሉ ያዳብራሉ። የተቀናጀ የትምህርት አቀራረብ ህጻናት በልዩ ልዩ ተግባራት ውስጥ እንዲሳተፉ፣ እንዲመራመሩ፣ ሀሳብ እንዲገልጹ፣ እንዲያብራሩና እንዲገመግሙ ማድረግን ይጠይቃል።

የቅድመ እንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚቀርብባቸው ሁለት የውህደት ዘዴዎች አሉ። እነሱም በአውድ ላይ የተመሠረተ ውህደት (Theme-based Integration) እና ሁለገብ ውሂደት (Interdisciplinary Integration for Standalone Competencies) በመባል ይታወቃሉ። የእኛ ሀገር የቅድመ እንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ ግብር የሚከተለው በዓለም ላይ ብዙ ሀገራት የሚተገብሩትን በአውድ ላይ የተመሰረተ ውህደት ነው፡ ፡ ይህ የውህደት ዓይነት መሰረት የሚያደርገው የተለያዩ የእድገትና የትምህርት መሰኮችን በአንድ አቀናጅተው ማቅረብን ነው። አውድ በተለያዩ ብቃቶች ላይ የተመሰረቱ ይዘቶችን አቀናጅተው ለማቀፍ ያገለግላል። ለአብነት፣ ‘ሁሉም ሰለ እኔ’ የሚለው አውድ ለዚህ ደረጃ ቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ከቀረቡ አውዶች አንዱ ነው። መምህራን ይህንን አውድ እንደ አቃፊ በመጠቀም የተቀናጁ ይዘቶችን እንዲያስተምሩ ይጠበቃል። ሳምንታዊ ብቃቶችን ለመተግበር እንደ ተረት፣ መዝሙር፣ እንቆቅልሽ፣ ጨዋታ፣ ጉብኝት፣ ሥራ፣ ውይይት፣ ፕሮጀክት እና የመሳሰሉት ዘዴዎች ይዘቶችን አቀናጅተው ለማቅረብ ሊጠቅሙ ይችላሉ።

ለአብነት፦

* በአንድ መዝሙር፣ ተረት፣ ጨዋታ ወይም ሌላ ተግባር ውስጥ ሶስትና ከዚያ በላይ (ቋንቋና ተግባቦት፣ ቅድመ ሂሳብ፣ አካባቢን መገንዘብና ሌሎች) ይዘቶችን በማቀናጀት ህጻናት እየተጫወቱ እንደሆነ ብቻ እየተሰማቸው እንዲማሩ ማድረግ ይቻላል።

1.11. የህጻናት ንቁ ተሳትፎ በትምህርት

በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የህጻናት ንቁ ተሳትፎ የህጻናትን የመማር ፍላጎትና ጉጉት ደረጃን የሚያመላክት ስሆን የትምህርት አቀባበላቸውንና ዕድገታቸውን ለማፋጠን ይረዳል፡፡ የህጻናት ንቁ የትምህርት ተሳትፎ ለተሻለ አዕምሯዊ፣ አካላዊ፣ ቋንቋ፣ ሞራላዊ፣ ማህበራዊና ስሜት ዕድገት ወሳኝ ነው፡፡ ተሳትፏቸውን ከፍ ከሚያደርጉ ዘዴዎች ወሳኝ የሚባሉት ተግባር-ተኮር ትምህርት መስጠት፣ በጨዋታ ማስተማር፣ ጤናማ ማህበራዊ ግንኙነት መፍጠር፣ ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን መረዳት፣ አርአያ መሆንና ምቹና ሳቢ የመማሪያ አካባቢን መፍጠር ናቸው፡፡

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ዋና ዋና ዓላማዎች የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ማረጋገጥ፣ ህጻናት ዛሬን መኖር እንዲችሉ ማድረግና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማዘጋጀት ናቸው፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት የህጻናትና የመምህራን ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ በጨዋታ መማር ዓላማዎቹን ለማሳካት ከሚረዱ ዘዴዎች አንዱ ከመሆኑም ባሻገር የህጻናትን አዕምሯዊ ዕድገት (የማወቅ ጉጉት፣ የፈጠራ ችሎታና ችግር የመፍታት ክህሎት መዳበር) ይደግፋል፡፡ ይህም ህጻናት ተጨማሪ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ፣ በርካታ ሀሳቦችን እንዲያመነጩ፣ እንዲተነብዩ፣ መላምቶችን እንዲያዳብሩ፣ መረጃን እንዲተረጉሙና ችግሮችን እንዲፈቱ እድሎችን ይፈጥርላቸዋል፡፡

1.12. ህጻን-ተኮርና በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ትምህርት

ጨዋታ ለህጻናት ቋንቋ፣ ልማድ፣ መብት፣ አሰራርና ተፈጥሮአዊ ሰጦታ ነው፡፡ ህጻናት በጨዋታ አማካኝነት አካባቢያቸውን ይፈትሻሉ፤ ይረዳሉ፤ እንዲሁም ይተረጉማሉ፡፡ ጨዋታ በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ የህጻናትን ሁለንተናዊ እድገት እውን ለማድረግ ወሳኝ የማስተማርያ ዘዴ ነው፡፡ አንዳንዶች ጨዋታ የህጻናትን አካዳሚክ ክህሎቶች ሊያሻሽል እንደማይችል በስህተት በመገንዘብ ከእድገት ጋር ብቻ ያያይዙታል፡፡ ህጻናት ለመግባባት፣ ለመተርጎም፣ ትርጉም ያላቸውን ፅንሰ-ሀሳቦች ለመፍጠር፣ መረጃን ለማደራጀት፣ አዳዲስ ሀሳቦችን ለመገንባትና ለማስተናገድ የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡፡

በጨዋታ ጊዜ የህጻናት እና የመምህራን ንቁ ተሳታፊ መሆን ውጤታማ መማርንና እድገትን እውን ለማድረግ ወሳኝ ነው፡፡ ህጻናት ራሳቸውን የመምራት እና በራሳቸው የመማር ተግበራትን (ነፃ ጨዋታ) የመጀመር እድል ሊኖራቸው ይገባል፡፡ መምህራን ደግሞ ህጻናት በራሳቸው ተነሳሽነት በሚጫወቷቸው ጨዋታዎች ውስጥ የመሳተፍ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በህጻናት ትምህርት የታቀዱ፣ ነጻና ድንገተኛ ጨዋታዎችንና ተግባራትን ማጣጣም ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ደረጃ ሊተገበሩ የሚችሉ የተለያዩ ህጻን-ተኮር ጨዋታዎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አዕምሯዊ ጨዋታዎች (ተግባራዊ ጨዋታ፣ እና የመርህ ጨዋታ) እና ማህበራዊ ጨዋታዎች (እንቅስቃሴ አልባ ጨዋታ፣ ለብቻ ጨዋታ፣ ትይዩ ጨዋታ፣ የቡድን ጨዋታ እና የትብብር ጨዋታ) በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ህጻናትን እያዝናኑ ለማስተማር ወሳኝ ናቸው።

የግል ሙከራዎች፣ የክፍል ውስጥ ጨዋታዎችና ተግባራት (መዝሙር፣ ተረት፣ እንቆቅልሽ፣ ውይይት)፣ ከክፍል ውጭ የሚደረጉ ጨዋታዎች፣ ጉብኝት፣ በፕሮጀክት ላይ የተመሰረቱ ተግበራት፣ በሥራ ላይ የተመሰረተ ትምህርት እና በማህበረሰብ ላይ የተመሰረቱ ተግበራት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ዋና ዋና ህጻን-ተኮር የማስተማሪያ ዘዴዎች ናቸው። በእነዚህ ሁሉ ተግበራት ህጻናት በራሳቸው ችግር እንዲፈቱና ተሳትፎዎቻቸውን እንዲያሳድጉ ተግባራትን እንዲያከውኑ ብቻ ሳይሆን ሀሳብም እንዲሰጡ ይደረጋል።

ህጻን-ተኮርና በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ትምህርት የሚከተሉት ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት ተብለው ይታሰባል።

* **በህጻናት የሚመሩ ተግባራት**፦ ህጻናት የራሳቸውን ተግባራት ሲመሩና ሲወስኑ የተሻለ ትምህርት ያገኛሉ። ስለዚህ መምህራን የሚያቀርቧቸው ተግባራት በህጻናት የሚተገበሩና የሚመሩ መሆን አለባቸው። ይህ አካሄድ የህጻናትን ፍላጎት ለማሟላትና ተግባሮቻቸውን ትርጉም ባለው መንገድ እንዲከታተሉ ለማድረግ ይረዳል።

* **ምርጫ**፦ ምንም እንኳን በተደራጀ ሥርዓተ ትምህርት በአብዛኛው የታቀዱ ተግባራት የሚከናወኑ ቢሆንም የህጻናትን ተሳትፎ ለማሳደግ በጨዋታና በተግባራት ወቅት ፍላጎታችውንና ምርጫቸውም ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል።

* **የህጻናት ቋንቋና አስተሳሰብ**፦ ህጻናት ሀሳባቸውን በቃልም ሆነ በምልክት ወይም በተግባር ሊገልጹ ይችላሉ። ስለዚህ ህጻናት ሀሳባቸውንና እይታቸውን በመረጡት ቋንቋና ተግባር መግለጽ እንዲችሉ የሚያግዙ ህጻን ተኮር ጨዋታዎችንና ተግባራትን ይሻሉ።

* **ማስተዋል እና መጠቀም**፦ በተግባር ተኮር ዘዴ ሰናስተምር የሚንጠቀማቸው የመጫዎቻ ቁሳቁሶች ህጻናት አዳዲስ ሀሳቦችንና ክህሎቶችን እንዲማሩ የሚያግዙ መሆን አለባቸው።

* **መልሰን ልንጠቀማቸው የሚንችላቸው ቁሳቁሶች**:- ህጻናት በመነካካት የሚማሩባቸው የመጫዎቻ ቁሳቁሶች ያስፈልጓቸዋል። ቁሳቁሶቹ በአካባቢያቸው የሚገኙ፣ ከህጻናት ባህልና ዕድሜ ጋር የሚጣጣሙ እና መልሰው መጠቀም የሚችሏቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል።

* **የመምህራን/የወላጆች ድጋፍ**:- በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመምህራንና የወላጆች ሚና ተግባራትን መምራትን፣ ማበረታታትን፣ ማመቻቸትንና መከታተልን ያካትታል። ይህንን በሚናደርግበት ጊዜ የህጻናትን የማሰብ፣ የመፍጠርና የመመራመር ፍላጎቻቸውንና ችሎታቸውን በማይገድብ መልኩ መሆን አለበት።

1.13. ህጻናትን ማዕከል ያደረገ ትምህርት ላይ የመምህራን ሚና

ህጻናት አዲስ ነገር የሚማሩት በመፍጠር፣ በመዳሰስ፣ በመሳተፍ፣ በመሞከር፣ በመመራመር እና በማሰላሰል ነው። በዚህ ሂደት የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን ንቁ የመማር አካባቢን ማዘጋጀት፣ መደገፍና መምራት ይጠበቅባቸዋል። ህጻናት በንቃት እየተሳተፉ እንደሆነ ማረጋገጥ፣ ምን እያደረጉ እንደሆነና እንዴት እየተማሩ እንደሆነ መከታተል እና ህጻናት ለራሳቸው ትምህርት ሀላፊነት እንዲወስዱ መምህራን ህጻናትን በማነሳሳትና አቅም በማሳደግ አጠቃላይ የትምህርት እንቅስቃሴውን መምራት ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን ህጻናት ተሳትፎቸውን እንዲያዳብሩ በማድረግ፣ እንቅስቃሴዎቻቸውን በመመልከት፣ ተግባራቸዉን በመመዝገብ እና እንዲያንፀባርቁ በማድረግ ንቁ ተሳታፊ መሆን አለባቸው፡ ፡ ህጻናት ራሳቸው በመረጡት እና በራሳቸው የሚመሩ የጨዋታ ተግበራትን መመልከት እንዲሁም በነዚህ የጨዋታ ተግበራት ውስጥ መምህራን በንቃት መሳተፍ፣መምራትና ማገዝ ይጠበቅባቸዋል። በአጠቃላይ መምህራን የመማሪያ አካባቢዎችን ማደራጀት (የተለያዩ ማዕዘናትን ማደራጀት)፤ የዕለት ተዕለት ተግባራትን በቅደም ተከተል ማደራጀት፤ ምቹና ደጋፊ የመማር አካባቢን ማደራጀት ፤ከህፃናት ጋር አዎንታዊ ግንኙነቶችን ማጎልበት፤ የህጻናትን ተሳትፎ እና ጽብረቃን ለማጎልበት አቅዶ መስራት፤ ህጻናት ያላቸውን ልምዶች በተለያዩ የዕለት ተዕለት ተግበራት ለማጠናከር መምህራን አቅደው መስራት ይጠበቅባቸዋል።

1.14. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም የዕለት ተዕለት ተግበራት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት በይዘት የተጨናነቀና በትምህርት ዓይነት የተደራጀ ባለመሆኑ የተለያዩ የዕለት ተዕለት ተግባራትን ያካትታል። ተግባራቶቹ ህጻን-ተኮር የማስተማር ዘዴን መሰረት ያደረጉ ሆነው በሁሉም ተግባራት ውስጥ የህጻናትና የመምህራን ሚና የጎላ ነው። ህጻናትን ከመቀበል እንስከ መሸኘት ድረስ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት (የቁርስ፣ የመተኛትና የእረፍት ጊዜን ሳያካትት) የሚከተሉት ናቸው።



ህጻናትን መቀበልና መሸኘት የሁል ጊዜ ተግባራት ናቸው። ከላይ የተጠቀሱት ቀሪዎቹ የዕለት ተዕለት ተግባራት እንደየአስፍላጊነታቸው በቀን ውስጥ ስድስቱ ብቻ) እየተመረጡ ይቀርባሉ። የእያንዳንዱ ተግባር ምንነትና ዝርዝር መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. ህጻናትን መቀበል፦

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ባህርያት ውስጥ አንዱ የመምህራንና የህጻናት ግንኙነት ነው። በዚህ ፕሮግራም የታቀፉ ህጻናት በራሳቸው ክፍል መጥተው ቁጭ ብለው የሚማሩ ባለመሆናቸው የወላጅና የመምህራን ቅብብሎሽ ያስፈልጋቸዋል። ለደህንነታቸው ሲባል ህጻናቱ ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡት በወላጅ ወይም በአሳዳጊ እገዛ ስሆን መምህራን እስከ ት/ቤቱ በር ድረስ ቀርበው ሊቀበሏቸው ይገባል። ይህ በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ለሚያስተምሩ መምህራን ዋነኛና ቀዳሚ ተግባር ተደርገው ይወሰዳል። የመቀበያ ጊዜ ህጻናት ነጻ ጨዋታዎችን የሚጫወቱበት፣ የባንዲራ ሥነ-ሥርዓት የሚያከብሩበትና ብሔራዊ የህዝብ መዝሙር የሚዘምሩበት እንዲሁም መምህራን የህጻናትን ጤንነትና ስሜት የሚከታተሉበት ነው።

2. የመዝሙር ጊዜ፦

ይህ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተለያዩ ይዘቶች በዜማ ታጅበውና ተቀናጅተው ለህጻናት መንፈሳቸውንና ፍላጎታቸውን መቀሰቀስ በሚያስችል መልኩ የሚቀርቡበት ጊዜ ነው። በዚህ ተግባር ህጻናት በሳምንት ውስጥ የተማሩትን የተቀናጀ ይዘት ሳይረሱ ለረጅም ጊዜ ማስታወስ ይችላሉ። በዚህ መምሪያ ውስጥ የተዘረዘሩ የሳምንት መዝሙሮች የሚቀርቡት የሚከተሉትን የድርጊት ቅደም ተከተል መሰረት ይሆናል።

* በቅድሚያ የህጻናትን የመዘመር ፍላጎት በማነቃቂያ ጥያቄዎች መቀሰቀስ
* በመቀጠል ሁል ጊዜ የዕለቱን መዝሙር ርዕስ ማስተዋወቅ
* አስቀድመው መዝመሩን ዘምረው አሊያም በቴፕ/ጂፓስ/ሞባይል ከፍተው ማስማት
* ህጻናት ስንኝ በስንኝ ተከትለው እንዲዘምሩ ማበረታታት
* ከህጻናት ጋር አብረው መዘመር ከዚያም ህጻናት ለብቻቸው በጋራ እንዲዘምሩ ማድረግ
* ሁሉም ህጻናት በትክክል መዘመር መቻላቸውን ማረጋገጥ
* በመጨረሻም የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና መንገር ያስፈልጋል።

3. የተረት ጊዜ፦

ተረት የፈጠራ ሥራ ሆነው የአንድን ማህበረሰብ አኗኗር፣ ባህል፣ ወግና እሴት ለትውልድ ማሻገር የሚያስችል ዘዴ ነው። በዚህ ዘዴ ሲማሩ ህጻናት የጊዜ ሂደትን፣ ታሪክን፣ የምክንያትና ውጤት ትስስርን እንዲሁም የተቀናጁ የትምህርት ይዘቶችን በቀላሉ ይገነዘባሉ፤ ያስታውሳሉም። ተረት በቃል፣ በንባብና በድራማ መልክ መቅረብ የሚችል ሲሆን የራሱ የሆነ ባህላዊ አተራረክ ዘዴ ያለው ነው። ዘዴው እንደየማህበረሰቡ ባህል የሚለያይ ቢሆንም ለምሳሌ በአማርኛ የሚቀርብ ተረት ቀጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ይከተላል።

አቅራቢ	ተቀባይ
ህጻናትዬ ተረት እንስማ አይደል?	እዎ!
እሺ! ተረት! ተረት!	የላም በረት ወይም የመሰረት!
በድሮ ጊዜ አንድ....... ነበር።	እሺ!
ከዚያ..............	እሺ!
ተረቴን መልሱ! አፌን በዳቦ አብሱ!	

4. የክፍል ውጭ ጨዋታ ጊዜ፦

ይህ ከክፍል ውጭ ደጅ ወይም ሜዳ ላይ የሚደረጉ አካላዊ እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ነጻና የታቀዱ ተግባራትን የሚያካትት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ህጻናት በግል፣ በጥንድና በትንሽና በትልቅ ቡድኖች እየተደራጁ ልዩ ልዩ የትንንሽና የትልልቅ ጡንቻዎች እንቅስቃሴን የሚፈልጉ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፤ ተግባራትን ያከናውናሉ። እንደ ጭቃ ማቡካት፣ አባሮሽና ሌሎች ጨዋታዎች የዚህ ጊዜ አካል ተደርገው ይወሰዳሉ።

5. የክፍል ውስጥ ጨዋታ ጊዜ፦

ይህ በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ በአብዛኛው የታቀዱ ትምህርታዊ ጨዋታዎችንና ተግባራትን የሚያካትት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ህጻናት በግል፣ በጥንድና በትንሽና በመጠነኛ ቡድኖች እየተደራጁ ልዩ ልዩ የትንንሽና የትልልቅ ጡንቻዎች እንቅስቃሴን፣ አዕምሯዊ ዝግጁነትንና ትኩረትን የሚፈልጉ ጨዋታዎችን ይጫዎታሉ፤ ተግባራትን ያከናውናሉ። እንደእንቆቅልሽ ያሉ ጨዋታዎች የዚህ ጊዜ አካል ተደርገው ይወሰዳሉ።

6. የተግባር ልምምድ ጊዜ፦

ህጻናት አዲስ ነገር ለማወቅ ካላቸው ጉጉት የተነሳ መጠየቅን፣ መመራመርን፣ መሞከርን፣ መነካካትን፣ ማዋሄድንና መለያየትን፣ መሰበርና መጠገንን እንድሁም ሀሳባቸውን በቃልና በተግባር መግለጽን ዋነኛ ምርጫቸው ያደጋሉ። ከዚህ መነሻ በዚህ ጊዜ ለህጻናት ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን በማቅረብ በግል፣ በጥንድ፣ በትንሽና በትልቅ ቡድን እየሆኑ እንዲተገብሩ ይደረጋል።

7. የውይይት ጊዜ፦

ውይይት ሀሳብ መለዋወጥንና መነጋገርን ያካትታል። ህጻናት በዚህ ጊዜ በተለያዩ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ በሰፊው ይነጋገራሉ። ይህ ተግባር የህጻናትን በራስ የመተማመን፣ የንግግር፣ ለአንድ ነገር ትኩረት መስጠትን፣ የማዳመጥና ሀሳብ የማፍለቅ ችሎታቸውን ያዳብራል።

8. በሥራ የመማር ጊዜ፦

ለህጻናት ትምህርት ቤት ሌላይኛው ቤታቸው ተደርጎ ይወሰዳል። በመሆኑም ህጻናት በዚህ ጊዜ በቤተሰባቸውና በማህበረሰባቸው ዘንድ የሚዘወተሩ የሥራ ዓይነቶችን መሰረት ያደረጉ ሥራዎችን በመስራት ልዩ ልዩ ክህሎቶቻቸውንና ችሎታቸውን ያሳድጋሉ ተብለው ይታመናል።

9. በፕሮጀክት የመማር ጊዜ፦

ፕሮጀክት ታቅደውና ታስበው ረዘም ላለ ጊዜ ህጻናት ፈትሸው፣ ጠይቀው፣ ተመራምረው፣ ሠርተውና አስተካክለው የሚያመጧቸው የግል፣ የጥንድና የቡድን ሥራዎችን ያካትታል። መምህራን የህጻናትን ሥራ የሚከታተሉ ሲሆን ህጻናት ግን በስተመጨረሻ ሥራቸውን ለክፍሉ አቅርበው ማብራሪያና መግለጫ እንዲሰጡ ይደረጋል።

10. የመስክ ጉብኝት ጊዜ፦

ይህ ወደ ክፍል በቀላሉ ማምጣት የማንችላቸውንና ህጻናት ትምህርት ያገኙባቸዋል ብለን የምናስባቸውን ቅርሶች፣ ታሪካዊ ቦታዎችና ኩኔቶች የምናሰቃኝበት ሌላይኛው በክፍል ውጭ የታቀደ ምልከታ የምናደግበት ወቅት ነው።

11. ህጻናትን መሸኘት፦

ህጻናት በራሳቸው ወደቤታቸው መሄድ ላይችሉ ይችላሉ። በመሆኑም መምህራን ደህንነታቸውን፣ ቁሳቁሶቻቸውን (የምሳ ዕቃ፣ መለማመጃ ደብተርና ወዘተ) በተገቢው መያዛቸውንና ለመሄድ ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠው ከወላጆቻቸው ወይም ከአሳዳጊዎቻቸው ጋር ያገናኟቸዋል።

1.15. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ልዩ ባህሪያት

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተቀናጅተው በሚቀርቡ ይዘቶች፣ በአቀራረብ ዘዴ፣ በመማሪያ አካባቢ አደረጃጀት፣ በመጫዎቻ ቁሳቁሶች፣ በህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ስልት፣ በቤተሰብና ማህበረሰብ ተሳትፎ፣ በህጻናትና መምህራን ግንኙነት እንዲሁም በመምህራን አቅም ማጎልበት ረገድ ከሌላው የትምህርት እርከን እጅግ ለየት ይላል። ተቀናጅተው የሚቀርቡ ይዘቶችና የአቀራረብ ዘዴዎች ከላይ በዝርዝር የቀረቡ በመሆናቸው ቀሪ መግለጫዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

1.15.1. የመማሪያ አካባቢ አደረጃጀት

የዚህ ደረጃ ትምህርት ህጻናት በክፍል ውስጥ ብቻ ቁጭ ብለው የሚማሩ ባለመሆናቸው የመማሪያ አካባቢያቸውን ለሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን።

ሀ. የክፍል ውስጥ አደረጃጀት

የክፍል ውስጥ አደረጃጀት የተለየ ሆነው የክፍሉ ጣሪያና ግድግዳ ጭምር ሳይቀር ትምህርታዊ ቁሳቁሶች ያሉበት መሆን አለበት። የምንከተለው በአውድ ላይ የተመሰረተ ውህደት ሥርዓት በመሆኑ የመማሪያ ክፍሎቻችንም በዚሁ ልክ የተደራጁ ይሆናሉ። የህጻናት ትምህርት ክፍል ሳቢ፣ ማራኪ፣ በመጫወቻ ቁሳቁሶች የበለጸገና በማዕዘናት የተደራጀ መሆን ይጠበቅበታል። ስለሆነም የዚህ ደረጃ ትምህርት የሚማሩ ህጻናት የሚማሩበት ክፍል በ4ቱ ዋና ዋና የመዳበር ዘርፎች ስም የተደረጁ ማዕዘናት ያሉት ክፍል ይኖራቸዋል ማለት ነው።

አካላዊ መዳበር	አዕምሯዊ መዳበር	የቋንቋ መዳበር	ማህበረ-ስሜታዊ መዳበር

ማዕዘናቱ በዕድገት ዘርፎች ስም የተሰየሙበት ዋነኛ ምክንያት የህጻናት ዕድገትና ትምህርት የሚለካው በዘርፎቹ በተሰየሙ የዕድገትና የመማር ውጤቶች ስለሆነ ነው።

1. **አካላዊ መዳበር** - የትልልቅና ትንንሽ ጡንቻዎች ዕድገትና መዳበርን የሚደግፉ ቁሳቁሶች ይደራጁበታል።
2. **አዕምረዊ መዳበር** - የማሰብ፣ ማሰላሰል፣ ምክንያታዊነትና ሌሎች ክህሎቶች የሚዳብሩበት ማዕዘን ነው።
3. **የቋንቋ መዳበር** - የንግግር፣ የተግባቦትና ሌሎች የቋንቋ ክህሎቶች የሚዳብሩበት ማዕዘን ነው።
4. **ማህረ-ስሜታዊ መዳበር** - የማህበራዊ መስተጋቢር፣ ስሜት መረዳትና ሌሎች ክህሎቶች ይዳብሩበታል።

ለ. የክፍል ውጭ አደረጃጀት

ይህ ሌላይኛው የመማሪያ አካባቢ ሰሆን ብዙ ጊዜ ለታቀዱና ለነጻ ጨዋታዎች የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይደራጁበታል። መጫወቻ አካባቢው ከጎጂ ነገሮች የጸዳ መሆን አለበት። ውጭ መደራጀት ካለባቸው የመማሪያና መጫወቻ ቁሳቁሶች የተፈጥሮ (ሳር፣ አሸዋ፣ ቅጠል፣ ጠጠር፣ ፍሬ፣ ጭቃ፣ እጽዋት፣ ነፍሳትና ወዘተ) እና ሰው ሰራሽ (ብሎኮች፣ መሹለኪያዎች፣ ሸርተቴዎች፣ ዡዋዡዌዎች፣ ጎማዎች፣ ኳሶች፣ ገመድ፣ መወጣጫዎችና ወዘተ) ይጠቀሳሉ።

1.16. የህጻናት እድገትና ትምህርት ምዘና

የህጻናትን የመማር እና የእድገት ደረጃ ምዘና በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መሠረታዊ ነገር ነው። መምህራን ስለህጻናት ጥንካሬ፣ ችሎታ እና ፍላጎቶች መረጃን በመሰብሰብ፣ በመተንተን እና ከእሱ በመነሳት ለህጻናት በየቀኑ የጫወታና የትምህርት መርሃ-ግብሮች በተመለከተ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ የሚረዳቸውን መደምደሚያዎችን ያካትታል። በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውስጥ የህጻናት መማር እና እድገት ምዘና ውስብስብ ቢሆንም የውጤታማ ማስተማርያ ዘዴና እድገት ልምዶች አካል ተደርገው ይወሰዳል።

የህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ቀጥተኛ ምልከታን፣ ቃለ-መጠይቆችን፣ ስታንዳርድ ፈተናዎችን፣ የደረጃ አሰጣጥ መለኪያዎችን እና ቼክ-ሊስቶችን፣ የህጻናትን የክፍል ሥራ ናሙናዎች መሰብሰብን እና የወላጅ አስተያየቶችን ያጠቃልላል። የምዘና ሂደቱ በቀጥታ ከሥርዓተ ትምህርት ይዘት እና በቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ክፍል ውስጥ ከሚጠቀሙት የማስተማሪያ ስልቶች ጋር የሚያገናኝ ሰፊ አቀራረቦችን ይይዛል።

የህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ሶስት ዓላማዎች አሉት። እነዚህም አንድ ልጅ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለመሳተፍ ብቁ መሆኑን ለመወሰን፣ ለዚያ ልጅ በክፍል ውስጥ ባለው አፈፃፀም ላይ በመመርኮዝ የግል የትምህርትና የእንክብካቤ እቅድ ለማዘጋጀት እና በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የልጁን መሻሻል ለመገምገም ነው።

አንዳንድ ጊዜ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህጻናትን ለመለየትና አስፈላጊ ሁሉ ድጋፍና እገዛ ለማድረግ ልዩ ምዘና በባለሙያ ይሰጣል። በሌላ በኩል በቅድመ አንደኛ ደረጃ የሚማሩ ህጻናት እድገትና ትምህርት ደረጃ ለመለካት የተደራጁና ስታንዳርድ ቴስቶችን በአመቱ አጋማሽ ወይም መጨረሻ መስጠት ይቻላል። የህጻናት ትምህርትና እድገት ምዘና ዘዴዎች በጨዋታ በፕሮጀክት እና በማህደረ-ተግባር ላይ የተመሠረተ ምዘናን ያካትታል።

በጨዋታ ላይ የተመሰረተ ምዘና ህጻናት ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን እየተጫወቱ ሳሉና ከተጫወቱ በኋላ የሚደረጉ ምልከታዎችንና የቃል ጥያቄዎችን ያካትታል። መምህራን ህጻናት ሲጫወቱ በስርዓት በመመልከት ስለእድገትና ስለትምህርት ብቃት ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ማግኘት ይችላሉ።

በፕሮጀክት ላይ የተመሠረተ ምዘና የህጻናትን የትምህርት እድገት ለመመዘን የሚያገለግል ሌላ ዓይነት አማራጭ ምዘና ሲሆን ይህም በእውቀታቸው፣ በፈጠራ ክህሎታቸው እና ችግር በመፍታት ችሎታቸው ላይ በማተኮር የህጻናትን አቅም መፈተሽን ያካትታል። ይህ የምዘና ሂደት መካከል የሚታየውን የአረዳድ ልዩነት ለማጥበብና በተቻለ መጠን ሁሉም ህጻናት አቅማቸውን እንዲያወጡ ይረዳቸዋል።

በማህደረ-ተግባር ላይ የተመሰረተ ምዘና የህጻናትን የዕለት ተዕለት ተግባራትን አደራጅተው መያዝንና ከዚያ መነሻ ልጆቹ ያለበትን ደረጃ የማየትና የማወቅ ሂደትን ያካትታል። ማህደረ-ተግባር ህጻናት በትምህርታዊ ተግባራት ላይ በሚሳተፉበት ጊዜ የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች የያዘ ስልታዊ እና የተደራጀ ስብስብ ነው። በማህደረ-ተግባር ውስጥ የተወከሉት የህጻናት ስራዎች የህጻናትን የመማር ብቃት ያለበት ደረጃን፣ የቀረቡ ይዘቶችን እና ስልቶችን ያንፀባርቃሉ። ማህደረ-ተግባራት በራሳቸው የግምገማ መሳሪያ አይደሉም። ስለህጻናት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በአግባቡ ማደራጀትና ተንትነው ለህጻናት አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ከቅድመ-አንደኛ ትምህርት መምህራን ይጠበቃል።

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን የህጻናትን እድገትና ትምህርት ሰመዝኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች መርሳት የለባቸውም።

- የተለያዩ የምዘና ስልቶችን (ምልከታ፣ የቃል ጥያቄ፣ ማህደረ-ተግባር፣ ቼክ-ሊስት) መጠቀም
- ምዘናው ተግባር-ተኮርና ከህጻናት ዕድሜ፣ ባህልና ቋንቋ ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን ማድረግ
- አወንታዊና መማርንና እድገትን የሚደግፍ አካባቢ መፍጠር
- በምዘናው ሂደት ውስጥ ወላጅና አሳዳጊ ያለውን ሚና መረዳትና ወላጆችን ማሳተፍ
- በህጻናት ሁለንተናዊ ዕድገትና የመማር ብቃቶች ላይ ትኩረት ማድረግ
- የምዘናን ውጤት ለህጻናት እድገትና ትምህርት መሻሻል መጠቀም
- የህጻናትን ደህንነትና ሚስጥር መጠበቅና ልጆቻቸው በተለይ በስታንዳርድ ፈተናዎች ሲመዘኑ ለወላጆች ማሳወቅ ያስፈልጋል።

1.17. የወላጅና አሳዳጊ ተሳትፎ በህጻናት ትምህርትና እንክብካቤ

የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ለህፃናት አጠቃላይ ስኬት መሠረት እንደመሆኑ መጠን ትኩረት መስጠቱ አስፈላጊ ነው። አንድ ሕጻን ከሰዎች ጋር የሚኖረው መስተጋብር የሚጀምረው ከቤተሰብ አባላትና በቅርብ ከሚንከባከቡት ጋር ነው። እነዚህ የመጀመሪያ ግኑኙነቶች የማህበራዊ ግንኙነት ክህሎቶች እድገትና ልጆች ስለራሳቸው እና በዙሪያቸው ስላሉት ሰዎች የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስተማር ወሳኝ ጊዜያት ናቸው። ቤተሰቦች የልጆቻቸው የመጀመሪያ አስተማሪዎች በመሆናቸው በእድገታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳርፉ መረዳት ተገቢ ነው። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የቤተሰብ ተሳትፎ በልጆች ትምህርት ላይ ያለው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው።

ቤተሰቦች ለልጆቻቸው እድገትና መዳበር የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤና ግብዓቶች ያቀርባሉ። በዚህም የህጻናትን ጤና እና እድገት በማረጋገጥ ረገድ ቀዳሚ ሚና ይጫወታሉ። ሌላው በቤተሰብ እና በትምህርት ቤቶች መካከል ቀጣይነት ያለው፣ በጋራ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተና፣ ጠንካራ አጋርነት ሲኖር የቤተሰብ ተሳትፎን ማረጋገጥ ይቻላል። የቤተሰብ ተሳትፎ በትምህርት ቤትና በቤተሰብ መካከል በሁለትዮሽ መተማመንና መከባበር ላይ የተመሠረተ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ በማድረግና ኃላፊነትን በመከፋፈል በቁርጠኝነት በመሥራት የልጆቻቸውን ትምህርትና እድገትን በንቃት መደገፍ ይገባል። ይህ በትብብር ላይ የተመሰረተ የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ግንኙነት ወላጆች እና መምህራን የልጆችን ብቃት ለማሳደግ፣ በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ የሚያጋጥማቸውን ችግሮቻቸውን ለመፍታት እና ግብዓትን በማሟላት በጋራ ጥረት እንዲያደርጉ መሰረት ይሰጣል።

1.18. የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመምህር መምሪያ አጠቃቀም

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን የመግቢያውን ክፍል፣ ስለቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት የተጻፉትን ጉዳዮች፣ የመመሪያዎቹን አተገባበር ቅደም ተከተል፣ የትምህርቱን ዓላማዎች እና መርሆዎችን በጥልቀት እንዲያነቡ ይጠበቃል። ከዚህም በተጨማሪ የተጠቆሙትን ንቁ የመማር ዘዴዎች፣ ግብአቶች፣ በልጆች ላይ ያተኮረና በጨዋታ ላይ የተመሠረተ ትምህርት አጠቃቀም፣ የእድገት እና የመማር ዘርፎች፣ የልጆች እድገት እና የመማር ውጤቶች እና የተጠቆሙ መደበኛ የሆኑና ያልሆኑ የግምገማ ቴክኒኮችን ማወቅ አለባቸው። በተጨማሪም መምህራን አካላዊ የመማር አካባቢዎችን እንዴት ማደራጀት እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው፤ የአካባቢ ቁሳቁሶችን የመጠቀም፣ የተለያዩ ማዕዘኖችን (የክፍል ውስጥ እና የውጭ ማዕዘኖችን) የማደራጀት እና ቤተሰብንና ማህበረሰብን የማሳተፍ ስልቶችን ተግባራዊ የማድረግ አስፈላጊነትን በመገንዘብ በስራ ሊያውሉት ይገባል። ከዚህም ጋር መምህራን የዕለት ተዕለት ተግባራትን እንዴት እንደሚያከናውኑ መረዳትና ዕለታዊ፣ ሳምንታዊ እና ዓመታዊ የትምህርት እቅዶችን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም መምህራን ይህን የመምህር መምሪያ ከህጻናት መለማመጃ ደብተር ጋር ትኩረት ሰጥተው በማቀናጀት መጠቀም ይኖርባቸዋል።

1.19. የክፍለ ጊዜ ድልድል

ይህ የ5 ዓመት ህጻናት ማስተማሪያ፣ ማሳደጊያና ማዘጋጃ የመምህር መምሪያ እንደመሆኑ መጠን ከህጻናት ዕድመና የእድገት ደረጃ ጋር የሚቀራረብ ድርጊት የያዘ የጊዜ ድልድል ያስፈልጋል። በዚህ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ህጻናት በአንድ ነገር ላይ የሚኖራቸው የትኩረት ደረጃ ጥሩ ቢሆንም የሚከናወኑ ተግባራት አሰልቺና ጊዜ የሚፈጁ መሆን እንደሌለባቸው ይታመናል። በመሆኑም ከላይ እንደማስተማሪያ ዘዴዎች የተዘረዘሩ ተግባራት የሚከተሉት የጊዜ ድልድል ይኖራቸዋል ተብለው ይጠበቃል። የዚህ ደረጃ ትምህርት የተደራጀው በቀን 6 ክፍለ ጊዜ ኖሮት አንዱ ክፍለ ጊዜ ከ25 ደቂቃ በማይበልጥ ሁኔታ ነው። ተረት፣ መዝሙር፣ የክፍል ውስጥ ጨዋታና ውይይት በቀን 25 ደቂቃ ብቻ ይሆናሉ ማለት ነው። ነገር ግን የመስክ ጉብኝት፣ በሥራ መማርና በፕሮጀክት መማር እንደየተግባራቱ ሰፋትና ጥልቀት እንከ አንድ ሰዓት ልዘልቁ ይችላሉ። የክፍል ውጭ ጨዋታ ግን ህጻናትን ወደውጭ ይዘው መውጣትን፣ የአካል እንቅስቃሴ ማድረግግና ነጻ ጨዋታዎችን የሚያካትት በመሆኑ በልዩነት የሁለት ክፍለ ጊዜያት (50 ደቂቃ) ቆይታ ይኖረዋል። ይህም ማለት የክፍል ውጭ ጨዋታ በሚኖርበት ጊዜ ህጻናት በመምህር መሪነት የሚከናወኑና ነጻ ጨዋታዎችን ለ50 ደቂቃ ያክል ልጫወቱ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪም አንድ ተግባር በሳምንት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚቀርብ ከሆነ ተግባሩ አንድ ዓይነት ቢሆንም በተሰጠው ክፍለ ጊዜ መሠረት የአቀራረብ እና የምዘና ስልቶችን በመቀያር መቅረብ ይኖርበታል።

ክፍል ሁለት

የመማር አውዶች

አውድ አንድ፡- ማህበረሰብ

ለአውዱ የተሰጠ ጊዜ፡- 5 ሳምንት/150 ክ/ጊዜ

መግቢያ

አውዱ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን አቀናጅተን ለማቅረብ የምንጠቀመው አቃፊያችን ነው። ይህ ማለት ህጻናት የሚማሩት በአውዱ መሰረት የተቀናጁ ይዘቶችን እንጂ ቀጥታ አውዱን አይደለም። ይህ የመማር አውድ የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ለማዳበር የሚያስችሉ ስድስት የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን በተቀናጀ የማስተማር ዘዴ ለማቅረብ የተዘጋጀ ነው።

በዚህ አውድ እንዲቀናጁ የታሰቡት ስድስቱም የትምህርት ይዘቶች (የቋንቋ እድገት፣ የቅድመ ስሌት፣ የአካላዊ መዳበር፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ዕድገት፣ ክዋና ስነ-ጥበባትና ሳይንስ) ሲሆኑ ህጻናት እነዚህን ይዘቶች በተቀናጀ መልኩ እንዲገነዘቧቸው ለማስቻል በህጻን ተኮር የማስተማር ዘዴ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ተግባራትን ማዘጋጀት ተችሏል። በዚህ አውድ የሚዳሰሱ ስድስቱም የትምህርት ይዘቶች ከህጻናቱ መማር ደርጃና እድገት ጋር ተቆራኝተው በዝርዝር ተቀምጠዋል። በመሆኑም በአውዱ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ለአምስት ሳምንታት ተዳራጅተዋል።

የእድገትና የመማር ውጤቶች፡-

ህጻናት ከዚህ አውድ ትምህርት በኋላ፡-

o መመሪያዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ማብራሪያዎችን ማዳመጥ እና ተግባራዊ ማድረግ

o ስለፍላጎታቸው፣ ስለ ወዳጆቻቸው፣ ስለታወቁ ህዝቦች፣ በአካባቢያቸው ስላሉት ነገሮች እና ስለ አካላዊ ባህሪያት መነጋገር

o የተለያዩ ድምፆችን፣ አመጣጡን ለይተው ማወቅ እና ከስዕሎች ጋር ማጣጣም

o አንድ ሰው የራሱ ድርጊት በሌሎች ሰዎች ስሜት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር መረዳት

o በተገቢው መንገድ ፍላጎቶችን፣ ምርጫዎች፣ ችሎታዎችን እና ስሜቶችን መግለጽ

o የመጫወቻ ደንቦችን ማወቅና እና መከተል

o እቃዎችን በመጠን፣ ርዝመት፣ ቅርጽ፣ እና ዓይነት መመደብ

o ዜሮ ምንም እንደሆነች ማወቅ

o እስከ 15 ቁጥሮችን በቃል መቁጠር ፣ማንበብና መጻፍ

o የንጽህናን አስፈላጊነት መረዳት፣ ንጽህናቸውንም መጠበቅ መቻል

o ራሳቸውን መረዳት መቻል

o ቁሶችን በመያዝ፣ በመቅለብ፣ በመግፋትና በመወርወር መቆጣጠር መቻል

o የታወቁ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መለየት እና ማብራራት መቻል

o የቅርብ አካባቢንና ደህንነት እንክብካቤ ተረድተው መንከባከብ

o የቤተሰብ አባላትና የሙዚቃ መሳሪያ ድምጽ መለየትና ማወቅ

o የቤትና የትምህርት ቤት አካባቢያቸውን ማድነቅ

አበይት ይዘቶች፦

- ራስን ማስተዋወቅና መግለጽ
- የሰው ሰውነት ክፍሎች
- የቅርብ አካባቢ
- ቁጥርና ቆጠራ
- ጤናና አካላዊ ጥንካሬ
- ፊደላትና ድምጾቻቸው
- ውበትን መረዳትና ማድነቅ
- የራስና የአካባቢ እንክብካቤ
- ማህበራዊ መስተጋብር
- መለየትና መመደብ
- ህትመትን መረዳት
- ፊደላትን ማንበብ፣ መገልበጥና መጻፍ
- የቃላት እውቀት
- ማወዳደርና ቅደም ተከተል ማስያዝ
- ባህላዊ ቅርሶች
- ሥርዓተ-ድርድር
- ሙዚቃዊ ምት ያላቸው እንቅስቃሴዎች
- የሀገር ፍቅር
- ሀገራዊ እሴቶቻችን
- ቅርጻ ቅርጾች
- ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አካባቢ

ሳምንት አንድ

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

* ሰላምታ ይለዋወጣሉ፤
* ራሳቸውንና ችሎታቸውን በትህትና ይገልጻሉ፤
* በአካላዊ ገጽታቸው እራሳቸውን ይገልፃሉ፡
* የአምስቱን የስሜት ህዋሳትን ስም ይጠራሉ፤
* የቅርብ አካባቢያቸውን ይገነዘባሉ፤
* የግል ንጽህናቸውን ይጠብቃሉ፤
* የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ ይለያሉ፤
* ዜሮ ምንም እንደሆነች ይገነዘባሉ፤
* እስከ 15 ያሉ ቁጥሮችን በቃል ይቆጥራሉ፤
* በአካባቢያቸው የሚሰሟቸውን ድምጾች ያሰመስላሉ።

ንዑስ ይዘቶች፦

- ራስን ማስተዋዋቅ
- ራስን መግለጽ
- ራስን ማዎቅ
- የሰውነት ክፍሎች
- የቅርብ አካባቢ
- ጤና
- ፊደላትና ድምጾቻቸው
- ቁጥርና ቆጠራ
- ውበትን መረዳት

ተግባር 1፡- መዝሙር

ሀ. ልጆች እንተዋወቅ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ሰላምታ መለዋወጥ፣ እራስን ማስተዋወቅ እና አካላዊ ገፅታ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

አካላዊ ገፅታንና ሰላምታ ሲለዋወጡ የሚያሳዩ ስዕሎችና እና ተንቀሳቃሽ ምስሎችና ሞዴል የሰውነት ክፍል

መዝሙር 1፡- ልጆች እንተዋወቅ

የሚወዳችሁ የማከብራችሁ
ሠላም ሠላም እንደምን ናችሁ
ልጆች እንተዋዎቅ 2x
ስሜ መሃመድ ነው
ቁመቴ በጣም እረጅም
መልኬ የጥቁር ቆንጆ
ጥርሶቼ በጣም ነጫጭ
ዓይኖቼ ጎላ ጎላ እኔ እለያለሁ
ሁል ጊዜ መጫዎት እወዳለሁ
ሰጫዎት ደስተኛ እሆናለሁ
ከሁሉም ጋር በፍቅር እኖራልሁ፡፡

ምዘና፡- የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል፡፡

ለ. ቤቴ-ጎረቤቴ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - በአካባቢ ያሉ ድምፆች፣ የቅርብ አካባቢ፣ የፊደላት ድምፅና ቅርፅ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

ውድ መምህር! ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር እየዘመሩ እንዲማሩ ለማስቻል ከላይ ያለውን መመሪያ ይከተሉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

የቅርብ አካባቢን የሚያሳዩ ስእሎች እና በአቅርብ አካባቢ ሊሰሙዋቸው የሚችሉ የተቀረፀ ድምፆች ቴፕ፣ ፍላሽ ፣የፍደላት ፍላሽ ካርዶች፣ ሰልክና ወዘተ

መዝሙር 2:- ቤቴ-ጎረቤቴ

ቤቴ ጎረቤቴ 2x
ሁሌም ከአጠገቤ አትጠፍም ከፊቴ
ከቤታችን ጀርባ አምስት ቤቶች አሉ
ከአምስቱ አራቱ ይመሳሰላሉ
ጎረቤቶቻችን እጅግ ደስ ይላሉ
ከቤታችን ደጃፍ ትልቅ ዛፍ ይገኛል
ሳሩና ቅጠሉ ያምራል ያስደስታል
ከቤታችን ደጃፍ ቦቢ ቁጭ ብሎ
ጠራ ጓደኞቹን ውውውው ብሎ
ውሾችን ፈርቼ በ - በሬን ዘጋው
ቡ- ቡቺን ሸሸው ቤ- ቤቴ ገባው
ከአስፋልቱ ላይ መኪኖቹ አሉ
ጺጵ ጺጵ እያሉ ደግሞ ይዘምራሉ።

ምዘና፦ የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል።

ተግባር 2፡- ተረት

ሀ. ጎበዟ መሰረት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የግል ንፅህና፣ አካላዊ መገለጫ፣ የቅርብ አካባቢ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት ከዚህ በመቀጠል የቀረበውን ተረት በማዳመጥ እየተዝናኑ እንዲማሩ ለማስቻል የተረት አቀራረብ ቅደም ተከተሎች መከተል ያስፈልጋል፡፡ ይህንኑን ተረት በዚህ ሳምን ሶስት ጊዜ ማለትም በመጀምሪያ ክፍለ ጊዜ መንገር፣ በሁለተኛ ክፍለ ጊዜ ህጻናት ተራ በተራ እየተነሱ እንዲያወሩ ማድረግና በሶስተኛ ቀን ህጻናቱ ተረቱን በድራማ መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር የሚሄድ ባህላዊ መንደርን የሚያሳይ፣ የግል ንፅህና አጠባበቅን የሚያሳይ እና አካላዊ መገለጫን የሚያሳይ ስዕል ወይም ተንቀሳቃሽ ምስል መጠቀም ይቻላል፡፡

ተረት 1፡- ጎበዟ መሰረት

በአንድ ባህላዊ የመኖሪያ ቤቶችና የተለያዩ ተከሎች ያሉበት ትንሽዬ መንደር የሚትኖር መሰረት የምትባል ጎበዝ ልጅ አለች፡፡ ዕድሜዋ 10 ነው፡፡ ለቤተሰቦቿ የመጀመሪያ ልጅ ነች፡፡ ቁመቷ አጭርና መልኳ ጠይም ነው፡፡ የራሷን ንጽህና በጣም ትጠብቃለች፡፡ እጆቿን ሳትታጠብ ፈጽሞ ምግብ አትበላም፡፡ ምግብ ከበላች በኋላና ከመጸዳጃ ስትመለስ እጆቿን በውሃና በሳሙና መታጠብ የዘወትር ልማዷ ነው፡፡ ጥፍሮቿንም ሁል ጊዜ ትቆረጣለች፡፡ የእግሮቿ ጣቶችም ስለምትታጠባቸው እጅግ ያምራሉ፡፡ ጥርሶቿን ሁል ጊዜ መፋቅ እና መቦረሽ ትወዳለች፡፡ በዙሪያዋ ላሉ ሌሎች ሰዎች ንጽህናና ጤናም ትጨነቃለች፡፡ ስታስነጥስና ስታስል እራሱ አፍንጫዋን በክንዷ ሸፍና ነው፡፡ መሰረት ሁል ጊዜ ለራሷና ለሌሎች ሰዎች ንጽህና ስለምትጨነቅ በምትኖርበት አካባቢ ጎበዝ ልጅ ናት ይሏታል፡፡ እሷም ንጽህናዋን በመጠበቋ ራሷንና ሌሎችን ከበሽታ ትከላከላለች በዝህ ተግባሯ የአካባቢው ማህበረሰብ ልጆቻቸው ልክ እንደ ጎበዟ መሰረት እንዲሆኑ በማሰብ ልጆቻቸውን መሞከር ጀመሩ ይባላል፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

የሚከተሉት ጥያቄዎችን በቃል መጠየቅና የተረቱን ፍሬ ሃሳብ መንገር ያስፈልጋል፡፡

1. በተረቱ ውስጥ ያለችው ልጅ ማን ናት?
2. ዕድሜዋ ስንት ነው?
3. የግል ንጽህናዋን የምጠብቃው እንዴት ነው?
4. የአካባቢው ሰዎች ጎበዛ የሚሏት ለምንድን ነው ?

ተግባር 3፦ ውይይት

ሀ. ሠላምታ መለዋወጥ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ትህትና፣ የቅርብ አካባቢ ሰላምታ አለዋወጥ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ ምስሎችን/ስዕል በማሳየት፣ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየት

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት በአካባቢያቸው ሰዎች እንዴት ሰላምታ እንደሚለዋወጡ እንዲነጋገሩ ለማስቻል የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች ጠብቀው ያበረታቷቸው።

- ለህጻናት ጊዜው የውይይት እንደሆነ መንገርና ዝግጁ ማድረግ
- በህጻናት መለማመጃ ደብተር ውስጥ በገጽ _____ ላይ የሚገኘውን ሰላምታ የሚሰጣጡ ሰዎች ስዕል ገልጠው እንዲመለከቱ መርዳት
- በመቀጠል ሁሉም ህጻናት እጃቸውን ተራ በተራ እያነሱ በሚኖሩበት አካባቢ ሰዎች ሰላምታ ስለሚሰጣጡበት ሥርዓት እና መቼ መቼ ሰላምታ እንደሚለዋወጡ እንዲያወሩ ማድረግ
- በመቀጠል ህጻናትን በየተራ በመጋበዝ እንዴት በትህትና ማውራት እና ከሰዎች ጋር መግባባት እንደምንችል ማለማመድ
- ህጻናት ሁለት ለሁለት እየሆኑ ትህትና በተሞላበት መንገድ ከሌሎች ጋር ሰላምታ እንዲሰጣጡ ማበረታታት
- በቀጣይ የተለያዩ በአካባቢያቸው ያሉ ማህበረሰቦች የሚለዋወጡትን ሰላምታ አይተውና ጠይቀው በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ
- ሁሉም ህፃናት ተራ በተራ ትህትና በተሞላበት መንገድ ሰላምታ እንዲለዋወጡ ማበረታት ያስፈልጋል።
- ሰላምታ በመለዋወጥ ሂደት ውስጥ የሚቸገሩ ህጻናት ካጋጠሟችሁ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

በተለያዩ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎች ሰላምታ እየተለዋወጡ የሚያሳይ ስዕልና ተንቀሳቃሽ ምስል

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ህጻናት ስለሰላምታ አለዋወጥ ያላቸውን ግንዛቤ በተለያዩ የቃል ጥያቄዎች ማረጋገጥ ያስፈላል።

ለምሳሌ፡- ሰዎች ጠዋት ምን ዓይነት ሰላምታ ይሰጣጣሉ? ከሰዓትሳ?

* ህጻናቱ ሰላምታ በሚሰጣጡበት ጊዜ ትክክለኛውን የአሰጣጥ ሥርዓት መከተላቸውን አትኩረው በመመልከት ምአረጋገጥ ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፡- ማነው በትክክል ሰላምታ መለዋወጥ የቻለው?

ተግባር 4፦ የተግባር ሥራ

ሀ. የራስ ስዕል መሳል፣ መቀባትና ስለስዕሉ ማውራት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- አካላዊ መገለጫ፣ የግል ችሎታ፣ ስለራስ ማውራት፣ ሰላምታ መለዋወጥ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በተግባር ሰርቶ ማሳየትና ገለጻ

የመምህር ሚና:-

ህጻናት የተጠቀሰውን የግል ተግባር በተነገራቸው መሰረት ያከውኗቸው ዘንድ ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ተከተለው ያሰሯቸው።

- ህጻናት ለተግባሩ ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ ፤
- እርሳስ፣ ላጲስ፣ መቅረጫ እና የተለያዩ ቀለም ማቅረብ
- በቅድሚያ በነጭ ወረቀት ላይ እርሶ ራሶትን ስለው ማሳየት፤
- ስሰሉ የአካል እና የፊት መገለጫዎትን በሚጠቁም መልኩ ይሁን ፡፡
- ቀጥለው ህጻናት በመለማመጃ ደብተራቸው በገጽ ____ ላይ ያለውን ባዶ ወረቀት እንዲገልጡ ማድረግ/ በወረቀት /በደብተር /ራሳቸውን እንዲስሉ ማበረታታት እና የሳሉትን ስእል አካዊ መገለጫቸውን ሊወክል የሚችል ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡
- ህጻናት ተራ በተራ እየተነሱ ስዕላቸውን ለክፍሉ እያሳዩ ስለራሳቸውና ስለአካል ክፍሎቻቸው እንዲያወሩ ማበረታታት
- ስዕሉን ስሰሉም ሆነ ስለራሳቸው ሲያወሩ የሚቸገሩ ልጆችን ዞረው በመመልከት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ
- የማየት ችግር ያለባቸው ህጻናት ሲያጋጥም ስዕል ሳይስሉ ስለራሳቸው መልክ፣ ችሎታ፣ ቁመናና የአካል ክፍሎቻቸው እንዲያወሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- በመጀመሪያ ክፍለ ጊዜ ስዕሉን ማሳል፣ በሁለተኛ ክፍለ ጊዜ ስዕሉን እንዲቀቡ ማድረኛ በሶስተኛ ክፍለ ጊዜ ስለስዕሎቻቸው እንዲያወሩ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

የመጫዎቻና መግሪያ ቁሳቁስ:-

* መለማመጃ ደብተር፣

* ነጭ ወረቀት፣

*እርሳስ፣

* ላጲስ፣

* ባለብዙ ቀለማት ክራዮንስ እና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ህጻናት ስዕላቸውን ስሰሉ ዞሮ መመልከትና ምን እንደሳሉ በቃል መጠየቅ

ለ. ፊደላትን መቁጠርና መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር መቁጠር፣ የፊደላት ቅርፅና ድምፅ፣ የዜሮ ዋጋ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ስርቶ ማሳየትና ገለጻ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት የተጠቀሰውን የግል ተግባር በተነገራቸው መሰረት ያከውኗቸው ዘንድ ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ተከተለው ያሰሯቸው፡፡

- 15 የሚሆኑ የመጀመሪያ ፊደላት ፍላሽ ካርዶችን ማቅረብ (ከ ‹በ› እስከ ‹ቦ› ፣ ከሰ እስከ ሶ እና እነት ፊደል ሸ)
- ፍላሽ ካርዶቹን አንድ በአንድ እየቆጠሩ እያነሱ ላዩ ላይ ያለውን ፊደል ሰም መጥራትና ቅርጹን አየር ላይ በጣት መጻፍ
- ይህንን ተግባር ህጻናት በቡድን እየሆኑ እንዲሰሩ ማድረግ
- ለአስራ አምስት ልጆች ቁጥር መስጠት (አንድ ሁለት.... እያሉ መጥራት)
- አስራአምስቱም ህጻናት በወረቀት ከ 1 እስከ 15 ቁጥር የተጻፈበት ወረቀት ልብሳቸውላይ መለጠፍ ቀጥሎ በቁጥራቸው ቅደም ተከተል መሰረት ተነስተው በመቆም የፊደል ፍላሽ ካርዶች ውስጥ አንድ አንድ እያንሱ በቁጥራቸው ተርታ የያዙትን ፈደል ስም እየጠሩ አየር ላይ በጣታቸው እንዲጽፉ ማበረታታት ከአስራምስቱ ህፃናት ተጨማሪ አንድ ህፃን ምንም ፊደል ሳይዝ እንዲቆም ያድርጉ ከዚያም ምንም አለመያዙን ከዜሮ ፅንሰ ሀሳብ ጋር ማገናኘት ዜሮ መነም ናት የሚለውን ሃሳብ ያብራሩላቸው
- በዚህ ተግባር ላይ ልዩ ድጋፍና እገዛ የሚፈልጉ ህጻናትን ለይተው መደገፍ
- ህጻናት ፊደሉን በአየር ላይ ለመፃፍ የሚያደርጉት ሙከራ ተደጋጋሚ ስራ ስለሚፈልግ ይህንን ተግባር በሳምንት ውስጥ ለሶስት ጊዜ በድግግሞሽ ማሰራት ያስፈልጋል፡፡
- ቀጥሎ የፊደል በ እና የፊደል ሰ ን ዝርያ ደግመው እንዲጽፉ ያድርጉ (ምሳሌ፡- በ-ቡ-ቢ-ባ-ቤ-ብ-ቦ እና ሰ-ሱ-ሲ-ሳ-ሴ-ሰ-ሶ) በመጨረሻም ሁሉም ህጻናት ሰንት ፊደላትን እንደናባቡ እና እንደፃፊበጋራ እንዲያወሩ ማድረግ

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* እርሳስ፣ ወረቀት፣ ደብተር፣ የፊደላት ፍላሽ ካርድ፣ በወረቀት ቁርጥራጭ የተጻፉ እስከ 15 ቁጥሮች* ባለብዙ ቀለማት ክራዮንስ እና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ህፃናቱ ያነሱትን ፊደል እንዲናገሩ እና ቁጥሩ ሰንተኛ ተራ ቁጥር ላይ እንደሚገኝ እና የዜሮን ፅንሰ ሀሳብ በቃል መጠየቅና የዕለቱን ፊደላት ደጋግመው እንድጠሩ መጠየቅ፤

* ህፃናቱ የተግባር ስራውን በሚሰሩበት ወቅት በተገቢው ሁኔታ እያከናወኑ መሆናቸውን በመመልከት ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው፡፡

ሐ. የስሜት ህዋሳትን መቁጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር መቁጠር፣ የስሜት ህዋሳት፣ ትህትና

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ስርቶ ማሳየትና ገለጻ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት የተጠቀሰውን የግል ተግባር በተነገራቸው መስረት ያከናውኗቸው ዘንድ ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ተከተለው ያሰሯቸው፡፡

- ህጻናት ለተግባሩ ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ ፤
- የስሜት ህዋሳት ስዕል በቻርት እና ሞዴል ማቅረብ ስለስሜት ህዋሳት ገለፃያድርጉ
- ቀጥሎ ህጻናት ተራ በተራ እየተነሱ ቻርቱን/ሞዴሉን እየተጠቀሙ የስሜት ህዋሳትን እየጠሩ ስንት እንደሆኑ እንዲቆጥሩ ማድረግ ተራቸው ሲደርስ ለተረኛው/ዋ ጓደኛቸው ሲያቃብሉም የትህትና ቃላትን በመጠቀም እንዲቀባበሉ መንገር
- ቀጥሎ የስሜት ህዋሳቱን በመሳል ተፈጥሮአዊ ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ይህንኑ ተግባር ህጻናት በአንድክፍለ ጊዜ ስለማይጨርሱ በመጀመሪያው ማስተዋወቅ፣ በሁለተኛ ቀን መሳልና መቀባት በመጨረሻም በተራ በተራ የሳሉትን በስነስርአት ክፍለ ማስተዋወቅ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የስሜት ህዋሳት ስዕል /ሞዴል፣ እርሳስ፣ ወረቀት/ደብተር፣ ቀለም

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ህጻናት ስዕላቸውን ሰስሉ ዞሮ መመልከትና ምን እንደሳሉ በቃል መጠየቅ

ተግባር 5፡- የክፍል ውሰጥ ጨዋታ

ሀ. የተቆራረጡ የስሜት ህዋሳት ስዕሎችን መግጠም (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ የስሜት ህዋሳት፣ ችሎታ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት የሚከተለውን ጨዋታ በተነገራቸው መሰረት ይከውኗቸው ዘንድ ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ተከተለው ያሰሯቸው፡፡

- የጨዋታውን ርዕስ በማስተዋወቅ ህጻናቱን ለጨዋታው ማዘጋጀት
- ቁጥር የተጻፈባቸው የስሜት ህዋሳት ስዕል ፐዝሎችን /ቁርጥራጮችን በአንድ ላይ በመደባለቅ በጠረጴዛው ወይም ወለል ላይ መበተን፤

• ቀጥሎ ተመሳሳይ ቁጥር የተጻፈባቸውን የስሜት ህዋሳት ቁርጥራጭ አስተውሎ መፈለግ

• ከተደባለቁ ቁርጥራጮች ውስጥ አንዱን አንስቶ እጅ ላይ ካለው ቁራጭ ጋር በመግጠም ትክክለኛ ስዕል ለማግኘት መሞከር፤

• ቁራጩ የማይገጥም ከሆነ ለብቻው ለይቶ ማስቀመጥና ከድብልቁ ቁርጥራጭ ውስጥ ሌላ መሞከር፤

• ቁርጥራጮቹ ሲገጥሙ ትርጉም የሚሰጥ ስዕል ከሆነ የስዕሉን ስም መጥራት፤ (ለምሳሌ ጆሮ፣ አፍንጫ፣ ዓይን.....) በማለት፤

• ህጻናት ጨዋታውን በተመለከቱት መሰረት እንዲሞክሩ ማድረግ

• ህጻናት ይህንኑ ጨዋታ በሌላ ቀን በቡድን ሆነው እየተጋገዙ እንዲጫዎቱ ማበረታታት

• ይህንን ጨዋታ በሳምንት ወስጥ ሶስት ጊዜ ማጫዎት ያስፈልጋል።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

* በካርቶን/በእንጨት ተቆራርጦ እላያቸው ላይ ቁጥር ተፃፎባቸው የተዘጋጁ የስሜት ህዋሳት ቁርጥራጭ፣ ጠረጴዛ...

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የቃል ጥያቄ፦ ህፃናቱ የገጣጠሙት የስሜት ህዋስ የትኛው እንደሆነ ይጠይቋቸው፤ አፍንጫ ለመግጠም የተጠቀማቹት ቁርጥራጭ ላይ የተጻፈው ስንት ቁጥር ነው?...

* ህፃናቱ የተቆራረጡትን የስሜት ህዋሳት ቁርጥራጮች በሚገጥሙበት ጊዜ በተገቢው ሁኔታ እያከናወኑ መሆናቸውን በመመልከት ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው።

ተግባር 6፦ የመስክ ጉብኝት

ሀ. በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶችን መቁጠር (2 ክፍለ ጊዜ)

***ቁልፍ ቃላት*፦** የቅርብ አካባቢ፣ መቁጠር፣ የግል ንፅህና

***የማስተማሪያ ዜዴ*:-** ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት

የመምህር ሚና፦

ህጻናቱን ከክፍል ውጪ ይዞ በመውጣት አካባቢያቸውን ከጎበኙ በኋላ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች ውስጥ 15 የሚደርሱ ቁሶችን ቆጥረው እንዲያመጡ ማድረግ ለምሳሌ (ጠጠር፣ ቁርጥራጭ እንጨት፣ ቅጠሎች...)

• የተባሉትን ለመፈጽም ለሚቸገሩ ህጻናት አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል።

• አንድ ህፃን ለዚህ ክፍለ ጊዜ የሚያመጣው አንድ ነገር ብቻ ነው፤ በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ደግሞ ሌላ የሚቆጠር ነገር ከአካባቢው ላይ አምጥተው ይቆጥራል።

• ጉብኝቱን እና ቆጠራውን ካከናወኑ በኋላ ተገቢውን የእጅ አስተጣጠብ በመከተል እንዲታጠቡ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መግሪያ ቁሳቁስ፡-

* በአካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ቁሶች (ቅጠል፣ ጠጠር፣ ተክሎች፣ እንጨት...)

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የቃል ጥያቄ፡- በጉብኝቱ ምን አያችሁ፣ ምን ቆጠራችሁ፣ ስንት ቆጠራቹ?...

* ህፃናቱ አካባቢያቸውን ለመቃኘት የሚያደርጉትን ጥረት፣ እስከ አስራ አምስት ቆጥረው ማምጣታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ተግባር 7፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. የኳስ ቅብብሎሽ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የቅርብ አካባቢ፣ ድምፆች፣ ቁጥር፣ ፊደላት

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናቱ ወደ ውጭ ወጥተው እየተዝናኑ እንዲማሩ ለማስቻል የውጭ ጨዋታውን በቅደም ተከተል መሰረት ያጫውቷቸው።

ጨዋታው ኳስ እየተቀባበሉ የእንስሳት፣ የመኪና፣ የቁጥር እና የፊደል ድምጾችን ማስመሰል ነው። ኳሱን ሲቀባበሉ ድምጹን ማውጣት ድምጽ ሳያወጠ የወረወሩ ህፃናት ከጨዋተው ውጭ ይሆናሉ።

• ለመጫወቻ የሚሆኑ ከአስር ያላነሱ ትንሽዬ ኳሶችን በቅርጫት በመያዝ ህጻናት ተሰልፈው ትከሻ ለትከሻ ተያይዘው ወደ ውጭ እንዲወጡ ማድረግ።

• በመጫዎቻ ስፍራ ላይ ለህጻናት ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ለምሳሌ ድንጋይ፣ እሾክና ወዘተ አለመኖራቸውን ማረጋገጥ ካሉም በጥንቃቄ ማሰወገድ

• አንድ ቡድን አስራ አምስት ሴትና ወንድ ህፃናት የቁጥር ድምፅ የሚያሙ ሁለተኛ ቡድን አስራ አምስት ሴትና ወንድ የእንሰሳትና የመኪና ድምጽ የሚያሰሙ እና አስራ አምስት ሴትና ወንድ ህፃናት የፊደል ድምጽ የሚያሰሙ ትንሽ አራርቀው ክብ ይሰሩ።

• እርሰዎ ለሁሉም ህጻናት በሚታዩበት ቦታ ሆነው መጠነኛ የሰወነት ማሟሟቂያ ተግባራት ማሰራት

• ቀጥሎ የመጀመሪያው ቡድን ጋር በመሄድ ከተወሰኑ ህጻናት ጋር ኳሱን እየተቀባበሉ በአካባቢያችን የሚሰሙ ድምጾችን ማሰመሰል (ኳሱን ለተረኛ ሲያቀብሉ መኪና ከሆነ ጿጿጿ ማለት፣ ውሻ ከሆነ ውውውው በማለት ለተረኛ ማቀበል)

• አንድ ቡድን ሲጫወት ሌሎች ተመልካች ይሆናሉ። ለምሳሌ፡- ቁጥር እስከ እስራ አምስት መጥራት ሲጫወቱ ሌሎች ጨዋታውን ይከታተላሉ።

• ይህ ጨዋታ ድግግሞሽ ስለሚፈልግ በተቀመጠለት ክፍለ ጊዜ ህፃናቱን እየተቀያየሩ ደጋግመው ማሰራት አስፈላጊ ነው።

• በመጨረሻም ልጆቹ ቅድም ወደ ውጭ ሲወጡ በተከተሉት ህግ መሰረት ስርዓታቸውን ጠብቀው ወደ ክፍል እንዲገቡ ማድረግ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

* ትንንሽ የፕላስቲክ/የጨርቅ ኳስ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የቃል ጥያቄ፦ ያወጡትን የእንስሳ፣ የመኪና፣ ቁጥር እና የፊደል ድምጽ ለየብቻ መጠየቅ በአካባቢያቸው ሌላ የሚያውቁት የተለየ ድምጽ ካለ ይጠይቁ፤ አካባቢያቸውን እንዲያስቡ ያግዛል።

* ህፃናቱ በሚጫወቱበት ጊዜ የጨዋታውን ህግና ስርዓት ጠብቀው እየተጫወቱ መሆናቸውን በመመልከት ድጋፍና ክትትል ያድርጉላቸው።

ሳምንት ሁለት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

- ስለጓደኞቻቸው መናገር
- ድርጊቶቻቸው በሌሎች ሰዎች ስሜት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ይገነዘባሉ
- የተለያዩ ድምፆችን ይለያሉ
- እራስንና የቅርብ አካባቢያቸውን ይገነዘባሉ
- በአካባቢው ያሉትን የሚያውቋቸውን ሰዎችን ምንነት ይገልጻሉ
- ትናንሽ ጡንቻዎችን መቆጣጠር ይለማመዳሉ
- የተለያዩ መዝሙሮችን በዳንስ ይዘምራሉ
- ዕቃዎችን በሁለት ምድቦች ይመድባሉ
- ድምፆችን እና የፊደላት ቅርጾችን ይለያሉ
- ለተለያዩ ፅሁፎች/ህትመቶች ምላሽ ይሰጣሉ
- እስከ 15 የሚደርሱ ቁሶችን/ነገሮችን ይቆጥራሉ

ንዑስ ይዘቶች፦

- እራስን ማስተዋወቅ
- እራስን መቆጣጠረ
- ድምፆችን መለየት
- እራስንና አካባቢን መንከባከብ
- ማህበራዊ ግንዛቤ
- የትናንሽ ጡንቻ መዳበር
- ፈጠራን መግለፅ
- ነገሮችን በአይነት መለየትና መመደብ
- የህትመት ግንዛቤ
- ፊደላትን ማንበብና ደግሞ መፃፍ
- ቁጥርና ቆጠራ

ተግባር 1፡- ተረት

ሀ. ወፍራሙ ሽምስዲን እና ጓደኛው ብሩክ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- በሰዎች ላይ ተፅኖ የሚያደርስ ድርጊት፣ ስለሚያውቁት ሰዎች ምንነት መግለፅ፣ የትናንሽ ጡንቻ መዳበር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት ከዚህ በመቀጠል የቀረበውን ተረት በማዳመጥ እየተዝናኑ እንዲማሩ ለማስቻል የተረት አቀራረብ ቅደም ተከተሎች መከተል ያስፈልጋል።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ኳስ፣ ልጆች በትምህርት ቤት ሲጫወቱ የሚያሳይ ሰዕል/ተንሳቃሽ ምሰል

ወፍራሙ ሽምስዲንና ጓደኛው ብሩክ

ተረት ተረት በአንድ መንደር ውሰጥ በሚገኝ ትምህርት የሚማር አንድ ሽምስዲን የሚባል በጣም ወፍራም ልጅ ነበር ሽምስዲን በውፍረቱ ምክኒያት እንደ ሌሎች ልጆች ፈጠን ብሎ መራመድና መሮጥ ያስቸግረዋል፡ ፡ በዚህም ምክንያት ልጆቸ እንሸነፋለን ብለው በማሰብ ከሱ ጋር ለመጫወት አይፈልጉም። እሱም ልጆች ሲጫወቱ ቁጭ ይመለከታል። የሽምስዲንን ትካዜ የተርዳው ብሩክ፤ ሽምሲ ለምንድው ከኛ ጋር የማትጫወተው ብሎ ጠየቀው። እሱም "እኔ መሮጥ አልችልም፤ ለዛም ልጆቹ አይወዱኝም" ብሎ ነገረው። ብሩክም ‹‹ከእኔ ጋር ትጫወታለህ አይዞህ ልጆቹም አይጠሉህም›› በማለት አበረታታውና እጁን ይዞ አሰነሳው። ከዚያ ብሩክ ኳስ በመያዝ በእጁ ሲያቀብለው ሽምስዲንም በእጁ ይቀበለዋል። መልሶ ሽምስዲን ወርውሮ ለብሩክ ያቀብለዋል። እንደዚያ እያደረጉ ሲጫወቱ ሳሉ ሌሎች ልጆች ተመለከቱአቸው ከዚያም ቀሰ በቀስ እየመጡ በሙሉ ተቀላቀሏቸው። ብሩክም ኳሱን በመያዝ ቆሞ አለና "ይሄ ልጅ ሽምስዲን ይባላል የኔ ጓደኛ ነው፤ እሱ ኳሰ መጫወት ይችላል። ከዚህ በኋላ ሁሌም አብረነው መጫወት አለብን" በማለት ነገራቸው። ሁሉም ልጆች ሽምስዲንን በማቀፍ ‹‹እኛም ካንተጋር እንጫወታለን አሉት›› የሽምስዲን ፊት በደሰታ አበራ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሁሉም በጋራ እየተጫወቱ ና ትምህርታቸውን እየተማሩ ኖሩ።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

የሚከተሉት ጥያቄዎችን በቃል መጠየቅና የተረቱን ፍሬ ሃሳብ መንገር ያስፈልጋል።

1. ሽምስዲንን የከፋው ለምን ይመስላችኋል?
2. ሽምስዲንን ተነሰቶ እንዲጫዎት ያደረገው ማን ነበር?
3. ሽምስዲንና ጓደኞቹ ኳሱን እንዴት እንደተቀባበሉ ማን ነው ያሚያሳየን?

ለ. አዲሱ ተማሪ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- በሰዎች ላይ ተፅኖ የሚያደርስ ድርጊት፣ ስለጓደኛ መናገር፣ እራስን ማወቅ፣ በአቅራቢያ ያለ አካባቢን መንከባከብ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት ከዚህ በመቀጠል የቀረበውን ተረት በማዳመጥ እየተዝናኑ እንዲማሩ ለማስቻል የተረት አቀራረብ ቅደም ተከተሎች መከተል ያስፈልጋል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ተክሎችን ሲንከባከቡ የሚያሳይ ስዕል/ተንሳቃሽ ምስል፣የትህርት ቤት ጊቢን እስከመጫወቻ ስፍራው የሚያሳይ ስዕል፡፡

አዲሱ ተማሪ

ተረት! ተረት! ከእለታት አንድ ቀን በላይኛው መንደር የሚኖሩት ወይዘሮ አስናቁ ልጃቸውን ታሪኩን ለመጀመሪያ ጊዜ ትምህርት ቤት ሊያስገቡት ይዘውት ሄዱ እዚያም እንደደረሱ ከመምህራኖቹ መካከል አንድ ምምህርት አገኙ እናትየውም መምህርት ባለፈው ያስመዘገብኩት ልጄ ይሄ ነው ተዋወቂው አለቻት፡፡ መምህርቷም በፈገግታ ታሪኩን እያየችው እንኳን ደኅና መጣህ ማሙሸዬ እኔ መምህርት አበበች እበላለው ስትለው ታሪኩም እኔኮ ስሜ ታሪኩ ነው እንጂ ማሙሽ አይደለሁም ማሙሽ የኛ ጎረቤት ነው አላት መምህርት አበበችም በጣም ይገርማል ከጎረቤትህ ማሙሽ ጋር ምንትሰራላቹ አብራቹ ትጫወታላቹ አለችው ታሪኩም አብረን ነው ምንጫወተው ደሞ መምህር እኔና ማሙሽኮ ጊቢ ውስጥ አበባ ተክለን ውሃ ሰናጠጣቸው ትልቅ ሆነው አድገውልናል ማየት ትፈልጊለሽ? አላት፡፡ መምህርቷም እንዴት የምትደንቁ ጎረቤታሞች ናቹ በጣም ጎበዝ ልጅ ነህ በርታ እሽ ታሪኩ ከጋበዝከኝ አንድ ቀን መጥቼ አያለው አለችውና አሁን ትምህርት ቤትህን ላስጎብኝህ በማለት ትምህርትቤቱን መጎብኘት ቀጠለ ታሪኩም በትምህርትቤቱ በጣም ተማረከ እናቴ ትምህርት ቤቱን ወድጀዋሉ እዝህነው መማር የምፈልገው አላቸው እናቱ እሺ የኔልጅ በቃ ነገ የመማሪያ ቁሳቁስህን ይዘህ ተመጣለህ በማለት መምህር አበበችን አመሰግነውና ተሰናብተው ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. መምህርት ማሙሽ ያለችው ማንን ነው?
2. ተክሎችን የተንከባከቡት ማንና ማን ናቸው?
3. ታሪኩ ስለጓደኛው ለማን ተናገረ?
4. በአጠቃላይ ከተረቱ ምን እንማራለን?

ተግባር 2፡- በሥራ መማር

ሀ. አካባቢን መንከባከብ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- በአካባቢ የሚገኙ ተክሎችን መንከባከብ፣ የጡንቻ መዳበር፣ ቁጥር መቁጠር መዘመርና መደነስ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን የቡድን ተግባር ህጻናት በተነገራቸው መሰረት ይከውኗቸው ዘንድ ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ተከተለው ያሰሯቸው፡፡

* በመጀመሪያ ህፃናቱን ወደ ውጪ ይዘዋቸው በማውጣት አካባቢያቸውን እንዴትና ምን እንደሚያፀዱ መንገር ማሳየትና አብሮ ማፅዳት

* በመቀጠልም በሚመቹ ቦታዎች ላይ ተክሎችን መትከል መኮትኮትና እና ውሃ ማጠጣት ሲጨርሱ የተከሉትን ተክሎች እንዲቆጥሩ ያድርጓቸው፡፡

* ቀጥሎ ከአካባቢያቸው ጋር የሚዛመዱ መዝሞሮችን እየደነሱ ይዘምሩ፡፡

* በመጨረሻም የተጠቀሙበትን እቃዎች ቦታው በመመለስ እጃቸውን በተገቢው መንገድ ይታጠቡ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* መኮትኮቻ፣
* ችግኝ/ዘር፣
* ውሃ ማጠጫ፣
* ውሃ፣
* አፈር፣
* መትከያ እቃ፣ ሳሙና፣ መጠረጊያ፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ ጂፓስ /ሞንታርቦ የተቀረጸ መዝሙር…

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡-

1. ልጆች አሁን ምን ተግባር አከናወንን?
2. ስንት ችግኞችን ተከላቹ/ዘራቹ?
3. አካባቢያችንን ስናፀዳ ምን ምን እቃዎችን ተጠቀምን? ከተከላቹ በኋላ ምን አደረጋቹ

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ፡፡

ተግባር 3፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ቀላል የእጅና የአይን ቅንጅት ተግባራት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ትናንሽ ጡንቻ በዳበር፣ የፊደላት ድምፀና ቅርፅ፣ እስከ 15 ቁሶችን መቁጠር

የማስተማሪያ ዜዴ:- በተግባር ስርቶ ማሳየትና ገለጻ

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን የቡድን ተግባር ህጻናት በተነገራቸው መሰረት ያከናውኗቸው ዘንድ ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ተከተለው ያሰሯቸው። በመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ የፊደላትን ስም እየተናገሩ በፍላሽ ካርድ የተዘጋጀን ፊደላት በመቆንጠጫ መቀባበል፣ በሁለተኛው እስከ 15 ፍሬ የሚሆኑ ዶቃዎች ውስጥ ክር መክተት እና መቁጠር፣በሶስተኛው ወረቀቶችን በተለያየ ቅርጽ መቀዳድና በሌላ ባዶ ወረቀት/ካርቶን ላይ ማጣበቅ...

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

*የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ የልብስ መቆንጠጫ፣ አሸዋ፣ ዶቃ፣ ክር፣ ወረቀት፣ ማጣበቂያ፣ ካርቶንና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፡-

1. ምን ተግባር አከናወናቹ?
2. በክር የከተታቹት ዶቃ ስንት ነው?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ስጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።

ለ.ቁሶችን በዓይነት መመደብ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ትናንሽ ጡንቻ በዳበር፣ ቁሶችን በአይነት መመደብ፣ ለተለያዩ የፅሁፍ አይነቶች ምላሽ መስጠት፣ መቁጠር

የማስተማሪያ ዜዴ:- በተግባር ስርተው ማሳየትና ገለጻ

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን የቡድን ተግባር ህጻናት በተነገራቸው መሰረት ይከውኗቸው

• በቅድሚያ ከአራት እስከ አምስት አባላት ያሉት ሴትና ወንድ ቡድን ይቦድኑ

• ቀጥሎ ነገሮችን በአይነት መመደብ እንዲለማመዱ በተለያየ እድሜ ላይ የሚገኙ የወንድና የሴት ስዕሎችን ከሁሉም ስዕል/ፎቶ በቁጥር ከሁለት በላይ መሆን ይኖርበታል (ሕፃን ወንድ/ሴት፣ ወጣት ወንድ/ሴት፣ አዛውንት ወንድ/ሴት) ቀላቅለው ይሰጡዋቸው።

• ሁሉም ቡድን የተሰጣቸውን ስዕል መለያ መሰረት በማድረግ በፆታ ይመድቡና ስዕልም ይቁጠሩ።

• በመጨረሻም ሁሉም ቡድን በየተራ የሰራውን ያስተዋውቃል ፣ሰዕሉን ቆጥሮ ይናገራሉ

• በቀጣይ ክፍለጊዜ የቤት እና የትምህርት ቤት እቃዎችን በመለየት እንዲመድቡ ያድርጉ ምሳሌ (ደብተር፣ መፃፍ፣ እርሳስ፣ መቅረጫ፣ ሳሃን፣ ቢላ፣ ማንኪያ፣ ሹካ፣ ኩባያ ...) በመቀላቀል በሁለት ምድብ እንዲመድቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* ሕፃን ወንድ/ሴት፣ ወጣት ወንድ/ሴት፣ አዛውንት ወንድ/ሴት፣ ፎቶ/ሰዕል፣ ደብተር፣ መፃፍ፣ እርሳስ፣ መቅረጫ፣ ሳሃን፣ ቢላ፣ ማንኪያ፣ሹካ፣ ኩባያና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. ስንት ወንድና ሴት ሰዕል ቆጠራቹ?
2. ምን ምን አይነት ሰዎችን አያቹ?
3. እናንተስ ያታቹ ምንድን ነው?
4. የክፍል ቁሳቁስ /የቤት ቁሳቁስ የትኞቹ ናቸው?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ፡፡

ሐ.የፊደላትን ድምጽና ቅርጽ መለየት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የፊደላት ድምፅና ቅርፅ፣ ትናንሽ ጡንቻዎች፣ ለተለያዩ የፅሁፍ አይነቶች ምላሽ መስጠት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ሰርተው ማሳየትና ገለጻ

የመምህር ሚና፡-

* የእለቱን የፊደል ቤተሰብ (ሸ-ሹ-ሺ-ሻ-ሼ-ሽ-ሾ እናከ-ኩ-ኪ-ካ-ኬ-ክ-ኮ) ፍላሽ ካርዶችን በየጠረጴዛቸው ላይ ያስቀምጡላቸው ፡፡

* እርሳስ ወረቀት ወይም መለማመጃ ደብተር በመስጠት የፊደላቱን ቅርፆች በማየት ይፃፉ ቀጥሎ የፃፉትን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ማድረግ፤

* ቀጣይ ክፍለ ጊዜ የተለያዩ በተዋወቋቸው ፊደላት የሚጀምሩ ህትመቶች/ሰዕሎችን በመስጠት ስለእነሱ ምንነት እንዲገልጹ ያድርጉ ምሳሌ፡- (የቡና ሰዕል፣ የባህላዊ ምግብ ሰዕል፣ የተለያዩ ቦታዎችና ማህበረሰቦች በጋራ ሲኖሩ የሚያሳይ ሰዕል፣ ማህበረሰቡ የሚገለገልባቸው ባህላዊ ቁሳቁሶች ሰዕል፣ ባህላዊ የቤት አሰራር ያሚያሳይ አካባቢ ፎቶ/ሰዕልና ወዘተ በመስጠት እንዲናገሩ ማበረታት፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የፊደላት ፍላሽ ካርድ፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ላጲስ፣ ባህላዊ ዕሴት ማሳያ ሰዕሎች፣ የባህላዊ ምግብ ሰዕል/ፎቶ፣ ባህላዊ ቦታዎችና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ግለ-ማህደር ማደራጀት

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. የማንን ፊደል ቤተሰብ ፃፉቹ ስንት ናቸው እነማን ናቸው?
2. ለመጻፍ ምን ተቀማችሁ?
3. ያያችሁት ስዕል ምንን ያሳያል?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ስጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ፡፡
* ስራዎቻቸውን በግለ-ማህደረ ተግባራቸው ውስጥ አደራጅተው ለውጣቸውን ይገምግሙ፡፡

መ. ቁሶችን መቁጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡-በአይነት መመደብ፣ መቁጠር፣ የፊደላት በድምፅና ቅርፅ፣ አካባቢን መገንዘብ፣ እራስን መገንዘብ፣ የማህበረሰብ መገልገያ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በተግባር ሰርተው ማሳየትና ገለጻ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት የሚከተለውን የግል ተግባር ከእርሶ የሚተላለፍባቸውን መመሪያ በመከተል እንዲተገብሩ ዝግጁ ያድርጉና ተግባሩን ያከናውኑ፡፡

* በቅድሚያ እስከ 15 የሚደርሱ የፊደል እና የቁጥር ፍላሽ ካርድ/ሞዴል በመቀላቀል በየጠረጴዛቸው ላይ ያስቀምጡላቸው፡፡
* ህፃናቱ የተቀላቀሉትን ፊደላትና ቁጥር በየመደባቸው እንዲመድቡ ያድርጉ በሁለት እንዲመድቡ ያድርጉ፡፡
* ቀጥሎ የመደቡትን ቁጥርና ፊደል እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
* ቀጥሎ አስራ አምስት የሚሆኑ ማህበረሰቡ የሚገለገልባቸውን የተለያዩ ቁሳቁሶች ይቁጠሩ፡፡
* ሁሉም ህጻናት ተግባሩን በተነገራቸው ልክ ማከናወን መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የፊደላት እና ከ1 እስከ 15 የቁጥር ፍላሽ ካርድ/ሞዴል፣ የማህበረሰብ መገልገያ ቁሳቁሶች/ሞዴልና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. ስንት ቁጥሮች ቆጠራቹ?
2. እነማንን ፊደላት አገኛቹ?
3. ስንት ቁሳቁስ ቆጠራችሁ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ስጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ፡፡

ተግባር 4፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ቁሶችን በሚያወጡት ድምጽ መለየትና መመደብ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- በአይነት መመደብ፣ ቁሶችን መቁጠር፣ ድምፆችን መለየት፣ ትናንሽ ጡንቻ መዳበር

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን ጨዋታ በተነገራቸው መምያ መሰረት ያከናውኑ ዘንድ ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ተከትለው ያጫውቷቸው።

- የጨዋታውን ርዕሰ በማስተዋወቅ ህጻናቱን ለጨዋታው ማዘጋጀት
- የእንሰሳትና የሙዚቃ መሳሪያዎች ምስል/ሞዴል እሰከ 15 የሚደርሱ ይሰጧቸው።

* በመቀጠልም በቅድሚያ ቁሶችን ይቁጠሩ ።

* ቀጥሎም ለሁለት ይመድቡ።

* በመጨረሻም ሁለት ሁለት ህፃናት በመሆን በድምጽ የመለየት ውድድር ይወዳደሩ አይናቸውን ጨፍነው ቁሶቹ የሚያወጡትን ድምፅ እንዲለዩ ያድርጉ ቀድመው የለዩት ተወዳዳሪዎች ጨዋታውን ይቀጥላሉ። የሳቱት ይወጣሉ። በዝህ መንገድ ሁሉም በየተራ ይመድባሉ፤ ይለያሉ።

ለምሳ ፡- የክራር ድምጽ ማሰማት ቁሱን እንዲናገሩ መጠየቅ ፣ የውሻ ድምጽ ማሰማትና ስሙን እንዲናጋሩ ማድረግ...

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የእንሰሳትና የሙዚቃ መሳሪያዎች ሰዐል/ሞዴል፣

* የእንሰሳትና የሙዚቃ መሳሪያዎች በድምፅ የተቀረፅ፣

*ቴፕ፣

*ፍላሽ

*ቴሌቭዥንና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፡-

1. የአንድ ሙዚቃ መሳሪያ/እንሰሳ ድምፅ በማስማት ይህ የምን ድምፅ ነው? ብሎ መጠየቅ....

* ህፃናቱ ጨዋታውን በሚጫወቱበት ወቅት ትኩረት ሰጥተው መጫወታቸውን በምልከታ ይከታተሉና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ድጋፍ ያድርጉ።

ተግባር 5፡- ውይይት

ሀ. ሀሳብ መግለጽ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ስለጓደኛ መናገር፣ እራስን ማወቅ፣ አካባቢን መገንዘብ፣ ሰዎች መግለፅ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ ሰእርቶ ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

ለህጻናት የሚከተለውን የውይይት መመሪያ በመስጠት እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

- ለህጻናት ጊዜው የውይይት እንደሆነ መንገርና ዝግጁ ማድረግ፤
- በቅድሚያ ስለራሰዎ ይንገሯቸው፡፡
- ከዚያ ህፃናት ሁለት ሁለት እየሆኑ ለጓደኞቻቸው ስለራሳቸው ይንገሩ፡፡
- በመቀጠልም ተራ በተራ እየተነሱ ስለጓደኞቻቸው የሰሙትን መልሰው ይናገሩ፡፡
- ከዚያም በአከባቢያቸው ስላሉ የሚያውቋቸው ሰዎች እና ስለሚኖሩበት የቅርብ አካባቢ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው
- ህጻናት ሀሳባቸውን በተቻላቸው መሰረት እንዲያንጸባርቁ የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ሁለት የሚያወሩ ሰዎች ያሉበት ሰዕልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከውይይቱ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- 1. ስለጓደኛህ/ሽ ምን አወቅሽ/ክ?

2. በአካባቢያችሁ ምን አይነት ሰዎች አሉ?

* ህፃናቱ በውይይቱ ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ... በተገቢ ማዳመጥና የማይሳተፉ ህጻናት ሲኖሩ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ ይኖርቦታል፡፡

ተግባር 6፡- መዝሙር

ሀ. ጓደኛዬ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ስለጓደኛ መናገር፣ ድርጊታቸው በሌሎች ላይ ተጽዕኖ መሳደር፣ ራሰን መገንዘብ አካባቢን መገንዘብ፣ ትናንሽ ጡንቻዎችን መቆጣጠር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምሰል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡ -

* ቀጥሎ ያለውን መዝሙር የአዘያዜም ስልቱን ጠብቀው ያዘምሯቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

* መቅረጸ ድምጽ፣ ቴሌቪዢን፣ ፍላሽ፣ ሞንታርቦ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክና ወዘተ…

መዝሙር 1:- ጓደኛዬ

ጓደኛዬን ላስተዋውቃቹ
አቤል ይባላል ስሙን ልንገራቹ
ስንጫወት እሱን ከተውኩት
በጣም ያዝናል ካልጠራሁት
ጓደኛዬን ላስተዋውቃቹ
ስሟ ፋኖሴ ነው ልንግራቹ
ስንጫወት እሷ ከተውኳት
በጣም ታዝናለች ካልጠራኋት
በሰፈራችን ያሉ ሰዎች 2x
ናቸው ጠንካራ ናቸው ጎበዞች 2x።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

መዝሙሩን በመዘመር ሂደት ውስጥ ህፃናቱ መልእክቱን መረዳታቸውን ለማወቅ ሊተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ የተለያ ጥያቄ ይጠይቁ።

ለምሳሌ - 1. ከመዝሙሩ ምን ተማራቹ?

2. የጓደኛው ስም ማነው?

* ህፃናቱ በመዘመር ሂደት ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ… በተገቢ ማዳመጥና የማይሳተፉ ህጻናት ሲኖሩ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ ይኖርቦታል።

ሳምንት ሶስት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

- ስለፍላጎታቸው ይናገራሉ
- የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታን ያሳያሉ
- ከአራት እስከ ስድስት የሚደርሱ ትክክለኛ የሎኮሞተር ያልሆኑ ክህሎቶችን ያሳያሉ
- ጤናማ ምግቦችን እና መጠጦችን ይረዳሉ
- የአደገኛ ሁኔታዎች ምንጮችን ይለያሉ
- የማህበረሰብ መገልገያ ቁሶችን ይለያሉ
- ትምህርት ቤት አካባቢን ያደንቃሉ
- ቁጥሮችን እስከ 15 በቅደም ተከተል ይደረድራሉ
- ፊደላትን ይጽፋሉ
- ቀላል የህዝብ ዳንሶችን ይለማመዱ

ንዑስ ይዘቶች፡

- ራስን ማስተዋወቅ
- የመወሰን ችሎታ
- የትልልቅ ጡንቻዎች ማዳበር
- የተመጣጠነ ምግብ
- ደህንነት እና ጥበቃ
- የቃላት እውቀት
- ለውበት ዋጋ መስጠት
- ቁጥሮችን ማወዳደር እና መደርደር
- ፊደላትን መጻፍ
- ባህላዊ ቅርስ

ተግባር 1፦ ተረት

ሀ. ጎበዟ ዳራሮ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፍላጎት፣ የተመጣጠነ ምግብ፣ ውሳኔ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት ከዚህ በመቀጠል የቀረበውን ተረት በማዳመጥ እየተዝናኑ እንዲማሩ ለማስቻል የተረት አቀራረብ ቅደም ተከተሎች መከተል ያስፈልጋል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ተረቱን ሊገልፅ የሚችሉ

* ምስሎች/ተንሳቃሽ ምስል፣

* የተለያዩ የሞያ አይነቶችን የሚሳይ ፎቶዎችና ወዘተ

ተረት 1፦ ጎበዟ ዳራሮ

ተረት! ተረት! እንዲት በታችኛው መንደር የምትኖር ዳራሮ የምትባል የደረጃ 2 ተማሪ ነበረች፡፡ ዳራሮ ከጓደኞቿ ጋር መጫወትና መቦረቅ ትወዳለች፡፡ ደስተኛም ናት ምክንያቱም ደግሞ ቤተሰቦቿ የሚሰጧትን የተመጣጠኑ ምግቦች በአግባቡ ስለምትመገብ ነው፡፡ ከእለታት አንድ ቀን የነ ዳራሮ መምህር ክፍል ገብተው የልጆቹን ፍላጎት እንዲህ በማለት ጠየቋቸው፡፡ ልጆች ስታድጉ ምን መሆን ትፈልጋላቹ? ህፃናቱም በየተራ እጃቸውን በማውጣት እኔ ፖሊስ፣ መምህር፣ መሀንዲስ፣ ጠፈር ተመራማሪ እያሉ ተናገሩ፡፡ ዳራሮም እጇን በማውጣት መምህር እኔ ሳድግ መሆን የምፈልገው ሀኪም ነው፤ ምክንያቱም ሁሉንም ሰዎች ከበሽታቸው ለማዳን ነው፡፡ አለቻቸው መምህሯም ልጆቹ የሚፈልጉት ሙያ ላይ ለመድረስ ጤናማ ሆነው ማደግ ስላለባቸው የተመጣጠነ ምግብ መመገብ እንዳለባቸው አስገነዘበቻቸው፡፡ ቤተሰባቸው የሚሏቸውን ነገር መስማትና ማክበር እንዳለባቸው ዳራሮ ጎበዝ እና ጤናማ የሆነችው ቤተሰብ የሚላትን ስለምትሰማ ነው፡፡ እናንተም እንደ እሷ መሆን አለባችሁ በማለት ነገሯቸው፡፡ ህፃናቱ እንደ ዳራሮ ለመሆን ቃል ገቡ ይባላል፡፡

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

የሚከተሉት ጥያቄዎችን በቃል መጠየቅና የተረቱን ፍሬ ሃሳብ መንገር ያስፈልጋል፡፡

1. ከተረቱ ምን ዓይነት ሙያዎችን ተዋወቃችሁ?
2. ዳራሮ ምን ዓይነት ልጅ ነች?
3. የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ለምን ይጠቅማል?
4. ተረቱ ምን ያስተምረናል?

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ.ባህላዊ ውዝዋዜ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- አደገኛ ሁኔታ፣ እንቅስቃሴ/ውዝዋዜ፣ ባህል

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ሰርቶ ማሳየትና ገለጻ

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን የግል ተግባር ህጻናት በተነገራቸው መሰረት ያከናውኗቸው ዘንድ ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ተከተለው ያሰሯቸው። በመጀመሪያው ህፃናቱ ከቆሙበት ቦታ ሳይንቀሳቀሱ ከአራት እስከ ስድስት የሚደርሱ አካላዊ እንቅስቃሴ ማሰራት፤ በቆሙበት ሆነው ባህላዊ ሙዚቃዎችን በመክፈት እንዲወዛወዙ ማድርግ፤ በእንቅሳቃሴያቸው ወቅትም ጉዳት ሊያደርሱባቸው የሚችል አደገኛ እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ ያስገንዝቡዋቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* ቴፕ፣ ፍላሽ፣ ስልክ፣ ሞንታርቦ፣ ጂፓስ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፡-

1. አካላችን/ጡንቻችንን የሚጎዱን እንቅስቃሴዎች ምን አያነት ናቸው?
2. ባህላዊ ጭፈራ ከመጨፈራችን በፊት ምን አደረግን?
3. ስትጨፍሩ ምን ተሰማችሁ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።

ለ.መለየትና ቅደም ተከተል ማስያዝ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ ውሳኔ፣ ምግብ፣ መለየት፣ መመደብ፣ ቅደም ተከተል

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ሰርተው ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን የግል ተግባር ህጻናት በተነገራቸው መሰረት ያከናውኗቸው።

- በቅድሚያ ስለጤናማ እና ጤናማ ያልሆኑ ምግብና መጠጦች ለህፃናት ገለፃ ያድርጉላቸው።ወንድ/ሴት) ቀላቅለው ይሰጡዋቸው።
- 15 የሚሆኑ ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ ምግቦችና መጠጦችን ስዕል/ፍላሽ ካርድ እና ከአንድ እስከ አስራ አምስት ቁጥር የያዙ ፍላሽ ካርድ/ሞዴል በማዘጋጀት ሁሉንም ቀላቅሎ መስጠት፤

• በመጀመሪያ ህፃናቱ ከተቀላቀለው ውስጥ ቁጥርና ምግቦችን እንዲለዩ ማድረግ፤

* ቀጥሎ ከምግቦቹ ውስጥ ደግሞ ጤናማ የሁኑና ያልሆኑትን በመለየት እንዲደረድሩ ያድርጉ።

* ቀጥሎ ጤናማ የሆኑ ምግቦች እና መጠጦችን ጤናማ ከልሆኑት በመምረጥ እንዲደረድሩ ማድረግ፤

* በመጨረሻም ቁጥሮችን ከአንድ ጀምረው በቅደም ተከተል እንዲደረድሩ ማድረግ ቀጥሎ ምግብ የሆኑትን እና መጠጥ የሆኑትን መለየት የሰሩትን ተግባር ለክፍል ጓደኛቸው እና ለመምህራኖቻቸው መንገር፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የቁጥር ፍላሽ ካርድ\ሞዴል፣ የተለያዩ ምግብና መጠጦችን የሚያሳይ ምስል/ሞዴል

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፡-

1. ጤናማ የሆኑ ምግቦችና መጠጦች የትኞቹ ናቸው?

2. ከ10 ቀጥለው የሚመጡ ቁጥሮች ስንትና ስንት ናቸው?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።

ሐ. እየደነሱ ፊደል መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የፊደል ቤተሰብ፣ መፃፍ፣ የህዝብ ዳንስ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ሰርተው ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን የግል ተግባር ህጻናት በተነገራቸው መሰረት ያከናውኗቸው።

• በቅዲሚያ ለህፃናቱ የፊደል ፍላሽ ካርድ/ሞዴል ያዘጋጁና በየጠረጴዛቸው ላይ ያሰቀምጡላቸው።

* ቀጥሎ የህዝብ ዘፈን ከፍተው ያሰሟቸው።

* የክፍል ጊዜውን የፊደል ቤተሰብ (ለ-ሉ-ሊ-ላ-ሌ-ል-ሎ እና አ-ኡ-ኢ-ኣ-ኤ-እ-ኦ) በመንገር ከፍላሽ ካርዱ ላይ እያዩ እንዲጽፉና የፃፉትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያበረታቱ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የፊደል ፍላሽ ካርድ/ሞዴል፣ እርሳስ፣ ወረቀት/ደብተር የተቀረጸ ሙዚቃ እና ማጫወቻ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፡-

1. ያየናቸው የፊደል ቤተሰቦች እነማን ነበሩ?

2. በማን ባህል ጨፈርን?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።

መ. ቀላል ባህላዊ ዳንሶች (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት:- ፍላጎት፣ አካል የማይጎዳ፣ ባህላዊ ዳንስ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በተግባር ሰርተው ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና:-

የሚከተለውን ተግባር ህጻናቱ በግል/በቡድን ያከናውኑ።

* በቅድሚያ ግን አካላችን ሊጎዱ ስለምችሉ አደገኛ ሁኔታዎች ገለፃ ያርጉላቸው (ለምሳሌ በጣም መዝለል፣ ሰውነትን ከመጠን በላይ መለጠጥ፣ ምንም ሳያሟሙቁ ከባድ እንቅስቃሴ ማድረግ፣

* ሲወዛወዙ ሰውነትን ከአቅም በላይ መለጠጥ...) በመቀጠል የተለያዩ ባህላዊ ሙዚቃዎችን ያዘጋጁና ህፃናቱ በየትኛው ባህል መደነስ እንደሚወዱ ፍላጎታቸውን ይጠይቁ፤

* ከዚያም ተመሳሳይ ምርጫ የመረጡትን ህፃናት በአንድ ቡድን ያደራጁ ቀጥሎ ሁሉም ቡድን ተራ በተራ የመረጡትን ሙዚቃ በመክፈት ወይም በመዝፈን አካላቸው በማይጎዳ መልኩ ውዝዋዜዎችን በቡድን እንዲሳዩ ያድርጉ ።

* በመቀጠል ከማህበረሰቡ መገልገያ ቁሶች መካከል በመምረጥ ስለው እንዲያቀልሙ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

* የተቀረጸ ባህላዊ እና ማጫወቻ ቴፕ፣ ጂፓስ፣ ሞንታርቦ፣ እርሳስ፣ ወረቀት/ደብተር፣ ቀለምና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ:-

1. በየትኛው ባህል ደነስን?
2. የማህበረሰቡ መገልገያ ቁሶች ምን ምን ናቸው?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።

ተግባር 3፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. የቤት ቁሳቁስ መደርደር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት:- ምርጫ፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁስ፣ 15 ቁጥር፣ ውሳኔ አሰጣጥ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ

የመምህር ሚና:-

የሚከተለውን ጨዋታ ጥለው የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎችን ተከትለው ያጫውቷቸው።

* ህፃናቱን በቡድን መመደብ ከዛም የተለያዩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን በስእልና በሞዴል ያዘጋጁ::
* በመቀጠልም ህፃናቱ ቁስ እስከ 15 በመምረጥ እንዲደረድሩና እንዲቆጥሩ ይንገረዋቸው ::
* ሲጨርሱም ለክፍል ጓደኞቻቸው ያከናወኑትን ተግባር እንዲገልፁ እድል ይስጡዋቸው::
* በመቀጠል የህብረተሰቡን መገልገያዎች ውስጥ የሚፈልጉትን መርጠው ሁለት ስዕል ሰለው ቀለም ይቀቡ፡፡
* በዝህ ተግባር የሚስሉትን ቁስና የሚቀቡትን ሲመርጡ የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታቸውን ያሳድጋሉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

* የተለያዩ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስ ስዕል/ሞዴል፣ እርሳስ፣ ቀለም፣ ወረቀት፣ ደብተርና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከጨዋታው በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፦

1. ምን ምን የቤት ቁሳቁሶችን አያቹ? ለምን ያገለግላሉ?
2. የትኛውን መገልገያ ቁስ ለመሳል ወሰናችሁ? ለምን እሱን መረጣቹ?

* ህፃናቱ ጨዋታውን በሚጫወቱበት ወቅት ትኩረት ሰጥተው መጫወታቸውን በምልከታ ይከታተሉና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ድጋፍ ያድርጉ፡፡

ተግባር 4፦ ውይይት

ሀ. አደገኛ ሁኔታዎችና መከሰቻ መንገዶቻቸው (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ አደገኛ ሁኔታ፣ ውሳኔ አሰጣጥ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና:-

ለህጻናት የሚከተለውን የውይይት መመሪያ በመስጠት እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

- በቅድሚያ የተወሰኑ አደገኛ ሁኔታዎችን ይንገሯቸው፡፡
- ከዚያ “አደገኛ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው እንዴት ይከሰታሉ፣ እንዳይከሰቱ እንዴት እራሳችንን እንከላከላለን?” በማለት እየጠየቁ ሀሳባቸውን እንዲያንሸራሽሩ ያድርጓቸው፡፡
- በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ደግሞ በቤት ውስጥ ከሚንጠቀማቸው የቤት ቁሳቁስ ውስጥ የአደገኛ ሁኔታዎች ምንጮችን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦ አደገኛ ሁኔታዎችን የሚያሳዩ ስዕሎችና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከውይይቱ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፦ 1. የአደገኛ ሁኔታዎች መነሻና ጉዳታቸውን መጠየቅ፤

* ህፃናቱ በውይይቱ ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ... በተገቢ ማዳመጥና መከታተል፡፡

ሀ. ጤናማ የሆኑና ያልሆኑ ምግቦችና መጠጦች (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ጤናማ፣ ምግብ፣ መጠጥ፣ ፍላጎት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ለህጻናት የሚከተለውን የውይይት መመሪያ በመስጠት እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

- ጤናማ የሆኑና ጤናማ ያልሆኑ ምግቦችና መጠጦች በተመለከተ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- ከዚያ የመወያያ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሀሳብ እንድለዋወጡ ያግዟቸው፡፡
- በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ደግሞ የእነሱን የምግብ ምርጫዎች/ፍላጎት ከእርሶ ጋር ሁሉም በጋራ ይወያዩ፡፡

የመጫዎቻና መግሪያ ቁሳቁስ፡-

የጤናማና ጤናማ ያልሆኑ ምግቦችና መጠጦች ስዕልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከውይይቱ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- 1. ጤናማ የተባሉ ምግቦች የትኞቹ ናቸው?

2. ጤናማ ያልሆኑትሳ?

* ህፃናቱ በውይይቱ ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ... በተገቢ ማዳመጥና መከታተል፡፡

ተግባር 5፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. እየቆጠሩ መደነስ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ ባህላዊ ዳንስ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱን ከክፍል ውጪ ይዞ በመውጣት አንድ ቡድን 15 አባላት ያሉት አድርገው ይመድቡ፡፡ እስከ 15 ቁጥሮች ያሏቸው የደረት ባጅ ያቅርቡላቸው፡፡ የህዝብ ዘፈን ከፍተው ቁጥራቸውን እየጠሩ እንዲደንሱ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መግሪያ ቁሳቁስ፡- የቁጥር ባጅ፣ ጂፓስ፣ ፍላሽና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከጨዋታው በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- 1. ይአደረሳችሁ ባጅ ቁጥር ስንት ነበር?

* ህፃናቱ በጨዋታ ወቅት የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ... በተገቢ ማዳመጥና መከታተል፡፡

ተግባር 6፡- መዝሙር

ሀ. እኔ ፍላጎቴን (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፍላጎት፣ ጤናማ ምግብ፣ የአደጋ ምንጮች፣ ትምህርት ቤትን ማድነቅ

የማስተማሪያ ዜዴ፡-

* በገለፃ፣ በመዝሙር፣

* ምስሎችን ማሳየት፣

* ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየት

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ጤናማ ምግብ፣ አደገኛ ነገሮችና የትምርትቤት አካባቢ የሚያሳይ ስዕል

መዝሙር 1፡- እኔ ፍላጎቴን

እኔ ፍላጎቴን ሁሌ እመርጣለሁ
ጤናማ ምግቦችን መመገብ ወደለሁ
የአደጋ ምንጮችን ቀድሜ ለያለሁ
ሰጫወት እራሴ ደግሞ ጠብቃለሁ
ትምህርት ቤቴን እወደዋለሁ
መጫወቻ ሰፍራን በጣም አደንቃለሁ
ቤተሰቦቼ ኑና ጎብኙልኝ
ትምህርት ቤቴን አድንቁልኝ፡፡

ምዘና፡- የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 7፦ የመስክ ጉብኝት

ሀ. ትምህርት ቤትንና አካባቢውን ማድነቅ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ስሜት፣ ትምህት ቤት፣ አካባቢ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በጉብኝት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* በቅድሚያ የዕለቱን ተግባር ርዕሰ ማስተዋወቅ፤

* ህፃናቱን ከክፍል ውጪ ይዞ በመውጣት የትምህርት ቤታቸውን አካባቢ የመማሪያ ክፍሎችን እየተመለከቱ ያስደሰታቸውን ነገር እንዲናገሩ ማድረግ፤

* በጉብኝታቸው ወቅት ከተመለከቱት ውስጥ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን እንዲናገሩ ያድርጉ።

* በመቀጠል በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ስለጎበኙት ነገር፣ ስለተደነቁበት ነገር ቦታ በተራ በተራ እንዲናገሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

* በመጨረሻም የዕለቱን ጉብኝት ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የትምህርት ቤት አካባቢን የሚያሳይ ስዕልና ሌሎች አስፈላጊ ተብለው የሚታሰቡ ቁሶችን መጠቀም ይቻላል።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከጉብኝቱ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፦ 1. ምን ምን ተመለከታችሁ?

2. ምን አስደነቃችሁ?

* ህፃናቱ በጉብኝት ጊዜ የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ... በተገቢ ማዳመጥና መከታተል።

ሳምንት አራት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

- የፊደላት ድምፅ እና ቅርጾችን ይለያሉ
- መሰረታዊ የጂኦሜትሪክ ቅርጾችን ከአካባቢው ጋር ያዛምዳሉ
- በእንቅስቃሴዎች መካከል ያለውን ልዩነት ይገነዘባሉ
- ቁሶችን በተለያየ ነጠላ ንድፍ/ቅጥ ይሰራሉ
- መደበኛ ምት እንቅስቃሴዎችን ያሳያሉ
- በአካባቢያቸው ያሉ ነገሮችን ስም ይለያሉ
- አቅጣጫን ከሌሎች አንፃር መውሰድ/መለየት
- ፊደሎች አስመስለው ይቀርፃሉ
- ቀላል ቁሶችን ይወረውራሉ
- መሰረታዊ ቀለሞችን ከተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮች ጋር በማገናኘት ይለያሉ

ንዑስ ይዘቶች፦

- የፊደላትን ድምፅ መለየት
- ግንኙነት፣ ትግበራና ዝምድና
- የአካል ብቃት
- ቅጥ/ጥለት
- ሙዚቃዊ እንቅስቃሴ
- የቃላት እውቀት
- የግል ችሎታ
- ፊደላትን መጻፍ
- ትናንሽ ጡንቻ መዳበር
- ጥበባዊ ግንዛቤ

ተግባር 1፦ ተረት

ሀ. የፊደል ቤተሰብ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መወርወር፣ በአካባቢ ያሉ ነገሮች፣ እንቅስቃሴ፣ አቅጣጫ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት ከዚህ በመቀጠል የቀረበውን ተረት በማዳመጥ እየተዝናኑ እንዲማሩ ለማስቻል የተረት አቀራረብ ቅደም ተከተሎች መከተል ያስፈልጋል።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ተረቱን ሊገልፅ የሚችሉ

* ምስሎች /ተንሳቃሽ ምስል፣

* የተለያዩ የሞያ አይነቶችን የሚሳይ ፎቶዎችና ወዘተ

ተረት 1፦ የፊደል ቤተሰብ

በድሮ ጊዜ በአንድ መንደር የሚኖሩ የፊደል ቤተሰቦች ነበሩ። እነዝህ ቤተሰቦች ሁል ጊዜ ከልጆቻቸው ጋር የመወያየት ልማድ አላቸው። ዛሬም እንደተለመደው የትምህርት ቤታቸውን ውሎ መጠየቅ ጀመሩ፡ ፡ ውይይታቸውም አካባቢያቸው ላይ ምን ምን ነገሮች እንዳሉ በሰም እንዲናገሩ ጠየቋቸው። የፊደሎቹም ልጆች ተራ በተራ መናገር ጀመሩ። "እኔ ምግብ ቤት አይቻለሁ፤ እኔ ደግሞ ሃኪም ቤት መኖሩን አውቄለሁ፤ እኔ ደግሞ ሱቅ አይቻለሁ" እያሉ መለሱ። ቤተሰቦቻቸውም ልጆቹ አካባቢያቸውን በጥንቃቄ በማየታቸው የዕለቱን ውይይት ጨርሰው እራታቸውን ተመግበው ወደ መኝታቸው ሄዱ። በማግስቱ ሁሌም እንደሚያደርጉት በጋራ እንቅስቃሴ መሰራት ጀመሩ። ልጆቹም ትምህርት ቤት የተማሩትን እንቅስቃሴ ወደፊት ወደኋላ፣ ወደግራ ወደቀኝ አቅጣጫቸውን በመቀያየር ሰሩ። በመቀጠልም ኳስ እየተወራወሩ ተጫወቱ። ከእስፖርት እንቅስቃሴ በኋላ ሁሉም ተጣጥበው ቁርሳቸውን ተመግበው ቤተሰባቸውን ተሰናብተው ወደትምህርት ቤታቸው ሄዱ። የፊደል ቤተሰቦቹ በደስታና በፍቅር ሁሌም እየተወያዩ በሰላም ኖሩ ይባላል።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

የሚከተሉት ጥያቄዎችን በቃል መጠየቅና የተረቱን ፍሬ ሃሳብ መንገር ያስፈልጋል።

1. የፊደል ቤተሰቦቹ ልጆች ስለአካባቢያቸው ምን ያውቃሉ?
2. ቤተሰቦቹ ስለምን ይወያያሉ?
3. ምን አይነት እንቅስቃሴ ይሰሩ ነበር?

በስተመጨረሻም ተረቱን መልሰው እንዲያወሩ ማበረታታት ያስፈልጋል።

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ፊደላትን መለየት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፣ ቅርፅ፣ ድምፅ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ሰርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን በስዕል ፍላሽ ካርድ /በፊደል ቻርት በማዘጋጀት ከጀርባው የሳምንቱን ፊደል ቤተሰብ (ዘ-ዙ-ዚ-ዛ-ዜ-ዝ-ዞ እና ደ-ዱ-ዲ-ዳ-ዴ-ድ-ዶ) በመፃፍ ያዘጋጁ፡፡

* ከዚያም ያዘጋጁትን ለህፃናቱ በየጠረጰየዛቸው ላይ ይሰጧቸው ለተወሰነ ጊዜ እንዲመለከቱ ያድርጉ በመቀጠል ስለያዙት ነገሮች ገለፃ ያድርጉ ምስሎቹ ሰው ሰራሽ እን ተፈጥሮ በማለት ከሰሙ ጋር ይንገሯቸው፡፡

* ከዚያም ህፃናቱ ምስሉን እያዩ በየትኛው ፊደል ስማቸው እንደሚጀምር እንዲሁም ተፈጥሮአዊ ነው ወይስ ሰው ሰራሽ የሚለውን ይጠይቋቸው፡፡

* በመጨረሻም የዕለቱን ፊደል እንዲጽፉ እና የፃፉትን ተራ በተራ በማንበብ የፊደሏን ድምጽ እና ቅርጽ እንዲለዩ ማስቻል ያፈልጋል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የፊደል ካርድ፣
* የተለያዩ በተፈጥሮ የሚገኙና ሰውሰራሽ የሆኑ ነገሮች ምስል፣
* እርሳስ፣
* የመለማመጃ ደብተር፣
* ላጲስና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. ተፈጥሮአዊ የምንላቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. ሰው ሰራሽ የምንላቸው ምንድን ናቸው?
3. ምን ፊደል ፃፍን?
4. የፊደሎቹ ቤተሰብ ስንትና እነማን ናቸው?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ፡፡

ለ. የጂኦሜትሪ ቅርፆችን ከአካባቢው ጋር ማዛማመድ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቀለም፣ ተፈጥሮ፣ የጂኦሜትሪ ሜትሪ ቅርጽ፣ አካባቢ፣ የነገሮች ስም

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ ስርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን የግል ተግባር ህጻናት በተነገራቸው መሰረት ያከናውኗቸው፡፡

• በመሰረታዊ ቀለማት የተቀለሙ (ሰማያዊ፣ ቀይ፣ ቢጫ) ባለቀለም የጂኦሜትሪ ቅርጾችን ያዘጋጁና ለህፃናቱ እያሳዩ ስማቸውን (ሶስት ጎን፣ አራት ጎን፣ ክብ) ይንገሩ፡፡

* በክፍል ውስጥ ያሉ የተለያየ የጂኦሜትሪ ቅርፅ ላቸውን ቁሶች ፊትለፊት በሚታይ መልኩ ያቀምጡ ለምሳሌ (ሳህን፣ ካርቶን፣ ጎጆ ቤትና ወዘተ ያዘጋጁ፡፡

* ካዘጋጁት ቁሶች መካከል አንዱን በማንሳት ምን አይነት ቅርጽ እንዳለውና ቀለሙ ምን አይነት እንደሆነ ከየትኛው የጆኦሜትሪ ቅርፅ ጋር እንደሚገናኝ ይጠይቁ፡፡ መልሳቸውን ከሰሙ በኃላ እርሰዎ ያብራሩላቸው፡፡

* በመቀጠል ህፃናቱ ተራ በተራ የጂኦሜትሪ ቅርጹን እየያዙ አካባቢያቸውን በመፈተሽ ያዙትን ቅርጽ የሚመሰል ነገር ጋር በማገናኘት በዚያም ያገናኙትን ነገር ስም እንዲናገሩ ማድርግ እንዲሁም ቅርጻቸውን፣ ቀለማቸውን በመናገር ቀለማቸውን ከተፈጥሮ ነገሮች ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ፡- መፅሀፍ ጎነ አራት ቅርጽ ሲኖረው ቀለሙ አረንጓዴ ነው ቅጠል ይመሰላል፣ የመመገቢያ ሰሀን ቅርፁ ክብ ነው ቀለሙ ነጭ ነው ጥጥ ይመሰላል...

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. ይህ ቅርጽ ምን ይባላል?
2. ከአካባቢያችሁ ከሉ ነገሮች ከምን ጋር ይመሳሰላል?
3. ካያችሁት ነገር ከተፈጥሮ ጋር የሚዘመድ የቱ ነው?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናዉኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ፡፡

ሐ. ቁሶችን በተለያየ ንድፍ መስራት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቅርፅ፣ ቁስ፣ ንድፍ፣ ፊደል፣ ቀለማት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ ስርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን የግል ተግባር ህጻናት በተነገራቸው መሰረት ያከናውኗቸው፡፡

ህፃናቱን ቀጥሎ የቀረበውን ተግባር ማከናወን እንዲችሉ በቅድሚያ ስለመሰረታዊ ቀለማት እና ስለ ነጠላ ንድፍ/ቅጥ ምንነት ያብራሩላቸው፡፡

* አስቀድመው የተለያዩ ቁሶችን ፀሀይ፣ሙዝ፣ሰማይ ፖም /አፕል ከፊደላት ደግሞ በድርብ የተቀረጹ እና መሰረታዊ ቀለም የተቀቡ (ለ፣አ፣ከ፣ዘ፣ዠ) የያዘ ምስል ያዘጋጁ፡፡

* ከዚያም ያዘጋጁትን ምስልና ፊደላት ከገለፃከተፈጥሮ እና ከስውሰራሽ ጋር የሚያገለጹበትን በመንገር ፊት ለፊታቸው ይስቀሉላቸው‹/በየጠረጰየዛቸው ላይ ያስቀምጡላቸው፡፡

* ቀጥሎ እርሶ ከተቀመጡት ምስሎች ነጠላ ነጠላ እያደረጉ ወደጎን ወይም ወደታች በእርሳስ በመጻፍና በማቅለም ይደርድሩ እና ያሳዩአቸው (ምሳሌ፡-ፀሀይ -- ፊደል፣ ሰማይ ----ፊደል፣ ፖም----ፊደል)

* በመቀጠል ህፃናቱበወረቀት/በደብተር በጥንቃቄ ነጠላ ንድፍ የመደርደር ተግባር እንዲያከናውኑ ያድርጉ ከፃፉ/ከሳሉ በኋላ መሰረታዊ ቀለም መቀባተቸው መዘንጋት የለበትም (ምሳሌ ፦ ጽሀይ ቢጫ- ፊደል ቀይ - ሰማይ ሰማያዊ) በዚህ መሰረት ተፈጥሮአዊ ነገሮች፣ መሰረታዊ እና ቀለማት በነጠላ ድርድር እንዲደረድሩ ማድረግ፤ ይህ ማለት እነዝህን ነገሮች በድግግሞሽ ስንሰራ ነጠላ ድርድር/ፓተርን እንለዋለን፡፡ ስለዝህ የተፈጥሮ መልካቸውን በመጠበቅ እንዲያቀልሙ ያድርጉ፡፡

* በቀጣይ የቀሩትን ፍደላትና ቁሶች ከተፈጥሮ ቀለማት ጋር እያዋሃዱ ይሰሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

በቻርት/በፍላሽ ካርድ/ወረቀት የተዘጋጀ የተፈጥሮአዊ ነገሮችና ፊደላት/ሞዴል፣ እርሳስ፣ ደብተር፣ ባለቀለም እርሳስ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ፣ ግለ ማህደርና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. ምን ለመሳል ምን ቀለም ተጠቀምን?
2. የቀረጽናት ፊደል ማን ትባላለች?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ስጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ፡፡

* የህፃናቱን ስራዎች በማህደረ ተግባራቸው ውስጥ አስቀምጠው ለውጣቸውን ይገምግሙ፡፡

መ . መሰረታዊ ቀለሞችን አካባቢያቸው ከሚገኙ ቁሶች ጋር ማዛመድ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቅርፅ፣ ስም፣ ቀለሞች

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ ስርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን የግል ተግባር ህጻናት በተነገራቸው መሰረት ያከናውኗቸው፡፡

• አስቀድመው የተለያዩ ቁሶችን ያዘጋጁ፡፡

* ያዘጋጁትን ቁስ ለሁሉም ህጻናት መታየት በሚችልበት ቦታ ላይ ያስቀምጡ፡፡

* የተዘረዘሩትን ቁሶች በአንድ መደዳ በመደርደር በሌላ አቅጣጫ ደግሞ የተለያዩ የቀለም ካርዶችን በመደርደር ህጻናት በየተራ እየተነሱ ከተደረደሩት ቁሶች በማንሳት ከቀለማቸው ጋር እንዲያዛንዱ ማድረግና የቁሶቹን ስሞች እንዲናገሩ በማድረግ ሁሉንም ህፃናት በተራ እንዲሳተፉ ያድርጉ፡፡

* በመጨረሻም ምን አይነት ተግባር እንዳከናወኑና ተፈጥሮአዊ የሆነኑትን እና እኛ የሰራነው ቀለም ለይተው እንዲያሳዩ ይንገሯቸው፡፡ ምሳሌ ቅጠል በተፈጥሮ ያገኘው ቀለም ሲሆን እኛ ስለን ስንቀባ ደገግሞ ሰውሰራሽ እንደሚባል ማሳየት ያስፈልጋል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮች በምስል ከተቻለ ደግሞ ሞዴ፣ ቀለሞች/የቀለም ካርድ/በወረቀት/በተቆራረጡ እንጨቶች ተቀብተው የተዘጋጁ.....

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. ተፈጥሮአዊ ቀለማት ምንና ምን ናቸው?
2. ሰው ሰራሽ የምንለው ምንድን ነው?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ፡፡

ተግባር 3፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ቀላል ቁሶችን መወርወር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መወርወር፣ ቅርፅ፣ ፊደል

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* በቅድሚያ ስሌዳ ላይ ጎላ በማድረግ ሶስት መሰረታዊ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን በመሳል በውስጣቸው የተለያዩ እናት ፊደላትን (ሰ፣ ከ፣ ለ፣ አ፣ ሸ፣ ዘ፣ ዠ፣ ደ፣ ጀ፣ ጸ..) ይጻፉ፡፡

* ከዚያም ሳጥን /ካርቶን በማዘጋጀት በውስጡ ሰሌዳ ላይ የሰሩትን ቅርፆች ይክተቱ፡፡ ከዚያም አስር ተማሪዎች ከፊት በመምረጥ ያስወጡና አምስት አምስት በማድረግ በሁለት ረድፍ ያስልፏቸው፡፡

* በአንደኛው ረድፍ ያለው ህጻን ካርቶኑን በመክፈት ከቅርፆቹ መካከል አንዱን በማውጣት በሌላኛው ረድፍ ከፊት ለተሰለፈው ሴት/ወንድ ህጻናት ወርውሮ እንዲያቀብለው ያድርጉ፡፡ የተወረወረላቸው ህጻናት ቅርፁን በማየት ሰሌዳው ላይ ከተሳሉት ቅርፆች ጋር በማዛመድ በውስጡ ያሉትን ፊደሎች ያነባሉ፡፡ ምሳሌ፡- ክብ ከሆነ በክብ ውስጥ ከተፃፈው ፊደል ውስጥ አንዱን እንዲጠሩ እና ቃላቱን እንዲናገር ለ-ለማ በማለት ይናገራሉ፡፡

* ከዚያ የወረወሩት ህጻናት ፊደልና ቃላቱን ለተጋገሩት ተረኛ ህጻናት በትክክል ከመለስ ቀጣይ ወርዋሪ እሱ ስለሚሆን ካርቶኑን ይሰጠዋል። በትክክል ካልመለሰ ግን ከጨዋታው ይወጡና በእርሱ ረድፍ ሌላ ተረኛ ይተካል። ጨዋታው እንዲህ እያለ ይቀጥላል።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ሳጥን/ካርቶን፣ የጂኦሜትሪ ቅርፆች፣ የፊደል ካርድ፣ ቾክ፣ ማርከርና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፦

1. አንተ/ቺ የመረጥሽው ቅርፅ ምን አይነት ነበር?
2. ቅርፆቹን ለማን አቀበልሽ/ክ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።

ተግባር 4፦ ውይይት

ሀ. በአካባቢያቸው ያሉ ነገሮችን ስም መለየት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ቀለም፣ አካባቢ፣ አቅጣጫ

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

* በአካባቢያቸው ስለሚገኙ ነገሮችና የሚገኙበት አቅጣጫ እንዲሁም መሰረታዊ ቀለሞች ጥያቄ በማንሳት እንዲወያዩ ያድርጉ።
* ህጻናት ሀሳባቸውን በነጻነት መግለጽ እንዲችሉ ይርዷቸው።
* በውይይቱ ወቅት ሁሉም ህጻናት መጠየቅም ሆነ ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ መስጠት መቻል አለባቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

* አካባቢን የሚያሳይ ምስል፣
* ቪድዮና መሰረታዊ ቀለማትን የያዘ ምሰል ወይም ራሱ ቀለሙ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከውይይቱ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፦ 1. በአካባቢያችን ምን ምን ነገሮች አሉ?

2. ስንት ቀለማትን አየን?

* ህፃናቱ በውይይቱ ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ... በተገቢ ማዳመጥና መከታተል።

ተግባር 5፡- መዝሙር

ሀ. ውርዬ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቅርፅ፣ አካባቢ፣ አቅጣጫ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የድመት ምስል የያዘ ችርት/ሞዴል፣
* አቅጣቻን ለመሳየት የሚጠቁሙ ምስሎች፣
* የጂኦሜትሪ ቅርጽ ምስል የያዘ ከርድ፣
* ወረቀት፣ እርሳስና ላጽስ

መዝሙር 1፡- ውርዬ

ውርዬ የቱጋር ናት
ከአቡሽ አጠገብ ናት
ይመስላል አይኗ ክብ
ጆሮዋ ሶስት ጎን
ውርዬ በጣም ተራበች
ጮኸች ሚያው እያለች
እንደውርዬ መጮህ
እስቲ እጁን ያሳየኝ፡፡

ምዘና፡- የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 6፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. በክብ መንቀሳቀስ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- እንቅስቃሴ፣ ጭፈራ፣ ምት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

* እስቀድመው በፍላሽ/በሞሞሪ/በሰልኮት ሶስት የተለያየ ምት ያላቸውን ሙዚቃዎች ያዘጋጁ፣

* ህፃናቱን ከክፍል ውጪ ይዞ በመውጣት ክብ እንዲሰሩ ያድርጉ፣

* የሰሩት ክብ ውስጥ በቅድሚያ ያለሙዚቃ እያጨበጨቡ ባሉበት ቆመው ይንቀሳቀሱ

* ቀጥሎ ያዘጋጁትን ሙዚቃ በመክፈት የሙዚቃውን መደበኛ ምት ሰልት በመጠበቅ ወደቀኝ እና ወደግራ አቅጣጫ እንዲቀሳቀሱ ያድርጉ

* ከትንሽ እንቅስቃሴ በኃላ ሁለተኛውን ሲከፍቱ የሙዚቃውን ምት በመከተል ወደፊትን ወደኋላ በዚህ መልኩ እንቅስቃሴያቸውን እንዲቀይሩ፣

* ሶስተኛው ሙዚቃ ሲቀየርም ቁጭ ብድግ እያሉ እንዲያደርጉ ይንገሩቸው ከዚያም የተነገራቸውን መመሪያ በመከተል እንዲተገብሩ ያድርጉ በሶስቱም ሙዚቃ ከተንቀሳቀሱ በኃላ በመጀመሪያው ሙዚቃ ወዴት አቅጣጫ እንደተንቀሳቀሱ በሁለተኛው ሙዚቃ ላይስ ሶስተኛው ላይስ ይለያያሉ ወይስ ምታቸው ተመሳሳይ ነበር በማለት ይጠይቃቸው ከዚያም የሰሩትን እንቅስቃሴ አቅጣጫውንና በየትኛው የአካል ክፍሎቻቸው እንቅስቃሴውን እንዳደረጉ ይግለፁላቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* ጀፓስ፣

* ቴፕ፣

* ፍላሽና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከጨዋታው በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡- 1. ምን አይነት እንቅስቃሴ አደረጋችሁ?

2. እስኪ ይህንን ምት ተከትለህ ተንቀሳቀስ/ሺ?

3. በየትኛው የአካል ክፍልህ በመጠቀም ተንቀሳቀስክ/ሽ?

* ህፃናቱ በጨዋታ ወቅት የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ… በተገቢ ማዳመጥና መከታተል።

ተግባር 7፡- የመስክ ጉብኝት

ሀ. ቁሶችን በቀለም እና በአቅጣጫ መለየት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቅርጽ፣ ቀለም፣ አካባቢ፣ አቅጣጫ፣ ሰም

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ከሰር የተቀመጠውን ጉብኝት ለህፃናቱ ምን እንደሚያከናውኑ ግልጽ ያድርጉላቸው ለዚህም ማብራሪያ በመስጠት፡፡

* በመጀመሪያ መሰረታዊ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን በተለያየ ቀለም ለህፃናቱ እንዲይዙ በመስጠት ወደውጪ ይዞ መውጣት በመቀጠልም ከያዙት ቅርፅና ቀለም ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮችን በጉብኝት ወቅት እንዲናገሩና እንዲያሳዩ እንዲሁም ቁሱን የት እንዳገኙት እንዲናገሩ እና የቁሱን መጠሪያ ሰም ያድርጉ፡፡

* ቀጥሎ ካሉበት አቅጣጫ ሆነው በጊቢ ውስጥ ያለው ቁስ፣ተክሎች፣ መጫወቻዎች በየትኛው አቅጣጫ እንደለ መግለጽ እንዲችሉ ያድርጉ ይህንንም ሁሉም ህፃናት አቅጣጫን ከሌሎች አንግል ለይተው የመናገር ልምምድ ያድርጉላቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የተለያዩ ቅርጾችን የያዘ ምስልና ሞዴል፣
* መሰረታዊ ቀለማት፣
* ራሱ ቀለሙ ወይም የቀለም ካርድ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ክእጉብኝቱ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- 1. ምን አይነት የቀለም ካርድ ይዘሃል/ሻል?

2. የያዝከው ቀለም ካርድ ከየትኛው የተፈጥሮ ቀለም ጋር ይመሳሰላል?

3. ቁሱን የት ጋር አገኘሽው/ኸው፣ መጫወቻው በየትኛው አቅጣጫ ነው ያለው?

4. ትልቁ ዛፍ ከቆምሽበት/ከቆምክበት በየት አቅጣጫ ነው ያለው?

* ህፃናቱ በጉብኝቱ ወቅት የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ... በተገቢ ማዳመጥና መከታተል፡፡

ሳምንት አምስት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

- ዕቃዎችን በጋራ ባህሪያቸው መለየት
- ለሌሎች ርኅራኄ ማሳየት
- በማህበረሰባቸው ውስጥ ያሉ ህዝቦች ያላቸውን ሃላፊነት መገንዘብ
- ከአካል አቀማመጥ በመነሳት 6-10 የአካል ክፍሎችን ይጠቁማሉ
- አገራዊ በጎነቶችን መለየት
- 4-6 እንቅስቃሴዎችን ከኳደኛ ጋር ማሳየት
- ከሌሎች ጋር ጥሩ ግንኙነት ለመፍጠር የግብረገብ እሴቶችን መለማመድ
- የጂኦሜትሪ ቅርጾችን ምስል መለየት
- ፊደሎችን ደግሞ መፃፍ
- ስእሎችን ማቅለም
- በአካባቢያቸው ሰላሉ ቁሶች/ነገሮች መናገር

ንዑስ ይዘቶች፦

- መለየትና እና መመደብ
- ማህበራዊ ግንዛቤ
- የቦታ ግንዛቤ
- የሀገር ፍቅር
- ትላልቅ ጡንቻ መዳበር
- የግብረገብ እሴት
- ቅርፅ
- ፊደላት መጻፍ
- የፈጠራ አገላለጽ
- ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ አካባቢ

ተግባር 1፦ ተረት

ሀ. እማማ ዝናሽ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- በጎነት፣ ሃላፊነት፣ ግብረ ገብ፣ ርህራሄ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከስር የተቀመጠውን ተረት ለህፃናቱ የተረት አቀራረብ ቅደም ተከተልን ጠመጠበው ይንገራቸው።

* ምስል ወይም ቪድዮ በመጠቀም ስለበጎ ስራ ይግለፁላቸው ከዚያም እማማ ዝናሽ የሚለውን የአንድ የሴት አዛውንት ምስል በማሳየት ተረቱን ይንገሯቸው፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ስለ በጎ ስራ የሚገልጽ ምስል ወይም ቪድዮ

ተረት 1፦ እማማ ዝናሽ

በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖሩ እማማ ዝናሽ የሚባሉ አዛውንት ነበሩ። እማማ ዝናሽ ከድሮ ጀምሮ እጅግ ሩህሩህና ደግ ሴት ነበሩ። እቤታቸው ሰው ሲመጣ በፍቅርና በፈገግታ በመቀበል ያላቸውን ነገር በማቅረብ አስተናግደው ይሸኛሉ፡የተቸገረ ሰው ሲያገኙ ትንሽ ትልቅ፣ሃብታም ድሃ ብለው ሳዩለዩ ሁሉንም በሚችሉት ነገር ያግዛሉ። ሰዎችን የሚያከብሩና የሚወዱ በሰፈሩ የተከበሩ ትልቅ ሴት ናቸው። እማማ ዝናሽ ጡረታ ከመውጣታቸው በፊት በመንገስት መስሪያ ቤት በህዝብ ግንኙነት ቦታ ላይ በሃላፊነት ይሰሩ ነበር። ሀላፊነታቸውንም በሚገባ በመወጣታቸው ብዙ ጊዜ ተሸልመዋል። ከልጅነታቸው ጀምሮ በሰፈራቸው በበጎ ስራ ተግባርና በአካባቢ እንክብካቤ ላይ በመሳተፍ የተለያዩ በጎ ተግባራትን ይሰራሉ። ይህንንም በጎ ተግባር ልጆቻቸው እና የልጅ ልጆቻቸው እንዲሰሩ ሁል ጊዜ ማታ ማታ ቀን የሰሩትን ይተርኩላቸው ነበር። እቤታቸው እንግዳ ሲመጣ ለእንግዳው የእግር ውሃ እንዲሰጡና የሚያድር ከሆነ እግር እንዲያጥቡ አስለምደዋቸዋል፡ ፡ የልጅ ልጆቻቸውም እንግዳ በመጣ ቁጥር እጅ ለማስታጠብና እግር ለማጠብ ይሽቀዳደማሉ የመጡትም እንግዶች ይመርቃቸውና ያመሰግናቸው ነበር ይባላል።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

የሚከተሉት ጥያቄዎችን በቃል መጠየቅና የተረቱን ፍሬ ሃሳብ መንገር ያስፈልጋል።

1. እማማ ዝናሽ ምን ያደርጉ ነበር?
2. የልጅ ልጆቻቸው ምን ለማድረግ ይሽቀዳደሙ ነበር?
3. እንግዶቹ ምን ያደርጉ ነበር?
4. እናንተስ እቤት እንግዳ ሲመጣ ምን ታደርጋላችሁ?

ተግባር 2፦ የተግባር ሥራ

ሀ. ቁስ ድርደራ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቅርጽ፣ ባህሪ፣ ሰዕል

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ሰርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልሰ

የመምህር ሚና፡-

* ከሰር የተቀመጠውን ተግባር ለህፃናቱ ቅደም ተከተል በመጠበቅ እንዲተገብሩ ያድርጓቸው።

* ተመሳሳይ ቅርጽ ያላቸው የጂኦሜትሪ ቅርፆችን በሞዴል ወይም በካርድ ያዘጋጁ፣

* ያዘጋጁትን ቅርጽ ለሳፃናቱ ይሰጧቸውና የቅርጹን ባህሪ በማየት ክብ፣ ጎነ ሶስት፣ ጎነ አራት፣ ሞላላ ለብቻ በማድረግ እንዲደረድሩና ሰማቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ

* ከዚያም ከተናገራቸው ቅርፆች ውሰጥ ተመሳሳይ ያላቸውን ቅርፆች ለምሳሌ፡- ክብ፣ክብ...... አንድ ላይ በመደርደር፣ በመደራረብ፣ ሌላ ቅርፅ እንዲሰሩ ማድረግና የሰሩትን ቅርጽ ሰም እንዲናገሩ ማድረግ፣

* በመጨረሻም ከደረደሩት ምሰል መካከል ክብ፣ ሞላላ፣ ጎነ አራትና ጎነ ሶሰትን ደጋግመው በደብተራቸው በመሳል መጠሪያቸውን እንዲናገሩ ማድረግ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾች ካርድ/ሞዴል፣

* ደብተር እርሳስ፣

* ላጲስ፣

* እንዴት እንደሚደረደር ማሳያ በቪድዮ የተቀረጸ ምሰልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፡-

1. ምን አይነት ቅርጽ ነው?
2. ይህንን ቅርጽ የሚመሰል ቁስ በቤታችሁ ምን አለ?
3. አንዱ ቅርጽ ከሌላው በምን ይለያል?
4. ቅርፁን በመደርደር ምን ሰራህ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።

ለ. ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ እንቅስቃሴ፣ አካል፣ ግብረ ገብ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ ስርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ከስር የተቀመጠውን ተግባር ለህፃናቱ ቅደም ተከተል በመጠበቅ እንዲተገብሩ ያድርጓቸው፡፡

* ህፃናቱን ሁለት ሁለት በማድረግ ይመድባቸው፣

* ከተመደቡት ህጻን ጋር በመሆን እንቅስቃሴ ለመስራት ሚዛናቸውን በመጠበቅ በትክክል በመቆም እንዲዘጋጁ ያድርጉ፣

* ከዚያም

1- ሲባል (እጅ በማለት ከጓደኞቻቸው ጋር በአክብሮት እንዲጨባበጡ)

2- ሲባል (ወገብ በማለት ወገብን ይዘው እንዲደንሱ ማድረግ)

3- ሲባል (እግር በማለት ወደላይ መዝለል)

4- ሲባል (አንገት በማለት አንገትን ግራና ቀኝ ማንቀሳቀስ)

5- ሲባል (ውስጥ እጅ በማለት ማጨብጨብ)

6- ሲባል (ጉልበት በማለት ጉልበታቸውን አጥፈው ቁጢጥ ይላሉ)

* ከዚያም አብረው ያሉትን ጓደኛቸውን እባክህን አንሳኝ በማለት እንዲያነሳቸው ይጠይቃለሉ ሲያነሳቸው እርስ በእርስ እንዲመሰጋገኑ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን የያዘ ካርድ/ሞዴል፣

* የአካል እንቅስቃሴን የሚያሳይ ቪድዮ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. በምናችን እናጨበጭባለን?

2. እግራችን የት አለ?

3. ለሚያግዙን ሰዎች ምን በማለት መመለስ አለብን?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ፡፡

* ሁሉም ህፃናት እንቅስቃሴዎቹን በትክክል መስራታቸውን ይከታተሉ፡፡

ሐ. ፊደላትን መቅረጽ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቅርጽ፣ ፊደል፣ ማቅለም

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ከሰር የተቀመጠውን ተግባር ለህፃናቱ ቅደም ተከተል በመጠበቅ እንዲተገብሩ ያድርጓቸው።

* ስሌዳ በመጠቀም የተለያየ ቅርፆችን በመሳል ውስጡ ፊደላትን በመፃፍ ደጋግመው እንዲፅፉ ማድረግ፣ ምሳሌ፡- (ተ-ቱ-ቲ-ታ-ቴ-ት-ቶ እና ቀ-ቁ-ቂ-ቃ-ቄ-ቅ-ቆ) ፡፡

* ፈደሉን ደግመው ከፃፉ በኃላ መልሰው የጂኦሜትሪ ቅርፁን ብቻ ከሰር በመሳል እንዲያቀልሙ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* ፊደላትን የያዘ ካርድ፣ የጂኦሜትሪ ቅርፅ ካርድ/ሞዴል፣ እርሳስ፣ ደብተር፣ ባለቀለም እርሳስና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፡-

1. ምን ፊደል ደግመን ፃፍን?
2. ፊደል ለ ምን አይነት ቅርጽ ውስጥ ገብታለች?
3. ምን አይነት ቀለም ተጠቅማችሁ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።

* ሁሉም ህፃናት እንቅስቃሴዎቹን በትክክል መሰራታቸውን ይከታተሉ።

መ. ስዕሎችን ማቅለም (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቀለም፣ አካላት፣ ቁስ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ከሰር የተቀመጠውን ተግባር ለህፃናቱ መመሪያን ተከትለው ያከናውኑ ዘንድ ይግለፁላቸው።

* በደብተራቸው የሰውነት ክፍል ምስልና የተለያዩ በአካባቢያቸው የሚገኙ ምስሎችን ሰለው ያዘጋጁ።

* ከዚያም ምስሎቹን በማቅለም እንደየዓይነታቸው እንዲያገናኙና/እንዲያዛምዱ ከዚያም ያገናኙትን በማሳየት የቁሶቹንና የሰውነት ክፍሎቹን ሰማቸውን እንዲናገሩ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* እርሳስ፣ ደብተር፣ ባለቀለም እርሳስ፣ የተቀባ ምስልና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፦

1. ከቁሶች መካከል ምን አቀለማችሁ?
2. ከሰውነት ክፍሎች መካከል ምን አቀለመችሁ?

* ህፃናት ደብተራቸው ላይ በትክክል ማቅለማቸውንና ማዛመዳቸውን ይመልከቱ እና ድጋፍ ለሚያስፈልገው ድጋፍ ያድርጉ።

ተግባር 3፦ የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. አሻንጉሊት ገጠማ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ የሰውነት ክፍል፣ አቅጣጫ፣ ርህራሄ፣ በጎነት

የማስተማሪያ ዜዴ፦ ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

ቀጥሎ የቀረበውን ጨዋታ የጨዋታውን ህግ ተከትለው እንዲጫወቱ ያግዟቸው።

* የሰውነት ክፍል ምስል የሚያሳይ ሞዴል/የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚነቃቀል አሻንጉሊት ያዘጋጁ።

* በመቀጠል ያዘጋጁትን አሻንጉሊት ወይም ሞዴል ለህጻናቱ በመስጠት ቀኝ እጅ ግራ እጅ፣ ቀኝ እግር፣ ግራ እግር፣ ቀኝአይን፣ ግራ አይን፣ ቀኝ ጆሮ፣ ግራ ጆሮ፣ አፍንጫ፣ ሆድ ወዘተ እየነካኩ እንዲጫወቱና እንዲንከባከባቸው ያድርጉ።

* በመሀል የአሻንጉሊት እጅ፣ እግር በማውለቅ ሰው ቢሆንስ እንዴት ሊያማቸው እንደሚችልና እኛ ደግሞ እጅና እግራቸውን በመመለስ መራራት መንከባከብ እንዳለብን እጅና እግር የሌላቸው ሰዎች ካሉ ደግሞ ለእነሱ በበጎነት ማገዝና መርዳት እንዳለብን ያሳዩአቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

አሻንጉሊት፣ የሰው ሞዴል፣ የሰው አካል ክፍሎች የሚያሣይ ስዕል

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፦

1. ሰዎች አካላቸው ሲጎዳ ምን ይሰማቸዋል?
2. እኛ ለጓደኞቻችን ርህራሄ የምናሳየው ለምንድን ነው?
3. ቀኝ እጅ፣ ግራእጅ፣ ቀኝ አይን ግራ አይን .... አሳየኝ/ዪኝ

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናዉኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።

* ሁሉም ህፃናት እንቅስቃሴዎቹን በትክክል መስራታቸውን ይከታተሉ።

ተግባር 4፡- ውይይት

ሀ. የሰዎች ሀላፊነትና የሀገር ደግነት (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሀገር መውደድ፣ ሀላፊነት፣ ደግነት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ከስር የተቀመጠውን ተግባር ለህፃናቱ ቅደም ተከተል በመጠበቅ እንዲተገብሩ ያድርጓቸው።

* በቅድሚያ ጊዜው የውይይት እንደሆነ ይንገሯቸው።

* የዕለቱን ውይይት ርዕሰ ያሰተዋውቁ።

* ምስል/ቪድዮ በመጠቀም ሰለሰዎች ሀላፊነትና ለሀገራቸው በጎ ተግባራትን የሰሩ ሰዎች በማሳየት ገለፃ ያድርጉላቸው፣

* ከዚያም ሰዎች ሰላላቸው ሀላፊነትና ሀላፊነታቸውን በአግባቡ በመወጣት ለሀገራቸው በጎ ተግባራት ሰለሰሩ ሰዎችና ከነዚህ ውስጥ ለሌሎች ሰዎች ርህራሄ በማድረግ በበጎ ሰራ ላይ ሰለተሰማሩ ሰዎች በማንሳት ሰላደረጉት በጎ ተግባራት እንዲወያዩ ማድረግ።

* ምሳሌ፡- በጎ የሰሩ ሰዎች አበበች ጎበና በራሳቸው ተነሳሽነት ወላጅ አልባ ህፃጽናትን ሰብሰበው የሚያሳድጉ፣ ክቡር ዶክተር ቢኒያም የመቄዶኒያ አረጋዊያን መርጃ ድርጅት የመሰረቱ

¨ሀላፊነት ላይ ያሉ ሰዎች ድግሞ፡- የሀገር መሪዎች፣ የትምህርት ቤት ሃላፊዎች፣ የሆስፒታል ሃላፊዎች... ወዘተ ሰላለባቸው ሃላፊነት በደንብ መወያየት

* ሀላፊነትን አለመወጣት የሚያሰከትለውንም ችግር አብረው ይወያዩ ።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከውይይቱ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡- 1. የሰዎች ሀላፊነት ምን ምን ናቸው?

2. በበጎ ተግባር ላይ የተሳተፉ ሰዎች ምን ይሰራሉ?

3. ከሀገራችን በጎ ሰራ የሰሩ/ የሚሰሩ ሰዎች ውስጥ ማንን ታውቃላህ/ሽ?

4. እናንተ ምን ሀላፊነት አለባችሁ?

5. ወላጆቻችሁ ምን ምን ሀላፊነት አለባቸው?

* ህፃናቱ በውይይቱ ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ... በተገቢ ማዳመጥና መከታተል።

ተግባር 5፡- መዝሙር

ሀ.ሀገሬ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቅርፅ፣ አካባቢ፣ አቅጣጫ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* ስለሃላፊነት፣ ስለበጎነት የሚገልፁ ምስሎች/ሞዴሎች

መዝሙር 1፡- ሀገሬ

ሀገሬ
አልሻም ማየት በሀገሬ
ወገኔ ወድቆ አዝኖ ዛሬ
ኑ ሰዎች በርቱ እንረዳዳ
ካልተጋገዝን ከባድ ነው እዳ
ሃላፊነት አለብን ከልብ
መተዛዘን የኛ ደንብ
መከባበር አስፈላጊ ነው
አብሮ ለመኖር ጠቃሚ እኮ ነው፡፡

ምዘና፡- የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል፡፡

ለምሳሌ፡- ከሌሎች ጋር መልካም ግንኙነት የምንፈጥረው እንዴት ነው?

ተግባር 6፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. ሀላፊነት መወጣት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- በአካባቢ ያሉ ቁሶች/ነገሮች፣ ሃላፊነት፣ ግብረ ገብ፣ ተግባቦት

የማስተማሪያ ዘዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ከሰር የተቀመጠውን ጨዋታ ለህፃናቱ ቅደም ተከተል በመጠበቅ እንዲጫወቱ ያድርጓቸው።

* እስቀድመው ከክፍል ከመውጣታቸው በፊት እንዴት መጫወት እንዳለባቸው ቪድዮ ወይም ምስል በመጠቀም ያሳዩአቸው፣

* ህፃናቱን ወደ ደጅ በማስወጣት በቡድን በመከፋፈል መመደብ፣

* የውጪ መጫወቻዎች ላይ እኩል ቁጥር በማድረግ በሸርተቴ፣ በእሽክርክሮሽ፣ በመሹለኪያ ትቦ፣ ዡዋዡዌ፣ መሰላል ላይ መመደብ፣

* በተመደቡበት መጫወቻ ላይ በስነ ሰርዓት ተራን በመጠበቅ እንዲጫወቱ እና የተሰጣቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ ያድርጉ።

* የተጠቀሱት መጫወቻ ላይ መውጣት የማይችሉ ህጻናት ካሉ በበጎነት እንዲያግዛቸው ይንገሩዋቸው፣ ያለተራ ለመጫወት የሚሞክሩ ህጻናት ካሉ ከሌሎቹ ጋር ለመግባባት ተራ ጠብቀው መጫወት እንዳለበቸው ይግለፁላቸው። ምክኒያቱም ሀላፊነትን አለመወጣት አብረውን ያሉ ሰዎችን ሊጎዳ እንደሚችል ይንገሯቸው።

* ተጫውተው ሲጨርሱ ምን መጫወቻ ላይ እንደተጫወቱና ማን እንዳጫወታቸው ያጫወታቸው ሰው የሰራ ድርሻው ምን እንደሆነ በተራ እንዲናገሩ እድል ይሰጣቸው።ምሳሌ፡- እኔ የተጫወትኩት መንሰላል ላይ ነው ያጫወተችን ደግሞ መምህርት ሰላም ነች ሃላፊነታ እኛን ማሰተማርና መንከባከብ ነው።

* በተጨማሪም ውጭ በሚጫወቱበት ጊዜ አከባቢያቸውን የማየጥ ልምድ እኒዲኖራቸው ምን ምን ቁሶች/ ነገሮች እንዳሉ በደንብ እዲመለከቱ በማድረግ በክፍል ውሰጥ ይጠይቋቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የውጭ መጫወቻዎች እሽክርክሮሽ፣ ሸርተቴ፣ ሚዛን፣ መንሰላል፣ መሹለኪያ ትቦ፣ ቪድዮና ምሰልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከጨዋታው በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡- 1. ምን አይነት መጫወቻ ላይ ተጫወታችሁ?

2. ስትጫወቱ ምን መጠበቅ አለባችሁ?

* ህፃናቱ በጨዋታ ወቅት የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ… በተገቢ ማዳመጥና መከታተል።

ተግባር 7፦ የመስክ ጉብኝት

ሀ. የቅርብ አካባቢን መጎብኘት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ መለያ ስም፣ አካባቢ፣ ሃላፊነት፤ ተግባቦት፣ ባህሪ

የማስተማሪያ ዜዴ፦ ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

ከስር የተቀመጠውን ተግባር ህፃናቱ ቅደም ተከተል በመጠበቅ እንዲተገብሩ ያድርጓቸው፡፡

* የመስክ ጉብኝት የሚደረግበት ጊዜ መሆኑን ይንገራቸው፣ በጉብኝት ወቅት ከሌች ጓደኞቻቸው ጋር በመግባባት መሆን እንዳለበት እንጂ በመገፋፋት በመረባበሽ ጉብኝቱን የተሳካ ማድረግ እንደማይቻል መንገር፡፡

* ከጉብኝት ጥሩ ጓደኝነት ትዥታ ማስቀረት እንዳለባቸው ይግለጹላቸው፡፡ በተጨማሪም በጉብኝት ወቅት አብራችሁ በስልኮትም ቢሆን ፎቶ በመነሳት አሳጥበው በክፍላቹ ውስጥ ይሰቀሉት፡፡ ይሁኔታ ለህፃናቱ ተግባቦት እና ባህሪ ጥሩ ይሆናል፡፡

* በጉብኝቱ ወቅት በትኩረት ማየት ስላለባቸው ነገሮች ይግለፁላቸው አካባቢያቸው ላይ ስለሚገኙ መገልገያ ቁሶች፣ በትምህርት ቤት ስላሉት ሃላፊነቶች፣ ስለ ክፍሎቹ፣ ቢሮዎች የመጫወቻ ሜዳ የመሳሳሉትን ማየት እንደሚገባቸው ይንገራቸው፡፡

* በአካባቢያቸው ላይ ስለሚገኙ ቁሶች መጠሪያ ሰማቸውን የማያውቃቸው ከሆነ እንዲጠይቁና በግቢ ውስጥ ያሉትን መገልገያ ክፍሎች እንዲጎበኙና በግቢ ውስጥ ያሉትን ሰራተኞች ሀላፊነት እንዲናገሩና የራሳቸውንም ሀላፊነት አብረው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

* ስለቅርብ አካባቢና ስለ ማህበረሰብ ሀላፊነት የሚገልጽ ምሰል/ሞዴል፣ ሞባይል ስልክ/ፎቶ ካሜራ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ክእጉብኝቱ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፦ 1. በጉብኝቱ ወቅት ምን ምን ክፍሎች ተመለከታችሁ?

2. ምን አይነት የማህበረሰብ ሀላፊነት አላቸው?

3. ከሰዎች ጋር ተግባቦት መፍጠር ለምን ያስፈልጋል?

* ህጻናት በጉብኝት ጊዜ የተፈለገውን እውቀትና ክህሎት ማግኘታቸውን ይመልከቱ፡፡

የአውድ 1 ማጠቃለያ መመዘኛ ቼክ-ሊስት

የህጻኑ/ኗ ስም:______________________________ ጾታ: _______ ዕድሜ______

ተ.ቁ	የ ሚጠበቀው የዕድገትና መማር ውጤት	ዝቅተኛ	መካከለኛ	ጥሩ	በ. ጥሩ
1	መመሪያዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ማብራሪያዎችን ማዳመጥ እና ተግባራዊ ማድረግ				
2	ስለ ፍላጎታቸው፣ ስለ ወዳጆቻቸው፣ ስለታወቁ ህዝቦች፣ በአካባቢያቸው ስላሉት ነገሮች እና ስለአካላዊ ባህሪያት መነጋገር				
3	የተለያዩ ድምፆችን፣ አመጣጡን ለይተው ማወቅ እና ከሰዕሎች ጋር ማጣጣም				
4	አንድ ሰው የራሱ ድርጊት በሌሎች ሰዎች ስሜት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር መረዳት				
5	በተገቢው መንገድ ፍላጎቶችን፣ ምርጫዎች፣ ችሎታዎችን እና ስሜቶችን መግለጽ				
6	የመጫወቻ ደንቦችን ማወቅና እና መከተል				
7	እቃዎችን በመጠን፣ ርዝመት፣ ቅርጽ፣ እና ዓይነት መመደብ				
8	ዜሮ ምንም እንደሆነች ማወቅ				
9	እስከ 15 ቁጥሮችን በቃል መቁጠር፣ ማንበብ፣ መጻፍ				
10	የንጽህናን አስፈላጊነት መረዳት፣ ንጽህናቸውንም መጠበቅ				
11	ራሳቸውን መረዳት				
12	ቁሶችን በመያዝ፣ በመቅለብ፣ በመግፋትና በመወርወር መቆጣጠር				
13	የታወቁ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መለየት እና ማብራራት				
14	የቅርብ አካባቢንና ደህንነት እንክብካቤ ተረድተው መንከባከብ				
15	የቤተሰብ አባላትና የሙዚቃ መሳሪያ ድምጽ መለየትና ማወቅ				
16	የቤትና የትምህርት ቤት አከባቢያቸውን ማድነቅ				

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፦ ____

____

____

____

አውድ ሁለት፦ እንስሳት

ለአውዱ የተሰጠ ጊዜ፦ 6 ሳምንት/180 ክ/ጊዜ

መግቢያ

ይህ የመማር አውድ የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ለማዳበር ታስቦ ስድስት የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን በተቀናጀ የማስተማር ዜዴ ለማቅረብ የተዘጋጀ ነው። በዚህ አውድ እንዲቀናጁ የታሰቡ ስድስቱም የትምህርት ይዘቶች (የቋንቋ እድገት፣ የቅድመ-ስሌት፣ የአካላዊ መዳበር፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ዕድገት፣ ክዋና ስነ-ጥበባትና ሳይንስ) ናቸው። ህጻናት እነዚህን ይዘቶች በተቀናጀ መልኩ እንዲገነዘቧቸው ለማስቻል በህጻን ተኮር የማስተማር ዜዴ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ተግባራትን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።ከዚህ አንጻር ክልሎች ትምህርቱን ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም አካባቢን መሠረት ባደረገ መልኩ መስጠት ተገቢ ነው ። በዚህ የመምህር መምሪያ፣ ደረጃ በደረጃ መምህሩ ምን መተግበር እንዳለበት ግልጽ ቢደረግም መምህራን የሕፃናቱን የችሎታ መጠንና የክፍሉን ሁኔታ በመገንዘብ ትምህርቱን ቅደም ተከተል በማስያዝ የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲጠቀሙ ዕድል ተሰጥቷቸዋል። በዚህ አውድ የሚዳሰሱ ስድስቱም የትምህርት ይዘቶች ከህጻናቱ መማር ደርጃና እድገት ጋር ተቆራኝተው በዝርዝር ተቀምጠዋል። በዚህ አውድ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ቅደምተከተላቸውን ጠብቀው ለስድስት ሳምንታት ተዳራጅተዋል።

የእድገትና የመማር ውጤቶች፦

ህጻናት ከዚህ አውድ ትምህርት በኋላ፦

- o የሚሰጡ ሆያትን ደግሞ መፃፍ
- o የታሪኮችን መልዕክት መልሶ መናገር
- o ከፆታዊ ወገኝትነት የፀዳ አስተሳሰብን ማከናወን
- o እንደ የራስን ጫማ ማሰር መሰረታዊ የሆኑትን ክሎቶችን በወላጅ እና በመምህር እገዛ ማከናወን
- o ትክክልና ስህተት የሆነውን ከማበረታታትና ከቅጣት አንጻር መረዳት
- o እስከ 15 ድረስ ያሉ ቁጥሮችን እና እቃዎችን ማዛመድ
- o እስከ 15 ድረስ ያሉ ቁጥሮችን ማግናኘት፣መገልበጥ፣መፃፍ እና የቁጥሮች ቅደም ተከተል ማስያዝ
- o የቁጥሮችን ቀዳሚና ተከታይ መለየት
- o የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እና መመገብያ ቦታ ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊነትን መግለፅ
- o እርሳስን በተገቢው ሁኔታ በመያዝ የሚለዩ ሆሄያትን እና ቁጥሮችን መፃፍ
- o ለተለያዩ እንቅስቃሴዎች ትንንሽ ጡንቻን መቆጣጠር እና መጠቀም

o በቤት ውስጥ የሚታወቁ እቃዎችና ባህሪያቸውን መግለፅ
o የሌሎችን ሃላፊነት ስራ እና ሙያዎች እውቅና መስጠት
o ግንባታን፣ መሳልን፣ ማቅለምን፣ ቀለም መቀባትን፣ ህትመትን፣ ቅርፃቅርፆችን መፍጠር
o መሰረታዊ የጆሜትሪ ቅርፆችን በአካባቢ ከሚገኙት ቅርፆች ጋር ማገናኘት

አበይት ይዘቶች፡-

- ራሰን ማስተዋወቅና ሰሜትን መግለጽ
- የሰው ሰውነት ክፍሎች
- የቅርብ አካባቢ
- ቁጥርና ቆጠራ
- ጤናና አካላዊ ጥንካሬ
- ፍደላትና ድምጾቻቸው
- የግል ንፅህና ልምዶች
- የራሰን መግዛትና መንከባከብ
- የእንሰሳት ሰም መለየት
- ማለያየትና መመደብ
- ህትመትን መረዳት
- የሆያት ድምፅና ቅርፅ
- ፍደላትን ማንበብ፣ መገልበጥና መጻፍ
- የቃላት እውቀት
- ማወዳደርና ቀደም ተከተል ማሰያዝ
- ቀለም መቀባት
- ሥርዓተ-ድርድር
- እንቅሰቃሴዎች
- ቅርጸ ቅርጾች
- ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አካባቢ
- ለችግር መፍትሄ መፈለግ
- የምግብ አይነቶች
- እራሰን ከአደጋ መጠበቅ
- የጆሜትሪ ቅርጾች
- ታሪክ መናገር
- የቴክኖሎጅ መሳሪያ
- ሌሎችን መርዳት
- ባህላዊ ጭፈራ
- ሳንቲም/ብር
- ሥራ ማክናወን

ሳምንት ስድስት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

- እራሳቸውን ያስተዋውቃሉ
- ስሜታቸውን ይገልፃሉ
- ከሌሎች ህፃናት ጋር ይግባባሉ
- ከ5 እስከ 8 ያሉ የሰውነት ክፍሎችን ይሰይማሉ
- የራሳቸውንና የጎረቤታቸውን አካባቢ ይፈትሻሉ፣
- የግል ንፅህና አጠባበቅ ልምዶችን ያዳብራሉ፣
- በአካባቢያቸው የሚገኙ ህይወት ያላቸውን ነገሮችን ይለያሉ፣
- ስዕሎችን በማየት የሰዎችን ስሜት ይገነዘባሉ፣
- ከ15 የማይበልጡ ቁሶችን ይቆጥራሉ ፣
- እስከ 15 ያሉ ቁጥሮችን ያነባሉ፣
- ፊደላትን ደግሞ ይፅፋሉ

ንዑስ ይዘቶች፦

- ራስን ማስተዋወቅ
- ራስን ማዎቅ
- ራስን መግለጽ
- የሰውነት ክፍሎች
- የቅርብ አካባቢ
- ጤና
- የቃላት እውቀት
- ንባብ
- ቁጥርና ቆጠራ
- ውበትን መረዳት
- መፃፍ

ተግባር 1፡- መዝሙር

ሀ. እስቲ ልንገራችሁ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ህይወት ያላቸው ነገሮች፣ የግል ንፅህና፣ የሰውነት ክፍል፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

*የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ስእል፣ የድመት ምስል፣ የሠውነት ክፍል ስዕል፣ የቁጥር ፍላሽ ካርድና ወዘተ

መዝሙር 1፡- እስቲ ልንገራችሁ

እስቲ ልንገራቹ የሰውነት ክፍሎቼን
አጸዳለው ከምግብ በፊት እጆቼን
በየጊዜው ጥርሰና ጥፍሮቼን
አፀዳለው የሰውነት ክፍሎቼን
አይን አንደኛ ነው ጆሮ ሁለተኛ
ሶስተኛ አፍንጫ ነው አንገት አራተኛ
ደረት አምስተኘኛ ወገብ ስድስተኛ
እጄ ሰባተኛተኛ እግር ሰምንተኛ
ሁልጊዜ ገላዬን እተጣጠባለሁ
የሰውነት ክፍሎቼን በደንብ እቆጥራለሁ
ህይዎት ያላቸውን እንስሳት እጽዋት
እንከባከባለሁ ሁሌ በብልሃት።

ምዘና፡- የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል።

ለ. እኔና ጓደኞቼ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ስም፣ ፊደል፣ መደሰት፣ መከፋት፣ መቁጠር

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

የቁጥርና የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ ቻርት፣ መቅረፀ ድምፅ፣ ሞባይል፣ፊላሽ፣ ስሜትን የሚገልፁ ምስሎች

መዝሙር 2:- እኔና ጓደኞቼ

ጓደኞቼ! ፊደላት በቅርጻቸውና በድምጻቸው የተለይዩ ናቸው

ሻላላ ሻላላ ሻላላ ሻላላ

በ ሰ ሸ ከ ቡ ሱ ሹ ኩ

ደ ጀ ዘ አ ዱ ጁ ዙ ኡ

ሻላላ ሻላላ ሻላላ ሻላላ

እኔ ሰሜ ሃና ነው መጫወትም እወዳለው

ጓደኞቼን አከብራለው ሲከፋቸው ይከፋኛል

እነሱማ ሲደሰቱ እኔም በጣም ደስ ይለኛል

አብረንም እንማራለን

ቁጥሮችንም እንቆጥራለን

እንጀምር 1 2 3 4 ቀጥሉ 5 6 7 8 ቀጥሉ

9 10 11 12 ቀጥሉ 13 14 15 በጣም ጥሩ

ቸብቸብቸብ ድገሙ ቸብቸብቸብ። 2x



ምዘና:- የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል።

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ. መሳልና መቁጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ስም፣ ቁጥር፣ መግባባት፣ ህይወት ያላቸውና የሌላቸው ነገሮች

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ሰርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረቡ የሰራ ተግባራት እንዲሰሩ ለማስቻል የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል መሰረት እንዲያከናውኑ ያድርጉኣቸው፡

- በመጀመሪያ ህፃናቱ በትናንሽ (4 እስከ 5 አባላት የያዘ) ከቡድን እንዲደራጁ ያድርጉ በመቀጠልም በየቡድኑ የጋራ መሳያ ወረቀጥ /ቻርት፣ እርሳስ፣ላጲስ… እና አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ይውሰዱ።
- ቀጥሎ ባደራጁት ቡድን ልክ ግማሹ ህይወት ያላቸው ነገሮች፣ ግማሹ ደግሞ ህይወት የሌላቸው ነገሮች የተፃፉበት ካርድ ያዘጋጁ። ከየቡድኑ አንዳንድ ህፃናት በማስነሳት እጣ እንዲያወጡ ያድርጉ።
- ቀጥሎ ሁሉም ቡድን የደረሰውን መሰራት ይጀምራል። በቡድኑ ውስጥ ያሉት ህፃናት በሙሉ ይሰላሉ። ምሳሌ፡- ህይወት ያላቸው የደረሳቸው ቡድኖች መጀመሪያ ምን ምን መሳል እንዳለባቸው ይመካከራሉ ከዚያ ሁሉምየቡድን አባላት ተከፋፍለው በመሳል ቀለም ይቀባሉ። ሌሎቹም በተመሳሳይ ይሰራሉ።
- የተሰጣቸውን ጊዜ ሲያበቃ ለጓደኞቻቸው ስማቸውን በመንገር የሳሉትን ሰዕል ምንነት ከተናገሩ በሁዋላ ቆጥረው እንዲያሳዩ ያድርጉዋቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* እርሳስ፣
* ወረቀት/ደብተር፣
* ላጲስ፣
* ቀለምና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ግሌ ማህደር

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፡-

1. ምን ሰዕል ሳላችሁ?
2. ለመሳል ምን ተጠቀማቹ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።
* በመጨረሻም ሥራቸውን በግሌ ማህደራቸው ውስጥ በማደራጀት ለውጣቸውን ይመልከቱ።

ለ.በአሸዋ ፊደላትን እና ቁጥሮችን መፃፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ስሜት፣ ንፅህና፣ መግባባት፣ ፊደል፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ ሰርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረቡ የተግባር ስራ እንዲሰሩ ለማስቻል ገለፃ ማድረግ፣ አስፈላጊ ቁሳቁስ ማቅረብ እና ዝግጁ ማድረግ አስፈላጊ ነው

 በመጀመሪያ ህፃናቱ ተራቸውን ጠብቀው ለመጫወት እራሳቸውን ተቆጣጥረው መጠበቅ እንዳለባቸው ሲሰሩም በመግባባት መሆን እንዳለበት መንገር ቀጥሎ የጓደኞቻቸውን ስሜት በመጠበቅ ደስተኛ ሆነው ተግባሩን እንዲያከናውኑ መንገር ተግባሩ የእጅ መቆሸሽ ስለሚያስከትል ሳሙናና ውሃ በማቅረብ እንዲታጠቡ ማድረግ ጤናማ ጉዳይ ነው።

 ቀጥሎ የአሸዋ ሳጥን/መዘፍዘፊያ/በሰፊ ካርቶን ውስጥ የተዘጋጀውን አሸዋ ከፊት ለፊት ጠረጴዛ ላይ ለሁሉም በሚታይ መልኩ ማስቀመጥ ከዚያም ህፃናቱ ተራ በተራ እየተነሱ ከፊደላትና ቁጥሮች ኮርነር ጋር ሄደው የሳምንቱን ቁጥር (10 እስ 15) እና ፊደል (ደ-ዱ-ዲ-ዳ-ዴ-ድ-ዶ እና ቀ-ቁ-ቂ-ቃ-ቄ-ቅ-ቆ) በመውሰድና ፊደላት እና ቁጥሮቹን በተዘጋጀው አሸዋ ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ። በመቀጠልም የሰሩትን ፊደላትና ቁጥሮች ለጓደኞቻቸው ይንገሯቸው ሲጨርሱም የወሰዱትን ፍላሽ ካርዶች/ሞዴሎች በቦታቸው መልሰው እጃቸውን ይታጠቡ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

* አሸዋ፣ የተላያየ ለአሸዋ መያዢያ የሚሆን መዘፍዘፊያዎች፣

* ሰፋፊ ካርቶኖች፣

* የፊደላትና ቁጥሮች ፍላሽ ካርድ፣ ስሜትን የሚገልፁ ምስሎች፣ ሳሙና እና ውሃ፣ ማስታጠቢያና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፦

1. ምን ፊደል፣ ስንት ቁጥር፣ ፃፍሽ/ክ?
2. በስራ ሰዓት የጓደኞቻችሁ ስሜት እንዴት ነበር?
3. ስርታችሁ ስትጨርሱ ምን አደረጋቹ?
4. የዛሬዋ ፊደል ቤተሰብ እነማን ናቸው?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።

* ሁሉም ህፃናት ፊደላቱንና ቁጥሮችን በትክክል መጻፋቸውን ይከታተሉ።

ሐ. ቁስ መቁጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት:- አስራ አምስት ቁጥር፣ ቁሳቁስ፣ መቁጠር

የማስተማሪያ ዘዴ:- በገለፃ፣ ስርቶ በማሳየት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና:-

ከስር የተቀመጠውን ተግባር ለህፃናቱ ቅደም ተከተል በመጠበቅ እንዲተገብሩ ያድርጓቸው።

* 15 የምሆኑ ተቆጣሪ ቁሶችን ማቅረብ፣
* ተራ በተራ እየተነሱ የተቀመጡ ቁሶችን እንዲቆጥሩና ከቀረቡ ፍላሽ ካርዶች ጋር እንዲያዛምዱ ያድርጉ።
* ተግባሩን ሁሉም ህጻናት ማከናወን እስኪችሉ ድረስ ያስሞክሯቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

* የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣
* በክፍል ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁሶች፣ጠረጴዛና ወዘተ

ምዘና:- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ:-

1. ስንት ቁስ እንደቆጠሩ፣ የቆጠሩትን ቁስ ምን እንደሆነ እና ኬት ቦታ እንዳነሱት መጠየቅ፤

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ።

ተግባር 3:- ውይይት

ሀ. ህይወት ያላቸው ነገሮች (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት:- ስሜት፣ መግባባት፣ መተዋወቅ፣ ህይወት ያላቸው ነገሮች

የማስተማሪያ ዘዴ:- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና:-

• በቅድምያ ለህፃናቱ በውይይት ወቅት መከተል ያለባቸውን ሂደት ግንዛቤ መፍጠር እና ዝግጁ ማድረግ፤

• በመቀጠል ሶስት ሶስት ህፃናት ወንድና ሴትን በመቀላቀል ቡድን መቦደን እና ለውይይት በሚመች መልክ ማስቀመጥ፤

• ለውይየጥ የሚሆኑ የተለያዩ ህይወት ያላቸው እና የሌላቸው ቆሶች በየቡድኑ ማስሰጠት የሰው፣ የዛፍ፣ የእንስሳት፣ የአበባ፣ የክፍል ናየቤት ቁሳቁስ ... አዘጋጅቶ በየቡድኑ የተለያየ መስጠት፤

• ህፃናቱ ቀጥሎ ያሉት የትኩረት ነጥብ መሰረት በማድረግ ይወያዩ (ህይወት ያለው ነገሮች ያላቸውን መለያ ባህሪ፣ ቅርፃቸውን መነሻ አድርገው ይወያዩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

* የተለያዩ ህይወት ያላቸውና የለላቸው ነገሮች (የሰው፣ የእንስሳት፣የተክሎች፣ የቤት/የክፍል ቁሳቁስ ስዕል/ በፍላሽ ካርድ/ሞዴል) እና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከውይይቱ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፦ 1. ህይወት ያላቸውና የሌላቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

2. ከጓደኞቻቹ ስትወያዩ ምን ገጠማቹ?

* ህፃናቱ በውይይቱ ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ... በተገቢ ማዳመጥና መከታተል።

ተግባር 4፦ ተረት

ሀ. ተግባቢው አብዲ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ቆጠራ፣ ስሜት፣ ጎረቤት፣ አብሮ መጫወት፣ ተፈጥሮ፣ ህኪም ቤት፣ ተግባቦት

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፦

ከሰር የተቀመጠውን ተረት ለህፃናቱ የተረት አቀራረብ ቅደም ተከተልን ጠመጠበው ይንገራቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ስለ በጎ ስራ የሚገልጽ ምስል ወይም ቪድዮ

ተረት 1፦ እማማ ዝናሽ

አብዲ የሚባል ተግባቢና ተጫዋች የሆነ በአንድ ቆንጅዬ የሆኑ የቆርቆሮ፣ የድንጋይ፣ የሣርና የጭቃ ቤቶች ያሉበት መንደር ውስጥ ይኖር ነበር። አንድ ቀን ከጎረቤት ጓደኞቹ ጋር ለመጫወት ወደነሱ እየሄደ ሳለ የጎረቤቶቻቸው ቤት አከባቢ ትልልቅ የፍረፍሬ ዛፎችና አበቦች ተውበው አየ። በጣም እያደነቀ ሲሄድ ከዛፎቹ ስር ጠግበው አረፍ ያሉ ሶስት ላሞች፣ ሁለት አህዮችና ሁለት ዶሮዎች ከ አራት ጫጩቶች ጋር በጠቅላላው 15 እንስሳትን እየቆጠረ እዛው ፈዞ ቀረ። ጎረቤቱ ወርቄ “አብዲ ምነው ቆመህ ቀረህ? ጨዋታውኮ አመለጠክ!” አለችው። እሱም እነዚህን ውብ ተፈጥሮዎች በማየት በደስታ ስሜት ውስጥ ገባሁ። “ነይ በቃ እንጫወት!” በማለት እየሳቁና ተፈጥሮን እያደነቁ በመሄድ ላይ ሳሉ ወርቄ “አብዲ ሰማህ እንዴ? ከታች ያሉት ጎረቤታችን ልጅ እኮ ሳይታጠብ ምግብ እየበላ ሆዱን አሞት ሀኪም ቤት ገባ” አለችው። አብዲም በጣም ደንግጦ መምህራችን እኮ ሁል ጊዜ ንፅህናችንን እንድንጠብቅ፤ ጥፍሮቻችንን እንድንቆርጥ፤ አፋችንን እንድናጸዳ ብዙ ነገር ነግራናለች። እሱ ግን አልሰማትም በማለት አዘነ። “ወርቄም አትዘኝ! ታክሞ ሲወጣ እንመክረዋለን፤ አሁን ወደ ጨዋታችን እንሂድ” በማለት ተያይዘው ወደ ጨዋታቸው ሄዱ ይባላል።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

የሚከተሉት ጥያቄዎችን በቃል መጠየቅና የተረቱን ፍሬ ሃሳብ መናገር ያስፈልጋል፡፡

1. የአብዲ ጎረቤት ቤቶች ከምን የተሰሩ ናቸው?
2. የአብዲ ጎረቤት ልጅ የታመመው ለምን ይመስላችኋል?
3. አብዲ መምህራችን ምን ነግራናለች አለ?

ተግባር 5፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ስሜት ማንበብ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ስሜት፣ ቁጥር፣ ትውውቅ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ስርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና:-

የሚከተለውን ጨዋታ ህጻናት በተነገራቸው የጨዋታው ህግና ስርዓት መሰረት እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡

* በመጀመሪያ የተለያየ ስሜትን የሚገልፁ ስእሎችን ማዘጋጀት እና ከሌሎች ስእሎች ጋር ቀላቅሎ ማስቀመጥ
* ከፊት ተጫዋች ልጆችን መምረጥ እና ከተሰበሰበው ስእል ውስጥ ሌሎቹ ተማሪዎች ከ1-15 እስኪቆጥሩ ድረስ ስሜት ገላጭ ስእሎችን መርጠው አውጥተው ስሜቱን መገንዘብ፤
* በመቀጠልም የራሳቸውን ስም ካስተዋወቁ በኋላና ስለራሳቸው ስሜት ተናግረው የያዙትን ስሜት ገላጭ ስዕል እንዲናገሩ ማድረግ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

ስሜት ገላጭ ስዕሎቭና ልጆች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡-

* ያነሳቹት ስዕል ምን አይነት ስሜትን ይገልፃል?
* ስንት ቁጥር ላይ ስእሉን አገኘክ/ሽ?
* ስንት ቁጥር ሲጠራ ስዕሉን አገኘሽ/ህ?
* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ፡፡
* ሁሉም ህፃናት እንቅስቃሴዎቹን በትክክል መሰራታቸውን ይከታተሉ፡፡

ለ. ፊደል የመጻፍ ውድድር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ መፃፍ፣ ተግባቦት፣ መከባበር፣ መደጋገፍ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን ጨዋታ ህጻናት በተነገራቸው የጨዋታው ህግና ስርዓት መሰረት እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡

* በቅድሚያ ህፃናትን 7 አባላት ባሉበት ሁለት ቡድን ያደራጁ

* ቀጥሎ ከዚህ በፊት የተዋወቋዋቸውን የተለያዩ የፊደላት ቤተሰብ ፍላሽ ካርድ (በእቃ አድርጎ) እርሳስ፣ ወረቀት ከተማሪዎቹ ፊትለፊት ለየቡድኑ መስጠት፤

* ከዚያም ሁለት ተወዳዳሪ ቡድኖችን ወደፊት ለፊት ያሰወጡና የጨዋታውን ሂደት ይንገሩዋቸው፡፡ በመቀጠል ሁለት ተወዳዳሪ ቡድኖች ወደ መወዳደሪያቸው ጠረጴዛ በመውጣት ከተዘጋጁ በኋላ የአንድ ፊደልን ሰባት ቤተሰብ ተመካክረው ይውሰዱ፡፡ ሁለቱም ቡድኖች ሰባት የአንድ ፈደል ቤተሰብ መውሰዳቸውን ካረጋገጡ በኋላ የማስጀመሪያ ምልክት ሰተው ውድድሩን ያሰጀምሩ፡፡

* በመጨረሻም ሁሉም አባላት ቀድመው የጨረሱበት ቡድን አሸናፊ ሲሆን የፃፉትን የፊደል ቤተሰብ ለክፍሉ ያነባሉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የፍደል ፍላሽ ካርድ፣

* እርሳስ፣

* ወረቀት፣

* ጠረጴዛና ላጺስ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡-

* የፃፉት የፊደል ቤተሰብ እነማን ናቸው? የአንድ የፊደል ቤተሰብ አባላት ሰንት ናቸው? በጨወታው ወቅት ያልተደጋገፈው ቡድን የእነማን ነው ለምን?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ፡፡

* ሁሉም ህፃናት እንቅስቃሴዎቹን በትክክል መሰራታቸውን ይከታተሉ፡፡

ሐ. እንቆቅልሽ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ መፃፍ፣ ተግባቦት፣ መከባበር፣ መደጋገፍ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

የሚከተለውን ጨዋታ ህጻናት በተነገራቸው የጨዋታው ህግና ስርዓት ጠብቀው እንዲጫወቱ ያድርጉ። ህፃናት ቀጥሎ የቀረቡትን እና እርሶ ሌሎችን በመጨመር ለተቀመጠው ክፍል ጊዜ ተጠቅመው እንቆቅልሾችን እንዲጠያየቁ በማድረግ በአግባቡ እንዲጫወቱ ያድርጉ።

* በተፈጥሮ እገኛለሁ። ለሰዎች አየር እሰጣለሁ። በፀሃይ ጊዜ ጥላ እሰጣለሁ። በመሬት ላይ እበቅላለሁ። እኔ ማነኝ?

መልሱ፡- እግር

* ከሰውነት ክፍል እመደባለሁ። ከታችኛው የሰውነት ክፍል እገኛለሁ። ሰዎች ከቦታ ቦታ በእኔ አማካኝነት ይንቀሳቀሳሉ። እኔ ማነኝ? መልስ፡ እግር

* ለምግብ መሰሪያነት፣ ለንጽህና መጠበቂያ አስፈላጊ ነኝ:: ለሰው ልጅ ህይወት በጣም አስፈላጊ ነኝ:: እኔ ማነኝ? መልስ፡ መልሱ፡ ውሃ

* ከእንሰሳቶች ዝርያ ውስጥ አንዱ ነኝ። በቤት ውስጥ እኖራለሁ። ከሰውነት ክፍሎቼ ሃይለኛ የሆኑ ጥፍሮችና ጥርሶች አሉኝ። ወተት እወዳሉ። አይጥን እድናለው። እኔ ማነኝ? መልስ፡ ድመት

* ሁለት እግር አለኝ። ሁለት ክንፎች አሉኝ። ስጋዬን ሰው ይጠቀመዋል። ከሰው ጋር ለማዳ ነኝ። እንቁላል ከኔ ይገኛል። እኔ ማን ነኝ? መልስ፡ ዶሮ

* የሰውነት ክፍል ነኝ። ከፊት ላይ እገኛለሁ። ጓደኞቼን እመለከትባቸዋለሁ። አነብባቸዋለሁ። እኔ ማነኝ? መልስ፡ ዓይን

* ቁጥር ነኝ። ከአስር ቀጥሎ እገኛለሁ። እኔ ማነኝ? መልስ፡ 11

* ቁጥር ነኝ በአስራ አንድና በአስራ ሶስት ቁጥር መካከል እገኛለሁ:: እኔ ማነኝ? መልሱ፡- 12

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የሰውነት ክፍል፣ ውሃ፣ የድመት ስዕል፣ የቁጥር እና የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ የተለያዩ ቤቶች ስዕልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡-

* በዛሬው የእንቆቅልሽ ጨዋታ ምን ምን ተማርን?

ተግባር 6፦ የመስክ ጉብኙት

ሀ. የአከባቢ ጉብኝት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- እርስ በርስ መደጋገፍና መከባበር፣ ስሜትን መጠበቅ፣ አከባቢ፣ በአግባቡ መታጠብ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኙት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

አቅጣጫ ማሳየት አስፈላጊውን መመሪያ መስጠት፣ በጉብኙት ውቅት ለህፃናቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ማስታወሻ እንዲይዙ ማነረታታት፣ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ድጋፍ ማድረግ፤

በቅድሚያ በመስክ ጉዞ ላይ መከተል ያለባቸውን መመሪያ ለህፃናት ማስረዳት ያስፈልጋል ፡፡

- ህፃናት የሚሄዱበት ቦታ በስነ መግባር እንዲያዩ አስቀድሞ መናገር፤
- እርስ በርስ መደጋገፍና መከባበር እንዳቸው የእንዳቸውን ስሜት መጠበቅ እንዳለባቸው መንገር
- ስለሚያዩት ነገር ማስታወሻ መያዝና በሪፖርት መልክ በሌላ ክፍለጊዜ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ፤
- በአካባቢያቸው የሚገኙ እንስሳትን፣ ዕጽዋትን፣ ነብሳትን እንደሚያዩ እና ያዩትን እንሰሳት ስም እና የአካል ክፍል፣ አኗኗራቸውን፣ ያልገባቸው ነገር ካለ ተራ በተራ አስገብኚያቸውን እንዲጠይቁ መንገር ለማስታወሻ ፎቶም ያስቀሩ፤
- በጉብኙት ወቅት በእጃቸው ማንኛውን የማያውቁትን ነገር እንዳይነካኩ መናገር፣ ከጉብኙቱ በኋላ እቤታቸው ሰውነታቸውን መታጠብ ትምህርት ቤት ደግሞ እጃቸውን በአግባቡ ይታጠቡ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* ማስታወሻ ደብተር፣

* እርሳስ፣

* የሚጎበኙ ቦታዎች

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ክእጉብኙቱ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- 1. በጉብኙቱ ምን ተሰማቹ?

2. ምን አይነት እንሰሳት፣ ነፍሳትና እጽዋቶች አያችሁ?

3. በአካባቢያችሁ ምን አይነት እንሰሳቶች አሉ?

* ህፃናቱ በጉብኙቱ ወቅት የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ... በተገቢ ማዳመጥና መከታተል፡፡

ሳምንት ሰባት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

* ራስን መግዛትን ይመጀምራሉ
* ራሳቸውንና አካባቢያቸውን መንከባከብ ይለማመዳሉ
* ራስን የመርዳት ችሎታን ያከናውናሉ
* ቀጥታ ህትመትን ይለማመዳሉ
* እስከ 10 ድረስ ቁጥሮችን ደግሞ ይፅፋሉ
* የተሰጣቸውን ቁጥሮችና ፊደሎች ያነባሉ
* የተሰጣቸውን ፊደላት ደጋግሞ ይፅፋሉ
* የቤትና የዱር እንስሳትና ይለያሉ

ንዑስ ይዘቶች፡-

- ራስን መግዛት
- ራስን ና የቅርብ አካባቢ መንከባከብ
- የትናንሽ ጡንቻ እድገት
- የፈጠራ አገላለጽ
- ቁጥሮችን መፃፍ
- ፍደላቶችን ማንበብ እና እንደገና መጻፍ
- እንስሳት

ተግባር 1፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ስዕል መሳልና ማቅለም (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ የቤት እንስሳት፣ የዱር እንስሳት፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በተግባር ስርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረቡ የስራ ተግባራት እንዲሰሩ ለማስቻል የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል መሰረት እንዲያከናውኑ ያድርጉኣቸው፡

የቤትና የዱር እንስሳትን የሚያሳይ ፍላሽ ካርድ/ሞዴል (አምስት የዱርና አምስት የቤት) የእንስሳቱን ስምና የሚኖሩበትን ሁኔታ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠል ስንት እንስሳትን እንደተዋወቁ በጋራ ይቁጠሩ፡፡ ቀጥሎም የእንስሳቱን ምስል/ሞዴል ለሁሉም ህፃናት በሚታይ ቦታ በማስቀመጥ ህፃናቱ ከሚያዩት የቤትና የዱር እንስሳት ውስጥ አንድ እንስሳት መርጠው በመሳል ቀለም ይቀቡ፡፡ ሲጨርሱም የትኛውን እንስሳት እንደሳሉ ለክፍል ጓደኞቻቸው ስሙን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቤትና የዱር እንስሳት የሚያሳይ ፈላሽ ካርድ/ቻርት እና ሞዴል፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣ ቀለም

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ግሌ ማህደር

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. ስንት የቤትና የዱር እንስሳት ተመለከታችሁ?
2. እነማን ናቸው ?
3. የሳልከው/ሽው/እንስሳ ምን ይባላል?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤ የማይሳተፉ ካሉ እንዲሳጠፉ ያድርጉ፡፡
* በመጨረሻም ሥራቸውን በግሌ ማህደራቸው ውስጥ በማደራጀት ለውጣቸውን ይመልከቱ፡፡

ለ. ፊደላትና ቁጥሮችን ማንበብ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ ፊደል፣ ራስንመግዛት፣ እንስሳት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

በቅድሚያ የተለያዩ እንስሳት ስእል ከጀርባ ውቁጥር የተፃፈበት ያዘጋጁ በመቀጠል የእንስሳቱን ስም የመጀመሪያ ፊደል ከእንስሳቱ ስዕል አጠገብ ይፃፉ፡፡ የእንስሳቱን ስዕል በአንድ ጠረጴዛ ላይ ያስቀምጡ ከዛም ህፃናቱ ካርዱን እያነሱ ፊደሉንና ቁጥሩን እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ይህንን ተግባር ሲያከናውኑ ህፃናቱ እራሰቸውን በመቆጣጠርና በመግዛት ሳይሻሙ እንዲያከናውኑ ይንገሯቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የእንስሳት፣ ፊደላት፣ ቁጥሮች ፍላሽ ካርድ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ግሌ ማህደር

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. በካርዱ ላይ ያለውን ፊደላቱን፣ እንስሳውንና፣ ቁጥሩን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

ሐ. ቁጥሮችን መጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ራስን መግዛት፣ ቁጥር፣ ደግሞ መፃፍ፣ ራስን መርዳት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

• ለተግባሩ የሚያስፈልግ ፍላሽ ካርድ እርሳስ ወረቀት/ደብተር ለሁሉም
ህፃናት መስጠት

• እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን በወረቀት/ፍላሽ ካርድ በመስጠት ገለፃ ማድረግ

• ከ1-10 ያሉ ቁጥሮችን በተገቢው አፃፃፍ ስርዓት ተከትለው በቅደም ተከተል እያዩ ደግመው ይፃፉ

• በሚጽፉበት ጊዜ እርሳሳቸው ቢሰበር፣ ቦታው ባይመቻቸው ሌሎችን በማይረብሽ መልኩ እርሳሳቸውን መቅረፅ፣ ቦታቸውን ምቹ ማድረግ መለማመድ ስለሚያስፈልግ ችግሮችን የመፍታት እና እራስን የመቆጣጠር ልምምድ ማድረግ ስላለባቸው ያንን ነያስተግብሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እርሳስ፣ ላጲስ፣ ደብተር፣ ወረቀት፣ ፍላሽ ካርድ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ግሌ ማህደር

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. ከአንድ ቀጥሎ ስንት ቁጥር አለ?

* ሲሰሩ እየተከታተሉ እርማት መስጠት፣ እራሳቸውን ለመግዛት የሚያደርጉትን ጥረት ተከታትሎ ማገዝ፣ ራስን የመርዳት ችሎታቸውን ማየት

ሐ. ቁጥሮችን መጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ራስን መግዛት፣ ፊደላት፣ ደግሞ መፃፍ፣ ራስን መርዳት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

• ህፃናቱ ፊደላትን ደግመው እንዲፅፉ ወረቀት እርሳስ እራሳቸው እንዲወስዱና በየቦታቸው ተቀምጠው እንዲዘጋጁ ያድርጉ በመቀጠልም በስሌዳ/በፍላሽ ካርድ የተለያዩ ፊደላትን (ገ-ጉ-ጊ-ጋ-ጌ-ግ-ጎ እና ነ-ኑ-ኒ-ና-ኔ-ን-ኖ) ያሳዩዋቸው በመቀጠልም ያዩትን ፊደል እንዲፅፉ ድርጉ በሚፅፉበት ጊዜም ለሚገጥማቸው ስህተት ችግር እራስን በመግዛት ሰሜትና በመረጋጋት መፍትሄ መፈለግ እንዳለባቸው ያስረዱዋቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እርሳስ፣ ላጲስ፣ ደብተር፣ ወረቀት፣ ፍላሽ ካርድ

ተግባር 2፡- ውይይት

ሀ. ራስን መርዳት እና እራስን መቆጣጠር (5 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ንፅህና መጠበቅ ፣ ጫማ ማድረግ፣ ልብስ መልበስ፣ መመገብ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናት ከታች በተዘርዘሩት ላይ እንዲወያዩ አቅጣጫና ፍንጭ ስጧቸው፡፡

- የራስንን ፅህና መጠበቅ
- እራስን ችሎ መልበስና ጫማ ማድረግ፣ ምግብ መመገብ

* ከዚህ በኋላ ህፃናትን ሶስት አባላት ባሉት ቡድን በመከፋፈል የልብስ ቁልፍ መዝጋትና መክፈትን፣ ጫማቸውን እንዴት ማሰርና መፍታት እንደሚችሉ እንዲለማመዱና በመረዳዳት እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በልምምድ ወቅት የሚገጥማቸውን ችግር እራስን በመቆጣጠርና በመረጋጋት እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም ይህን ማድርግ ለማይችሉ ህፃናት አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ቅኡልፍ ያለው ልብስ፣ ማሰሪያ ያለው ጫማ፣ የምግብ ቁሳቁስ ሞዴል/ሰዕልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ግሌ ማህደር

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. እራሳችንን እንዴት እንረዳለን እና እራሳችንን እንዴት እንቆጣጠራለን በማለት ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት እራሳቸውን ለመግዛት የሚያደርጉትን ጥረት ተከታትሎ ማገዝ ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 3፡- ተረት

ሀ. መልካሙና ፈቲያ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ ቁጥር፣ ማንበብ ፣መፃፍ፣ቀጥታ ህትመት፣ መረጋጋት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከስር የተቀመጠውን ተረት ለህፃናቱ የተረት አቀራረብ ቅደም ተከተልን ጠመጠበው ይንገሯቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የሚበጠበጥ የውሃ ቀለም፣ የተለያዩ የቅጠል ሞዴሎች፣ የተዘጋጀ የህትመት ስራ ሞዴል

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

የሚከተሉት ጥያቄዎችን በቃል መጠየቅና የተረቱን ፍሬ ሃሳብ መንገር ያስፈልጋል።

1. መልካሙና ፈቲያ ምን አይነት ልጆች ናቸው?
2. መልካሙና ፈቲያ ህትመት የሰሩት በምንድን ነው?

* ይህንን ተረት በድራማ መልክ የሚያሳዩ ከሆነ ደግሞ ችሎታቸውን በደንብ መመልከት ያስፈልጋል።

ተግባር 4፡- በሥራ መማር

ሀ. እንስሳትን መንከባከብ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የቤት እንስሳ፣ እራስን መግዛት፣ ጥንቃቄ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

* ህፃናቱ የተለያዩ የቤት እንስሳትን ሞዴል በማዘጋጀት የእንስሳት እንክብካቤን እና አመጋገብን በተግባር በመስራት እንዲረዱ ያድርጉ።

* ህፃናቱም እንክብካቤውን አስመስለው ሲተገብሩ እራስን የመግዛት ተግባራትን እንዲፈፅሙና እራሳቸውን እንዲጠብቁ ያስታውሷቸው።

ለምሳሌ ድመትን ሲንከባከቡ ማቀፍና መሳም ቢፈልጉ ማድረግ እንደማይችሉ አውቀው እራሳቸውን እንዲቆጣጠሩ ማድረግ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የእንስሳት ሞዴል፣
* የቤት እንስሳት የሚመገቡት የተለያ የምግብ ሞዴልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡-

1. ምን ሥራ ሰራችሁ?
2. ራሳችንን እንዴት እንገዛለን?
3. እንስሳትን ለመንከባከብ ምን ምን ሰራችሁ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ።

ተግባር 5፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. አክስቴ እንዳለች (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- እራስን መግዛት፣ እራስን ማገዝ፣ ፊደል፣ ቁጥር፣ እንስሳት

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ከሰር የተቀመጠውን ጨዋታ ለህፃናቱ ቅደም ተከተል በመጠበቅ እንዲጫወቱ ያድርጓቸው፡፡

* ይሄን ጨዋታ ህፃናትን በማጫወት እራሳቸውን መግዛት መቻል እንዲለማመዱ ያድርጉ፡ "አክስቴ እንዳለች" የሚለውን ጨዋታ ለማጫወት የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች ይከተሉ፡፡

1. "አክስቴ እንዳለች የሚል አስደሳች ጨዋታ ልንጫወት ነው" ማለት

2. ህጻናቱ ማየት እና መስማት እንዲችሉ ሁሉም ህፃናት በግማሽ ክብ እንዲቆሙ ማድረግ፤

3. በዚህ ጨዋታ "አክስቴ እንዳለች" ብዬ የምትሰሩትን ተግባር ስነግራችሁ ብቻ ታደርጋላችሁ፡፡ አክስቴ ሳልል ምንም ብላችሁ ማድረግ የለባችሁም፡፡ ትዕዛዝ ያላከበረ ከጨዋታ ውጪ ይሆናል፡፡

ለምሳሌ፡- አክስቴ እንዳለች ልብሳችሁን ቆልፉ፣ ጫማችሁን እሰሩ፣ ፊደል በ ን አምጡ 9 ቁጥርን አምጡ የቤት፣ የዱር እንስሳት ስም ጥሩ... ፡፡

4. እንደዚህ የተለያዩ ትዕዛዛት በመስጠት እራሳቸውን እንዲገዙና እንዲቆጣጠሩ በማድረግ ያጫውቷቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደልና ቁጥር ካርድ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከጨዋታው በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- 1. ጨዋታው ላይ እነ ማንን ፊደላት፣ ቁጥሮችና እንስሳት ጠራን?

2. በጫወታው ምን ዓይነት ትዛዛትን አከናወንን?

* ህፃናቱ በጨዋታ ወቅት የሚያደርጉትን ተሳትፎ፣ የሚያነሱትን ሃሳብ... በተገቢ ማዳመጥና መከታተል፡፡

ተግባር 6፡- መዝሙር

ሀ.እሞክራለሁ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁጥር፣ መፃፍ፣ እንስሳትን መለየት፣ መግባባት፣ ራስን መቆጣጠር

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል፣ የቁጥርና የእንሰሳት ካርድ

መዝሙር 1:- እሞክራለሁ

ፊደሎችን ለማንበብ እሞክራለው
ቁጥሮችንም ለማንበብ እሞክራለው
እንሰሳትንም ለመለየት እሞክራለው
ከሰው ጋር ለመግባባት እሞክራለው
እራሴን መቆጣጠር እሞክራለው
ከመናገሬ በፊት ቆም እልና
እሰባለው እንደገና
የቻልኩትን በመሞከር
እኔ ራሴን እችላለሁ 2x

ምዘና፡- የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል።

ለ.እንስሳቶች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፊደል፣ እንስሳት፣ ራሰን መቻል፣ ጥንቃቄ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምሰል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል፣ የቁጥርና የእንሰሳት ካርድ/ሞዴል

መዝሙር 2:- እንስሳት

እንስሳት ሳያቸው በጣም ደስ ይላሉ
አንበሳ ዝሁን ብለው ይጠራሉ
ነብርና ጥንቸል እንዲሁም ጦጢት
በጫካ ውስጥ ነው ደግሞ ሚኖሩት
እሉ እንስሳቶች ከኛ ጋር ሚኖሩ
የቆዳቸው ቀለም በጣምን የሚያምሩ
ከነሱ ጋር ሰውል ራሴን እችላለው
አብሬ ስጫወት እጠነቀቃለው
ፍየልና በጉ ድመትና ውሻ
ው... ውሻ የኔ ማስታወሻ
ላ... ላም እንዳንቺ የለም
በ... በግ አብረን እንደግ
ፍ... ፍየል የምትበላው ቅጠል
ድ... ድመት የምትጠጣው ወተት
ፍየልና በጉ ድመትና ውሻ
የተሰጡኝ ናቸው ለኔ ማስታወሻ።

ምዘና፡- የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል።

ሳምንት ስምንት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፡-

* የሆሄያት ድምጾች ከቅርጾች ጋር ያገናኛሉ፣
* የተሰጡ ፊድላቶች ደግሞ መጻፍ ይችላሉ፣
* ለችግሮች መፍትሄዎችን ይፈልጋሉ፣
* የተሰጡ ስዕሎችን ቀለም መቀባት እና ማድመቅ ይችላሉ፣
* የጡንቻ እንቅስቃሴዎችን በትክክል ማከናወን ይችላሉ፣
* 5-7 የተለመዱ ምግቦችን ይለያሉ፣
* እራሳቸውን ከአደጋ ጠብቃሉ፣
* እስከ 15 ቁጥሮችን መፃፍ ይችላሉ፣

ንዑስ ይዘቶች፡-

- የጅኦሜትሪ ምስሎችን መለየት እና መመደብ
- ፍደሎችን እንደገና መጻፍ
- ውሳኔ የማስተላለፍ ክህሎት
- ውበትን ማድነቅ
- የአካል ብቃት
- አመጋገብ
- ደህንነት እና ጥበቃ

ተግባር 1፡- መዝሙር

ሀ. የምግብ ዓይነቶች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - የምግብ ዓይነት፣ እንቅስቃሴ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ስዕል/ሞዴልና የአካል እንቅስቃሴ አመላካች ስዕል...

መዝሙር 1:- የምግብ ዓይነቶች

ልጆች እንመገብ ምግብ ጠቃሚ ነው
ሀይልም የሚሰጡ ናቸውና ገንቢ
ከየአይነታቸው መመገብ ይገባል
በሽታን አጥፍቶ ጡንም ይሰጣል
እንጀራና ዳቦ እንባሻና እና ቂጣ
ገንፎና ጨጨብሳው አምርት የሚያሰወጣ
ሁልን ስንመገብ እያመጣጠንን
እንቅስቃሴንም መስራት አለብን
ምግብ እንመገብ እስፖርቱን እንስራ
በእንቅስቃሴም እንሁን ጠንካራ።

ምዘና፦ የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል።

ተግባር 2፦ የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. የፊደል ቅርጽና ድምጽ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የፊደል ድምጽ፣ መፍትሄ፣ የፊደል ቅርጽ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ስርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና:-

በዚህ ክፍለ ጊዜ ህጻናት የፊደላቱን ድምጽ ከቅርጽ ጋር ፈልጎ የማገናኘት ጨዋታ ይጫወታሉ። ስለዚህ፦

- ከዚህ በፊት የተዋወቁት የፊደል ቤተሰብ በሳጥን ውስጥ ቀላቅሎ በጠረጴዛ ላይ ሶስት ቦታ ለሶስት ተወዳዳሪዎች ማዘጋጀት (በሶስቱም ሳጥኑ ውስጥ ያለው ፊደል ተመሳሳይ መሆን አለበት) ።

 እርሶ አንድ ፊደል በመጥራት ቀጥሎ ከሳጥኑ ውስጥ በፍጥነት ከሳጥኑ ውስጥ ፊደል ፈልገው በማግኘት ሰሙን መናገር ቀጥሎ በጥቁር/ነጭ ሰሌዳ ያገኙትን ፊደል ይፃፉ። ይህ የጨዋታው አካሄድ ሲሆን ሶስቱ ህፃናት ተለያየ ፊደል ድምፅ ይነገራቸው። የተነገራቸውን ፊደል 1 2 3 በማለት ቆጥረው ፍለጋውን ያስጀምሩ።

 ቀድሞ ያገኙ ህጻናት የፊደሉን ድምጽ መናገር እና ልክ እንደእርሶ መፃፍ፤

 ከተወዳዳሪዎቹ ያላገኘ ህጻን ካለ ከቀጣይ መልሰው እንዲወዳደር ማድረግ ያስፈልጋል። ምክኒያቱም ህፃናት አንዴ ስላቃታቸው አልችልም የሚል ስሜት እንዳይዛቸው በፍጥነት ፍደል ማግኘት የሚችሉበትን የተለያዩ ዘዴዎችን በመንገር ለችግራቸው መፍትሔ የሚፈልጉበትን መንገድ አውቀው አሸናፊ መሆን እንደሚቻል ይለማመዳሉ። በዚህ መልኩ የፊደላትን ድምጽና ቅርፅ አውቆ መጻፍን ለችግራቸው መፍትሄ መፈለግን በተሰጠው የክፍል ጊዜ ድግግሞሽ ይለማመዱ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፍደል ፍላሽ ካርድ፣ የፊደል ሞዴል፣ እርሳስ፣ ማርከር፣ ጠመኔ/ቾክ/፣ ወረቀት፣ ስሌዳ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡-

* ዛሬ ድምፃቸውን የተዋወቅናቸው ፊደላትን እነማን ናቸው?
* ችግር ሲያጋጥመን እንዴት መፍትሔ ማግኘት እንችላለን?
* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤

ለ. የምግብ ዝግጅት ውድድር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ከአደጋ መጠበቅ፣ ጡንቻን ማንቀሳቀስ፣ የምግብ ዓይነት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ጨዋታው የምግብ ዝግጅት ውድድር ነው። ስለዚህ ለዚህ የሚሆኑ ነገሮችን ማዘጋጀት እና ምግብ ለመሰራት ምን ማድረግ እንደሚገባ ገለፃ ያድርጉ። እንዲሁም አንድን ተግባር ሰናከናውን ችግር ቢያጋጥመን በራሳቸው መፍትሄ መፈለግን በራሳቸው ማሳብ እንዳለባቸውና በምግብ ዝግጅቱ ወቅት ለማሸነፍ ሲባል ጉዳት እንዳይደርስባቸው የጥንቃቄ ስልቶችን ይጠቁሙ።

ቀጥሎ የሚወዳደሩ ህፃናት አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ሁለት ቡድኖችን ይሰራሉ። ለዚህም ቀጥሎ ያለውን ቅደም ተከተል መከተል አስፈላጊ ነው።

 አስፈላጊ ግብአት ሸንኩርት እና የመሰሪያ ቁሳቁስ፣ ቲማቲም፣ ምስር/ሽሮ፣ ድስት፣ መክተፊያ፣ ቢላዋ፣ ሳህን ሞዴሎች፣ ውሃ፣ ዘይት፣ ጨው፣ የምድጃ ሞዴል፣ ሁለት ተረጴዛ … ማዘጋጀት፤

 የመጀመሪያዎቹን ተወዳዳሪዎች በመጋበዝ ለውድድሩ ከጓደኛቸው ጋር ተመካክረው እንዲዘጋጁ መንገር፡፡ ቀጥሎ እየተጋገዙ ግብኣታቸውን እና እቃቸውን እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ ዝግጁ ሲሆኑ ደቂቃ ሰተው ማስጀመር፤ ቀድሞ የጨረሰው እና በአግባቡ የሰራው ቡድን አሸናፊ ይሆናል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ሸንኩርት እና የመስሪያ ቁሳቁስ፣ ቲማቲም፣ ምስር/ሽሮ፣ ድስት፣ መክተፊያ፣ ቢላዋ፣ የሳህን ሞዴሎች፣ ውሃ፣ ዘይት፣ ጨው፣ የምድጃ ሞዴል፣ ሁለት ጠረጴዛና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡-

* ምግብ ለማዘጋጀት ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ?

2. ምግብ ስንሰራ ጉዳት እንዳይደርስብን መውሰድ የሚገባን ጥንቃቄ ምድን ነው?

3. ምን ዓይነት ምግብ ሰራን?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤

ተግባር 3፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. ድምጽ መለየት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ከአደጋ መጠበቅ፣ ጡንቻን ማንቀሳቀስ፣ የምግብ አይነት

የማስተማሪያ ዘዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ጨዋታውን ህፃናቱን ወደ ውጭ ይዘው በመውጣት በተቀመጠው የአጨዋወት መመሪያ መሰረት ያጫውቱ፡፡

• በቅድሚያ የህፃናት መጫወቻ አከባቢ በህፃናት ላይ ጉዳት አለማድረሱን ማረጋገጥ እና ለነሱም በጨዋታ ጊዜ ጉደት እንዳይደርስ ስለሚደረግ ጥንቃቄ መንገር፤

• እንዲሁም በቡድን ጨዋታ ለምያጋጥማቸው ችግር በአሰተውሎት ተነጋግረው ችግራቸውን እንዲፈቱ መንገር፤

• አምስት አምስት አባላት ያሉት ቡድን ይመሰርቱ፡፡ ለሁሉም ቡድን የአንድ እንሰሳ ስም እና ድምፅ ይሰጧቸው፡ ፡ ለምሳሌ፡- ለአንድ ቡድን የዶሮ ይሰጠውና ኩኩሉሉ ድምፅ እያሉ ጓደኛቸውን ይፈልጋሉ፤

• ሁሉም ህፃናት አይናቸውን በመጨፈን/በጨርቅ በማስር የተሰጣቸውን የእንስሳት ድምፅ ሲያስሙ አይናቸውን ሳይከፍቱ ተመሳሳይ ከሆነ የእንስሳት ድመምፅ ጋር እንዲፈላለጉ እና እንዲገናኙ በማድረግ፤ ተመሳሳይ ድምፃች ቡድን እንዲፈጥሩ ያድርጉ፤

• ህፃናት የእጃቸውን፣ የእግራቸውን ጡንቻ በትክክል ማንቀሳቀስ እንዳለባቸው መጠቆምና ለዚህም እንቅስቃሴ እንዲረዳ ቦታውን ሰፋ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

* ተመሳሳይ ድምፆችን በማፈላለግ ቀድሞ ሁሉም በመገናኘት ቡድን የፈጠሩ አሸናፊ መሆናቸውን በመግለፅ ደረጃ ያውጡ እና ያበረታቱ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ትኤፕ/ጂፓስ/ሞንታርቦና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ከጨዋታው በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፦ 1. በጨዋታው ላይ የስንት እንስሳት ድምጽ ሰማችሁ?

2. የዶሮ ድምጽ እንዴት ነበር?

3. ስትጫወቱ ምን ችግር ገጠማችሁ፤ እንዴትስ ፈታችሁ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው በመከታተል ሁሉም እያከናወኑ መሆኑን ያረጋግጡ፤

ተግባር 4፦ የተግባር ሥራ

ሀ. ቁጥርና ፊደል ደጋግሞ መጻፍ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ቁጥር፣ ጡንቻን መንቀሳቀስ፣ መፍትሄ መፈለግ

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በተግባር ሰርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረቡ የሰራ ተግባራት እንዲሰሩ ለማስቻል የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል መሰረት እንዲያከናውኑ ያድርጉኳቸው፡

- ከአንድ እስከ አስራ አምስት የሚደርሱ የቁጥር እና የፊደል ፍላሽ ካርዶች (ፐ-ፑ-ፒ-ፓ-ፔ-ፕ-ፖ) ያዘጋጁ።
- ሞዴል እና ፍላሽ ካርድ ያዘጋጁ እና ቁጥሩን ከህፃናቱ ጋር እየቆጠራቹ በቅደም ተከተል አስቀምጡ።
- ቀጥሎ እርሳስ፣ ወረቀት፣ ደብተር፣ መለመማመጃ መጽሃፍ በመስጠት ቁጥሮቹን እና ፊደሎቹን ተገቢ የእርሳስ አያያዝ፣ ተገቢ የሆነ አጻጻፍን ተከትለው በቅደም ተከተል መፃፍ እንዳለባቸው ምሳሌ ይስጡ። እነሱ ያንን ተከትለው እንዲተገብሩ ያድርጉ።
- ሲጽፉ ቢበላሽባቸው፣ ከመስመር ቢወጡ እርሳስ ቢሰበርባቸው… መሳሰሉት ችግር ሲገጥማቸው ችግሩን ለመፍታትና መፍትሄ ፈልገው የተሰጣቸውን ተግባር በአግባቡ እንዲጨርሱ ያሳታውሷቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

እርሳስ፣ ወረቀት፣ ደብተር፣ መለማመጃ መጽሀፍና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* "ስንት ቁጥር ጻፋችሁ?፣ ለመጻፍ የትኛውን ጡንቻችሁን ተጠቀማችሁ?፣ ስትጽፉ ምን ችግር ገጠማችሁ፤ እንዴትስ ፈታችሁ?" በማለት ይጠይቋቸው።

ለ. እንስሳትና የምግብ ዓይነቶችን መቀባት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መሳል፣ ጡንቻን መንቀሳቀስ፣ መሳል፣ መቀባት፣ ምግብ፣ እንስሳት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ሰርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱ ስዕል በመሳልና በመቀባት ልምምድ በማድረግ የእጅ ጡንቻዎቻቸውን በትክክል የመጠቀም ችሎታ ያዳብራሉ ስለዝህ ይህን ተግባር በአግባባቡ በተደጋጋሚ ያሰሩ፡፡ እርሶም ሰርተው ያሳዩ፡፡

- በነጠብጠብ ተሰርቶ የተዘጋጁ የቤትና የዱር እንስሳት፣ የምግብ አይነቶች ስዕል ቀለም ለመቀባት በሚመች መልኩ ማዘጋጀትና ለህፃናቱ ለየግላቸው መሰጠት፤
- እርሳስ፣ ከእንስሳቱ እና ከምግቦቹ ተፈጥሮኣዊ ቀለም ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቀለሞች ማዘጋጀትና በግላቸው የሚጠቀሙበት በየጠረጴዛው መስጠት፤
- ቀጥሎ በጥንቃቄ በነጠብጣብ የተዘጋጀውን ስዕል አድምቀው ቀለም የመቀባት ተግባር ያከናውኑ፤
- ቀለሙን በጋራ የሚጠቀሙ ከሆነ አንዱ የያዘውን በተራ እንዲጠብቁ እስከዚያ ያልተያዘውን እንዲቀቡ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እርሳስ፣ በነጠብጣብ የተዘጋጁ የእንስሳትና የምግብ አይነቶች ስዕል፣ የተለያዩ ቀለማትና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የሰራችሁት ተግባር ምንድን ነበር? ምን አይነት እንስሳ እና ምግብ ቀባችሁ? ስትሰሩ ምን ተቸግራችሁ ነበር? እንዴትስ ችግራችሁን ቀረፋችሁ? ብለው መጠየቅ...

ተግባር 5፡- ውይይት

ሀ. ራስን ከአደጋ መጠበቅና ችግር መፍታት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- አደጋ፣ ራስን መጠበቅ፣ ችግር መፍታት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናት ራስን ከአደጋ መጠበቅና ችግር መፍታት የሚቻልባቸው መንገዶች ላይ ሀሳብ እንዲለዋወጡ፡-

* በቅድሚያ የራስዎን ሀሳብ ያጋሯቸው፡፡
* ህጻናት ተራ በተራ እጅ እያነሱ ሀሳብ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

አደጋ የሚያደርሱ ቦታዎች ስዕል፣ ችግሩን በራሱ እየፈታ ያለን ሰው የሚያሳይ ስዕልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ግሌ ማህደር

ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፡-

1. እራሳችንን እንዴት ከአደጋ እንጠብቃለን?
2. ችግሮቻችንን እንዴት መፍታት እንችላለን?

ተግባር 6፡- በፕሮጀክት መማር

ሀ. የተለመዱ የምግብ ዓይነቶች ሞዴል መስራት (2 ክፍለ ጊዜ)

ለ. እንስሳትን ከጭቃ መስራት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የተለመዱ ምግቦች፣ እንስሳት፣ መቀባት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ ስርቶ ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

ስለፕሮጀክቱ ገለፃ ማድረግ፣ መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚያልቅ መንገር፣ ስርተው ሲጨርሱ እንዲያቀርቡት እና ስለስራቸው አጠቃላይ ሁኔታ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ ጥያቄ መጠየቅ ድጋፍ ልሚሹ ልዩ ፍላጎት ህፃናት እንደፍላጎታቸው መጠን መደገፍ፣ ማበረታታት....

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ለሚሰሩት የእንስሳት ሞዴል የሚያገለግሉ የተቦካ ወረቀት፣ ሰውሰራሽ /የተፈጥሮ ጭቃ፣ ወረቀት፣ ክርቶን፣ ከለር፣ ከተር፣ መቀሰ፣ ማጣበቂያ...

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ስለሰሩት ፕሮጀክት እንዲገልጹና ሲሰሩ ምን ችግር እንደገጠማቸው፣ እንዴት እንደፈቱ መጠየቅ.....

ተግባር 7፡- ተረት

ሀ. ቀበሟ ጦጢት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ ቁጥር፣ ማንበብ ፣መፃፍ፣ቀጥታ ህትመት፣ መረጋጋት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከሰር የተቀመጠውን ተረት ለህፃናቱ የተረት አቀራረብ ቅደም ተከተልን ጠመጠበው ይንገራቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የጦጢት ስዕል ተረቱ ላይ የተጠቀሱ ምግቦች፣ ፍራፍሬ ስዕል/ሞዴል

ቀበጧ ጦጢት

ተረት! ተረት! መንደራችን ካለው የእርሻ መሬት ትንሽ ራቅ ብሎ ከሚገኝ ዛፎች ውስጥ የሚኑሩ ቀበጧ ጦጢትናከ እናቷ ጋር ይኖሩ ነበር ከዛፎቹም ለምለም የአትክልት ሰፍራ አጠገብ ይገኛል የተለያዩ የሚጣፍጡ ሙዝ ፣ቲማቲም፣የአተር እና የሸንብራ እሸት መብላት ትፈልጋለች። ነገር ግን እናቷ ሁልጊዜ ለቁርስ ሙዝ ብቻ፣ ለምሳ ሙዝ፣ ለእራትም ሙዝ ው የምትሰጣት ሁል ጊዜ ተመሳሳይ ምግብ በመሆኑ ደስተኛ አይደለችም ጤንነቷም ተጎድቷል ስለዚህ አንድ ቀን ከእናቷ ተደብቃ ለብቻዋ ሄዳ የተለያዩ ምግቦችን ለመብላት እሰባ እግረ መንገዷንም እሰፖርት እየሰራችና ጡንቻዎቿን እያፍታታች ነበር ቀበጧ ጦጢት ብዙ ተክሎች ወዳሉበት በመሄድ ሶሰት ማንጎ፣ ሁለት ቲማቲሞች፣ ሦስት ዱባ፣ አራት የሚጣፍጡ ፓፓያ አምስት የአተር እሸቶችን በላች። በዚህ ጊዜ የቀበቷ ጦጢት ሆድ እንደ ኳስ ተነፋ። መሄድም አቃተት። ዛፍ ስር ቁጭ ብላም ማልቀሰ ጀመረች። የጢጢት እናት ልጅዋ እያለቀሰች አገኘቻት። ከመሬት አንስታም ውኃ ሰጠቻት ከዚያም ልጄ የተለያዩ ምግብ መብላት ጠቃሚ ቢሆንም ግን በመጠኑ መብላት እንደሚገባ ነገረቻት ከለበለዚያ ለጉዳት እንደሚዳርገው መከረችው። በሁለተኛው ቀን ቀበቷ ጦጢት በጣም ተሻላት። እናቱ የሰጠችውንም ምክር በመሰማት እራሱን ከጉዳት ለመጠበቅ ቃል ገባች የተሰጠውንም የቅጠል ቀንበጥ ምንም ሳያስተርፍ በላ።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

የተረቱን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅ ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፡-

1. ጦጢት ምን ትመገብ ነበር?
2. ለምን ታመመች?

ሳምንት ዘጠኝ

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

* ስለሰውነትክፍሎችመዝሙርመዘመር
* የጂኦሜትሪምስሎችንደግሞመስራት
* ህይዎትያላቸውነገሮችንስዕልቀለምመቀባት
* የትልልቅጡንቻዎችክህሎቶችትክክለኛተግባርማሳየት
* የታሪክ መፃህፍት በመመልከትታሪኮችመናገር
* የተሰጡትን ፊደላቶች ደጋግሞመፃፍ
* ጥምር ንድፍ መሰራት
* ከሌሎች ጋር ተራ ጠብቀው መጫወት
* የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች በመጠቀም መፃፍ
* ስለ የቤት እና የዱር እንሰሳት ልዩነት መናገር

ንዑስ ይዘቶች፦

- ቃላቶች
- ቅርጾች
- አገናኞች፣ ግንኙነቶች እና መተግበሪያዎች
- የትላልቅ ጡንቻ እድገት
- ንባብ
- ፍደላቶች መጻፍ
- ንድፍ
- የግንኙነት ክህሎቶች
- በዲጂታል ማንበብና መጻፍ ችሎታ
- እንስሳት

ተግባር 1፡- መዝሙር

ሀ.የሰውነት ክፍሎች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ህይውት ያላቸው፣ የቤት እና የዱር እንስሳት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ህይወት ያላቸው ነገሮች ስዕል፣የሰውነት ክፍል ስዕልና ተንቀሳቃሽ ምስል ፍላሽ ካርድ/ሞዴል

መዝሙር 1፡- የሰውነት ክፍሎች

1 2 3 4 የሰውነት ክፍሎች እንወቅ ሕፃናት፣
ዓይን፣አፍንጫ፣ምላስ፣ጆሮ እንዲሁም ጉልበት፣
እንከባከባቸው ጤናማ ለመሆን ሁሉን በፅዳት፣
ጡንቻን ለማዳበር ያስፈልጋል እስፖርት፣
አፍንጫ ለማሽተት፣ዓይን ለማየት፣
ምላስም ለመቅመስ ያገለግላሉ ጆሮም ለመሰማት፡፡
ስዕልም ለመሳል ያስፈልጋል እርሳስ
ህይወት ያላቸውን እስቲ እንናገር
እንስሳት እፅዋት የሚያድግ ነገር
ከሰውነት ክፍሎች አንዱን በመምረጥ
ማስዋብም ይቻላል በቀለም እርሳስ፡፡

ምዘና፡- የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል፡፡

ለ.ኑ ልጆች እንጫወት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ህይወት ያላቸው ነገሮች፣ ተራ መጠበቅ፣ አካል መዳበር

የማስተማሪያ ዘዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

ህይወት ያላቸው ነገሮች ስዕል፣የሰውነት ክፍል ስዕልና ተንቀሳቃሽ ምስል ፍላሽ ካርድ/ሞዴል

መዝሙር 2:- ኑ ልጆች እንጫወት

ህይወት ያላቸውን ነገሮች
እንወቅአቸው ልጆች
እንስሳትና እፅዋት
ይፈልጋሉ ትኩረት
ኑ ልጆችእንጫወት
ሳንጣላ በመግባባት
በመጠበቅ ተራችንን
እንዲዳብር አካላችን።

ምዘና፡- የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅና በመጨረሻም መንገር ያስፈልጋል።

ተግባር 2:- በሥራ መማር

ሀ.ቤት መገንባት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ተራ መያዝ፣ ትላልቅ ጡንቻ፣ ጂኦሜትሪ

የማስተማሪያ ዘዴ:- በተግባር፣ በውይይት፣ በገለፃና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

* በመጀመሪያ ህፃናቱን ወደ ሚመች ቦታ ያውጧቸውና በቡድን በመከፋፈል በአሸዋ/በእንጨት የቤት ሞዴል በመስራት ወይም ደግሞ እመርት ላይ በጠመ/በከሰል በመሳል ሶስት ጎን እና አራት ጎን በመጠቀም በተራ እና በመግነጋገር የቤት ቅርፅ በትልቁ እንዲሰሩ እና ቤት እንዲገነቡ ያድርጉ።

* በመቀጠልም የሰሩትን ቤት በሞዴል እቃዎች እንዲያስተካክሉ ያድርጉ፤ ለምሳሌ፡- ወንበር አልጋ… በማስመሰል የቤት ቁሳቁስ አስመስለው ይስሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

*ጠመኔ፣ ከሰል፣ የቤትመሰሪያ፣ ካርቶን፣ እንጨት፣ አሸዋ የቤት ቁሳቁስ ሞዴልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡-

1. ቤት ለመሰራት ምን ተጠቀማችሁ?
2. ምን ዓይነት እንቅስቃሴ አደረጋችሁ?
3. ምን ቅርፅ ተጠቀማችሁ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ።

ለ. ጥንድ ንድፍ መስራት (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ተራ መያዝ፣ ንድፍ፣ የሰውነት ክፍል፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር፣ በውይይት፣ በገለፃና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቢቻል ወደ ውጭ ይዘዋቸው ቢወጡ አሸዋው ላይ ወተው የእጅና የእግር ድግግሞሽን ንድፍ ለመስራት ያስችላቸዋል የቀረውን ክ/ጊዜ ደግሞ በክፍል ውስጥ መስራት ይጭላሉ የእጅና የእግር ቅርፅ አሸዋ ላይ በማተም ንድፍ (ፓተርን) በማሠራት ነገሮችን በሥርዓት በመደርደር እንዲለማመዱ የሚከተለውን ቅደም ተከተል በመከተል ያጫውቷቸው።

1. አሸዋ ማዘጋጀት፡
2. በአሸዋው ላይ የእጅና የእግር ቅርፅ በቅደም ተከተል ሠርቶ ማሳየት (ለምሳሌ፡- እጅ እጅ እግር እግር…)
3. ባዩት መሠረት ተራ በተራ ሁሉም ሕፃናት ይህን ቅደም ተከተል ተከትለው ንድፍ እንዲሠሩ ማድረግ። ለምሳሌ የእንስሳት ስእል ካርዶች፣ የተለያዩ የተዋወቁ ፍደላቶች ካርድ እና እስከ 15 ድረስ የቁጥሮች ካርድ በማዘጋጀት ካርዱን በመጠቀም እየደረደሩ ከቀላል ንድፍ በመነሳት ወደ ከባድ ንድፍ እየሰሩ እንዲያሳዩ ድጋፍ በማድረግ ይለማመዱ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

*እሸዋ፣ የእንስሳት፣ የቁጥር፣ የፊደል፣ ካርድና ሞዴል፣ እርሳስ ወረቀት፣ ጠረጴዛና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

1. የትኛውን የሰውነት ክፍል በመጠቀም ንድፍ ሰራችሁ?
2. ባለሰንት ድግግሞሽ ንድፍ ሰራህ/ሽ?
3. የምን የምን ንድፍ ሰራህ/ሽ? ምንተጠቀምሽ/ህ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ፡፡

ተግባር 3፡- የተግባር ሥራ

ሀ. መጸፍና የጡንቻ እንቅስቃሴ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መፃፍ፣ አካል መዳበር፣ የሰውነት ክፍል፣ ተራ መጠበቅ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ሰርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልሰ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረቡ የሰራ ተግባራት እንዲሰሩ ለማስቻል የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል መሰረት እንዲያከናውኑ ያድርጉኣቸው፡

 በመጀመሪያ ከሰውነት ክፍላቸው ትላልቅ ጡንቻ የሚባሉትን በመቀጠልም የተለያዩ ትላልቅ ጡንቻዎቻቸውን የመዳብሩ ተግባራትን በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ በማዘጋጀት (ለምሳሌ፡- ጎማ መግፋት፣ መሰላል መውጣት፣ ገመድ መዝለል/መጎተት፣ ኳሰ መወርወር፣ ቁሳቁሶችን ከቦታ ቦታ ማዘዋወርና የመሳሰሉትን ተራቸውን ጠብቀው እንዲያከናውኑ ያድርጓቸው፡፡

 ቀጥሎ የእለቱን ፊደል (ሐ-ሑ-ሒ-ሓ-ሐየ-ሕ-ሖ እና ጠ-ጡ-ጢ-ጣ-ጤ-ጥ-ጦ) ደጋግመው እንዲፅፉና የፃፉትን እንዲያነቡ ያድርጉ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ጎማ፣ ኳሰ፣ ገመድ፣ የተለያዩ ቁሳቁሶችና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* "ምን አይነት እንቅሰቃሴ አደረጋችሁ?"

* "በየትኛው የሰውነት ክፍልሽ/ህ እንቅሰቃሴዎቹን ሰራሽ/ህ??" በማለት ይጠይቋቸው፡፡

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ፡፡

ተግባር 4፦ የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ድርብ ንድፍ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- እንስሳት፣ ንድፍ፣ ተራ መጠበቅ፣ ፊደላት

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

በዚህ ክፍለ ጊዜ ህጻናት የፊደላቱን ድምጽ ከቅርጽ ጋር ፈልጎ የማገናኘት ጨዋታ ይጫወታሉ። ስለዚህ፦

* ህፃናቱን በሁለት ቡድን በመክፈል የቤትና የዱር እንስሳት በማለት ቡድን ይሰጡዋቸው።

* በመቀጠልም የቤት እንስሳት ቡድኖች ለምሳሌ፦ በግ በግ ፍየል ፍየል በግ በግ... በመሆን በተራ እንዲሰለፉ ያድርጉ፤ በተመሳሳይ የዱር እንስሳት ዝሆን ዝሆን ቀጭኔ ቀጭኔ ዝሆን... ዝሆን በመሆን ንድፉን በመከተል እንዲሰለፉ ያድርጉ፤

* ከዚያም የእንስሳው ስም የመጀመሪያው ፊደል ሲጠራ እንስሳውን በማስመሰል ከፊት እንዲቆሙና በሰሌዳ ላይ ተራቸውን ጠብቀው ፊደሉን እንዲፅፉ ያድርጉ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ወረቀት፣ እርሳስ፣ ደብተር ጠመኔ/ማርከር፣ ጥቁር/ነጭ ሰሌዳ፣ የቤትና የዱር እንስሳት ምስል/ሞዴል

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

1. ባለስንት ንድፍ ሰራችሁ?
2. ያስመሰላችሁት እንስሳ ስም የመጀመሪያ ፊደል የምን ፊደል ቤተሰብ ነው?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ።

ተግባር 5፦ ተረት

ሀ. አበበ ቢቂላ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ትላልቅ ጡንቻ፣ ቴክኖ ሎጂ፣ ታሪክ፣ ተራ መጠበቅ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከስር የተቀመጠውን ተረት ለህፃናቱ የተረት አቀራረብ ቅደም ተከተልን ጠመጠበው ይንገራቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ትላልቅ ጡንቻ ማዳበሪያ ተግባራት ስዕል/ተንቀሳቃሽ ምስል፣ ስልክ ፣ የአበበ በቂላ ፎቶና ወዘተ

አበበ ቢቂላ

በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች ነበሩ። ስሚራ የምትባል ሴት ልጅ አለቻቸው። የስሚራ አባት ሁል ጊዜ ለስሚራ የታሪክ መፀሀፍትን ስዕሎች እያሳዩ ታሪክ ይነግሯት ነበር። እሷም አባቷ የነገራትን ታሪክ መፀሀፍ ይዛ በመሄድ ለጓደኞቿ ትነግራቸዋለች። አንድ ቀን የአበበ ቢቂላን ታሪክ በስዕል የተደገፈ መፅሀፍ ይዛ ለጓደኞቿ እያሳየች ነገረቻቸው። አበበም ትላልቅ ጡንቻው እንዴት እንደዳበረ እና ለሩጫ ከመዘጋጀቱ በፊት የሚሰራውን እንቅስቃሴ እያሳየች ትነግራቸው ጀመር። በዛ መሀል አንዱ ጓደኛዋ እኔ በእናቴ ስልክ ቪዲዮውን አይቼዋለው አላት እና ደግሞም እቤቱ በእናቱ ስልክ እና በአባቱ ኮንፒውተር ፊደላትና ቁጥር እንደሚፅፍ ነገራቸው። መምህራቸውም እንደ አቤል መፃፍ ትፈልጋላቹ ብላ ጠየቀቻቸውና ስልኳን ስታወጣ ህፃናቱም አዎ በማለት ተሻሙ። መምህርቷም ቆይ እንደዚ አይደለም በየተራ ሁላችሁም ትፅፋላችሁ አለቻቸውና ስልኳን ከፍታ ቁጥርና ፊደላት አጻፈቻቸው። ህፃናቱም በጣም ተደስተው አመሰገኗት።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

የተረቱን ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅ ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፡-

1. ስሚራ የማንን ታሪክ ነገረቻቸው?
2. የስሚራ ጓደኛ ፊደልና ቁጥር በምን ላይ ፃፍኩ አለ?

ተግባር 6፡- ውይይት

ሀ. የሰሙትን ታሪክ መልሰው ማውራት (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቴክኖሎጂ፣ ታሪክ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና:-

መምህርት ህፃናቱን በቡድን በመክፈል ስለተለያ ስለሰሙት ታሪክ እንዲወያዩ ያድርጉዋቸው:: በመቀጠልም ከዚህ በፊት የነገሩዋቸውን የታሪክ/ተረት መፀሀፍት በመስጠት እየተመለከቱ እንዲናገሩ ያድርጉ:: ቀጥሎም ተረቱ በምን ቴክኖሎጂ ሊፃፍ እንደቻለ እና እነሱም መጠቀም እንደሚችሉ በማሳየት ይንገሩዋቸው::

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተረት መፀሀፍት፣ ኮንፒተር፣ ስልክና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

1. ምን ታሪክ ተናገራችሁ?

* ህጻናት ውይይቱን በትክክል መካፈላቸውን ይመልከቱ።

ተግባር 7፡- የመስክ ጉብኝት



ሀ. የትምህርት ቤት ግቢ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ተራ መጠበቅ፣ ጂኦሜትሪ፣ ንድፍ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ህፃናቱን በትምህርት ቤት ግቢያቸው ውስጥ ይዞ በማዞር እየጎበኙ የሚመለከቱትን ቁሶች ከጂኦሜትሪ ቅርፆች ጋር እንዲያመሳስሉና እንዲናገሩ ያድርጉ፤

* እንዲሁም ተክሎችን በመመልከት ቅጠላቸውን ተመልክተው እንዲያስተውሉና ንድፋቸውን በየተራ እንዲናገሩ ካደረጉ፤

* በኋላ ክፍል ገብተው ያዩትን ቅርፅ/ንድፍ እንዲስሉ ያርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የጂኦሜትሪ ቅርጽ፣

* በግቢ ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች፣

* እርሳስ፣

* ወረቀት/ደብተርና ላጲስ...

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

1. በጉብኝት ወቅት ምን አይነት ቅርፅ ምን ላይ ተመለከታርችሁ?
2. የቱ ጋር ተመለከታችሁ?
3. የምን ንድፍ አያችሁ?
4. በጉብኝት ወቅት ምን አጋጠማችሁ?

* በጉብኝት ወቅት ህጻናት አስፈላጊውን ሁሉ መረጃ ማግኘታቸውን ያረጋግጡ፡፡

ሳምንት አሰር

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ

* ነገሮችን በባህሪያቸው መሰረት ማነፃፀር፣
* የእቃዎች እንቅስቃሴዎችን ማሰስ፣
* ሌሎችን የመርዳት ሃላፊነት መገንዘብ፣
* የራሳቸውን የሰውነት ክፍሎች በመጠቀም ከ6 እስከ 8 የተለያዩ ቅርጾችን መፍጠር፣
* ቀላል ባህላዊ ጭፈራዎችን ማከናወን፣
* የኢትዮጵያ ሳንቲሞችንና ኖቶች መለየት፣
* የታሪክ መፃህፍት በመመልከት ታሪኮች መናገር፣
* እስከ 10 የሚደርሱ ቁጥሮችን መገልበጥ፣

ንዑስ ይዘቶች፦

- መለኪያ
- ዲጂታል የማንበብና መፃፍ ችሎታ
- ማህበራዊ ግንዛቤ
- የጠፈር ግንዛቤ
- ጥበባዊ ግንዛቤ
- ገንዘብ
- ንባብ
- ቁጥሮችን መፃፍ
- የመጀመሪያ ምህንድስና ክህሎቶች

ተግባር 1፦ የተግባር ሥራ

ሀ. ተመሳሳይ መለየት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- በባህሪ መመደብ፣ የሰውነት ክፍል መጠቀም፣ ማነፃፃር የቁስ እንቅ ስቃሴ፣ መቁጠር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ስርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

የተወሰኑ ትናንሽ ነገሮችን በመሰብሰብ በአንድ ላይ ያቀለቀቅሏቸው፡፡የተደባለቁትን ህፃናቱ በዓይነት በዓይነት/ በተመሳሳይነትን ፈልገው በአንድ መመደብ፡፡ በመቀጠል ስንት የተለያዩ ነገሮች እንዳገኙ ጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ሁሉንም ጠጠሮች በአንድቡድን፣ አዝራሮችንና ቅጠሎችን በሌላ ቡድን፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል ቀጥሎ የተለያየ መጠን ያላቸውን ዘንጎች ለሕፃናቱ በማደል በመጠናቸው እንዲደረድሩ ለማድረግ የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች በመከተል ያሠሯቸው፡፡

የተለያዩ መጠን ያላቸውን ዘንጎች በቁመት እና በውፍረት ማዘጋጀት፤ ሕፃናትን በቡድን በቡድን በመክፋል ማስቀመጥ፤ ዘንጎቹን ለቡድኖቹ ማደል፤ ህጻናት የተለያያ ቁመት ያላቸውን ዘንጎች አጭር፤ መከከለኛ እና ረዥም ብለው እንድደረዲሩ እና የተለያያ ውፍረት ያላቸውን ዘንጎች ቀጭን፣ መከከለኛ እና ወፍራም ብለው እንዲደረድሩ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቁልፍ አዝራሮች፣ የቅጠል ሞዴል፣ ጠጠሮች፣ ባለቀለም ዘንጎች ፣የተቆራረጡ እንጨቶችና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ህፃናቱ ያነሱት ቁስ ምንነት እንዲገልፁና እንዲቆጥሩ ይጠይቁዋቸው፡፡

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ፡፡

ለ. ነገሮችን በይዞታቸው መደርደር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መገልበጥ፣ መረዳት፣ ሀላፊነት፣ የአካል እንቅስቃሴ

'ዘ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ስርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* የተለያዩ ቁሶችን ይዘት የሚገልፁ ባዶ፣ ሙሉ፣ ያነሰ፣ የበለጠ ወዘተ በማለት እንዲያወዳድሩ ያድርጉ፡፡

* አራት አንድ አይነት የፕላስቲክ ውሃ መያዣዎች ማዘጋጀት፤ በአንደኛው እቃ ዉሃ መሙላት፤

* በሁለተኛው ዕቃ ግማሽ ዉሃ መጨመር፤ በሶስተኛው ሩብ ዉሃ መጨመር እና አራተኛውን ባዶ መተው፤

በመቀጠል እቃዎቹን እያቀያየሩ የሚይዙትንም የውሃ መጠን እያቀያየሩ ልዩነታቸውን ማረጋገጥ፤ ህጻናቱን በቡድን በቡድን እንዲቀመጡ ማድረግ፤ የተዘጋጀዉን አራቱን የፕላስቲክ ዉሃ መያዣዎችን ለእያንዳንዱ ቡድን መስጠት፤ ህጻናት ከባዶ ወደ ሙሉ እና ከሙሉ ወደ ባዶ በቅደም ተከተል እንዲደረድሩ ማድረግ፤ በስተመጨረሻም ለህጻናት ስለነገሮችን በስርዓት ስለመደርደር እና ማወዳደር ያስገንዝቧቸዉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ውሃ፣ መዘፍዘፊያ/ማስታጠቢያ**ምዘና፦** የቃል ጥያቄና ምልከታ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

1. ግማሽ የያዘው የትኛው እቃ ነው?
2. ሙሉ የያዘው የትኛው ነው?
3. የተለያ የውሃ መጠን የያዙት ለምን ይመስላችኋል?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ።

ሐ. ቁጥር መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ እንስሳት፣ ቁጥር፣ የብር ኖት

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በተግባር ሰርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

ቀጥሎ የቀረቡትን ተግባራት በመለማመጃ ደብተራቸው፣ በወረቀት፣ በደብተር ላይ እንዲሰሩ ያደርጉ። ቁጥሮችን ከአንድ እስከ አስር ፅፎ በመስጠት እንሱም አስመስለው ደግመው እንዲፅፉ ማድረግ አስፈላጊ ነው ይህን ሲያከናውኑ አጠገባቸው ከሚቀመጡ ህፃናት እርስ በርስ የመረዳዳት ባህልን እንዲያዳብሩ ማበረታታት ለምሳሌ ቁጥሩን ቅርጽ ጠብቆ ለመጻፍ የሚቸገሩ ካሉ እርስበርስ እንዲረዳዱ፣ እርሳስ ቢሰበር አንዳቸው ለአንዳቸው መቅረጽ፣ ለጺስ ቢያስፈልጋቸው አንዳቸው አንዳቸውን የማገዝ ሀላፊነት መውሰድ አስፈላጊ ነው።

በመቀጠል ስዕልና ቁጥር ማዛመድ ከ10 ያልበለጡ የቤትና የዱር እንስሳት ስዕሎች እና ቁጥሮችን እንዲያዛምዱ ማድረግ። ቀጥሎ ቁጥሮችን እና የብር ኖቶችን ማዛመድ (ምሳሌ 1 ቁጥር አንድ ብር፣ 2 ቁጥር ሁለት ብር፣ አምስት ቁጥር አምስት ብር)...

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የእንስሳት ስዕል፣ ቁጥሮች፣ ወረቀት፣ደብተር፣ እርሳስ፣ ቀለም፣ የብር ኖትና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

1. ስንት ቁጥሮችን ጻፋችሁ?

* ህጻናት ቁጥሮቹን ሰጽፉና ሰያዛምዱ ቀርበው ማየት ያስፈልጋል።

ተግባር 2፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. እንስሳትን መምሰል (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የታሪክ መፅሀፍት፣ መናገር፣ እንቅስቃሴ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

እንስሳት እርስ በእርስ በመረዳዳት ጠላታቸውን እንደሚከላከሉ የሚያሳይ የተለያዩ የእንስሳት አኗኗር እና እንቅስቃሴዎችን የሚያሳይ ቪዲዮ በማሳየት የእንስሳት አረማመድ ባህርያቸውን እንዲረዱ ያድርጉ። በቀጣይ ህፃናት ቡቡድን በመክፈል ተራ በተራ የተለያዩ የእንስሳት እንቅስቃሴ እንዲናገሩና በማስመሰል እንዲያሳዩ ያርጉ (አንድ ቡድን የውሻ፣ አንድ ቡድን የጅብ፣ የድመት ...) በተጨማሪም የተለያዩ እንስሳትን ድምፅ በማስመሰል የራሳቸውን የሰውነት ክፍል ተጠቅመው አረማመዳቸውን እያሳዩ ይጫወቱ።

 እንዲሁም በሰውነት ክፍላቸው ከ6 እስከ 8 የሚደርሱ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እንዲያሳዩ ማድረግ ያስፈልጋል ምሳሌ ቁጭ ብድግ ፣ እጅ ወደጎን፣ ወደኋላ፣ ወደፊት፣ በአንድ እግር መቆም፤

 በተጨማሪም የተለያዩ የእንስሳት ታሪኮችን የያዙ በሰዕል የተደገፊ መፅሀፍትን ያንብቡላቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ተንቀሳቃሽ ቪዲዮ፣ እንስሳት ምስል የያዘ ቪዲዮ፣ የእንስሳት ታሪክ የያዘ መጽሃፍ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

1. ምን አይነት እንስሳት አስመሰላችሁ?
2. የሰማችሁት ታሪክ የማን ነው?
3. በአካላቹ ሰንት አይነት እንቅስቃሴ ሰራቹ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ።

ተግባር 3፡- በሥራ መማር

ሀ. መስሎ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መረዳዳት፣ ሃላፊነት መውሰድ፣ የብር ኖት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

* በቅድሚያ የዕለቱን ተግባር ያስተዋውቁ።

* የታመመ ሰው መርዳት፣ የወደቀ ህፃን መርዳት፣ አይናቸው የማያዩትን መንገድ መምራትና መንገድ ማሻገር፣ የተቸገሩትን መርዳት የመሳሰሉትን በክፍል ውስጥ በመሰሎ ጨዋታ እንዲለማመዱት ያድርጉ።

* ለምሳሌ፡- ዜብራን በካርቶን በመሰራት፣ መኪና የሚነዱ ህፃናት፣ አንድ መንገደኛ አዛውንት መንገድ ማሻግር ሌሎች አሳቸውን ይዘው ሲያሻግሩ አስመስለው ይሰሩ። በሌላ ቀን ደግሞ የታመመ ሰው ተጋግዘው ሀኪም ቤት ሲወሰዱና ወዘተ እየቀያየሩ ያጫውቱ።

* እንዲሁም የኢትዮጲያ የብር ኖቶችን አይነትን መጠን እንዲሁም አገልግሎት እንዲለዩ ሃኪም ቤት ህምምተኛ ለማሳከም ሄደው ብሩን ለህክምና በመክፈል፣ መድሃኒት በመግዛት ጥቅም ላይ ማዋል እንዲችሉ፣ ሁሉም በአቅማቸው ለተቸገረ ሰው የገነዘብ መዋጮ ማድረግ እንዲችሉ ማድረግ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

* የብር ኖት/ሞዴል፣ የህክምና ሰፋራ፣ በካርቶን የተዘጋጀ ዜብራ፣የካርቶን/ከተለያዩ ፕላሰቲኮች የተዘጋጁ መኪናዎች፣ መሰሎ ጨዋታው ለመጫወት የሚያስፈልጉ አልባሳትና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፦

1. ሃላፊነት እንዴት እንወስዳለን?
2. የታመመ ሰውን እንዴት እንረዳለን?
3. ለተቸገሩት ሰዎች ስንት ስንት ብር አዋጣሽ/ህ? የተቸገረ ሰው ረድታችሁ ታውቃላችሁ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ።

ለ. ሁለቱ ልጆችና አዛውንቱ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- እንቅስቃሴ፣ መርዳት/መታዘዝ፣ የሰውነት ክፍል

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

* ድራማውን የሚተውኑ ሶስት ሕፃናት በመምረጥ ሰለድራማው ገለፃ ማድረግ እና እንደ እድሜያቸው ሁኔታ እና እንደ አካላቸው መጠን ገፀባህሪ መስጠት፣ በመቀጠል እንደሚታውኑት ገፀ ባህሪ አልባሳቱን ማስተካከል ከዚያም እያንዳንዳቸው የሚናገሩትን መንገር እንዲያውቁት ማሰያዝ እና በተሰጠው ክፍለ ጊዜ ሌሎች ልጆችን በመምረጥ ማስተፍ፤

ሁለቱ ልጆች እና ሽማግሌው

አባባ ደጉ፡- ሽማግሌ በመንደር ወስጥ እየሄዱ ይታያል

ጫላ፦ ተማሪ ሕፃን

ሶፊያ፦ ተማሪ ሕፃን

 ጫላና እና ሶፊያ የተለያዩ የሰውነት ክፍላቸውን ተጠቅመው የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እየሰሩ ይታያል

አባባደጉ፦ በመንገድ እየሄዱ ሳሉ ከዘራቸው ይወድቃል። ድንገት አጠገባቸው ሁለት ሕፃናት ሲጫወቱ ያያሉ። ከዚያም ወንዱን ልጅ "እባክህ የኔ ልጅ ከዘራውን አቀብለኝ" አሉት።

ጫላ፦ ‹‹እረ እየተጫወትኩ ነው እራሰዎ ያንሱ›› ይላቸዋል

አባባደጉ፦ "አይ የኔ ልጅ ምናለ ብታቀብለኝ" ብለው እየተንቀጠቀጡ አጎንብሰው ሊያነሱ ሲሉ ሶፊያ እየሮጠች ትመጣለች።

ሶፊያ፦ "ቆይ አባባ እኔ ላንሳሎት" በማለት አንስታ ትሰጣቸዋለች።

ጫላ፦ "አንቺ ሶፊያ አትጫወችም" ይላታል።

ሶፊያ፦ "ቆይ ከዘራቸውን ልስጣቸው፤ አንተ ግን ለምን አታነሳላቸውም ቆይ? ለመምህርት/ር ነው የምናገረው" ትላለች

ጫላ፦ "አቃጣሪ አቃጣሪ" ይላታል።

አባባደጉ፦ ከዘራውን ከተቀበሉ በኋላ "ጎሽ ተባረኪ የኔ ልጅ! አመሰግናለሁ እደጊ ብለው ይመርቋታል"

ሶፊያ፦ አየህ! አንተም ብታነሳላቸው ኖሮ ትመረቅ ነበር። ደግሞ መልካም ስራ መስራት ጥሩ ነው" አለችው።

ጫላ፦ "እሺ በቃ! ሁለተኛ አይለመደኝም" አለና ወደ አባባ ደጉ በመቅረብ ይቅርታ ጠየቀ።

አባባ ደጉ፦ በል ልጄ ተባረክ! ይቅርታ አድርጌልሃለሁ እደግ አሉት።

ጫላ፦ እሷ ስትመረቅ ከፍቶት ስለነበር በጣም ደስ ብሎት ወደ ጨዋታቸው ይመለሳሉ።

አባባ ደጉ፦ መንገዳቸውን ቀጥለው ይሔዳሉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

* ለድራማው የሚሆኑ የአዛውንት አልባሳት፣ የእስፖርት ትጥቅ፣ ዱላ/ከዘራና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከተግባሩ በኋላ ይዘቱን መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፦

1. ሶፊያና እና ጫላ ምን እየሰሩ ነበር?
2. አባባ ደጉ በመንገድ ሲሄዱ ምን አጋጠማቸው?
3. የአባባ ደጉን ዱላ ማን አነሳላቸው?
4. የአዛወንቱ ስም ማነው?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ።

ተግባር 4፦ ተረት

ሀ.እናት አይጥና ልጅ ታሪክ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መረዳዳት፣ ሃላፊነት፣ ታሪክ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ስለ አይጥ እናትና ልጅ ታሪክ ከማንበባችሁ በፊት ስዕሎቹን በማሳየት ቀጣዩ ታሪክ ስለምን እንደሆነ ግምታቸውን እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ “ይህ ታሪክ ስለምን ይመስላችኋል?” በማለት ስታነቡት ህጻናት ጥያቄ እንዲጠይቁ ወይም አስተያየት እንዲሰጡ ዕድል ይስጧቸው፡፡ እንደገና ልታነቡት ትችላላችሁ፡፡ ስታነቡት ቃል በቃል በጣቶቻችሁ እያመለከታችሁ ይሁን፡፡ ህጻናት ቃላቶችን አንድ በአንድ በመከታተልና በመመልከት ማንበብ ይወዳሉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የአይጥ፣ የቤት፣ የምግብና የሰው ስዕል

እናት አይጥና ልጅ ታሪክ

በድሮ ዘመን እናትና ልጅ አይጥ አብሮ ይኖሩ ነበር፡፡ እናትየው አይጥ ሁሌ እየዞረች የሰዎች ትርፍራፊና ሳይከደኑ የሚቀመጡ ምግቦችን በየሰው ቤት ተደብቃ እየገባች ለልጇ ትመግባታለች፡፡ በለሊት ተነስታ ከቤት ለቤት እየዞረች ለልጇ ምግብ እያመጣች መመገቧን ቀጠለች፡፡ የሰው ቤት ስትገባ የቤቱ ባለቤቶች እንዳይሰሙ በጥንቃቄ የተጣሉትን ምግቦች ትለቃቅማለች፡፡ የምትጠነቀቀው ባለቤቶቹ ካዩአት ስለሚገዱላት እና ለልጇ ምግብ የሚያመጣላት ስለማይኖር ነው፡፡

ከእለታት አንድ ቀን ልጇ “እናቴ አንቺ እየዞርሽ ጥሩ ጥሩ ምግብ እየበላሽ ያንቺን ትራፊ ታመጪልኛለሽ? እኔም መሄድ አለብኝ” ስትላት ልጄ እኔ ምንም ሳልመገብ ነው ላንቺ የማመጣው አንቺ የሰው ቤት ከሄድሽ ይገድሉሻል ትላታለች እኔ አንቺን የመጠበቅ ሃላፊነት አለብኝ በማለት አስረዳቻት፡፡ ትንሷ አይጥ ግን የእናቷን ምክር አልሰማ በማለት አንድ ቀን ተነስታ የሰው ቤት ስትሄድ ማሙሽ በማየቱ እየሮጠ ሄዶ በእግሩ ጨፍልቆ ገደላት ማሙሽ ይህንን በማድረጉ ተደሰ ተዘለለ፡፡ ትንሷ አይጥ የእናቷን እንክብካቤ ሳትረዳ በመቅረቷ ህይወቷን አጣች፡፡

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

1. እናት አይጥ ለልጇ ምግብ የምታመጠው እንዴት ነበር?
2. ትንሷ አይጥ ምን ለማድረግ አሰበች?
3. ምን አጋጠማት?
4. ታሪኩ እንዴት ተፈጸመ?

ተግባር 5፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. ቅርጽ መሥራትና ሃላፊነት መወጣት (2 ክፍል ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ትላልቅ ጡንቻወች፣ እንስሳት፣ ባህላዊ ጭፈራ፣ ኃላፊነት፣ ሌሎችን መርዳት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናትን ወደውጭ ይዘው በመውጣት በቡድን ይክፈሏቸው፡፡ በአንድ ቡድን ቢያንስ አሰር ሴትና ወንድ ያለበት ቡድን ያደራጁ፡፡

- በቅድሚያ በየቡድናቸው ክብ ይሰ፡፡ሩ ቀጥሎ እርሶ ለሁሉም በሚታዩበት ቦታ በመሆን በሰውነቶ የተለያዩ ቅርፆችን እየሰሩ በማሳየት እነሱም እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- ቀጥሎ ህፃናቱ በየቡድናቸው ተራ በተራ የራሳቸውን ፈጠራ በሰውነታቸው እየፈጠሩ የተለያዩ ቅርጾችን እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- ቀጥሎ ልጆች በቸርነትና በኃላፊነት ተግባር ሊሳተፉ የሚችሉባቸውን እንቅስቃሴዎች ማመቻቸት፤ ለምሳሌ፡- የቤት እንሰሳትን መንከባከብ (አንዱ ቡድን የቤት እንሰሳ ሆኖ ሌላኛው ሲንከባከብ)፣ ወፎችን መመገብ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ላይ መሳተፍ ለምሳሌ፡- አታክልት መንከባከብ፣ ወሃ ማጠጣት፣ አከባቢን ማጽዳት ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፤
- ባህላዊ ሙዚቃዎችን በመክፈት በየቡድናቸው የተለያዩ ውዝዋዜዎችን እንዲጫዋቱ ማድረግም አሰፈላጊ ነው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የአትክልት ማጠጫ፣ የአካባቢ ጽዳት የሚያገለግሉ የፅዳት እቃዎች ፣ ወፎችን ለመመገብ ጥራጥሬ፣ ውሃ ና ውሃ ማጠጫ ሳህን፣ የእንሰሳት መመገቢያ እቃ፣ ሳር፣ ሞንታርቦ፣ ጂፓስ፣ ሰልክ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

1. ምን አይነት እንቅስቃሴ ሰራሽ/ህ?
2. የትኛውን የሰውነት ክፍል ተጠቀምን?
3. ምን አይነት የማህበረሰብ አገልግሎት ውሰጥ ተሳተፍሽ/ክ?
4. ማንንና እንዴት ተንከባከባችሁ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ፡፡

ለ. ትንሹና ትልቁ ጎማ (1 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- በሰውነት፣ የተለያዩ ቅርጾች፣ መሰራት፣ ባህላዊ ጭፈራ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱን ወደውጭ ይዞ በመውጣት በቡድን በማድረግ ጨዋታውን ህግ ጠብቆ እንዲጫወቱ ማድረግ ህፃናቱ ኃላፊነትን የመወጣት ልምምድ ማዳበር ስለሚያስፈልጋቸው

* ተራን ጠብቆ መጫወት፣ ሲሸነፉ መሸነፋቸውን አምኖ መቀበልን እንዲለማመዱ ይሄን ጨዋታ አጫውቷቸው፡ ፡ ትንሹ ጎማ ትልቁ ጎማ ተሽከረከረን ጨዋታ እንደሚከተለው ማጫወት፡-

• በመጀመሪያ 9 ወንዶችን እና 9 ሴቶችን በመምረጥ 6ቱን ሕፃናት መጀመሪያ ክብ እንዲሰሩ የቀሩት 12 ሕፃናት ደግሞ ከመጀመሪያው ክብ ዳርበው ሌላ ክብ እንዲሰሩ ማድረግ እና ተራቸውን የሚጠብቁት ሌሎቹ ህፃናት ያሉት እያጨበጨቡ ትንሹ ጎማ ተሽከረከረ ሲሉ ከመሀል ያሉት ይሽከረክራሉ፣

• ከመሀል ያሉት ደግሞ ቆመው ትልቁ ጎማ ተሽከረከረ እያሉ ሲያጨበጭቡ ከዳር ያሉት በተራቸው ይሽከረከራሉ በዚህ ሁኔታ ሁሉንም ሕፃናት በማሳተፍ ጨዋታውን ማስቀጠል።

• ትልቁ ጎማ ተሽከረከረ ሲባል ትንሹ ጎማ የሆኑት ያልቆሙካሉ/ትንሹ ጎማ ተሽከረከረ ሲባል ከትልቁ ያልቆሙ ካሉ ከጨዋታው ውጪ እንዲሆኑ እየተደረገ በተራቸው እንዲጫወቱ አድርጉ፡

• ቀጥሎ የሚወዱትን ባህላዊ ጨዋታ እየመረጡ ጭፈራ እንዲያሳዩ ለሁሉም ህፃናት እድል ይስጡ እንዲሁም ስለባህሉ ገለጻ እንዲያደርጉእና ሚያውቁትን ባህል ዘፈን በድምፃቸው እንዲያሰሙ እድል ይስጧቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ሞንታርቦ፣ ጂፓስ፣ ስልክ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

1. ምን አይነት ጨዋታ ተጫወታችሁ?
2. በጨዋታው ላይ የነበራችሁ ሃላፊነት ምን ነበር?
3. የትኛውን ባህል ውዝወዜ ሰራሽ/ህ?

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን ክትትል ያድርጉ።

ተግባር 6፡- ውይይት

ሀ. ሳንትሞችና የብር ኖቶች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሳንቲም፣ የብር ኖት፣ ግብይት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የሳንቲምና የብር ኖት የያዙ ሞዴሎች፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣ ደብተር

የመምህር ሚና፡-

መምህርት ህፃናቱን ቀጥሎ የቀረቡትን የመወያያ ነጥቦች በመንገር ሕፃናት እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡

 ብር እና ሳንቲሞችን ለሕፃናት በማሳየት ከዚህ በፊት ያውቁት እንደነበረ ለምን እንደሚጠቅም እና ልዩነታቸውን እንዲገልፁ እድሉን በመስጠት፣ ለመነሻ የሚሆን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተራ በተራ እድል በመስጠት ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ እድል መሰጠት፤

ለምሳሌ ሳንቲምና የብር ኖት ልዩነትና ጥቅማቸው፣ ብሮችን እና የሳንቲም ስእሎችን /ሞዴል/ትክክለኛውን ብር እና ሳንቲም በማሳየት እሄ የስንት ብር ኖት ነው? የመሳሳሉ መወያያዎችን መጠየቅ እና መወየያት

 ቀጥሎ የሳንቲሞችና የብር ኖቶችን ፍላሽ ካርድ ለየቡድኑ በመስጠት ከትንሽ ወደ ትልቅ እንዲደረድሩ ያድርጉ፡ ፡ ምሳሌ 1 ብር፣ አምስት ብር፣ አሰር ብር፣ ሃምሳ ብር፣ መቶ ብር፣ ሁለት መቶ ብር

 በመጨረሻም የብር ኖቶችን እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

1. ትንሹ የብር ኖት የቱ ነው?

2.ገንዘብ ለምን ጥቅም ይውላል?

* ህጻናት ውይይቱን በትክክል መካፈላቸውን ይመልከቱ፡፡

ሳምንት አሰራ አንድ

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

* የጀግኖችን 5 ሚናዎች መጥቀስ፣
* ስለ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ አካባቢ ስሜት መግለፅ፣
* ትክክልና ስህተት የሆነውን መረዳት፣
* በጊዜ ሂደት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን መለየት፣
* ቀላል ተግባራትን ማከናወን፣
* ትላልቅ ፍደላትን ከትናንሽ ፊደላት ጋር ማዛመድ፣
* የድምጽ ፍጥነት ላይ ተመስርቶ እንቅስቃሴ ማከናወን፣
* እስከ 15 የሚሆኑ እቃዎችን ከቁጥሮች ጋር ማዛመድ፣
* በድራማ ቀላል የሰው አፈ ታሪክ መስራት፣

ንዑስ ይዘቶች፦

• የሀገርፍቅር
• የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አካባቢ
• ግብረገብነት
• ጊዜ
• የግልነጻነት
• ፍደላት መጻፍ
• ሙዚቃዊ እንቅስቃሴዎች
• የዕቃዎች እና ቁጥሮች ተዛማጅነት
• ባህላዊ ቅርሶች
• ቁጥሮችን መፃፍ

ተግባር 1፡- መዝሙር

ሀ. ትንሿ ድመት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ፣ እንቅስቃሴ፣ ትክክልና እንስሳት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የድመት ምስል የያዘ ካርድ፣ ቴፕ/ጂፓስ/ሞባይልና ወዘተ

መዝሙር 1፡- ትንሿ ድመት

ይህች ትንሽ ድመት ቀበጠች
በቅርጫት ታዝላ ገበያ ዋለች
ይህች ትንሽ ድመት ጠገበች
የላም ወተቷን ጠጥታ ቤት እየዋለች
5፣ 6፣ 7፣ ጊዜ እየዘለለች
ከመሬት ወድቃ እግሯን ተሰበረች
በጣም ስለተጎዳች አለቀሰች
ድጋሚ ላለመዝለል ማለች
አዘነች በጣም እናቷም አይታት
አይዞሽ ልጄ ብላ አባበለቻት
ዳግም እንዳትዘል ምክር ሰጠቻት 2x፡፡

ምዘና፡- "ድመቷ ምን አደረገች? ከመዝሙሩ ውስጥ ተፈጥሮአዊ ነገር የሆኑት የትኞቹ ናቸው? ድመቷ ያደረገችው ትክክል ነበር?" በማለት ይጠይቋቸው፡፡

ለ. አንደኛ መሆን (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፊደል፣ ተግባራት፣ ጀግንነት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የድመት ምስል የያዘ ካርድ፣ ቴፕ/ጂፓስ/ሞባይልና ወዘተ

መዝሙር 2:- አንደኛ መሆን

አንደኛ መሆንን እሻለሁ
ጠዋት ተነስቼ
ፊቴንና እጆቼን እተጣጠባለሁ
ቁርሴን ተመግቤ ወደ ትምህርቴ እሄዳለሁ
ደግሞም ትምህርት ሲያልቅ
ቤቴ እመለሳለሁ
እማዬና አባዬን በስራ እግዛለሁ
በእረፍት ጊዜዬ ቁጭ ብዬ አጠናለሁ
አንደኛ ለመሆን ጥረት አደርጋለሁ
ስለዚህ ሁል ጊዜ ደብተር እገልጣለሁ
ፈ ፈረሰ አ አይጥ እያልኩ ፊደል አነባለሁ።

ምዘና፡-

* "ጠዋት ተነስተን ምን ምን እናደርጋለን?" በማለት ይጠይቋቸው።

* የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ በቃል ይንገሯቸው።

ተግባር 2፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. እንቆቅልሽ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ፣ ትክክልና ስዕተት፣ ጀግንነት

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ከሰር ያለውን እንቆቅልሽ የእንቆቅልሽን ስርዓት በተከተለ መልኩ እርስዎ ጠያቂ በመሆን ህጻናቱ ደግሞ መላሽ በመሆን ያሰራቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የአጼ ሚኒልክ ሰዕል/ፎቶ፣ የነብር፣ አንበሳ፣ ውሻ ሰዕል፣ የመሬት ሰዕልና ወዘተ

እንቆቅልሽ ምን አውቅልህ/ሽ

የዱር አራዊት ነኝ፡፡ የምመገበው የሌሎችን እንሰሳት ስጋ ነው፡፡ የምፈራና የምከበር ነኝ፡፡ ሰዎች የጀግንነት መገለጫ አድርገው ሰያሜዬን ይጠቀሙታል፡፡ የጫካ ንጉሰ በመባል እታወቃለው፡፡ እኔ ማነኝ?

መልሱ፡- አንበሳ

እናንተ ቤት ጸሩብኛላችሁ፡፡ ዛፎች ይተከሉብኛል፡፡ እንሰሳትም ይኖሩብኛል፡፡ በተፈጥሮ የተገኘሁ ነኝ፡፡ እኔ ማን ነኝ?

መልሰ›- መሬት

እናትና አባቴን እከብራለው፡፡ ከጓደኞቹ ጋር በጋራ እጫወታለሁ፡፡ ታዛዥነኝ፡፡ ምን አይነት ሰነ ምግባር አለኝ፡፡

መልሰ፡- ጥሩ/ደመልካም

የቤት እንሰሳት ነኝ፡፡ የምኖረው ከሰዎች ጋር ነው፡፡ የምታወቀው ሌባ ጠባቂ ተብዬ ነው፡፡ የምመገበው የተሰጠኝን ምግብና አጥንት ነው፡፡ እኔ ማን ነኝ?

መልሱ፡- ውሻ

የምኖረው በጫካ ነው፡፡ የምመገበው ስጋ ነው፡፡ የድመት ዝርያ ነኝ፡፡ በመሮጥ እታወቃለው፡፡ ጥፍሮቼም በጣም አደገኛ ናቸው፡፡ እኔ ማነኝ?

መልሱ- ነብር

የሀገር መሪ ነበርኩኝ፡፡ መንገድ፣ መብራት፣ ሰልክ የተሰራው በእኔ ጊዜ ነው፡፡ ትምህርት በእኔ ጊዜ ተጀምሯል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ መኪና ያሽከረከርኩት እኔ ነበርኩኝ፡፡ እኔ ማን ነኝ?

መልሱ፦ አጼ ሚኒልክ

ምዘና፡- የእያንዳንዱን እንቆቅልሽ ፍሬ ሀሳብ በቃል መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

ለ. የፊደል ወጥ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቀላል፣ እንቅስቃሴ፣ ፊደል

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ይህንን ጨዋታ ለማጫወት የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራትን ያከናውኑ፡፡

* በቅድሚያ አስፈላጊ ሁሉ ግብዓቶችን ያዘጋጁ፡፡

* በመቀጠል የጨዋታውን ርዕስ ያስተዋውቁ፡፡

* ከዚያ የተዘጋጁ ቁሶችን በመጠቀም የፊደል ወጥ ሰርተው ያቅምሷቸው፡፡ (የፊደል ወጡን ሰሩ ባዶ ካርቶኑን እንደድስት፣ የፊደል ፍላሽ ካርዶችን እንደወጡ ግብዓቶች አድርገው ይጠቀሙ፡፡ የወጥ አሰራሩን ካሳያቿቸው እኋላ እያንዳንዱ ህጻን እየተነሳ ከድስቱ ውስጥ ካርድ ያነሳና የፊደሉን ሰም እንዲጠራ ያድርጉ፡፡

* በመጨረሻም ከዚህ በፊት የተዋወቋቸውን ተመሳሳይ ፊደላት እንዲያዛምዱ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደላት ፍላሽ ካርዶች፣ ባዶ ካርቶን፣ ማማሰያ እንጨትና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፡

ሁሉም ህጻናት ያነሱትን ካርድ እያዩ ፍደሉን እንዲጠሩ ያድርጓቸው፡፡

ሐ. በቁጥር ቡድን መፍጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ተፈጥሮአዊ፣ ቁጥር፣ ድምጽ፣ ጀግንነት

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናት በቡድን በማደራጀት የተለያዩ የእንስሳት ገፅ ባህሪ በመወከል እንዲጫወቱ ይርዳቸው፡፡

* "በቁጥሮች ቡድን መፍጠር" የሚለውን ጨዋታ እንደሚጫወቱ መግለጽ፡፡

* ሁሉም ህፃናት በክብ እንዲቆሙ ማድረግ፡፡

* ለሁሉም ህፃናት 15 አይነት እንስሳትን የያዘ ምስል ናአብሮ ቁጥር ያለበትን ምስል በማዘጋጀት የቡድን ቁጥራቸውንም አስራ አምስት በማድረግ ይመድባቸው፡፡ ከዚያ በተመደቡበት ምድብ ውስጥ ያዘጋጁትን ካርድ መሀል ላይ በማድረግ አንድ አንድ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡ ሁሉም ህጻን መውሰዱን ያረጋግጡ፡፡

* የያዙትን ካርድና በማየት እንዲዘጋጁና እንደ ደረሳቸው እንስሳት በማስመሰል ድምፅ እንዲያወጡ ማድረግ፡፡

* ከሁሉም ቡድን አንበሳ የደረሰው ህጻን አንበሳ ሲባል ጀግና እንደሆንና መሀል በመግባት እንደ አንበሳ እያስመሰለ ቁጥር እንዲጠራ የተጠራውን ቁጥር የያዙት ህፃናት ክቡ ውስጥ እንዲገቡና እጅ ለእጅ እንዲያያዙ ማድረግ ሁሉም ከተጠራ በኋላ ቁጥሩ በፍጥነት ሲጠራ 1 2 3 4 5 ...... 15 ሆነው በፍጥነት እንዲሽከረከሩ ማድረግ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የእንስሳትና ቁጥሮችን የያዘ ፍላሽ ካርድ፣ ሞዴል፣ ቴፕ/ጂፓስ/ሞንታርቦና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ፡

“እስከ አስራ አምስት ድረስ ቁጠርልኝ? እንደማን ሆናችሁ ስራችሁ?” በማለት ይጠይቋቸው።

* ህፃናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ ትኩረት ሰጥተው መተግበራቸውን በመከታተል ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያድርጉ።

ተግባር 3፡- የመስክ ጉብኝት

ሀ. የትምህርት ቤት ግኡብኝት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ፣ ቁጥር፣ ተግባር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

• ህጻናቱ በግቢያቸው ውስጥ ያሉትን ነገሮች እንዲጎበኙ አሰልፈው ወደውጭ ይዘው ይውጡ።

• ያዩዋቸውን ነገሮች ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮች በማለት እንዲናገሩና በተለይ በቀላሉ መያዝ የሚችሉትን ነገሮች ለምሳሌ ጠጠር፣ ድንጋይ፣ ቅጠል፣ ቁርኪ፣ የሀይላንድ ክዳን የመሳሰሉትን ለቅመው እንዲይዙ ማድረግ፣

• ከዚያም ከጉብኝቱ በኋላ ምን ምን እንዳዩ ተፈጥሮአዊ የሆነው የቱ እንደሆነ እና ሰው ሰራሽ የሆነው የቱ እንደሆነ ለይተው ይናገሩ።

• ለቅመው ያመጡትን እንዲቆጥሩና ብዛታቸውን እንዲናገሩ፣ ምን ያህሉ ተፈርሮአዊና ሰው ሰራሽ እንደሆኑ ለይተው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችንና ቁጥሮችን የያዘ ካርድ፣ሞዴል፣ ጠጠር፣ ድንጋይ፣ ቅጠል፣ ቁርኪ፣ የሀይላንድ ክዳንና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

1. ተፈጥሮአዊ ነገሮችን ምን አገኛችሁ?
2. ሰው ሰራሽ ነገሮችን ምን ምን አያችሁ?፣
3. ስንት ቁሶችንቆጠራችሁ?

* በጉብኝት ወቅት ህጻናት አስፈላጊውን ሁሉ መረጃ ማግኘታቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 4፦ ውይይት

ሀ. የጊዜ ሂደት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ፣ ድርጊት፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

* በቅድሚያ በወረቀት/በቻርት ክብ በመስራት ቀላ ያለ ቢጫ/ብርቱካናማ ቀለም ይቀቡና የቱን ጊዜ እንደሚወክል ያወያዩአቸው።

* ቀጥሎ ማታን ደሞ በምን ሊወከል/ሊገለጽ እንደሚችል ሃሳብ ከነሱ ይጠይቁ። ህፃናቶች የውይይት ሃሳብ እንዲያቀርቡ እድል ከሰጡ በኋላ ግማሽ ክብ ሰርቶ ጥቁር ቀለም በመቀባትና ከዋክብቶችንም በመስራት የቱን ጊዜ እንደሚያሳይ ያወያዩ።

* ፀሀይና ጨረቃ ተፈጥሮአዊ መሆናቸውን ቀንና ሌሊትም በተፈጥሮ የሚለዋወጡ መሆናቸውን ይንገራቸው።

* በጠዋት፣ በቀን፣ በማታና በሌሊት የሚከናወኑ ተግባራትን በሥዕል ያሳያቸውና ፣ለምሳሌ፦ ጥርስን በቡርሽ መቦረሽ/በመፋቂያ መፋቅ፣ እጅንና ፊትን በሳሙና መታጠብ፣ መስታወት ማየት (መስታወት፣ ቡርሽ፣ ሳሙና) ሰው ሰራሽ እንደሆኑ ይግለጹላቸው።

* በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ውስጥ ትምህርት ቤት ሲውሉና እቤት ሲሆኑ ምን እንደሚያከናውኑ፣ የሚያከናውኑበትን ሰዓት ጠዋት፣ ምሳ ሰአት፣ ማታ በማለት እርስ በእርስ እንዲወያዩና የተወያዩበትን ሀሳብ ከውይይቱ በኃላ እንዲናገሩ ያበረታታቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የሰዓት ሰዕል፣ ቀለም፣ ወረቀትና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

1. በየእለቱ የምንጠቀማቸው ሰው ሰራሽ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

* ህጻናት ውይይቱን በትክክል መካፈላቸውን ይመልከቱ።

ለ. ጀግኖች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ጀግንነት፣ ሚና፣ ትክክል፣ ስህተት

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

* የተለያዩ ለሀገራቸው ትልልቅ ስራዎችን የሰሩ ሰዎችን ፎቶ/ምስል በማቅረብና እንዲወያዩ ማድረግ፤

* ለዚህም ቀጥሎ ያለውን ይከተሉ (የሯጮች፣ የሀገር መሪዎች፣ በጎተግባር ላይ የተሰማሩ፣ አርአያ የሆኑ የወላጆች፣ አካል ጉዳተኛ ሆነው ታዋቂ የሆኑ ሰዎች… ከሁሉም ሴትና ወንድ ጾታን የሚወክሉ ሆነው መቅረብ አለባቸው)

* በቅዲሚያ ቢያንስ ሶስት/አራት ህጻናት የያዘ ቡድን ማደራጀት

* ፀሃፊ እና ሰብሳቢ መምረጥ

* የመወያያ ጥያቄ መስጠት 1. ጀግና የሚባሉት ምን የሰሩ ሰዎች ናቸው፣ ለእናንተ ጀግናቹ ማነው፣ ትክክል እና ስህተት የሚባሉ ነገሮች ምንድናቸው …)

* ውይይቱን ሲጨርሱ ሁሉም በተወካዮቻቸው አማካኝነት የተወያዩበትን እንዲያቀርቡ ማድረግ

* ሲያቀርቡ ከብቃቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥያቄዎች በየመሃሉ መጠየቅ ይኖርቦታል (ስህተት የምንሰረው እንዴት ነው? ስህተት ላለመሰራት ምን ማድረግ ይኖርብናል? ጀግና መሆን ያለብን መቼ ነው?

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የተለያዩ የጀግንን ተግበር የሰሩ ሰዎች ፎቶ/ሰዕል፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣ በሰልክ /በቴሌቪዢን…

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

1.ካያችሁት ውስጥ ንግስት ጣይቱ ምን ሰራች?

2. የቃቄ ወረድ ምንሰራች?

ተግባር 5፦ ተረት

ሀ. ድመትና ትንሿ አይጥ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ተፈጥሮና ሰው ስራሽ፣ ትክክልና ስህተት፣ ጊዜ፣ ጀግንነት

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፦

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የድመትና የአይጥ ምሰል/ሞዴል፣ የጊዜን መፈራረቅ የሚጠቁም ቻርት/ቪድዮ፣

ድመትና ትንሿ አይጥ

አይጥ እና ድመት በአንድ መንደር ውስጥ የሚኖር ውሮ የሚባል ድመት ነበር አንድ ቀን ጠዋት ተነስቶ ውጪውን ሲመለከት ፀሀይ ወጥታ ደስ የሚል ሙቀት እየሰጠች መሆኑን በማየቱ ከቤቱ በራፍ ላይ ጋደም ብሎ ፀሀይ መሞቅ ጀመረ ሙቀቱ ደስ አለው ውሮ የሚኖርበት ቤት ውስጥ አይጥ የሚባል የለም እያደነ ይበላቸዋል በዚህም ጀግናው ድመት ይባላል፡፡

ከተኛበት ቤት ግድግዳ ስር ኮሽ-ኮሽ የሚል ድምፅ ሰማና ቀና ብሎ ሲያይ ትንሽ ቀዳዳ ከግድግዳው ስር ተመለከቶ ምንም ሲያጣ ተመልሶ ጋደም አለ። አሁንም ኮሽ-ኮሽ የሚል ድምፅ ሰማና ቀና ብሎ ሲመለከት አንዲት ትንሽ አይጥ ከቤቱ ግድግዳ ስር ባለው ትንሽ ቀዳዳ አንገቷን አውጥታ ውጪውን ታያለች። ውሮ ሊይዛት ብድግ ሲልጉድ ጓዱ ውስጥ ግብት አለች። ውሮ ተናደደ "ቆይ እንደገና ትመጫለሽ" በማለት ዛተና ጋደም ብሎ መጠበቁን ቀጠለ። አይጥ ከጉድጓድ ውጪ ያለውን ማየት ስለፈለገች እንደገና ብቅ አለች ውሮ በፍጥነት ሊይዛት ተነሳ ትንሷ አይጥ ፈጥና ወደ ጉድጓድ ዘላ ስትገባ አንድ ጥግ ላይ የነበረው ድንጋይ እግሯን መታት እያነከሰች ወደ ጉድጓድ ውስጥ ገባች እናቷ አየቻትና " ልጄ ምን ሆነሽ ነው የምታነክሽው ? ወደ ውጪ ወጣሽ እንዴ? ውሮ ይበላሻል፤ ወደ ውጪ አትውጪ አላልኩሽም! ልጄ የእናት ትእዛዝ አለመስማት ጥሩ አይደለም" ስትላት ትንሷ አይጥ በማዘን "እናቴ ይቅርታ አድርጊልኝ ሁለተኛ አልወጣም ምክርሽን እፈፅማለሁ" አለቻት።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

1. ውሮ አይጥ በማደኑና ከቤት ውስጥ በማጥፋቱ ምን ስም ወጣላት?

2. ሰው ሰራሽ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

3. አይጧ ትክክል ያልሆነ ተግባር ምን ፈፀመች?

ተግባር 6፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. መስሎ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ፣ ትክክልና ስህተት፣ ጊዜ፣ ጀግንነት፣ ትወና

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናቱ ከላይ ያለውን ተረት በተግባር እንዲሰሩ ይርዳቸው ለዚህም ከወረቀት/ከካርቶን ገጸ ባህሪያቱን የሚወክል የፊት ማስክ ያዘጋጁላቸው።

* የተረቱን ገፀባ ህርያት ወክለው ሲጫወቱ ተረቱን የተገነዘቡበትን አግባብ በመረዳት እገዛ ያድርጉላቸው፡

* በተረቱ መሰረት እንዲጫወቱ ሶስት ሶስት በማድረግ ይመድባቸው። እናት አይጥ፣ ትንሽ አይጥና ድመት...

* እርስ በእርስ አይጥ በመሆን ሲጫወቱ እንዳይሰማቸው ደግመው ድመት በመሆን እንዲተውኑ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተረት መፅሀፍ፣ አልባሳት፣ የፊት ማስክ፣ የፀሀይ ምስል በቻርት ከፍ ብሎ የተሳለ የድመትና የአይጥ ምስል

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

1.ምን ወክላችሁ ተጫወታችሁ?

2. ድመትና አይጥ ምን አደረጉ?

የአውድ 2 ማጠቃለያ መመዘኛ ቼክ-ሊስት

የህጻኑ/ኗ ስም፡______________________ **ጾታ፡** ________ **ዕድሜ**______

ተ.ቁ	የሚጠበቅ ተፈላጊ የዕድገትና የመማር ብቃት	ጥሩ	በ. ጥሩ	እ. በ. ጥሩ
1	የሚሰጡ ሆያትን ደግሞ መፃፍ			
2	የታሪኮችን መልዕክት መልሶ መናገር			
3	ከፆታዊ ወገኝትነት የፀዳ አስተሳሰብን ማከናወን			
4	እንደ የራስን ጫማ ማሰር መሰረታዊ የሆኑትን ክሎቶችን በወላጅ እና በመምህር እገዛ ማከናወን			
5	ትክክልና ስህተት የሆነውን ከማበረታታትና ከቅጣት አንጻር መረዳት			
6	እስከ 15 ድረስ ያሉ ቁጥሮችን እና እቃዋችን ማዛመድ			
7	እስከ 15 ድረስ ያሉ ቁጥሮችን ማግናኘት፣ መገልበጥ፣ መፃፍ እና የቁጥሮች ቅደም ተከተል ማስያዝ			
8	የቁጥሮችን ቀዳሚና ተከታይ መለየት			
9	የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እና መመገብያ ቦታ ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊነትን መግለፅ			
10	እርሳስን በተገቢው ሁኔታ በመያዝ የሚለዩ ሆሄያትን እና ቁጥሮችን መፃፍ			
11	ለተለያዩ እንቅሰቃሴዎች ትንንሽ ጡንቻን መቆጣጠር እና መጠቀም			
12	በቤት ውሰጥ የሚታወቁ እቃዎችና ባህሪያቸውን መግለፅ			
13	የሌሎችን ሃላፊነት ስራ እና ሙያዎች እውቅና መስጠት			
14	ግንባታን፣ መሳልን፣ ማቅለምን፣ ቀለም መቀባትን፣ ህትመትን፣ ቅርፃቅርፆችን መፍጠር፣			
15	መሰረታዊ የጆሜትሪ ቅርፆችን በአከባቢ ከሚገኙት ቅርፆች ጋር ማገናኘት			

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፦ ____

____

____

____

አውድ ሶስት፦ ሥራ

ለአውዱ የተሰጠ ጊዜ፦ 5 ሳምንት/150 ክ/ጊዜ

መግቢያ

ይህ አውድ ሥራ ተብለው የተሰየመና ለዚህ ደረጃ ትምህርት ከተመረጡ ስድስት አውዶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በዚህ አውድም በሌሎች አውዶች ይቀናጁ የነበሩ የትምህርት ይዘቶች የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ባማከለ መልኩ እንዲደራጁ ታስበው ቀርቧል፡፡ አውዱ ህጻናት በአካባቢያቸው ስለሚያዩአቸው ልዩ ልዩ ሥራዎች ባህሪያት፣ ጠቀሜታዎች፣ ክቡርነትና አስፈላጊነት እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል፡፡ የተቀናጀ ትምህርት የሚቀርበው በአንድ ተግባር ውስጥ ቢያንስ ከሶስት በላይ ይዘቶች ተቀናጅተው መቅረብ ስችሉ ነው፡፡ በዚህ አውድ ስር የተቀናጁ ይዘቶች (ቅድመ ስሌት፣ የቋንቋ እድገት፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ የአካል መዳበር፣ የማህበራዊና ስሜት መዳበር እንዲሁም የስነ-ጥበባት ግንዛቤ) ከሥራ ዓይነቶች ጋር ተቆራኝተው እንዲቀርቡ የታሰቡ ናቸው፡፡

የእድገትና የመማር ውጤቶች፦

ህጻናት ከዚህ አውድ ትምህርት በኋላ፦

- ሆሄያት/ፊደላት እና የድምፃቸውን ቅላፄ መረዳት
- የሆያት ቤተሰብ ድምጽ እና ቅርፅ መለየት፣
- ስዕሎች፣ሆሄያት እና ቀላል ቃላቶችን ማነበብ፣
- ከሌላ አቅጣጫ በመዞር አቅጣጫ መያዝ፣
- ከሁለት አማራጮጭን መለየትና ምርጫ ማድረግ፣
- እስከ 20 ድረሰ ያሉትን ቁጥሮች ወደፊት እና ወደኋላ መቁጠር፣
- ቀላል ንድፍ (ነጠላ ንድፎች) መረዳትና መፍጠር፣
- የጎደሉ ቁጥሮችን መለየት፣
- ከ5-7 የሚደርሱ የተለመዱ ጤናማ ምግቦች እና መጠጦች መለየት፣
- በመንቀሳቀስ እና ሳይንቀሳቀሱ ትክክለኛ አፈጻጸም ክሎታቸውን ማሳየት፣
- በድምፅ ፍጥነት መሰረት እንቅስቃሴዎችን በመምረጥ ተግባራትን ማከናወን፣

አበይት ይዘቶች፡-

- ራስን ማስተዋወቅ
- ራስን ማወቅና መግለጽ
- የሰው ሰውነት ክፍሎች
- ጤናና አካላዊ ጥንካሬ
- ማንበብ
- ቁጥርና ቆጠራ
- ውበትን መረዳትና ማድነቅ
- ገንዘብ
- ራስን መቆጣጠር
- ራስንና የቅርብ አካባቢን መንከባከብ
- ፊደላትን መገለበጥ
- የትንንሽ ጡንቻዎች መዳበር
- ማህበራዊ መስተጋብር
- ውሳኔ ሰጭነት
- ጥንቃቀና ደህንነት
- የቃላት ዕውቀት
- ምግብ
- ቁጥሮችን መወዳደርና መደረደር
- ድምጾችን መለየት
- ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አካባቢ
- ሥርዓተ-ድርድር
- የሀገር ፍቅር ስሜት
- የባህል ቅርሶች
- ድጂታል ሊቲሬሲ
- መለካት
- ቅርጸ-ቅርጽ
- ሀገራዊ እሴቶቻችን

ሳምንት አስራ ሁለት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

- የቅርብ የቤተሰብ አባላት ስምና ዝምድናቸውን ይናገራሉ፣
- ስለ ፆታ ነጻ ጽንሰ-ሐሳብ ያገኛሉ፣
- ስዕል በመሳል ስሜታቸውን እና ፍላጎታቸውን ይገልፃሉ፣
- የአምስት የስሜት ህዋሳት ተግባር ይገልፃሉ
- በአካል እንቅስቃሴ ግዜ አካባቢውን ንፁህ ማድረግ ለምን እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ
- የህትመት ስዕሎችን በማየት የሰዎችን ስሜት ይረዳሉ፣
- እስከ 15 የሚደርሱ ቁሶችን ይቆጥራሉ፣
- በቤት ውስጥ የሚጠቀሙ እቃዎች ስዕል ይስላሉ፣
- የኢትዮጵያ ሳንቲሞች እና የብር ኖት ስም ይናገራሉ፣

ንዑስ ይዘቶች፡-

- ራስን ማስተዋወቅ
- ራስን መወቅና መግለጽ
- የሰው ሰውነት ክፍሎች
- ጤና
- ማንበብ
- ቁጥርና ቆጠራ
- ውበትን መረዳትና ማድነቅ
- ገንዘብ

ተግባር 1፦ መዝሙር

ሀ. አባቴ ገበሬ ነው (3 ክፍል ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቤተሰብ፣ ብር፣ የቤት እቃ፣ እህት፣ ወንድም፣ እናት፣ አባት፣ ሰት፣ ወንድ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር! ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ሞያዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች/ተንቀሳቃሽ ምስሎች



መዝሙር 1:- የቤተሰብ ሥራ

አባቴ ገበሬ ነው ማረስ ነው የሚወደው
እናቴ ነጋዴ ናት ዕቃ ትሸጣለች በብዛት
ወታደር የሆኑ ወንድሞችም አሉ
ሀገርን ከጠላት የሚከላከሉ
የአክስቴ ስራ አስተማሪ እኮ ነው
ትውልድን ማስተማር ሀገርን ማልማት ነው
እህቴ ኢንጅነር ናት ቤቶች የምትሰራ
ቤተሰቡን ሁሉ የሚያኖር በጋራ
ወንድሜ ግን ሐክም ነው ሰውን የሚያክም
መድሃኒቱን ሰቶ ህመም የሚያድን
ሴትም ሆነች ወንዱ ሁሉን ይሰራሉ
የሚያቅታቸው የለም ሁሉን ይችላሉ፡፡

ምዘና፡- “በመዝሙሩ ውስጥ ያሉት ቤተሰቦች ምን ምን ስራዎችን ይሰራሉ? ፣ የሴትና የወንድ ስራ ተብሎ የተለየ ስራ የቱ ነው?” በማለት ይጠይቋቸው፡፡

ለ. የስሜት ህዋሳት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - የስሜት ህዋሳት፣ አክስት፣ ማየት፣ መስማት፣ መቅመስ፣ መዳሰስ፣ ማሽተት፣ገንዘብ፣ ቁሶች

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የሰሜ ዋሳት ስዕሎች/ሞዴል፣ ተንቀሳቃሽ ምስሎች፣ ሞንታርቦ፣ ስልክ/ቴፕ ሪከርደርና ወዘተ

መዝሙር 2:- የስሜት ህዋሳት

አምስት የሰሜት ህዋሳት ለሁሉም ሰው የተሰጡት
ጥቅማቸውን እንወቀወቅ ጤናቸው እንጠብቅ
ሁለት አይኖች አሉኝ የማይበት ገንዘቦቹን እቃዎቹን ምለይበት
ሁለት ጆሮ አለኝ ልሰማበት የተሰጠኝ
የእክስቴን ድምፅ ሰማሁኝ የፊደል ድምጽ ተሰማኝ
አንድ አፍንጫ ቅርጹ እንደዋንጫ ተግባረማ ማሽተት ብቻ
ጥሩ ሲያሸት ጤና ይሰጣል መጥፎ ሽታ በሽታ ያመጣል
እጆች ሁለት የሚያማምሩ አስር ጣቶች አሉት ከኔ ጋር ቁጠሩ
የሰሜት ሃዋሴ እነዚህ ናቸው ለተግባራቸው የቆሙ ናቸው፡፡

ምዘና፡- "በመዝሙሩ ውስጥ ያሉት ቤተሰቦች ምን ምን ሰራዎችን ይሰራሉ? ፣ የሴትና የወንድ ሰራ ተብሎ የተለየ ሰራ የቱ ነው?" በማለት ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ሀሳብን በስዕል መግለጽ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ስሜት፣ ቤተሰብ፣ መሳል፣ ፍላጎት

የማስተማሪያ ዘዴ፡- በተግባር ስርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ለዚህ ሳምንት ሁለት የተለይዩ የግል ተግባራት ቀርበዋል፡፡ ህጻናት ሁለቱንም ተግባራት በተቀመጡ መመሪያዎች መሰረት እንዲሞክሯቸው ያድርጓቸው፡፡

በዚህ ተግባር ህጻናት በስዕል ስሜታቸውን እና ፍላጎታቸውን እንዲገልጹ፣ ቤተሰባቸውን እና የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን እና ስለራሳቸው በስዕል ይገልጻሉ፡፡ ይህንን ለማስፈጸም የሚከተሉትን የድርጊት ቅደም ተከተሎች መከተል ያስፈልጋል፡፡

- ለተግባሩ የሚያስፈልጉ የመጫዎቻ ቁሳቁሶችን (እርሳስ፣ ወረቀት፣ ላጽስ፣ መቅረጫና ቀለም ወዘተ) ማቅረብ፤
- ህፃናቶቹ ስለቤቴሰብ አባላት፣ የቤት ውስጥ መጠቀሚያ ቁሶች እና ስሜታቸውን በመሳልና ቀለም ይቀቡ፤
- ሁሉም ህጻናት ስዕል እንዲስሉና ስለሳሏቸው ስዕሎች ና ስለስሜታቸው በስዕሉ የሳሉትን ለሌሎች ተነስተው እንድገልጹ ማበረታታት፤
- የሁሉንም ህጻናት ሥራ ቀርበው መመልከትና ድጋፍ ለሚሹ አስፈላጊ ድጋፍ ማድረግ፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እርሳስ፣ ቀለም፣ ወረቀት፣ መቅረጫ፣ ላጲስ/የተለያዩ ስዕሎች የቤተሰብ እና የቤት መገልገያ ቁሳቁስ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ማህደረ ተግባር

* ህፃናቱ የሳሉት ስዕል ምንነት እንዲገልፁና እንዲቆጥሩ ይጠይቁዋቸው፡፡

* ህፃናቱ የሚስሏቸውን ስዕሎች በማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ያስቀምጡላቸው፡፡

ለ. የስሜት ህዋሳትን ከጭቃ መስራት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መቁጠር፣ መሳል፣ የስሜት ህዋሳት

የማስተማሪያ ዘዴ፡- በተግባር ስርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

- ተስለው የተዘጋጁ አምስቱን የስሜት ህዋሳትን የሚያሳዩ ፍላሽ ካርድ እያሳዩ ጥቅሙን ይንገሯቸው፤
- ቀጥሎ እነሱም የስሜት ህዋሳትን እንዲስሉና ቀለም ቀብተው ስለስሩት ስዕል ጓደኞቻቸው ይግለፁ፤
- ህጻናት የሁሉንም ህጻናት ስዕል በመሰብሰብ አስራ አምስት አስራ አምስት እያደረጉ እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የስሜት ህዋሳት ስዕል/ሞዴል፣ እርሳስ፣ ቀለም፣ ወረቀት/ደብተር

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ማህደረ ተግባር

* ህፃናቱ የሳሉት ስዕል ምንነትና ጠቀሜታ እንዲገልፁና እንዲቆጥሩ ይጠይቁዋቸው፡፡

* ህፃናቱ የሚስሏቸውን ስዕሎች በማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ያስቀምጡላቸው፡፡

ሐ. የቤት ዕቃ ስዕል መሳልና መቁጠር (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ወንድ፣ ሴት፣ ፆታ፣ ስሜት፣ መቁጠር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በተግባር ስርቶ ማሳየት፣ ገለጻና ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

• ልዩ ልዩ የቤት ዕቃዎች ስዕል የያዘ ፖስተር መለጠፍና ህጻናቱ ፖስተሩን እያዩ ስዕል እንዲስሉ ማድረግ፤

* የሳሉትን ስዕል ከፍ አድርገው ማሳየትና መቁጠር እንዲችሉ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቤት ዕቃዎች ስዕል፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ላጺስና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ማህደረ ተግባር

* ህፃናቱ የሳሉት ስዕል ምንነትና ጠቀሜታ እንዲገልፁና እንዲቆጥሩ ይጠይቁዋቸው፡፡

* ህፃናቱ የሚስሏቸውን ስዕሎች በማህደረ ተግባራቸው ውስጥ ያስቀምጡላቸው፡፡

ተግባር 3፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ገዢና ሻጭ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ግብይት፣ ገዢ፣ ሻጭ የቤት ቁሳቁስ፣ ፆታ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

• ለግብይት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን (ሳህን፣ ኩባያ ፣ማንኪያ ፣ ሹካ ፣ጀበና ፣ሲኒ፣ ሽክላ /ብረት ድስት …ወዘተ) ሱቅ ማእዘን ማዘጋጀት እና ነገዴ ተማሪ ወንድ እና ሴት ማድረ

• የኢትዮጵያ የብር ኖት እና ሳንቲም ናሙና ማዘጋጀት

• ህጻናትን ከሁለቱም ጾታ በየተራ ገዢና ሻጭ ሆነው/መሰለው መተዎን፤

• ሁሉም በየተራ እየተነሱ ቦታውን እየተቀያየሩ ተግባሩን ያከናውኑ፤

• በግብይት ወቅጥ ገንዘብን በአግባቡ ይጠቀሙ ዋጋ መጠየቅ መክፈል፣ መልስ መስጠትና መቀበል የማይዘነጉ ነገሮች ናቸው፡፡

• ይህንን ጨዋታ እንደልብ መጫዎት ለሚቸገሩ ህጻናት ቀርበው አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍና ክትትል ማድረግዎን አይርሱ፡፡

• በመጨረሻም ለሞዴልነት ከቀረቡት የቤት ቁሳቁሶቹ ውስጥ በተራ በተራ አስራ አምስት እንዲቆጥሩ ያድርጉ ተግባሩን በተሰጠው ክፍለ ጊዜ ከፋፍለው ይጠቀሙ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

(ሳህን፣ ኩባያ፣ ማንኪያ፣ ሹካ፣ ጀበና፣ ሲኒ፣ ሸክላ/ብረት ድስት ...ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ማህደረ ተግባር

* ህፃናቱ ምን ምን ነገሮችን እንደገዙ ይጠይቁዋቸው፡፡

* ህፃናቱ በትክክል መጫወታቸውን በምልከታ ያረጋግጡ፡፡

ለ. የቆጠራ ውድድር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ መቁጠር፣ የስሜት ህዋሳት፣ የቤት ቁሳቁሰ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

ለዚህ ሳምንት 2 የክፍል ውስጥ ጨዋታ ቀርበዋል በተሰጠው መመሪያና እና ቅደም ተከተል መሰረት ማጫወት ያስፈልጋል፡፡ ሁለት ህፃናት በአንድ ጊዜ ይዳደራሉ የተሰጣቸውን ስዕሎች /ሞዴሎች/ አንድ በአንድ እያነሱ ስማቸውን እየተናገሩ ይቆጥራሉ ቀድሞ የጨረሰ የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል፡፡

• በቅድሚያ አምስት የስሜት ህዋሳት ስዕል/ሞዴል፣ አምስት የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሰ ስዕል/ሞዴል፣ አምስት የሳንቲም እና የብር ኖቶች ስዕል/ሞዴል በተለያየ ሁለት ጠረጴዣ ላይ ያዘጋጁ፤

• ቀጥሎ ሁለት ሁለት እየሆኑ በመነሳት በተነገራቸው መሰረት የቀረበውን አቀላቅለው ስማቸውን እየተናገሩ ይቆጥራሉ የቆጠሩትን አስራ አምስት ቁጥር በወረቀት ይፅፋሉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ከጨዋታው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ለምሳሌ የሰሜት ህዋሳት፣ የቤት ወሰጥ መገልገያ ቁሳቁሰ እና የብር ኖቶች የሚያሳዩ ስዕሎች

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ማህደረ ተግባር

* ህፃናቱ “ስንት የሰሜት ህዋሳት አሉ?” በማለት ይጠይቁዋቸው፡፡

* ህፃናቱ በትክክል መጫወታቸውን በምልከታ ያረጋግጡ፡፡

ሐ. እንቆቅልሽ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ አስር ብር፣ ሃምሳ ብር፣ የቅርብ ቤተሰብ፣ ዓይን፣ ኩባያ፣ ብርጭቆ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ዓይን፣ መሃንዲስ፣ ብርጭቆ፣ እክስት፣ ገንዘብ፣ አስር ብርና ሃምሳ ብር የሚሉት መልሶች እንዲሚሆኑ በማሰብ የእንቆቅልሽ አጠያየቅ ስርዓት ጠብቀው ያጫውቷቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የብር ኖት ሞዴል፣
* የስሜት ህዋሳት ሞዴል፣
* ኩባያና ብርጭቆ፣ የቤተሰብ ስዕል/ፎቶ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ህፃናቱ ከእንቆቅልሹ ፍሬ ሀሳቦች ይጠይቁዋቸው፡፡

ተግባር 4፡- በፕሮጀክት መማር

ሀ. መረጃ መጠየቅና መሳል (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ዝምድና፣ ቤተሰብ፣ ፍላጎት፣ ስዕል መሳል፣ ፆታ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ ስርቶ ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት ይህንን የፕሮጀክት ስራ ሀረፃናት ጊዜ ተሰቷቸው እቤት ሰርተው እንዲመጡ ለማስቻል የሚከተሉትን የድርጊት ቅደም ተከተሎች መከተል ያስፈልጋል፡፡

• ህጻናት በአከባቢያቸው በቅርብ ስለሚያውቋቸው ቤተሰባቸው /ዘመዶቻቸው ሴትና ወንድ በፆታ ለይተውና ዝምድናቸው ምን እንደሆነ ጭምር ወላጆቻቸውን በመጠየቅ ክፍል መጥተው እንድያወሩ የቤት ተግባር ሥራ አድርገው መስጠት፤

* በመቀጠል እነዚህ ዘመዶቻቸው ሴቶችና ወንዶች ምን ምን ስራ እንደሚሰሩ ይጠይቁ በሴትና በወንድ ጾታ ይለዩ (ምሳሌ፡- እክስቴ እልማዝ ሴት ነች ስራዋ ነጋዴ ናት አባቴ ካሳ ይባላል ወንድ ነው ስራው እናጺ....)
* ጻናቱ ወደፊት መሆን ስለሚፈልጉት/ስለሚወዱት ሙያ ስዕል ይሳሉ፤ እንዲሁም በቤታቸው ስለሚሰሩ ጾታን መሰረት ያዳረጉ ሥራዎችም ቤተሰባቸውን ይጠይቁ፡፡
* ለፕሮጀክቱ የተሰጠው ጊዜ ሲያበቃ የጠየቁትን፣ የሳሉትን ይዘው በመምጣት ራሳቸውን ካስተዋዎቁ በኋላ ከወላጆቻቸው ያገኙትን መረጃ መነሻ በማድረግ ሀሳባቸውን እንድለዋዎጡ መጋበዝ፤ ስፍላጎታቸው በሳሉት ስዕል አስደግፈው እንዲናገሩ እድሉን ያመቻቹ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ወረቀት፣ እርሳስ፣ ቀለም፣ ከተር፣ መቀስ፣ ማጣበቂያ...

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ግሌ ማህደር

ስለስሩት ፕሮጀክት እንዲገልጹና በየመሃሉ እንዴት እንደሰሩ፣ከማን ጋር እንደሰሩ፣ ሲሰሩ ምን ችግር እንደገጠማቸው፣ እንዴት እንደፈቱ መጠየቅ.....

ተግባር 5፡- ተረት

ሀ. አባባ ጌታሁንና ቤተሰባቸው (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ዝምድና፣ ቤተሰብ፣ ፍላጎት፣ ስዕል መሳል፣ ፆታ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ለምሳሌ የተለያዩ ቤተብ ፣ የተለያዩ ስራ ላይ ተሰማርተው ያሉ ሰዎች፣ የስፖርት ሜዳን ሲያፀዱ የሚያሳይ ምስል

አባባ ጌታሁንና ቤተሰባቸው

ከቅርብ ዘመዶቻችን መሃል አንዱ የሆኑት አባባ ጌታሁን የእናቴ ወንድም አጎቴ ናቸው። አጎቴ ሶስት ሴቶችና ሁለት ወንዶች ልጆችን ከበለቤታቸው ጋር አፍርተው እነሱም በተለያዩ የሙያ ዘርፎችላ ተሰማርተዋል በአስተማሪነት፣ በጋዘጠኝነት፣ በግበኝነት፣ በሌክተሪክ ስራ የተሰማሩ ሲሆኑ የመጨረሻ ልጃቸው ገና መመረቋ ስለሆነ ስራ አልገባችም በተሰቡ የአጎቴ ቤተሰቦች ደስ የሚሊል ቤተሰባዊ ግንኙነት ያላቸው ሲሆን በሳምንት ሁለት ቀን በጠዋትበመነሳት ስራ ከመሄዳቸው በፊት በጋራ እስፖርት የመስራት ልምድ አላቸው ነገር ግን እስፖርት የሚሰሩበትን ቦታ በጋራ ያጸዳሉ ምክኒያቱ እስፖርት የምንሰራበት ሰፍራ ንጹህ ካልሆነ የተለያዩ ስለታማ እና ሹል ነገሮች ሰውነታችችን ሊጎዱን ይችላሉ፣ ድንጋይ፣ እሾህ፣ የተለያ ባክቴሪያዎችና ጀርሞች ሊኖሩ እና እኛን ሊያጠቁን ስለሚችሉ እና ልብሳችንም እንዳይቆሸሽ ሲባል ማጽዳት አስፈላጊ ነው ስለዚህ እናንተም እንደ አጎቴና ቤተሰቡ እፖርት የምትሰሩበትን ስፋራ ማፅዳት እንዳለባችሁ ፈጽሞ መዘንጋት የለባችሁም።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

1. የአባባ ጌታሁን ልጆች ምን ምን የሰራ አይነቶች ላያ ተሰማርተዋል?
2. ቤተሰቡ ምን የማድረግ ልምድ አላቸው?
3. የስፖርት መሰሪያ ቦታን ማጽዳት ለምን ያስፈልጋል?
4. ከተረቱ ምን ተማራችሁ?

ተግባር 6፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. ካስ ቅብብል (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- እካል የሚጎዱ ነገሮች፣ እንቅስቃሴ፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ጨዋታው ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የታከለበት ስለሆነ ህፃናቱን ወደውጭ ይዘው በመውጣት በቡድን በመመደብ የአጨዋወት መመሪያውን ተከትላው እንዲጫወቱ ያድርጉ ፡፡

- የመጫወቻውን ሜዳ ከህፃናቱ ጋር በመሆን ያፅዱ ምክኒያቱም ከስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች በፊት ቦታውን ንፁህ ማድረግ አስፈላጊ ነው ምክኒያቱ በጨዋተው ወቅት ህፃናቱ በሚጫወቱበት ጊዜ አካላቸውን የሚጎዱ ነገሮች ለምሳሌ ሽቦ፣ሚስማር፣ ድንጋዮች … እንዳይኖሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡
- ሴት እና ወንድ ሕፃናት ለየብቻ እነዲሆኑ ይስለፉ ቀጥሎ አስራ አምስት እስራ አምስት በመሆን ቡድን ይመስርቱ የተወሰኑ ሕፃናትን ከየቡድኑ በማሰወጣት አባላቱ አስራ አምስት መሆናቸውን ይቁጠሩ ከወንድም ሆነ ከሴት አስራ አምስት ያልሞሉትን ደግሞ የሁለቱን ፆታ የተቀላቀለበት ቡድን አድርገው እነሱ ስንት እንደሆኑ እርሶ ቁጠሩት፡፡
- በወረቀት የተዘጋጀ ከ1 እስከ 15 ቁጥር የተፃፈበት በልብሳቸው ላይ ይለጥፉ ከዚያ ክብ ሰርተው አንድ ለሁለት ሁለት ለሶስት ……. ቁጥሩን እየተሩ ኳሱን ይቀባበላሉ
- ሁለት ዙር ተቀባበሉ በኋላ ቅብብሎሹን አቁመው በቁጥራቸው ቅደም ተከተል ይሰለፉ ከዚያም የተጠቀማችሁበት ቁሳቁስ ቦታው በመመለስ የጽዳት ስራ እና ስፖርት ስለሰሩ በሳሙና እጃቸውን እና ፊታቸውን ታጥበው ወደክፍላቸው ይግቡ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፅዳት እቃዎች እነደ መጥረጊያ፣ መፈሻ፣ ጓንት፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣ ኳስ፣ ውሃ፣ ሳሙና

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

1. ወደውጭ ወተን የደረግነው ምን ነበር?
2. የመጫወቻ ሜዳን ከእንቅስቃሴ በፊት ማጽዳት ለምን ያስፈልጋል?
3. ቡድን የሰራነው እንዴት ነበር?
4. እያንዳንዱ ስንት አባላት በውስጡ ነበሩት?

* ህጻናት ጨዋታውን በትክክል መጫወታቸውን ያረጋግጡ፡፡

ሳምንት አሰራ ሶስት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ

- ራሳቸውን መቆጠጠር ይጀምራሉ
- የግል ንጽህናቸውን መጠበቅ ይጠብቃሉ
- የሌሎች ሰዎችን ልምድ ሞያ ያውቃሉ
- የውሃ መቅጃ እቃ ይጠቀማሉ
- እየደነሱ የተለያዩ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣
- ፍደላትን ያዛምዳሉ፣
- የተሰጣቸውን ፊደላት ያነባሉ፣
- እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን ወደ ፊትና ወደ ኋላ ይቆጥራሉ፣

ንዑስ ይዘቶች

- ራስን መግዛት
- ራስንና የቅርብ አካባቢን መንከባከብ
- ማህበራዊ ግንዛቤ
- የትንንሽ ጡንቻዎች እድገትና መዳበር
- የፈጠራ አገላለጽ
- መጻፍ
- ማንበብ
- ቁጥርና ቆጠራ

ተግባር 1፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ፊደላትን ማዛመድ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - የሌሎች ልምድ፣ ሙያ፣ ፊደላትን ማዛመድ፣ ፊደላትን ማንበብ

የማስተማሪያ ዘዴ:- በተግባር፣ በገለጻ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና:- ቀጥሎ የቀረበውን የግል ተግባር በተዘረዘሩ የአሰራር ቅደም ተከተሎች መሰረት ያሰሯቸው።

 በቅድሚያ እርሳስ፣ ላጲስ፣ መቅረጫ፣ ከዚህ ክፍለጊዜ በፊት የተዋወቁትን ፊደላት ፍላሽ ካርድ /ሞዴል በማዘጋት በየወንበራቸው ላይ ያስቀምጡላቸውና በእርሶ እርዳታ የፊደል ዝርያውን በቅደም ተከተል ያንብቡ፡

 ቀጥሎ ተፅፎ የተዘጋጀ የፊደል ቤተሰብ የማዛመድ መልመጃ በወረቀት፣በደብተር/በመለማመጃ መፅሃፍ እንዴት እንዲሚያዛምዱ ከምሳሌ ጋር ይስጧው።

 ሁሉም ህፃናት ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋ ልምድ እየተከፋሉ ይሰሩበመጨረሻም የሰሩትን ከመጀመሪያ ጀምሮ ያለውን ከጓደኞቻቸው ያገኙትን ልምድ (የማንበብ፣የመፃፍ፣ የፊደል ቤተሰብን በቅደም ተከተል መደርደርና ማንበብ ...) በየተራ ያቅርቡ። ይህንን ተግባር ደጋግመው ለተሰጠው ክፍል ጊዜ ያሰሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እርሳስ፣ ላጲስ፣ መቅረጫ፣ ፊደላት ፍላሽ ካርድ/ሞዴል፣ በወረቀት፣ በደብተር/በመለማመጃ መፅሃፍ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ማህደረ ተግባር

* ህፃናቱ ምን ስዕል እነደጻፉ ይጠይቁዋቸው።

* ህፃናቱ በትክክል ምእተግበራቸውን በምልከታ ያረጋግጡ።

ለ. የንጽህና አጠባበቅ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ራሰን መቆጣጠር፣ ልምድ፣ ሙያ፣ የግል ንፅህና፣ ውሃ መቅጃ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

 ህፃናቱ ነገሮችን በራሳቸው በሚያከናውኑበት ወቅት ድርጊቶቻቸውን የመቆጣጠር ችሎታ በተግባሩ ውስጥ እንዲያዳብሩ ክትትልና ድጋፍ ያድርጉ።

 ውሃ በባልዲ በባልዲ፣ ጀግ/ኩባያ መዘፍዘፊያ፣ የፕላስቲክ፣ አሻንጉሊት ማዘጋጀት እነዚህን ሶስት ተማሪ በአንዴ ማሳተፍ እንዲቻል በሶስት ቦታ ያዘጋጁ።

 ቀጥሎ እርሶ ጀግና/ኩባያን ተጠቅመው ከባልዲ ውሃ እየቀዱ በመዘፍዘፊያ /በማስታጠቢያ ላይ እጅትን፣ ፊት ... በመታጠብ በፎጣ በማድረቅ፣ ሴት/ወንድ አሻንጊሊትን ገላ እና ፀጉር ማጠብ፣ ፀጉር መሰራት ያሳዩ

 ቀጥሎ በዚያ መሰረት ሶስት ሶስት እየሆኑ በተዘጋጀላቸው ቁሳቁስ ተጠቅመው ተግባሩን ያከናው እርሶም ድጋፍ ለሚሹ እደም ተከተል እንዲጠብቁ ድጋፍ ያርጉ ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የውሃ ባልዲ ከውሃ ጋር፣ ሳሙና፣ ጀግ፣ ማሰታጠቢያ /መዘፍዘፊያ/፣ አሻንጉሊት

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ማህደረ ተግባር

* ህፃናቱ “ምን ተግባር ሰራችሁ?” በማለት ይጠይቁዋቸው።

* ህፃናቱ በትክክል መሰራታቸውን በምልከታ ያረጋግጡ።

ሐ. ወደፊትና ወደኋላ መቁጠር (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ወደፊት መቁጠር፣ ወደኋላ መቁጥር፣ አቅጣጫ፣ ልምድ መውሰድ፣ ራሰን መቆጣጣር

የማስተማሪያ ዜዴ:- ስርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

 በቅዲሚያ የቁጥር ፍላሽ ካርድ /ሞዴል ቢያንስ ለሶሰት ልጆች በሚሆን መልኩ በየጠረጰየዛቸው ላይ ያሰቀምጡ (1 እስከ 5) የሚሆኑ ቁጥሮችን በየጠረጴዛቸው ላይ መሰጠት፤

 እርሶ በጥቁር/በነጭ ስሌዳ ለሁሉም ህፃናት በሚታይ መልኩ ቁጥሮችን ጎላ አድርገው ከፃፉ በኋላ ወደፊትና ወደኋላ ቆጥረው ያሳዩ፣ ቀጥሎ አጠገባቸው በመሄድ በፍላሽ ካርዱ ሰርተው ያሳዩና እነሱም እንዲሰሩ ያበረታቱ፤

 በየተቀመጡበት ቦታ በጠረጴዛቸው ላይ በቅዲሚያ እተነጋገሩ ቁጥሩን በቅደም ተከተል ይደርድሩ ከዚያ እርሶ እንዳሳዬአቸው እነሱም ይሰሩ ሲሰሩ እርሰ በርሰ እኒዲደጋገፉ እንጂ እኔብቻ ልንካ/ልቁጠር፣ ልደርድር በማላት ሳይጨቃጨቁ ቁጥሩን ደርድረው ወደፊትና ወደኋላ ይቁጠሩ ህጻናቶች ተረኛ ሲሰራ እና ሲቆጥሩ ሌሎች በተኩረት የመከታተል ልምድን ያዳብሩ፡፡ ህጻናት እራሳቸውን የመቆጣጠር ልምምድ በተግባሩ ውስጥ ያዳብሩ፡፡

 ሲጨርሱ የተጠቀሙት የቁጥር ፍላሽካርድ የሚቀመጥበት ማዕዘን ወሰደው በመረዳዳት ያሰቀምጡ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣ ነጭ/ጥቁር ስሌዳ፣ ማርከር እና ሌሎችም

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ማህደረ ተግባር

* ስንት ቁጥሮችን ቆጠራቹ ?
* ይህ ከአንድ፣ ከሁለት … ቀጥሎ ስንት ቁጥር ነው?
* ህፃናቱ በትክክል መሰራታቸውን በምልከታ ያረጋግጡ፡፡

መ. ፊደላትን ማንበብና ማዛመድ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ማንበብ፣ ማዛመድ፣ ልምድ መውሰድ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ስርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

 የሳምንቱን የፊደል ቤተሰብ (ጨ-ጬ-ጪ-ጫ-ጬ-ጭ-ጮ) አዘጋጅቶ በፍላሽ ካርድ በየጠረጴዛቸው ላይ መሰጠት፤

 ቀጥሎ ካርድ ተጠቅመው እና በጥቁር/በነጭ ስሌዳ የፊዶሎቹን ቤተሰብ በመፃፍ አንብበው ያሳዩ በመቀጠል ከነሱ ጋር በጋራ አንብቡ፣ ያነበባችሁትን ተመሳሳይ ፊደል እንዴት እንደሚዛመድ ያሳዩ፤

 ከእርሶ ባገኙት ልምድ ተነሰተው አጠገባቸው ያሉትን የፊደል ቤተብ በቅደም ተከተል እንዲያነቡ፤

 ተራ በተራ በመነሳት አንድ የፊደል ቤተሰብ አንስተው ከነበቡ በኋላ ያዛምዱ፡፡

 የሰሩትን የፊደል ቤተሰብ በደብተር/በመለማመጃ መጽሃፋቸው ላይ እንዲያዛምዱ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-
የፊደል ቤተሰብ ፍላሽ ካርድ፣ እርሳስ፣ እርሳስ፣ ደብተር/በመለማመጃ መጽሃፋቸው፣ ነጭ/ጥቁር ስሌዳ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታ

* ፍደሎቹን ማስነበብና እንዲያዛምዱ መጠየቅ

* ህጻናት ተግባሩን በትክክል መፈጸማቸውን ተከታትለው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 2፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. በቆጠራ መደነስ (3 ክፍል ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መዘመር፣ መደነስ፣ ልምድ መውሰድ፣ ወደኋላ፣ ወደፊት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ጨዋታውን ለማጫወት ቀጥሎ ያለውን ቅደም ተከተል ተግባራዊ ያድርጉ፡፡ ጨዋታው አምስት ቡድን ያሉት ህፃናት መዝሙር ከተከፈተ በኋላ ወደፊትና ወደኋላ እየደነሱ ይቁጠሩ 1 2 3 4 5 ቀጥሎ 5 4 3 2 1)፤ ተራቸውን የሚጠብቁት ቦታቸው ላይ ሆነው ደግሞ ከመዝሙሩ ጋር አብረው ይዘምራሉ፡፡

* የተለያዩ ከዚህ በፊት የሚያውቋቸውን መዝሙር በሲዲ፣በቴፕ ሪከርደር፣ ፍላሽ፣መዝሙር የተቀረጸበት፣ ሞንታርቦ፣ ቴሌቪዥን ማዘጋጀት አምስት አባላት ያሉት ቡድን መሰራት፤

* ከመጀመሪያው ቡድን ጋር እርሶ አብረው በመደነስ እና በመቁጠር ህፃናቱ ከእናንተ ስራ ልምድ እኒዲወሰዱበማድረግ ቀጥሎ ቀጥሎ ሁሉም በየተራ እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣ ቴፕ ሪከርደር፣ ፍላሽ፣ ሞንታርቦ፣ ቴሌቪዥን፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* “ከአምስት በፊት የሚገኘው ስንት ቁጥር ነው? ስንት ቁጥሮችን ቆጠራችሁ? ይህ ስንት ቁጥር ነው?” በማለት ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት በጨዋታው ተሳታፊ መሆናቸውን መከታተልም ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 3፡- መዝሙር

ሀ. ቲቲዬ ይህች ናት (2 ክፍል ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - የሌሎች ሙያ፣ ችሎታ፣ ውሃ መቅደት፣ እቃ መጠቀም፣ ራስን መቆጣጠር፣ንጽህና

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች፣ የተለየዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ የሚያሳዩ ስዕሎች/ሞዴሎች፣ አሻንጉሊት

መዝሙር 1:- ቲቲዬ ይህች ናት

ተረት ተረት የመሰረት
አንድ ልጅ ነበረች ቲቲዬ የሚሏት
በጣም ደስ የምትል ሁሉ እሚወዳት
የሌሎችን ስራ ማየት ትወዳለች
ችሎታቸውንም በጣም ታደንቃለች
ሞያንም ለመልመድ ጥረት ታደርጋለች
ጥርሶችን የማጽዳት እጅን የመታጠብ
ፀጉርን የመታጠብ ገላን የመታጠብ
ችሎታ አግኝታለች
እቃዎች ተጠቅማ ውሃ ትቀዳለች
ራሷን መቆጣጠር ትሞካክራለች
ሁሉንም ለመልመድ ጥረት ታደርጋለች
ቲቲዬ ጎበዝ ናት ፣ቲቲዬ ንፁህ ናት
ቲቲዬ ሞያ አላት ቲቲዬ ይቺ ናት፡፡

ምዘና፡-

“ቲቲ ምን ምን ሙያዎችን ትሞክራለች?፣ ከመዝሙሩ ምን ተማርን?” በማለት ይጠይቋቸው፡፡

ለ. ኑ እንቁጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - መቁጠር፣ ወደፊት እና ወደኋላ፣ መቸኮል፣ ረጋ ማለት

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቁጥር ፍላሽ ካርድ

መዝሙር 2:- ኑ እንቁጠር

ጓደኞቼ ኑ እንቁጠር ወደፊት ቁጥር
12 3 4 5 6 7 8 9 10 (አሰር)
ጓደኞቼ ኑ እንቁጠር ወደኋላ
10 9 8 7 6 5 4 3 2 1
አቸኩሉ ረጋ በሉ ራሳችሁን ተቆጣጠሩ
1 ወደፊት 10 ወደኋላ 2 ወደፊት 9 ወደኋላ
3 ወደፊት 8 ወደኋላ 4 ወደፊት 7 ወደኋላ
5 ወደፊት 6 ወደኋላ 6 ወደፊት 5 ወደኋላ
7 ወደፊት 4 ወደኋላ 8 ወደፊት 3 ወደኋላ
9 ወደፊት 2 ወደኋላ 10 ወደፊት 1 ወደኋላ።

ምዘና፡-

1. ከ1 ወደፊት ብንቆጥር ስንት ስንት እንላለን?

2. ከ10 ወደኋላ ብንቆጥር ስንት ስንት እንላለን?

ሐ. መስራት እወዳለሁ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ማቀድ፣ የዘወትር ተግባር፣ ፊደላት፣ መደነስ፣ ንፅህና መጠበቅ፣ ትዕዛዝ መጠበቅ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የሰዎች ስዕል

ምዘና፡-

1. ስራ ከመጀመራችን በፊት ምን ማድረግ አለብን?

2. ከመዝሙሩ ምን እንማራለን?

ተግባር 4፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. ሙያዎችን ማስመሰል (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ንጽህና መጠበቅ፣ ገበሬ፣ ሀኪም፣ መሀንዲስ፣ ትህትና፣ ምስጋና

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ጨዋታው ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የታከለበት ስለሆነ ህፃናቱን ወደውጭ ይዘው በመውጣት በቡድን በመመደብ የአጨዋወት መመሪያውን ተከትላው እንዲጫወቱ ያድርጉ ።

* ለመስሎ ጨዋታው የሚያፈልጉ ግብዓቶችን ማዘጋጀትና ህጻናትን በየሙያ ዘርፉ ማአራጀት፤
* የአንድ ሙያን ተግባር አስመስለው ማሳየት፤
* ህጻናት በመረጡት ሙያ መሰረት ምሰለው እንዲጫወቱ ማበረታታት፤
* የእያንዳንዱን ሙያ ምንነት፣ ጠቀሜታና ክቡርነት ማስረዳት፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቤት ሥራ የሚሰሩ ሰዎች፣ ምግብ አብሳይ ሰው፣ ሹፌር፣ መምህር፣ ገበሬና ወዘተ የሚያሳይ ስዕል

ምዘና፡-

1. የእያንዳንዱን ሙያ ምንነት በቃል መጠየቅ።
2. ሙያውን አስመስለው መተወናቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር 5፦ ተረት

ሀ. ጓደኞሞቹ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ታዛዥ፣ ትህትና ባህሪ፣ ስነ-ምግባር፣ የግል ንጽህና፣ ገዢና ሻጭ፣ ግንበኛ፣ ደላላ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስዕላዊ መግለጫ

ጓደኞሞቹ

በአንድ አከባቢ የሚኖሩ ሁለት ጉደኞሞች ነበሩ። ስማቸው በለጠና ክብሩ ይባላል። ሥራቸው ግንበኝነትና ድለላ ነው። በለጠ ቤትና የቤት እጥሮችን እየገነባ ይውላል። ሁል ጊዜ ከሥራ በኋላ የሥራ ቦታውንና የራሱን የግል ንጽህና ሲለሚጠብቅ ደስተኛ ነው። ጥሩ ገቢ ስለሚያገኝ ሙያውን በጣም ይወደዋል። ክብሩ ደግሞ የድለላ ቢሮ ውስጥ የሚሰራ የሚገዙና የሚሸጡ ንብረቶችን ለገዢና ለሻጭ ይታወቃል በዚህም ገንዘብ በማግኘት ቤተሰቦቹን ያስተዳድራል። ሁለቱ ጓደኛሞች በሰራ ቦታቸው በጣም ምስጉን ናቸው ምክኒያቱ ሰዎችን የሚያከብሩ በነገሮች ራሳቸውን የሚቆጣጠሩና ቁጥብ፣ ታዛዥ የሆኑ፣ ስነምግባር ያላቸው ናቸው ሁለቱም በልጅነታቸው አንድ አከባቢ ያደጉና አንድ ትምህርት የተማሩ ናቸው በስፋራቸውም ሰውን አክባሪና ታዛዥ ነበሩ ስለዚህ አሁንም አድገው በሰራ ቦታቸው ላይ ያንን ባህሪ ስለሚያሳዩ ተወዳጅ ለመሆን ችለዋል።፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

1. እናንተ ምን አይነት ሙያ ቢኖራችሁ ትመኛላችሁ?
2. በሰዎች ዘንድ ተወዳጅ ለመሆን እና በስራችን ውጤታማ ለመሆን ምን አይነት ባህሪ ሊኖረን ይገባል?

ለ. ሁለቱ እንግዶች (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፊደላት፣ ቁጥር፣ ራስን መቆጣጠር፣ ሙያ፣ መግባባት፣ መሞከር ፍላጎት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስዕላዊ መግለጫዎችና የፊደል ካርዶች

ሁለቱ እንግዶች

በአንድ መንደር የሚኖሩ 10 ጓደኛሞች ነበሩ፡፡ ሁሉም የ5 ዓመት ልጆች ናቸው፡፡ ስማቸው ሀ፣ ለ፣ መ፣ ሠ፣ ረ፣ ሸ፣ ቀ፣ በ፣ ተ እና ቸ ይባላል፡፡ ሰው አክባሪና ደስ የምል ጸባይ አላቸው፡፡ የተቸገረን ሰው መርዳት ይወዳሉ፡፡ አንድ ቀን ሰፈር እየተጫወቱ ሳሉ ሁለት እንግዳ ልጆች መጡና አብረን እንጫወት አሏቸው እነሱም በደስታ እሺ ብለው አብረዋቸው መጫወት ጀመሩ በመሃል አንዱ ልጅ እኔ ነኝ የምቀድመው በማላት “በ እና ሀ ን” ገፈተረቸው እና ተጣሉ ከሩቅ ሲያዩ የነበሩ የሰፈራቸው ትልቅ እናት በፍጥነት መተው ልጆች ያደረጉት ነገር ትክክል እንዳልሆነ እና ሲጫወቱ እራሳችሁን መቆጣጠር እንዳለባቸው ችግርም ካለ ጨዋታውን አቁማችሁ በመነጋገር መፍታት አሰፈላጊ መሆንን አስረድተው አስታረቁ፡፡ ሁለቱ እግዳ ልጆችም “በጣም ይቅርታ! እኛ ሰፈር ሁሉም እንደዚህ ስለሚያደርግ ነው፡፡ ከዚ በኋላ ግን እንታረማለን፡፡ ሰፈርም ሄደን ጓደኞቻችንን እንደናተ እንዲሆኑ እንመክራለን” በማለት ይቅርታ ጠየቁ፡፡ ትልቋ እማማ ግን ለመሆኑ ሰታድጉ ምን መሆን እንደሚፈልጉም ጠየቃቸው፡፡ ሀ መሃንዲስ መሆን አለች፡፡ ለ መምህር፡፡ መ ነጋዴ ሠ ደግሞ ገበሬ፡፡ ረ ሹፌር እና ሸ ደግሞ ሊስትሮ መሆን ይፈልጋሉ፡፡ ቀ እና በ ሐኪም መሆን ይመኛሉ፡፡ ተ እና ቸ ደግሞ የኮምፒዩተር ባለሞያ እንደሚፈልጉ ተናገሩ ከሌላ ሰፈር የመጡት ሁለቱ እንግዶች ግን እኛ አናውቀውም አሉ፡፡ ጊዜ እንዳላቸውና ልክ እንደ ሌሎች በትምህርታቸው በደንብ እየተማሩ መሆን የሚፈልጉትን እንዲያስቡ ነግረው በትምህርታቸው እንዲበረቱና ባህሪያቸው መልካም መሆን እንዳለበት ነግረው ተግባብተው እንዲጫወቱ ነግረው ሐየዱ ጓደኛሞችም በአግባቡ አብረው መጫወት ጀመሩ፡፡እንዲበረቱ መክሯቸው ሄዱ ይባላል፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

1. 10 ጓደኛሞች የተባሉት እነማን ነበሩ?
2. ከተረቱ ምን እንማራለን?

ተግባር 6፡- በሥራ መማር

ሀ. የምግብ ዝግጅት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ንጽህና፣ ሙያ፣ ልመምድ፣ ፊደላት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

* ህጻናት በቤታቸው ከሚዘወትሩ የምግብ አይነቶች ውስጥ የመረጡትን አይነት እንዲሰሩ/እንድለማመዱ ለማስቻል የሚከተሉትን የድርጊት ቅደም ተከተሎችን መከተል ያስፈልጋል፡፡

ምግብ ከመሰራታችን በፊት የምንሰራበት ቦታ ማጽዳት፣ የግል ንጽህናችንን መጠበቅ፣ ፀጉር መሸፈን መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ ሁሉም ህፃናት በአንድ ቀን መለማመድ ስለማይችሉ ያመጡት እንዳይበላሽባቸው የተለያየ ቡድን እድርገው በተለያየ ክፍለ ጊዜ ያሰሯቸው፡፡ በቡድን ሲሰሩ መተባበር፣ መከባበር፣ አንዱ ለአንዱ መታዘዝ፣ መደማመጥ ለሚሰሩት ስራ ውጤታማነት ወሳኝ እንደሆነ ይንገሯቸው፡፡ በተጨማሪም ምግብ መሰራት ከመጀመራቸው በፊት የምግብ አሰራርን የሚያሳይ ቪዲዮ/ሰዕል ከልሆነ ደግሞ የእርሶን ልምድ ያካፍሏቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ድስት፣ መክተፊያ፣ ቢላ፣ ማማሰያ፣ ህፃናቱ ለመሰራት የሚፈልጉት የምግብ አይነት ለመሰራት የሚያስችላቸው የተለያዩ ግብኣቶች አስመስለው ማቅረብ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን እንደሰሩ መጠየቅ

* ምግቡን ሲያዘጋጁ ዞሮ መመልከትና ማበረታታት

ተግባር 7፡- ውይይት

ሀ. የሙያዎች ዓይነትና ባህሪያት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሙያ፣ ባህርሪ፣ ስሜትን መቆጣጠር፣ ራስን መምራት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* በአከባቢያችን የሚዘወተሩ የሙያ ዓይነቶች፣ ባህሪያቸውና በአንድ ሙያ ውስጥ ብቁ መሆን በሚሉ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ እንዲሰጣጡ ማድረግ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡- የተለያዩ ሙያዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ (ሁሉንም ሙያ ዓይነቶችና ባህሪያቸው መጠየቅ)

ሳምንት አስራ አራት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

o ቀላል ተረቶችን ይናገራሉ፣

o ከሁለት አማራጮች አንዱን መምረጥ፣

o ከጓደኞቻቸው ጋር ከ4-6 የሚሆኑ ተግባራትን በመስራት ያሳያሉ፣

o እስከ 7 የሚደርሱ ጤናማ ምግቦችንና መጠጦችን ይለያሉ፣

o ደህንነቱ ካልተጠበቀ አከባቢ ራሳቸውን ይጠብቃሉ፣

o የሳምንት ቀናትን ስም ይጠራሉ፣

o መዝሙር እየዘመሩ ይደንሳሉ፣

o እስከ 10 ካሉ ቁጥሮች ሁለት ቁጥሮችን ይሆናልና ያንሳል ምልክቶችን ተጠቅመው ያወዳድራሉ፣

o የተሰጣቸው ፍደላትን ደጋግመው ይፅፋሉ፣

o ቁሶችን በተመሳሳይ ባህርያቸውና መገለጫዎቻቸው ይመድባሉ፣

o የድምጾችን ምንጭ ይጦቅማሉ

ንዑስ ይዘቶች፡-

 ራስን ማስተዋዋቅ

 ውሳኔ ይሰጣሉ

 የትልልቅ ጡንቻዎች መዳበር

 የተመጣጠነ ምግብ

 ደህንነትና ጥበቃ

 የቃላት እውቀት

 ጥበብን ማድነቅ

 ቁጥሮችን ቅደም ተከተል ማስያዝ

 መጻፍ

 በዓይነት መለየትና መመደብ

 ድምጾችን መለየት

ተግባር 1፡- መዝሙር

ሀ. እኔ እለያለሁ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ምርጫ፣ አካል መጎዳት፣ ባህሪ፣ መመደብ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የአካባቢ ሰዕል ፣በጥሩ ቦታ ልጆች ሲጫወቱ የሚያሳዩ ቪዲዮዎች፣ ቴፕ ሪከርደር፣ ሞንታርቦ

መዝሙር 1፡- እኔ እለያለሁ

እኔ እለያለሁ ምርጫዬን አውቃለሁ
እሳትና ውሃን መለየት ችላለሁ
እሳቱን ደፍሬ በፍፁም አልነካም
አካሌን እንዲጎዳ በፍጹም አልፈቅድም
እጠነቃቀለሁ ጨዋታ ሰጫዋት
የሚጎዳኝ ነገር ፍፁም በሌለበት
የማይጎዳ ነገር በደንብ እለያለሁ
በአይነታቸው እና በባህሪያቸው
መመደብ እችላለሁ እኔ እለያለሄ፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከእመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለ. የሳምንቱ ቀናት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ምርጫ፣ የሳምንቱ ቀናት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

የሳምንቱ ቀናትን የያዙ ካርዶች፣ በሳምንት ውስጥ የሚከወኑ ተግባራት የሚያሳዩ ስዕሎች

መዝሙር 2፡ የሳምንቱ ቀናት

የሳምንቱ ቀናት ሰባት ናቸው
ሰባቱም ቀናት ልዩነት አላቸው
ሰኞ ማክሰኞ ሬቡዕ እና ሀሙስ
አርብ ቅዳሜ ቀጥሎም እሁድ
ከሰኞ እስከ አርብ እንማራለን
ቅዳሜና እሁድ ቤተሰብ እንረዳለን
መማር መጫወትም እኛ እንወዳለን
ነገር ግን መማርን እናሰበልጣለን፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከእመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ቁስ ማወዳደር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ይበልጣል፣ ያንሳል፣ ማወዳደር፣ ትልቅና ትንሽ፣ ከ1 እስከ 10 ቁጥር፣ ተግባር ማከናወን

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱ የማወዳደር ጽንሰ ሃሳብ ግልፅ እንዲሆንላቸው ተግባሩን ከእርሶ ጋር እና ከጓደኞቻቸው ጋር በመጨረሻም ለብቻቸው እየሰሩ እንዲማሩ ምቹ ሁኔታን ይፍጠሩ፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ ያለውን ተግባር በቅደም ተከተሉ መሰረት እንዲሰሩ ከ 1 እስከ 10 ቁጥር ፍላሽ ካርድ፣ የተሰጣቸው ቁጥሮች ልክ ቁስ ከፊት ለፊታቸው ይደርዱሩ፡፡ እስቀድመው ቁሱን ከቆጠሩ በኋላ የትኛው እንደሚበልጥና የትኛው እንደሚያንስ ያሳዩአቸው፡፡

* ከ ፍላሽ ካርዱ ላይ ያሉትን ከ 1 እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን እንዲያነቡ ማድረግ፡፡
* ከቁጥሮቹ ትይዩ የተቀመጡ ቁሶችን እንዲቆጥሩና ትልቅና ትንሽ ቁጥር ያላቸውን እንዲለዩ ማድረግ፤
* እመጨረሻም ብዙ ቁጥር ያለው ቁስ ይበልጣልና ጥቂት ቁጥር ያለው ቁስ ያንሳል በማለት ያወዳድሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከእ1 እስከ 10 ያሉ ቁጥሮች ፍላሽ ካርድና በቁጥሮቹ ልክ የተደረደሩ ተቆጣሪ ቁሶች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ያወዳደሯቸው ቁጥሮችን ይጠይቋቸው፡፡

* ቁጥሮቹንና ቁሶቹን በሚያወዳድሩበት ጊዜ ሁሉም ህጻናት በትክክል መሰራታቸውን ያረጋግጡ፡፡

ለ. በባህሪይ መለየት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ይበልጣል፣ ያንሳል፣ ማወዳደር፣ ትልቅና ትንሽ፣ ከ1 እስከ 10 ቁጥር፣ ተግባር ማከናወን

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

የተለያዩ ቁሶችን አቅርበው በባህሪያቸው መመደብና መለየት

* ለምሳሌ፡- ሳህን፣ ኩባያ፣ ማንኪያ (ባህሪያቸው መመገቢያ ናቸው፤ ነገር ግን በቅርጽ ይለያያሉ)፣ የተለያዩ የቸርቅ ቁርጥራጮች (ለልብስ መስሪያ ያገለግላሉ፤ ግን በአይነት ይለያያሉ)፣ ሳሙና፣ የጥርስ ብሩሽ/መፋቂያ (ለንጽህና መጠበቂያነት ያገለግላሉ፤ ግን የተሰሩበት ይለያያል) … በዚህ መልኩ የተለያዩ ቁሶችን እያደባለቁ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡
* ሁሉም ህጻናት ተራ በተራ እጅ እያነሱ እተነገራቸው መሰረት ያሳዩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ቁሳቁሶች ስዕልና ሞዴል (የጨርቅ ቁርጥራጮች፣ ሳህን፣ ኩባያ፣ ማንኪያ፣ሳሙና፣ የጥርስ ብሩሽ)

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

ተቀራራቢ አገልግሎት የሚሰጡ ቁሶችን በመጥራት በባህሪያቸው እንዲለዩ ይጠይቋቸው፡፡

* ሁሉም ህጻናት ተግባሩን በተገለጸው መሰረት ማከናወናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ሐ. ፊደል መጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - መፃፍ፣ እንቅስቃሴ፣ ዳንስ፣ መዘመር

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

የክፍለ ጊዜውን የፊደል ቤተሰብ (ረ-ሩ-ሪ-ራ-ሬ-ር-ሮ- እና ሀ-ሁ-ሂ-ሃ-ሄ-ህ-ሆ) ደግመው እንዲፅፉ በቅድሚያ ፊሎቹን ያስተዋውቁ እና አብራችሁ አንብቡ፡፡ እነሱም እንዲያነቡ ያበረታቱ፡፡ ቀጥሎ እርሳስ፣ ወረቀት/ የመለማመጃ ደብተራቸው ላይ የተዘጋጀውን ፊደል ቤተሰብ ቅርፁን ጠብቀው ደግመው ይፃፉ፡፡ ሲጨርሱ ከዚህ በፊት የሚያውቁትን በመዘመር ከ4 እከ ስድስት የሚደርሱ እንቅስቃሴዎችን በዳንስ መልኩ ይንቀሳቀሱ፡ :

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

እርሳስ፣ ወረቀት/መለማመጃ ደብተር፣ ሞንታርቦ፣ ስልክ/ጂፓስ

ምዘና:- የቃል ጥያቄ፣ ምልከታና ግለማህደር

"የፃፋችሁት የፊደል ቤተስ እነማን ናቸው?፣ ምን አይነት መዝሙር ዘመርን?፣ ስንት አይነት ዳንስ ደነስን?* በማለት ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት ተግባሩን በተገለጸው መሰረት ማከናወናቸውን ያረጋግጡ፡፡
* ህጻናት የጻፏቸውን ፊደሎች በግለማህደራቸው ውስጥ ያስቀምጡላቸው፡፡

ተግባር 3:- በሥራ መማር

ሀ. ሚና መላበስ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት:- ቀላል ተረት፣ ስራ፣ ሚና

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና:-

* በዚህ ክፍለ ጊዜ ህፃናቱ የእርሶን ሚና አስመስለው ሌሎቹን ህፃናት ተረት እንዲያስተምሩ ይንገሩ፡፡ ሚናው የተረት ክፍለ ጊዜ ተግባራትን አቅደው ልክ እንደ እርሶ የተረት አተራረትን ቅደም ተከተል ተከትለው መተረት ነው፡፡ እርሶ ለሚያወሩት ተረት ደግሞ ስዕላዊ መግለጫ እንደሚያስፈልገው መጠቆምና እነሱ ደግሞ ለሚያወሩት ተረት ተስማሚ ስዕላዊ መግለጫን ይጠቀሙ፡፡ በመሆኑም ቀጥሎ የቀረበውን በሚና ጨዋታው ውስጥ ተግባራዊ ያድጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

ለሚተርቱት ተረት አስፈላጊ ስዕሎች፣ ገዋን፣ ቾክ፣ ማርከር፣ እስክሪብቶ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* የአንድ ህጻን ስም በመጥራት ስለአወራው/ስለአወራችው ተረት መጠየቅ እንዲሁም በተረቱ ውስጥ ስለነበሩ ሃሳቦች መጠየቅ፤

ተግባር 4፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. እየዘመሩ መደነስ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ከስጋት ነፃ ማድረግ፣ ዳንስ፣ መዝሙር፣ ተግባራትን ማከናወን መቻል

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ውድ መመህር ህፃናቱን ወደውጭ ይዘው ይውጡ።

- በቅድሚያ የሚጫወቱበት ቦታ ለጉዳት የሚዳርጋቸው ነገር ካለ ቆሞ ብለው በማጤን እነዲናገሩ እና አካባቢውን ከአደጋ ስጋት ነፃ የማድረግ ተግባር አከናውኑ፤
- ቀጥሎ በሞንታርቦ፣ በቴፕ ለመደነስ የሚያመችእና የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ያዘጋጁ ከዚያ ህፃናቱን በአስር አስር ቡድን በጦታ ሰብጥር ይምረጡ፤
- በአንድ ጊዜ ከአራት ያላነሱ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በተመሳሳይ ቅርፅ ቡድኑ መስራት እንዳለቤት እርሶ ከመዝሙር ጋር ሰርተው ያሳዩ። ለምሳሌ፡- ወደጎን እጅ መዘርጋት፣መዝለል፣ ሙሉ ሰውነትን ማሽከርከር፣ እግር ከፍቶ ወገብ መያዝ ... ሌሎችን

እነሱ መዝሙሩን እየዘመሩ አንድ የቡድን መሪ ከፊት በመሆን ቡድኑን እየመራ ተመሳሳይ እንቅስቃሴ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ቴፕ፣ ጂፓሰና ተያያዥነት ያላቸው ቁሶች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ብእአጠቃላይ ስላከናውኗቸው ተግባራት በቃል መጠየቅ፤

* ህጻናት ጨዋታውን በትክክል መጫወታቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 5፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. መለየትና መመደብ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ጤናማ ምግበ፣ ጤናማ ያልሆነ ምግብ፣ ጤናማ መጠጥ፣ ጤናማ ያልሆነ መጠጥ፣

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ጤናማ ስለሆኑ እና ስላልሆኑ ምግብና መጠጦች ለህፃናቱ በስዕል አስደግፈው ይግለፁ። ቀጥሎ የመለየትና የመመደብ ጨዋታ እንዲጫወቱ ህግ ነግረውና አስፈላጊ ፍላሽ ካርዶችን አዘጋጅተው ያጫውቱ።
* ጤናማ ምግብ መጠጥ የምንላቸው ውስጥ ለምሳሌ በአብዛኛው እቤት ውስጥ በተለያየ መልኩ የሚዘጋጁ ናቸው እንደ ቂጣ፣ ገንፎ፣ ጎመን፣ ስላጣ፣ እንጀራ፣ ዳቦ እቤት የተዘጋጁ የተለያዩ የፍራፍሬ ጁሶች፣ ውሃ፣ ወተት...
* ጤናማ ያልሆኑ በተለይ ለህፃናት ምሳሌ የታሸጉ ብስኩቶች በርገር፣ ፒዛ፣ የታሸጉ ጁሶች፣ ለስላሳ መጠጦች
* ሴትና ወንድ ህፃናት ሁለት ሁለት ሆነው የተቀላቀሉትን ጤናማ የሆኑና ያልሆኑ ምግብና መጠጦችን ስእል/ካርዶች ለይቶ በየመደባቸው መመደብ ቀድሞ የጨረሰ አሸናፊ ይሆናል።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ምግቦችና መጠጦች ስዕል

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* “ጤናማ እና ጤናማ ያልሆኑ ምግብ እና መጠጠጦችን እነማን ናቸው?” በማለት ይጠይቋቸው።

ተግባር 6፡- ውይይት

ሀ. የጤናማ ምግቦችና መጠጦች ጠቀሜታ (2 ክፍለ ጊዜ)

ሀ. የጤናማ ያልሆኑ ምግቦችና መጠጦች ጉዳት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ጤናማ ያልሆነ ምግብ፣ ጤናማ ያልሆነ መጠጥ፣ የጤና ጉዳት፣ ጤናማ ምግብና መጠጥ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* በቅድሚያ ጤናማ የሆኑና ያልሆኑ ምግቦችና መጠጦች ምንነትና ጉዳት በቃል ይንገሯቸው።
* በመቀጠል ሁሉም ህጻናት እጅ እያነሱ ስለመወያያ ርዕሱ ሀሳብ እንዲሰጡ ይጋብዟቸው።
* ጥያቄ በሚነሳበት ሰዓት ህጻናት ራሳቸው ሀሳብ እንዲሰጡበት ያበረታቱ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ጤናማ ያልሆኑ ምግብና መጠቶችን የሚያሳዩ ምስሎች፣ እርሳስ፣ ላጲስ፣ ወረቀት

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

1. ጤናማ ያልሆኑ ምግብ እና መጠጠጦችን እነማን ናቸው?
2. ምን ጉዳት አላቸው?

* ህጻናት ውይይቱን በትክክል መካፈላቸውን ይመልከቱ።

ሳምንት አስራ አምስት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

- o በቁሶች መካከል ከ4-6 ተመሳይነትና ልዩነት ያሳያሉ
- o የቤቴሰብ ፍደላትን ድምጽና ቅርጽ ይለያሉ
- o ሰዕል ያቀልማሉ
- o ቀለል ያሉ ዳንሶችን ይደንሳሉ
- o በአንድ ድርድር ቁሶችን ይደረድራሉ፣
- o ሰማቸውን ይገለብጣሉ፣
- o ሰዕል በማየት የሰዎችን ሰሜት ያነባሉ፣
- o ከሁለት በላይ ልጆች ጋር ይጫወታሉ፣
- o የተፈጥሮንና ሰው ሰራሽ ቦታዎችን ያደንቃሉ

ንዑሰ ይዘቶች፦

- የቃላት እውቀት
- የፍደላትን ድምጽ መገንዘብ
- ግንኙነት፣ ዝምድናና ትግበራ
- የአካል ብቃት
- ቅጥ/ጥለት
- መጻፍ
- ቃላት ማንበብ
- ከሌሎች ጋር የመቅረብ ክህሎት
- የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አከባቢዎች

ተግባር 1፦ የተግባር ሥራ

ሀ. ስዕል ማቅለም (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ስዕል ማንበብ (ስሜትን)፣ ስዕል መቀባት፣ ስም መጻፍ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ስርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

ለዚህ ሳምንት ሶስት የግል የተግባር ሥራዎች የቀረቡ ስሆን በተቀመጠላቸው ክፍለ ጊዜ ደጋግሞ ማስራት ውጤታማ ያደርጋል። ለዚህ ክፍለ ጊዜ ህፃናቱ በግላቸው እና ከጓደኞቻቸው ጋር በተግባር እየሰሩ የሚማሩበት በመሆኑ ሁኔታዎችን ምቹ ማድረግ ያስፈልጋል።

- በቅድሚያ ስሜትን የማንባብ፣ የመናግር፣ እና የመግለጽ ክሂላቸውን ለማዳበር የተለያዩ ስሜቶችን የሚገልጹ ስዕሎች/ሞዴሎችን በመሰጠት በትኩረት ተመልክተው ያዩትን በየተራ ተነስተው ስሜቱን እንዲገልጹ ያድርጉ።
- ቀጥሎ የወንድና የሴት ሙሉ ምስል ለማቅለም የሚሆን የተለያዩ ስሜትን በፊታቸው ላይ የሚታይ በወረቀት/በደብተር ቀድሞ አዘጋጅተው ለሁሉም ህፃናት አዘጋጅተው በመሰጠት የፈለጉትንና ስሜታቸውን የሚገልፅላቸውን ቀለሞች ይቀቡ። በሰዕሉ መጨረሻ ሰማቸውን ይፃፉላቸው እና እነሱ ደግመው ይጻፉ።
- በመጨረሻም ስለአቀለሙት ስዕል እና የሥዕሉን ስሜት ለክፍል ጓደኞቻቸው ይገለፁ ስማቸውንም ያንብቡ፤ እርሶም የሰሩትን በማያት ያድንቁ እርማት ይሰጡ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

የተለያዩ ስሜትን የሚያሳዩ ምሰሎች፣ ለማቅለም የተዘጋጀ ስሜት ገላጭ የወንድና ሴት ስዕል፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

ምሰል አሳይተው ስሜት፣ ያቀለሙትን ስዕል ምንነትና ስሜት፣ የሰማቸው መነሻ ፊደል ይጠይቋቸው።

* ስዕሎቹን ሲያቀልሙም ሆነ ስማቸውን ሲገለብጡ ቀርበው መመልከት ያስፈልጋል።

ለ. የፊደል ቤተሰብ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፊደል መፃፍ፣ የፊደል ድምጽ፣ ሰም መጻፍ፣ ከጓደኛ ጋር መደነሰ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ስርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

- የእለቱን የፊደል ቤተሰብ ማዘጋጀትን በየጠረጴዛው አንድ ቤተሰብ መሰጠት እና ከእርሶ ጋር የማንበብ እና በቅደም ተከተላቸው የማስቀመጥ ተግባርን ያከናውኑ።
- የእለቱ የፊደል ቤተሰብ (መ-ሙ-ሚ-ማ-ሜ-ም-ሞ) ለህፃናቱ ያስተዋውቁ እንዲሁም ከፊደሎቹ ጋር የሚቀራረብ በአካባቢያቸው የሚገኝ ነገሮች/ቁሶች ጋ እንዲያመሳክሩ ማድረግ፤

ለምሳሌ (‹ሙ› ትመስላለች ፣ ‹መ› መነጽር ትመስላለች …) እያሉ የእለቱን ፊደል አምሳያ አብራቹሁ ፈልጉ።
 ወረቀት እና እርሳስ በመስጠት ያነበቡትን ፊደል በየጠረጴዛቸው ላይ በቅደም ተከተል በመደርደር ከዚያ እያዩ ደግመው ይፃፉ። እንዲሁም ከእለቱ እና ከዚህ በፊት ከተዋወቋቸው የፊደል ቤተሰቦች ተጠቅመው ስማቸውን ይፃፉ።
 ድጋፍ ለሚሹት ደግሞ እርሶ ጽፈው በመስጠት ደግመው ይፃፉ ቀጥሎ ተራበተራ ፊደላቱንና ስማቸውን ያንብቡ።
 ሲጨርሱ ሁለት/ሶስት ህፃናት በጋራ በመሆን በሚያውቁት መዝሙር እየዘመሩ ይደንሱ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ቤተሰብ ፍላሽ ካርድ/ሞዴል፣ እርሳስ፣ ወረቀት/ደብተር፣ ሞንታርቦ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ፊደል አሳይቶ ማስነበብ፣ አንድ በአንድ እየተነሱ የፊደሉን ቤተሰብ በቅደም ተከተል እንዲያነቡ መጠየቅ
* ሁሉም ህጻናት ተግባሩን በተገለጸው መሰረት ማከናወናቸውን ያረጋግጡ።

ሐ. ተመሳሳይና ልዩነት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ተመሳሳይ፣ ልዩነት፣ ቁስ መደርደር፣ በጋራ መጫወት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

* ይህ ተግባር ህፃናቱ ከጓደኞቻቸው ጋር በቡድን በተግባር እየሰሩ የሚማሩበት በመሆኑ ሁኔታዎችን ምቹ ማድረግ ያስፈልጋል። የሚሰራው ተግባር ቁሶችን ተመሳሳይነት እና ልዩነት እየገለፁ መለየት ነው።
* ተግባሩን ሁለት እና ሶስት በመሆን በጋራ እንዲሰሩ ያድርጉ። ለዚህም ለክፍለ ጊዜው የተዘጋጀውን መፃፍ እና ደብተር፣ ማርከርና እርሳስ፣ ሁለት ሌትር እና ግማሽ ሌትር የውሃ ፕላስቲክ ኮዳ (ሃይላንድ)፣ የፕላስቲክ ጎድጓዳ ሳህኖች በመጠን እና በቀለም የተለያዩ፣ ባለቀለም ዘንጎች፣ ተቀለሙ በቁመት የተለያዩ እንጨቶች ….. ማዘጋጀት እና እርሶ ለይተውና መድበው ያሳዩ። ቀጥሎ ህፃናቱ ተግባሩን ማከናወን፤
* ቁሶችን በቁመታቸው (ረጅምና አጭር)፣ በስፋታቸው (ሰፊና ጠባብ)፣ በመጠናቸው (ወፍራምና ቀጭን)፣ ባለቀለም (ቀይ፣ ነጭ፣ አረንጓዴ፣ ሳማያዊ፣ ቢጫ …) በማለት ቁሶቹ ያላቸውን ተመሳሳይነት እና ልዩነት እያዩ መለየትና መመደብ፤ በመጨረሻም የለዩትንና የመደቡትን ልዩነታቸውና ተመሳሳይነታቸውን ይግለጹ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ቤተሰብ ፍላሽ ካርድ/ሞዴል፣ እርሳስ፣ ወረቀት/ደብተር፣ ሞንታርቦ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የቁሶቹን ተመሳሳይነትና ልዩነት ደጋግሞ መጠየቅ
* ሁሉም ህጻናት ተግባሩን በተገለጸው መሰረት ማከናወናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 2፡- መዝሙር

ሀ.ፊደሎች ነን እኛ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - የፊደል ቤተሰብ፣ መጫወት፣ መሳል፣ መቀባት፣ ተፈጥሮን ማድነቅ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ አልባሳት፣ የተፈጥሮ አከባቢን የሚያሳይ ስዕልንና ወዘተ

መዝሙር 1፡- ፊደሎች ነን እኛ

ሀ... ሁ... ሂ... ሃ... 2x — ተጠምተናል ውሃ 2x
ሰ... ሱ... ሲ... ሳ... 2x — አልበላንም ምሳ 2x
ቀ... ቁ... ቂ... ቃ... 2x — ኑ እንጫዎት በዕቃ 2x
ሱ... ሱሪ ከሰር አድርገን — ሸ... ሸሚዝ እንለብሳለን
ት... ትምህርት ቤት ሄዴን — እ... እውቀት እንገዛለን፡፡
ስ ... ስዕሎቹን ስለን — ቀ ... ቀለም እንቀባለን
ተ ... ተፈጥሮን ለማድነቅ — በ ... በጣም እንወዳለን
በ... በአንድ ላይ ሆነን — ስ ... ስራ እንሰራለን፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለ. ተፈጥሮ ልዩ ናት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፣ መጫወት፣ መደሰት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተፈጥሮ አካባቢን የሚያሳዩ ፎቶዎችንእ ስዕሎች

መዝሙር 2:- ተፈጥሮ ልዩ ናት

ከቁሶች መካካል ሰውም የሰራቸው
እጅግ ውብ ነገሮች አስተማሪ ናቸው
ተፈጥሮ ልዩ ነው እኔ ደስ ይለኛል
ሰወጣ ሰገባ በጣም ይደንቀኛል
ኑ እስቲ ጓደኞቼ በጋራ እንጫዎት
በተፈጥሮ ጸጋ እብረን እንደሰት
ተፈጠሮን እንሳል ደግሞም እናቅልም
በጣም ያሰደሰታል ያላቸው ቀለም።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 3፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. የጠፋውን መፈለግ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ስሜት፣ ስእል፣ የፊደል ቤተሰብ፣ ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* የጠፋውን ፈልግ የሚለውን ጨዋታ ለማጨወት የተለያዩ የፊደል ቤተሰቦችን፣ የተለያዩ ስሜትን የሚያሳዩ ስእሎችን፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የሆኑ ነገሮችን የሚያሳይ ስእል ያዘጋጁና ቀጥሎ ያለውን ቅደም ተከተል ጠብቀው እንዲጫዎቱ ያድርጉ።

* የፊደል ቤተሰብ፣ የስሜት የሚገልጹ ስእሎችና የተፈጥሮና ሰው ስራሽ የሆኑ ነገሮችን የሚያሳይ ስእል በተለያዩ ሳህኖች ውስጥ በማድረግ ጠረጴዛ ላይ ማቅረብ፤

* የጠፋውን መፈለግ ጨዋታን ስርተው ማሳየት ምሳሌ ከፊደል ቤተሰብ አንዱን በማጉደል የጎደለውን መጠየቅ፣ ከተፈጥሮእና ሰው ስራሽ አንዱን በማጉደል የጎደለው ተፈጥሮ/ሰው ስራሽ በማለት መጤቅ፤

* ቀጥሎ ሁሉት ሁለት ህጻናት እየሆኑ የጠፋውን የመፈለግ ጨዋታ ይጫዎታሉ፡፡ በዚህ መሰረት ሁሉንም ህጻናት እያበረታቱ እንዲጫዎቱ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ካርድ፣ ስሜትን የሚያሳዩ ምስሎች/ሞዴሎች፣ የቤተሰብ ስእል፣ ተፈጥሮንና ሰው ስራሽን የሚገልጹ ስእሎች፣

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* የተለያዩ ስሜቶችን እንዳሳዩ ማድረግ፣ ተፈጥሮና ሰው ስራሽ ቁሶችን መለየታቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ

* ህፃናቱ ሲጫዎቱ ተገቢውን ትእዛዝ ተከትለው መፈጸማቸውን ማረጋገጥ፣

ተግባር 4፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. ተመሳሳይ ቁሶችን ለይቶ መደርደር (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መለየት፣ ቁሶች፣ መደነስ፣ መደርደር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

በዚህ ክ/ጊዜ ህጻናት ቁሶችን በፍጥነት ለይቶ የመደርደር ጨዋታ ይጫዎታሉ፡፡ የሚያገለግሉ ቁሶችን ይዘው ወደ ውጭ በማሰዎጣት ጨዋታውን ያጫውቱ፡፡ በአንድ ጊዜ ከ2 እስከ 4 የሚደርሱ ህጻናት መጫዎት ይችላሉ፡፡

 ቁሶችን እናንተ ከተቀመጡበት ፊት ለፊት አምስት ሜትር ርቀት ላይ ቀላቅሎ ማስቀመጥ፤ ተመሳሳይ ደግሞ በሌለኛው አቅጣጫ ማስቀጥ፤

 በመጀመሪያ እርሶ ስርተው በማሳየት ቀጥሎ የመጀመሪያዎቹ ሶስት/ሁለት/ አራት….ተወዳዳሪዎች ከቁሶች መሀል ለይተው እንዲያመጡ (ለአንዳቸው ትንንሽ ኳሶችና ትልልቅ የወሃ ፕላስቲክ ሌላቸውም እንደዚያ የተለያዩ ቁሶች ከተለያዩ መጠን ይዘው በፍጥነት ወደመነሻቸው መምጠት እና ከተተመሳሳያቸው ጋር መደርድር እና በትክክል ለይተው ይዘው የተመለሱ አሸናፊ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ከአንድ እስከ ሶስት የወጡት ሙዚቃ ተከፍቶላቸው ይደንሱ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ትልልቅ እና ትንንሽ የወሃ ፕላስቲክ፣ ትልልቅና ትንንሽ ኳሶች የተላያየ ቀለም ያላቸው ኩባያዎችና ሌሎች

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* "ምን አይነት ጨዋታ ተጫወታችሁ?፤ ትልልቅና ትንንሽ ቁሶች ልዩነታቸው ምንድ ነው? " ብለው መጠየቅ፤

* ህጻናት ጨዋታውን በትክክል መጫወታቸውን ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 5፦ በፕሮጀክት መማር

ሀ. ኬሮግራፊ መስራት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ተመሳሳይ እንቅስቃሴ፣ ዳንስ፣ ስም

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ ስርቶ ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

ለዚህ ፕሮጀክት ይበቃል የሚሉትን ቀን የተሰጠውን ክፍለ ጊዜ መሰረት አድርገው መስጠት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የተወሰኑ ክፍለ ጊዜዎችን ለመለማመጃ እንዲጠቀሙ ያድርጉ፡፡ ለቡድናቸው ስያሜ ይስጡ፣ መዝሙር/ሀገርኛ ሙዚቃ ይምረጡ፡፡

 በተሰጣቸው የልምምድ ጊዜ የተለያዩ አይነት የእንቅስቃሴ አይነቶችን በተማሳሳይ ቅርጽ ይሰሩ፡፡ ምሳሌ (ልክ በቴሌቪዥን እንደሚያዩት አይነት ውዝዋዜ)… ለፕሮጀክቱ የተሰጠው ጊዜ ሲያበቃ ህፃናቱ የሚፈልጉትን አለባበስ ተጠቅመው እንዲያቀርቡ ይደረግ፤

 ዝግጅታቸውን ሲያቀርቡ እንግዶችን ይጋብዙ፤ ከተቻለም የውድድር ስሜት እንዲኖረው ማድረግም ይቻላሉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ቴፕ፣ ስልክ፣ ተለያዩ ባህላዊ እና ዘመናዊ አልባሳት

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

* "የሰራችሁት የዳንስ አይነት ምን አይነት ነው?፤ የቡድናችሁ ስያሜ ምን ይባላል?፤ ለምን ይህንን ስያሜ መረጣችሁ?" በማለት ይጠይቋቸው፡፡

* ህፃናቱ ሲጫዎቱ ተገቢውን ትእዛዝ ተከትለው መፈጸማቸውን ማረጋገጥ፣

ተግባር 6፦ የመስክ ጉብኝት



ሀ. አከባቢን መጎብኘት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፣ መለየት፣ ስም

የማስተማሪያ ዜዴ:- ስርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* በትምህርት ቤታቸው ግቢ ያሉ ቤቶችን፣ እጽዋቶችን፣እአዋፋትን፣… እንዲመለከቱ ይአበረታቷቸው፤

* በተቻለ መጠን የሚያዩት አከባቢ ልዩነት እና አንድነት እንዲገነዘቡ ያድርጓቸው። ምናልባት በርካታ ህፃናት ከሆኑ ጉብኝት ጊዜውን በሁለት/በሶስት ቡድን ከፋፍለው ያስጎብኙ።
* ህፃናቱ በጉብኝት ወቅት መውሰድ ስለሚገባቸው ጥንቃቄ መንገር እንዲሁም አብሮ ካሉ ጎብኚዎች ተነጥሎ ለብቻ መሄድ የተከለከለ መሆንን ማሳወቅ፤
* በጉብኝት ወቅት ያዩትን ተፈጥሮኣዊ እና ሰው ሰራሽ ነገሮች ለይተው ይፃፉ፤
* እርሶም በማስታወሻ እየፃፉ በስልኮት የጉብኝት ፎቶ ከህፃናቱ ጋር ይነሱ።
* ከጉብኝቱ አረፍ በማለት ካዩአቸውት ነገሮች መካከል ሁለት ነገሮች (አንድ የተፈጥሮ እና አንድ ሰው ሰራሽ) እንዲስሉና እንዲቀቡ ያድርጉ፤ ስማቸውን ይፃፉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

* ወረቀት፣ ማስታወሻ ደብተር፣ እርሳስ፣ ከለር፣ ካሜራ፣ ስልክ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

1. በተፈጥሮ ያሉ ነገሮች ውስጥ ምን ምን አያችሁ?
2. ሰው ሰራሽ ከሆኑት ምን ምን አያችሁ?

* ህጻናት የሚስሏቸውን ስዕሎች ቀርበው መመልከትና ምን እንደሳሉ መጠየቅ ያስፈልጋል።

ተግባር 7፦ ውይይት

ሀ. ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፣ መመደብ፣ ስያሜ መስጠት፣ መለያ

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

* በቅዲሚያ ጊዜው የውይይት እንደሆነ ይንገሯቸው።
* ቀጥሎ ስለሰው ሰራሽና ተፈጥሮ አከባቢዎች መረጃ ይስጧቸው።
* ህጻናት ተራ በተራ እጅ እያነሱ የተፈጥሮ አከባቢ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ዕድል ይፍጠሩላቸው።
* ሁሉም ህጻናት ስለተፈጥሮ አከባቢ ሀሳብ መስጠታችውን ካቆሙ ቀጥለው ስለሰው ስራሽ አከባቢ እንዲያወሩ ያድርጓቸው።
* ከተቻለ የተፈጥሮና ሰው ስራሽ አከባቢዎችን የሚያሳዩ ስዕሎችን በማሳየት ገለጻ ያድጉላቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦ የተፈጥሮና ሰው ስራሽ አከባቢዎችን የሚያሳዩ ስዕሎችና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ስለተወየዩበት ነግር እንዲገልጹ ማበረታታት፣ በውይይት ጊዜ እያንዳቸው የሰጡት ሃሳቦችን መጠየቅ

ተግባር 8፦ ተረት

ሀ. መንገደኛው ነጋዴ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፣ መጨዋት፣ ስም፣ ተመሳሳይ፣ ልዩነት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰዕላዊ መግለጫ (ተራራ፣ ቤት፣ ወንዝ፣ መኪና፣ ከተማና ወዘተ)

መንገደኛው ነጋዴ

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ነጋዴ ወደ ገበያ ይሄዳል። እየሄዴ መንገድ ላይ ሁለት ህጻናት እየተጫወቱ ያገኛቸዋል፡ ፡ ስማቸውን ጠየቃቸው። ሁለቱም ህጻናት እድሜያቸው 5 ነው። መልካቸውም ጸይም ነው። ልጆቹ የለበሱት ልብሰም ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን አንደኛው ልጅ ረዥም ሲሆን ሁለተኛው አጭር ነበር። የአንደኛው ጸጉር ሉጫ ሆነው የሁለተኛው ግን ከርዳዳ ነበር። ነጋዴውም ልጆቹን ከተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አከባቢዎች የትኛውን አብልጠው እንደሚወዱ ጠየቃቸው። አንደኛው ህጻን የተፈጥሮ አከባቢዎችን (ተራራ፣ ወንዝ፣ ሜዳና ጫካ) እንደምወድ ነገረው። ሁለተኛው ልጅ ግን ሰው ሰራሽ አከባቢዎችን (ፓርክ፣ ከተማና መዝናኛ) እንደምወድ ነገረው። ነጋዴውም ከልጆቹ ጋር የነበረውን ቆይታ ጨርሶ ወደ ገበያው አልፎ ሲሄድ ልጆቹ እየተጫዎቱ ቆይተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ ይባላል።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

1. ከተረቱ ምን ተማራችሁ?
2. ህፃናቱን ያገኘው ሰው ስራው ምን ነበር?
3. የልጆች እድሜ ስንት ነው?
4. ስማቸው ማን ማን ይባላል?

ሳምንት አስራ ስድስት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

o ስለተፈጥሮ አከባቢ ይገልፃሉ፣

o ቁሶች እንዴት እንደተፈጠሩ ይገነዘባሉ፣

o ከሌሎች ጋር በጋራ መኖር ይችላሉ፣

o ቁሶች ባሉበት አቅጣጫ ሰውነታቸውን ማንቀሳቀስ ይችላሉ፣

o ለልዩ ልዩ ሙያዎች ክብር ያሳያሉ፣

o መጥፎንና ጥሩን ይለያሉ፣

o ቅርጻ-ቅርጾችን ይገለብጣሉ፣

o ፊደላትን ደጋግመው ይፅፋሉ፣

o እስከ 10 ያሉ ቁጥሮችን ይፅፋሉ፣

o ቁሶችን በርዝመታቸው ይለካሉ፣

o ቀለል ያሉ ባህላዊ ዳንሶችን ይደንሳሉ፣

ንዑስ ይዘቶች፦

- የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አከባቢ
- ድጂታል ሊትሬሲ ክህሎት
- ከሌሎች ጋር የመግባባት ክህሎት
- የሀገር ፍቅር ስሜት
- የሰፓሽያል ግንዛቤ
- ሞራላዊ ዕሴቶች
- ቅርጻ-ቅርጽ
- መጻፍ
- ቁጥር መጻፍ

ተግባር 1፡- መዝሙር

ሀ. ተፈጥሮና ፍቅር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ተፈጥሮ፣ መጥፎ፣ ጥሩ፣ ቅርፆች

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ተፈጥሮን የሚያሳዩ ስዕሎች፣ በጋራ የሚኖሩ ሰዎችን የሚያሳይ ስዕል/ተንቀሳቃሽ ምስልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለ. ሙያ ክቡር ነው (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽ፣ መጫወት፣ መደሰት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ሙያተኞችን የሚያሳዩ ስዕሎች፣ በጋራ የሚኖሩ ሰዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች፣ ሞንታርቦ፣ ቴፕ፣ ስልክ

መዝሙር 2:- ሙያ ክቡር ነው

ወታደር ፖሊሱ ሃኪም እና ኢንጂነር
የስራ አይነት ናቸው በሰው የሚፈጠር
ጽዳት የሚያጸዱ የቤት ውስጥ አገልጋይ
አስፈላጊ ናቸው ደምቀን እንድንታይ
ከሁሉም ከሰዎች ጋር አብሮ ለመኖር
በጣም ያስፈልጋል ስራቸውን ማክበር
ስራማ ክቡር ነው እጅጉን በጣም
ትንሽ ነው ትልቅ ነው የሚባል የለም
ስለዝህ ተስማምቶ መኖር ይሻለናል
የሁሉንም ሞያ ማክበር ይበጀናል።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ፊደላትን መጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፊደል፣ ደግሞ መፃፍ፣ ሞያ፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዘዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ለዚህ ሳምንት የተዘጋጁትን የፊደል ቤተሰብ (ዐ-ዑ-ዒ-ዓ-ዔ-ዕ-ዖ) ፍላሽ ካርድ በማቅረብ ለህፃናቱ መስጠትና በእርሶ ድጋፍ ማንበብ።

- ቀጥሎ በወረቀት/በመለማመጃ መፅሃፋቸው ተፅፎ የተዘገጀውን የፊደሎቹን ቤተሰብ ደግመው እንዲጽፉ ማድረግ፤
- ቀጥሎ ህፃናቱ የእርሶን ሚና በመውሰድ እንደመምህር በመሆን የፊደል ቤተሰቡን ለክፍሉ ህፃናት ያስነብቡ፤ ይህንን ሁሉም ህፃን እንዲሞክረው ያድርጉ።
- ምክኒያቱም ከስራዎች አንዱ የመምህርነት ስራ ስለሆነ በቀላሉ ሙያውን እንዲወዱት ይረዳል፤ ለመማርም ክብር ይሰጣሉ።
- በመጨረሻም ሰንት ቤተሰብ እንደፃፉ እያነበቡ ይቁጠሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እርሳስ፣ ደብተር/የመለማመጃ መፅሃፍ፣ የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ የመምህር ገዋን ነጭ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* “የፃፋችሁት የፊደል ቤተሰብ እነ ማን ናቸው?፣ ሰንት ናቸው?፣ የመምህር የሰራ ድርሻ ምንድን ነው? “ በማለት ይጠይቋቸው።

ለ. ቁጥር ደግሞ መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁጥር፣ ደግሞ መፃፍ፣ ሰው ሰራሽ፣ ፈጠራ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ለዚህ ክፍለ ጊዜ የተዘጋጁትን የቁጥር ፍላሽ ካርድ/ሞዴል በማቅረብ ለህፃናቱ መስጠትና በእርሶ ድጋፍ ቁጥሩን ማንበብ፤ ቀጥሎ ደግመው እንዲጽፉ ማድረግ፤

* የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣ እርሳስ፣ ላጲስ፣ ደብተርና/ወረቀት /የመለማመጃ ደብተር፣ መቅረጫ አሰቀደመው ይሰጧቸው። ከዚያ በነጭ ወረቀት፣ በጥቁር/በነጭ ሰሌዳ ላይ እርሶ ቁጥር ፅፈው ማሳየት፤ ቁጥሩን ደግመው እንዲጽፉ ማድረግ።

* ቀጥሎ ህፃናቱ በደብተራቸው ላይ በፍላሽ ካርድ ላይ ያለውን ቁጥር ደጋግመው እንድጽፉ ማድረግ፤

* በመጀመሪያ ቀን እሰከ 5 ያሉ ቁጥሮችን ካሰሞከሯቸው በኋላ በሁለተኛ ቀን ቀጣይ እሰከ 10 ያሉ ቁጥሮችን እያነበቡ ያጻፏቸው።

* ቀጥሎ ቁጥር ሰው ሰራሽ መሆናቸውን እና እነሱም የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር እንደሚችሉ መንገር እና የራሳቸውን ፈጠራ ለማውጣት እንዲሞክሩ ያድርጉ ቁጥሮችን በወረቀት ቀርጸው እንዲያወጡ ያበረታቱ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እርሳስ፣ የመለማመጃ መፅሃፍ ፣ የቁጥርፍላሽ ካርድ፣ የመምህር ገዋን ነጭ፣ እርሳስ፣ ላጺስ፣ ወረቀት፣ መቅረጫ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

የሚከተሉትንና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* የፃፋችሁት ስንት ቁጥር ነው?

* ሰው ሰራሽ ነገሮች ውስጥ እክፍል ውስጥ ምን አለ?

ሐ. መሳልና መለካት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቅርፆች፣ ሰው ሰራሽ፣ ርዝመት፣ ቁስ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ለዚህ ክፍለ ጊዜ ለማስተማር የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾችና የተለያዩ ቁመት/ርዝመት ያላቸው ቁሶች በማቅረብ የቁሶቹን ስም እና አገልግሎት እንዲሁም ሰው ሰራሽ ቁስ እንዴት እንደተፈጠረ በግልጽ በሚገባቸው ቃላት መንገር፤

ቀጥሎ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ደብተር፣ ከለር በመስጠት እነሱም የጆኦሙትሪ ቅርጾችን አሰደግፈው ይሳሉና ቀለም ይቀቡ፡፡ እርሶም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ እርማትና ማበረታቻ ያድርጉ፡፡ ከዚያም የተለያየ ቁመት ያላቸውን ዘንጎች እንዲያለካኩ እና ረጅም አጭር መካከለኛ በማለት እንዲናገሩ እድል ይፍጠሩ፡፡

የመማሪያና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡-

እርሳስ፣ የመለማመጃ መፅሃፍ፣ የጂኦሜትሪ ቅርጾችና የተለያዩ ቁመት/ርዝመት ያላቸው ቁሶችና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* “ምን ቅርጽ ሰራችሁ?፣ ምን ዓይነት ቀለም ቀባችሁ?” በማለት ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት ተግባሩን በትክክል ማከናወናቸውን ይከታተሉ፡፡

ተግባር 3፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. በአካል እንቅስቃሴ አቅጣጫን መጠቀም (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- አቅጣጫ፣ ቁስ ማንቀሳቀስ፣ አቅጣጫን መጠቀም

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ይህንን ጨዋታ ለማጫዎት የሚከተሉት የድርጊት ቅደም ተከተሎችን ይከተሉ፡፡

* የውሃ ፕላስቲክ ወይንም መጠነኛ ተንቀሳቃሽ ቁስ ማቅረብ፤
* የጨዋታውን ርዕሰ መንገርና አጨዋወት አስመስለው ማሳየት፤
* ህጻናት ሁለት ሁለት እየሆኑ በመነሳት ፊት ለፊት እየተያዩ ቀኝ ግራ እጆቻቸውን እንድያንቀሳቅሱ ማድረግ (እጃቸው ወዳለበት ያሉ ቁሳቁሶን እየጠቆሙና እየጠሩ)፤
* በማሃል አስተማሪዋ ቁስ በሚትልበት ጊዜ ቀድመው ቁሱን የሚያነሳው ልጅ ቁሱ ከምን እንደተሰራና ለምን እንደሚጠቅም እንድያወራ ይደረጋል።
* ቁሱን ቀድመው ማንሳት ያልቻለው ህጻን አጠገቡ ላይ ያሉ ማናቸውንም ቁሳቁሶች እንዲጠራና ከምን የተሰሩ እንደሆኑ እንድያብራራ ይደረጋል።
* በተሸናፊው ህጻን ምትክ ሌላ ህጻን ይጠራና ጨዋታው በዚህ መልኩ ይቀጥላል፤

የመማሪያና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡-

ሰው ሰራሽ/የተፈጥሮ ቁሶች፣ አቅጣጫን የሚያሳዩ የተለያዩ ምስሎች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* “በምን አካል እንቅስቃሴ ምን አቅጣጫ ጠቆማችሁ?” በማለት ይጠይቋቸው።
* ህጻናት ተግባሩን በትክክል ማከናወናቸውን ይከታተሉ።

ለ. ፊደል የመገልበጥ ውድድር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል መፃፍ፣ ማንበብ፣ ባህላዊ ውዝዋዜ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ይህንን ጨዋታ ለማጫዎት የሚከተሉት የድርጊት ቅደም ተከተሎችን ይከተሉ።

- የፊደላት ፍላሽ ካርድ፣ እርሳስ፣ ላጲስና ነጭ ወረቀት ያቅርቡ፤
- ህጻናት ሁለት ሁለት እየሆኑ በመነሳት በደረሳቸውን ፍላሽ ካርድ ላይ ያለውን ፊደል በመገለበጥ ይፎካከሩ፤
- ቀድሞ በትክክል የገለበጠው ህጻን የፊደሉን ስም፣ ቅርጽና ድምጽ አውርተው በጨዋታው አሸናፊ ሲሆን የተሸነፈውን ህፃን በሌላ ጠረጰየዛ ላይ እንዲያለማመድ ማድረግ፤
- ሌላ ተረኞች መተው ይወዳደራሉ፤ ሌላ ካርድ ይሰጣቸዋል፤ ይፅፋሉ። አሸናፊ እና ተሸናፊ ካለ ልክ እንደመጀመሪያው ጓደኛውን ያለማምዳል።
- ጨዋታውን እየተቀባበሉ እስከመጨረሻው እንድጫወቱ ይደረጋል።
- በመጨረሻም የተለያዩ ባህላዊ ሙዚቃዎችን ከፍተው አሸናፊዎችን እንዲወዛወዙ ማድረግ ቀጥሎ የተሸነፉ ህፃናትን ማቀላቀል ያስፈልጋል።

የመማሪያና የመጫዎቻ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ እርሳስ፣ ደብተር/ወረቀት፣ ሞንታርቦ/ስልክ/ቴፕና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ስንት ፊደል እንደፃፉ፣ ፊደሎቹ እነማን እንደነበሩና ምን ምን ሙዚቃዎች እንደሰሙ ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ተግባሩን በትክክል ማከናወናቸውን ይከታተሉ።

ተግባር 4፦ ተረት

ሀ. ሽልንጌ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ስራ፣ መልከምነት፣ መጥፎ፣ ጥሩ፣ ከሌሎች ጋር መግባባት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መስረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስዕላዊ መግለጫዎች (የተለያዩ ሥራዎች የሚትሰራ ሴት ስዕልና ወዘተ)

ሽልንጌ

ሽልንጌ የምትባል ጎበዝ ሴት ነበረች። ሽልንጌ በጣም ሥራ ወዳድ ነች። እሷ የሚትመርጠው የሥራ አይነት የለም። ሊሰትሮ ሆና ሰርታ ተውቃለች። ወፍጮ ቤት የጽዳት ሠራተኛም ነበረች። ሚኒባስ ላይ ረዳት ሆና አገልግላለች። የተወሰነ ጊዜ ጫቃ ለሳኝም ነበረች። አሁን ላይ ያን ሁሉ ስርታ ባገኘችው ገንዘብ ሆቴል ከፍታ ትነግዳለች። ሽልንጌ ሰው ታከብራለች። መጥፎ እና ጥሩ የሚባሉ ነገሮችን በደንብ ሰለምታውቅ የሰውን ገንዘብ አትወስድም። ወሸት አትናገርም። የተቸገረን ሰው ትረዳለች። ከሌሎች ሰዎች ጋር በመግባባት ትኖራለች፤ ያላትን ለሌሎች ማካፈል ትወዳለች። ልጆቿንም አስተምራለች። ሰው ሁሉ የራሱ ሥራ እንዲኖረው ትመክራለች። እሷ በሚትሰሯቸው ሥራዎች ጎረቤቶቿ ልጆቻቸውን “እንዴ ሽልንጌ ሀገራችሁን ወደዱ!” እያሉ ይመክራሉ። ሽልንጌ አሁን ሀብታም ሆናም ሥራ አትመርጥም።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

የሚከተሉትንና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

1. በተረቱ ላይ ሽልንጌ ጎበዝ ሀገር ወዳድ ሴት የተባለችው ለምን ይመስላችኋል?
2. ሽልንጌ ምን ምን አይነት ስራዎች ስርታልች?
3. ከሰዎች ጋር ያላት ግንኙነት ምን አይነት ነው?

ለ. ደናሿ ጦጢት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- አቅጣጫ፣ ተፈጥሮአዊ አካባቢ፣ ሰው ሰራሽ አካባቢ፣ መደነስ፣ አቅጣጫ፣ ሀገር መውደድ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በጥያቄና መልሰ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አካባቢን የሚያሳይ ፎቶ፣ የጦጢት ስዕልና ወዘተ

ደናሿ ጦጢት

በድሮ ጊዜ አንድ ከሰው ጋር ተላምዳ የምትኖር ጦጢት ነበረች፡፡ መደነስ ትወዳለች፡፡ ሁል ጊዜ ወደ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮ አከባቢዎች በመሄድ ዳንሷን ትኮመኩማለች፡፡ ሌሎች እንስሳት ቆመው ይመለከቷታል፡፡ ሰኞ ወደ ተራራ ከወጣች ማክሰኞ ወንዝ አከባቢ ሄዳ ትደንሳለች፡፡ ረቡዕ ገበያ መሃል ትሄድና ገባያተኛውን ሁሉ በዳንሷ ታፈዛለች፡፡ ሀሙስ ደግሞ ወደ ትምህርት ቤት ሄዳ በእረፍት ሰዓት ተማሪዎችን ታዝናናለች፡፡ አርብ ዙረቷን ጨርሳ ጫካ ውስጥ ለመሰሎቿ ትደንሳለች፤ ስትደንስ ደግሞ ወደተለያዩ አቅጣጫዎች በእግሯ፣ በእጇ፣ በአንገቷ እያመላከተች በዚያ በኩል የምታያቸውን ቁሶች እየጠቆመች ሲሆን በብዛት ግን የምትደንሰው እጆቿን ወገቧ ላይ አድርጋ “ሀገሬን እወዳለሁ!... ሀገሬን እወዳለሁ!” እያለች ነበር፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

የሚከተሉትንና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

1. ጦጢቷ የምትደንሰው ዬት ዬት ሄዳ ነው?
2. እስቲ የጦጢቷን ዳንስ አብረን እንደንስ?
3. ጦጢት ስትደንስ በየትኛው የሰውነት ክፍሎቿ ነበር አቅጣጫን የጠቆመችው?

ተግባር 5፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. እየደነሱ ቁሶችን በርዝማኔ ማወዳደር (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- በቁመት ማወዳደር፣ ልዩነት፣ ባህላዊ ውዝዋዜ፣ መደነስ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥለው የቀረበውን የውጭ ጨዋታ ከታች በተዘረዘሩ የድርጊት ቅደም ተከተሎች መሰረት ያጫውቷቸው፡፡

* የተለያዩ ርዝማኔ ያላቸውን እንጨቶች ያዘጋጁ፤
* ህጻናት በተለመደው ስርዓት ወደ ውጭ ከውጡ በኋላ መጠነኛ የማሟሟቂያ የአካል እንቅስቃሴ ያሰሯቸው፤
* በመቀጠል የቀረቡላቸውን እንጨቶች በርዝማኔያቸው መሰረት እንድያወዳድሩ ማድረግ፤
* በእንጨቶቹ መካከል ያለውን ልዩነት እንድያወሩና ቤታቸው ካሉ ቁሳቁሶች ጋር በሃሳብ እንድያወዳድሩ ማበረታታት፤

* ቁሱን ያነሱበትና ያሳቀመጡበት አቅጣጫ በሰውነታቸው እንዲጠቁ ማድረግ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ባለቀለም/በአካባቢ የሚገኙ የተለያዩ መጠን ያላቸው እጃቸው ላይ ጉዳት የማያስከትሉ እንጨቶች፣ ሞንታርቦ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

የሚከተሉትንና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

1. የተጫወቱትን ጨዋታ መልሰው እንዲያብራሩ፣ በየትኛው የሰውነት ክፍል አቅጣጫን እንደጠቆሙና ምን አይነት ቁስ እንዳነሱ ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 6፡- በፕሮጀክት መማር

ሀ. ስለባህላዊ ቁሶች፣ ዳንሶችና ዘፈኖች መጠየቅና ማውራት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ባህላዊ ቁሳቁሶች፣ መልክም እሴቶች፣ ባህላዊ ዳንስ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ ስርቶ ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት ቤት ወላጆቻቸውን በመጠየቅ በአከባቢያቸው ስላሉ የባህል ቁሳቁሶች፣ የባህል ዳንሶችና ዘፈኖች፣ መልካም ስለሆኑ ባህላዊ ዕሴቶቻችን ክፍል ለጓደኞቻቸው እንድያወሩ ያበረታቷቸው፡፡ እያንዳንዱን ርዕስ ለአንድ አንድ ክፍለ ጊዜ በመመደብ ህጻናት አስቀድመው ቤት ጠይቀው እንዲመጡ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም ሲያቀርቡ ከቻሉ መገለጫዎችን (ፎቶና ስዕል) ይዘው በመምጣት ማቅረብ እንደሚችሉ ይንገሯቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከሚያቀርቡት ፕሮጀክት ስራ ጋር የሚሄዱ ስዕሎች እና ቁሶች እልባሳትና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ስለፕሮጀክታቸው አጠቃላይ ነገር ከሚያቀርቡት ተነስተው መጠየቅ

ተግባር 7፡- የመስክ ጉብኝት



ሀ. አከባቢን ማወቅ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የተፈጥሮአምንነት፣ የሰው ስራሽ ምንነት፣ ስዕል መሳል

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ህፃናቱን ቀጥሎ በተቀመጠው መመሪያ/ቅደም ተከተል መሰረት አድርገው ጉብኝቱን ያከናውኑ፡፡

• ሕጻናት አካባቢ ስለሚለው ጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፤

• በአካባቢ የተለያዩ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮች እንደሚገኙ በሚረዱት መጠን ማስገንዘብ፤

• ተፈጥሮአዊ ነገሮች የምንላቸው በተፈጥሮ የምናገኛቸው ሕይወት ያላቸውና የሌላቸው ነገሮች ሲሆኑ እጸዋት፣ ሰው፣ እንስሳት፣ ውሃ፣ አፈር፣ ድንጋይ፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ አየር፣ ነፋስ፣ ደመናን የሚያጠቃልል እንደሆነ ማስገንዘብ፤

• ሕጻናትን ጉብኝት በመውሰድ በአካባቢያቸው ስለሚገኙ ነገሮች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፤

• ከጉብኝት መልስ ስላዩዋቸው ነገሮች እንዲወያዩ ማድረግ፤

• እጸዋት በሚባለው ተፈጥሮአዊ ነገሮች ሥር ዛፎች፣ ሣሮች፣ ልዩ ልዩ ተክሎች፣ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬዎች እንደሚካተቱ ማሳወቅ፤

• በእንስሳት ሥር የቤት እንስሳት፣ የዱር እንስሳት፣ በራሪና ጥቃቅን ነፍሳት፣ አዕዋፍና የውሃ ውስጥ እንስሳት እንደሚካተቱ በማስገንዘብ በተገቢው መንገድ እንዲረዱ ማድረግ/ለምሳሌ የቤት እንስሳት ድመት፣ ውሻ... የዱር እንስሳት አንበሳ፣ ነብር፣ ጅብና ወዘተ

• ሰው ሰራሽ ነገሮች ቤት፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር እንደሆኑና ሌሎች በተመሳሳይ በአካባቢያቸው የሰው የሥራ ውጤት የሆኑትን ሕጻናት እንዲናገሩ ማበረታታት፤

• ክፍል ሲመለሱ ያዩትን አካባቢ በስዕል እንዲገልጹ ማድረግ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ነገሮችን የሚያሳይ ስዕልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

1. ሰው ሰራሽ የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

2. የተፈጥሮ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

* ህጻናት በጉብኝቱ ወቅት የሚፈለገውን ሁሉ ማድረጋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

የአውድ 3 ማጠቃለያ መመዘኛ ቼክ-ሊስት

የህጻኑ/ኗ ስም:_______________________ ጾታ: _______ ዕድሜ_______

ተ.ቁ	የሚጠበቀው የመማር ውጤት	ዝቅተኛ	መካከለኛ	ጥሩ	በጣም ጥሩ
1	ሆሄያት/ፊደላት እና የድምፃቸውን ቅላፄ መረዳት				
2	የሆያት ቤተሰብ ድምጽ እና ቅርፅ መለየት፣				
3	ሰዕሎች፣ሆሄያት እና ቀላል ቃላቶችን ማነበብ፣				
4	ከሌላ አቅጣጫ በመዞር አቅጣጫ መያዝ፣				
5	ከሁለት አማራጮጭን መለየትና ምርጫ ማድረግ፣				
6	እስከ 20 ድረሰ ያሉትን ቁጥሮች ወደፊት እና ወደኋላ መቁጠር፣				
7	ቀላል ንድፍ (ነጠላ ንድፎች) መረዳትና መፍጠር፣				
8	የጎደሉ ቁጥሮችን መለየት፣				
9	ከ5-7 የሚደርሱ የተለመዱ ጤናማ ምግቦች እና መጠጦች መለየት፣				
10	በመንቀሳቀሰ እና ሳይንቀሳቀሱ ትክክለኛ አፈጻጸም ክሎታቸውን ማሳየት፣				
11	በድምፅ ፍጥነት መሰረት እንቅስቃሴዎችን በመምረጥ ተግባራትን ማከናወን፣				
12	በአካባቢያቸው ያሉ ነገሮችን፣ ቁሳቁሶችን፣እንስሳትን፣ዕፅዋትን እና የታወቁ ህዝቦችን መመርመር እና መረዳት መቻል፣				
13	ቀላል ባህላዊ ጭፈራዎችን ማከናወን፣ ቀላል ዘፈኖችን መዘመር እና በግጥም መንቀሳቀሰ				
14	የተለመዱ ተረቶችን፣ በመዝሙር፣ በዳንሰና በድራማ መልክ ማከናወን				

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፦ ____

____

____

____

አውድ አራት፡- ህዋ

ለአውዱ የተሰጠ ጊዜ፡- 5 ሳምንት/150 ክ/ጊዜ

መግቢያ

ይህ አውድ ህዋ የተሰኘ ስያሜ ያለው ሲሆን እንደሌላው ጊዜ ሁሉ ስድስቱንም የመማር ዘርፎችን አቀናጅቶ ማስተማር ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። ለ5 ተከታታይ ሳምንታት የሚቆይ የትምህርት ይዘቶችን የያዘ ነው። በዚህ የመምህር መምሪያ ለእያንዳንዱ ሳምንት የተቀመጡ ስድስት ተግባራት ህዋ ቅኝት የቀርቡ ናቸው። ይህን አውድ ለማስተማር የምንጠቀምባቸው ዘዴዎችም ተረት፣ መዝሙር፣ ጨዋታ፣ የተግባር ሥራ፣ የፕሮጀክት ስራና ሌሎች ተግባራትን ከይዘቱ ጋር በማቀናጀት ነው።

የእድገትና የመማር ውጤቶች

ህጻናት ከዚህ አውድ ትምህርት በኋላ፡-

* በመጠን የተለያዩ ፊደላትን በቅርጻቸው ማመሳሰል መቻል
* ቅርጾችን መለየትና መስራት
* ፊደላትን እና ቁጥሮችን አየር ላይመጻፍ
* ፊደላት እና ቁጥሮችን በአሸዋ ላይ መሰራት
* መመሪያዎችን፣ ጥያቄዎችንና መግለጫዎችን አዳምጠው መፈጸም
* ፊደላትን ደጋግመው መጻፍ
* የግጭት መፍታት ባህልማዳበር
* ራስን የመንከባከብ ክህሎት ማዳበር
* የተለያዩ ምናባዊ ጨዋታ መጫዎት
* ቀለል ያሉ ተግባራትን ማቀድና ማከናወን መቻል
* ሁለት ቁጥሮችን እኩል ይሁናል ያንሳል ወይም ይበልጣል ምልክት ተጠቅመው ማወዳደር መቻል
* ቀላል ድርድሮችን ተገንዝበው መደርደር መቻል
* ልዩ ቀናትንና ዕለታዊ ክንውኖችን መለየት
* የሳምንት ቀናትንና የዓመት ወራትን መለየት
* ጤናማ ምግብና መጠጥ መምረጥ
* ወደተቃራኒ አቅጣጫ መንቀሳቀስና መሰመሮችን ደጋግመው ማሰመር መቻል
* ጎጂ ሁኔታዎችን፣ ደህንነቱ ያለተጠበቀን አከባቢ እና የደህንነት ምልክቶችን መለየት
* የገንዘብን ጥቅምና ዋጋ መገንዘብ
* የባህል ልብሶችን ድርድርና ቀለም መለየት

ሳምንት አስራ ሰባት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፡-

- መመሪያን በመከተል ስራን መሰራት ይችላሉ
- ፍላጎታቸውን በትህትና መግለጽይችላሉ
- ተግባራትን ያለጾታ ገደብ ያከናውናሉ
- የተለመዱ የሰውነት ክፍሎች ጥቅምይረዳሉ
- ያሉበትን ቦታና አካባቢያቸውን ያገናዘበ እንቅስቃሴዎችን ስርተውያሳያሉ
- ህትመትን በማየት የምስሎችን ስም ይረዳሉ
- እስከ 15 የሚደርሱ እቃዎችን ይቆጥራሉ
- ቁሶችን ቀለም መቀባትይችላሉ

ንዑስ ይዘቶች፡-

- ራስን ማስተዋወቅ
- ራስን መግለጽ
- ራስን ማወቅ
- የሰውነት ክፍሎች
- የቦታ ግንዛቤ
- የህትመት እውቀት
- ቁጥሮችን መቁጠር
- ጥበብን ማድነቅ

ተግባር 1፡- ውይይት

ሀ. የሰማይ ቁሶች መለየትና መቁጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ ምስሎች፣ የሰውነት ክፍል ጥቅም፣ ህትመት፣ ስም

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ቀጥሎ የቀረበውን የውይይት ርዕስ ከሰር ያለውን የድርጊት ቅደም ተከተል በመጠበቅ ያወያዩአቸው፡፡

• ውይይት ጊዜ ሁሉም ህጻናት ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት፡፡

• አስቀድሞ ህጻናቱን በቡድን መክፈል፣ ለየቡድኑ የተለያየ ስዕል/ ሞዴል መስጠት (ለአንዱ ቡድን የፀሃ፣ ለሌላው የጨረቃ፣ ለሎች የኮከብ...)

• ለሁሉም ቡድን የሚሰጡት መጠኑ 15 የሚደርሱ የጸሃይ፣ የጨረቃ፣ የኮከብ፣ የፕላኔት፣ ምስል የያዙ ሞዴሎች/ ፍላሽ ካርዶች መሆን አለባችሁ

• ህጻናቱ ሰዕሎቹን አይተው የት እንደሚገኙ፣ ምን እንደሚጠቅሙን ምን አይነት የተፈጥሮ ቀለም እንዳላቸው እንዲወያዩ ማድረግ እንዲቆጥሩና ፣በቃል ለቡድናቸው እንዲያብራሩ ማድረግ፡፡

• እርሶ በተለያዩ ቻርቶች ሞዴል በትልቁ የተሳሉ የፀሃ፣ የጨረቃ ፣የኮከብ እና የፕላኔት ሰዕል በማዘጋጀት ህጻናቱ ሊደርሱበት በሚችሉበት ቦታ ላይ በማስቀመጥ ህጻናቱ በቡድናቸው የተወያዩትን ስእሉን ተጠቅመው እንዲያቀርቡ ማድረግ

• እንዲሁም በቀጣይ ሰዕሉ/ሞዴሉ ላይ የሚያዩትን የሰማይ ቁሳቁሶች ሰም እንዲጠሩ ማድረግ ቁሶቹን እንዲመለከቱ ፣እንዲዳሰሱ ማድረግና ቁሶችን ለማወቅ የተረዱባቸውን የሰሜት ህዋሳት እንዲወያዩና እንዲናገሩ ማበረታታት፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፀሃይ፣ የጨረቃ፣ የኮከብ፣ የፕላኔት ሰዕልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን የሰማይ ቁሶችን ታውቃላችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ሁሉም ህጻናት የጨዋታው ተሳታፊ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 2፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ . የዳንስ ውድድር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- አካላት፣ ቁጥር፣ መመሪያ፣ ፆታ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

• ህፃናቱን ከክፍል ወደ ውጪ በማሰወጣት በቡድን መክፈል ከዚያም የዳንሰ ውድድር እንደሚያደርጉና በዳንሰ ውድድሩ ከምት የወጣ ከጨዋታ ውጪ እንደሚሆን ህግ መንገር፣

• በውድድሩ ህግ መሰረት የዳንሰ ውድድር እንዲያካሂዱ ማመቻቸትና ውድድሩን አሰራ አምሰት አሰራ አምሰት ልጆች በጋራ እየሆኑ እንዲሰሩ መምራት፡፡

• በዳንስ እንቅስቃሴያቸው ያሉበትን ቦታ እንዲገነዘቡና ስለ ቡድን አባላት ብዛት ቆጥረው እንዲናገሩ ማድረግ፣ ስለቦታው ያላቸውን ግንዛቤ ቀኝ፣ ግራ፣ ከፊት፣ ከኃላ፣ መሀል በማለት ለመደነስ የቆሙበትን አጠገባቸው ካለው ህጻን አንፃር እንዲናገሩ ማድረግ፣ ለመደነስ የተጠቀሟቸውን የሰውነት ክፍሎች ሰምና ጠቀሜታ እጅ-ለማጨብጨብ እያሉ እንዲናገሩ ማድረግ።

• በመጨረሻ የቁጥር ፍላሽ ካርድ በማሳየት ከቡድናቸው ጋር እንዲቆጥሩ ማድረግ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣ የሰውነት ክፍል ስዕልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* “ምን ምን የሰውነት ክፍሎችን ተጠቀማችሁ? የቡድን አባላቶቹ ብዛት ስንት ነበር?” ብለው ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት የጨዋታው ተሳታፊ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ለ. በቅርጽ ውስጥ መዝለል (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የሰውነት ክፍል ጥቅም፣ እንቅስቃሴ፣ ቦታን መገንዘብ፣ ጾታ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

 በቅድሚያ በመሬት ላይ በቾክ/በከሰል/በቀለም በአንድ ሜትር ርቀት የጂኦሜቲሪ ቅርጾችን (ሁለት ክብ፣ ሁለት ሶስት ጎን፣ ሁለት ኣራት ማዕዘን) ይሰሩ። ሰርተው ያዘጋጁት ቅርጽ ግን ሁለት ህጻናትን መያዝ የሚችል እንጂ በጣምም ያልሰፋ በጣምም ያላነሰ መሆን ይኖርበታል።

 ቀጥሎ በየቅርጹ አንድ ወንድና ሴት ህፃናትን የመጀመሪያ ተወዳዳሪዎችን መርጠው ያስገቡ እና ሁሉም የሚያውቁትን ምት ያለው መዝሙር መክፈትና በቅርጹ ውስጥ ሆነው ከቅርፁ ሳይወጡ ሁለት ሁለት ተያይዘው እንዲደንሱ ማድረግ።

 ቀጥሎ በቅርጹ ውስጥ መሮጥ፣ ቁጭ ብድግ ማለት ... እንዲሰሩ ማድረግ

 ከቅርጹ የወጣ፣ ከጓደኛው ጋር የተላቀቀአቁሙ ሳይባል ያቆመ ከጨዋታው ይወጣል ማለት ነው ስለዚህ ከሶስቱ ቡድን እስከ ተፈቀደው ሰዓት መመሪያውን ተከትሎ የቆየ አሸናፊ ይሆናል ማለት ነው።

 በዚህ መሰረት ሁሉንም ህፃናት ተራ በተራ ያሉበትን ሁኔታና ቦታ እያገናዘቡ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ቴፕ/ሞባይል፣ ጂፓስ፣ ሞንታርቦ፣ ቾክ፣ ቀለም

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የሚከተሉትንና ሌሎች ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

1. ምን አይነት እንቅስቃሴ አደረክ/ሽ?
2. በየትኛው የሰውነት ክፍልሽ/ህ ተንቀሳቀስክ/ሽ?

ተግባር 3፡- መዝሙር

ሀ. ቢራቢሮ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፍላጎት፣ አካላት፣ እንቅስቃሴ፣ ማድነቅ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቢራቢሮ ምስል የያዘቻርት፣ የሰውነት ክፍልሞዴል/ምስል የያዘ ካርድ፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ

መዝሙር 1፡- ቢራቢሮ

በአየር በሰማይ ስትበሪ ላየሽ
ውቧ ቢራቢሮ በጣም ታምሪያልሽ) 2x
መልክሽ ቡራቡሬ ቀለምሽ ቢጫ አለው
ክንፎችሽ ያምራሉ ውበትሽ ለዛ አለው
ቀለምሽ ልዩ ነው ነጭና ቡናማ
እንደስታለን ስናይሽ እኛማ
ዥንጉርጉሩ መልክሽ ልዩ ሰበት አለው
ክንፎችሽን ልይዝ እከተልሻለሁ
በአየር በሰማይ ስትበሪ ላየሽ
ውቧ ቢራቢሮ በጣም ታምሪያለሽ 2x

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡- ቢራቢሮ ምን ዓይነት ቀለማት አሏት?

ለ. የሰማይ ኮከብ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁጥር፣ ሰም፣ ማድነቅ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

መምህር ህጻናት ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው በማዘመር እየተዝናኑ እንዲማሩ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ የኮከቦች ሰዕልና ወዘተ

መዝሙር 2:- የሰማይ ኮከብ

የሰማይ ኮከቦች እጅግ ታምራላችሁ
ውበታችሁ ደምቆ ትታዩናላችሁ
ኑ ልጆች በአንድ ላይ እንሰብሰብና
ኮከብን እንቁጠር እንመልከትና
1 2 3 4 በጣም ትንሽ ኮከብ
5 6 7 ብርሃናማ ኮከብ
8 9 10 ትልልቅ ኮከቦች
11 12 13 አንጸባራቂዎች
14 15 በጣም ብዙ ናቸው
በሰማዩ ላይ ደምቋል እዩት ውበታቸው 2x

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡- ኮከቦች የት ይገኛሉ?

ስንት ኮከብ ቆጠራችሁ?

ተግባር 4፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ምናባዊ ጉብኝት (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ አካላት፣ ፍላጎት

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ይህ ተግባር ህጻናት ወደ ህዋ ደርሰው እንዲመለሱ የሚያደርግ ምናባዊ ጨዋታ ነው፡፡ይህን ምናባዊ ጨዋታ ለማጫወት ገላጭ የሆነ ምስልና ትረካ ቀድመው ማዘጋጀት ይኖርብዎታል፡፡ከዛም ልጆቹ አይናቸውን እንዲጨፍኑ በማድረግ ትረካውን ይንገሯቸው፡፡

ምሳሌ:-ልጆችዬ ሁላችንም አይናችን እንጨፍን፣ ጎበዞች፣ አሁን ከእኔ ጋር እጃችንን ወደጎን ዘርግተን እየበረርን ወደ ሰማይ አብረን እንሄዳለን፤ እየተከተላችሁኝ ነው አይደል? ጎበዞችዋ..ው.. ሰማዩን አያችሁት? እጃችሁን ዘርጉና ንኩት ፀሀይንስ አያችኋት? እኔ የጸሃይዋን ሙቀት አልቻልኩትም! አረረ እጄን አቃጠለችኝ:: አሁን እየመሸ ስለሆነ ጸሃይ እየጠለቀች ነው:: ዋ..ው.. ጨረቃ ወጣች፣ ኦ..ኦ.. ኮከቦች ደግሞ እንዴት ያብረቀርቃሉ? አሁን ያላችሁበት ቦታ ሆናችሁ ጨረቃንና ከዋክብትን እየነካችሁ መጫዎት ትችላላችሁ፡፡

እሰኪ ኮከቦቹን እንቁጠራቸው 1 2 3 ......15 በማለት ለትንሽ ደቂቃ አይናቸውን እንደጨፈኑ በምናባቸው እንዲቃኙ እድል መስጠትና ሁሉም አይናቸውን እንዲገልጡ ማድረግ፡፡

• ልጆች በምናባቸው ወደ ሰማይ ሄደው እዚያ ስላዩአቸው ቁሶች እንዲያወሩ በማድረግ በሚያወሩበት ጊዜ ምን እንዳስደሰታቸውና ፍላጎታቸው ምን እንደነበረ በትህትና እንዲናገሩ ማበረታታት፤ ስንት ኮከቦችን እንደቆጠሩ፣ በምናባቸው ኮከቦቹን እንደ ተመለከቱና እንዲዳስሱ እንዲናገሩ ማበረታታት፤

• እርስ በርስ እንዲዳማመጡና ወደ ሃሳባቸው እንዲመለሱ በማድረግ እዚያ ስለነበራቸው አካላዊ እንቅስቃሴና ስለሰሯቸው ሥራዎች እንዲናገሩ ማበረታታት፤

• በመጨረሻም በምናባቸው ያዩትን በሰዕል እንዲስሉ እርሳስ፣ ወረቀት/ደብተር፣ ቀለም መስጠትና ያዩትን ቀለም ቀብተው ለክፍል ጓደኞቻቸው በትህትና እያሳዩ ገለፃ ያርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እርሳስ፣ ቀለም፣ ወረቀት ወይም መለማመጃ ደብተርና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* “በምናባቹ ምን ምን ነገሮችን ጎበኛችሁ?፤ በጉብኝቱ ወቅት የእናንተ ፍላጎት ምን ነበር?፤ ስንት ኮከብችን ቆጠራችሁ?” በማለት ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 5፦ በሥራ መማር

ሀ. ቀለም መቀባት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ ማቅለም፣ ተግባራት፣ ስም

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

• በቅድሚያ ሰማይ ላይ የሚገኙ ቁሶችን (ጸሃይ፣ ጨረቃ፣ ዳመና፣ ኮከብ) የሚያሳይ ትልቅና ከለር የተቀባ ስዕል ግድግዳ ላይ ይሰቀሉላቸው፡፡

• ለእነሱ ደግሞ በነጠብጣብ የተሰሩ ጸሃይ፣ ጨረቃ፣ ዳመና፣ ኮከብ በወረቀት አዘጋጅተው ይሰጧቸው፡፡

• ስዕሉን እያዩ በወረቀት/ደብተር ላይ ያሉትን ያልተቀቡ ስዕሎች እንዲያደምቁ ያግዟቸው፡፡

• ስዕሎቹን እያዩ የመረጡትን በወረቀት ላይ ስለው የተፈጥሮ ቀለማቸውን አስመስለው እንዲቀቡ ያድርጉ፡፡

• ሲጨርሱ የሰሩትን ስዕል ለክፍል ጓደኞቻቸው በማሳየት ስለስዕሎቻቸው እየተነሱ እንዲያወሩ ስለ ስራዎቻቸው አድናቆት እነዲገላለጹ እድል ይስጧቸው፡፡

• በክፍሉ ውስጥ ህፃናቱ በፍላጎታቸው ከሰሯቸው የሰማይ ቁሳቁሶች ውስጥ ስንት ኮከብ ፣ ስንት ጨረቃ፣ ስንት ፀሃይ … እንደተሳለ እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡

• በመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ …….. ላይ ያሉትን ያልተቀቡ የሰማይ ቁሶች ስዕል ከለር እንዲቀቡ ያመቻቹ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የኮከብ፣ የጨረቃ፣ የፀሀይ፣ የዳመና ምስል፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ወረቀት፣ መለማመጃ ደብተርንአ ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* “ምን ምን ነገሮችን አቀለማቸሁ?፣ ካቀለማችሁት ውስጥ የቱን አደነቃችሁ?” በማለት ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ወቅት በትክክል ተሳታፊ መሆናቸውን ዞረው በመመልከት ያረጋግጡ፡፡

ለ. ቁስ መቁጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ ማተም፣ ተግባራት፣ ስም፣ መመሪያ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱን ቀጥሎ የቀረበውን ተግባር ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ ያሰሯቸው፡፡

• ክፍል ውስጥ ካሉት ማእዘናት የተለያዩ ትናንሽ ቁሳቁሶችን የሚፈልጉትን ቁስ በትህትና ገልጸው አስቀድመው ይዘው እንዲመጡ ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ፡- ቅጠል፣ ቁልፍ፣ የኮከብ ስዕል፣ የሀይላንድ ክዳን፣ ቆርኪ፣ የመሳሰሉትን ይዘው ወደ ጠረጴዛቸው ይውሰዱ::

• ከዚያም የተሰጣቸውን ቁሶች እስከ አስራ አምስት እንዲቆጥሩ ያድርጉ፤ ሲሰሩም ሆነ ሲንቀሳቀሱ ያሉበትን ቦታ ክፍል ውስጥ መሆንን አውቀው እንዲንቀሳቀሱ ይግለፁላቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የኮከብ ቅርፅ፣ ቆርኪ፣ የሃይላንድ ክዳን፣ ቁልፍ፣ ቅጠል፣ ደብተር፣ የውሃ ቀለም

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* "ስንት ቁሶችን ቆጠራችሁ?፣ ከቁሶቹ ውስጥ የቱን መረጣችሁ?" በማለት ይጠይቋቸው።

* ህጻናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ወቅት በትክክል ተሳታፊ መሆናቸውን ዞረው በመመልከት ያረጋግጡ።

ተግባር 6፡- ተረት

ሀ. ለምለም (4 ክፍለ ጊዜ)

***ቁልፍ ቃላት*፡-** ማቅለም፣ አካላት፣ ፍላጎት

***የማስተማሪያ ዜዴ*፡-** በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

***የመምህር ሚና*፡-**

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የአካል ክፍሎች ምስል/ሞዴል፣ ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ሲማሩ የሚያሳይ ፎቶ

ለምለም

በአንድ ትንሽዬ መንደር የምትኖር ለምለም የምትባል ልጅ ነበረች። ስዕል መሳል እና ማቅለም በጣም ትወዳለች። በክፍል ውስጥ አስተማሪዋን በጥሞና ታዳምጣለች፣ አንድ ነገር ስትፈልግ ይቅርታ በመጠቄ ነው ለምሳሌ መፀዳጃ ቤት መሄድ ስትፈልግ እንኳን ይቅርታ መምህር ወደ መጸዳጃ ቤት መሄድ እችላለሁ ብላ በትህትና መጠየቅ ትወዳለች። ከዕለታት አንድ ቀን አስተማርዋ የሰውነት ክፍሎችዋን ጥቅም እንድትናገር ጠየቀቻት። እሷም ቶሎ ብላ እጆቼ ለመዳሰስ፣ ዓይኖቼ ለማየትና ጆሮዎቼ ለመስማት ይጠቅሙኛል አለች። ትንሽ ቆይታ እህህ ምላሴ ለመቅመስ፣ እግሮቼ ለመሄድና አፍንጫዬ ለማሽተት ይጠቅመኛል ብላ መለሰችላት፡ ፡ አስተማሪዋም በጣም ጎበዝ ልጅ አጨብጭቡላት ብላ ለጓደኞቿ አስጨበጨበችላት። ከዚያም መምህራቸው ሁሉም ልጆች ልክ እንደለምለም እንዲናገሩ እድል ሰጠቻቸው ልጆቹም ለምል እንዳለችው እያሉ የሰውነት ክፍሎቻቸውን ጥቅም ዘረዘሩ በልጆቹ የተደሰተችው መምህርም ለሁሉም ህፃናት እርሳስ፣ ወረቀትና ቀለም በመስጠት የሰውነት ክፍሎቻቸውን እንዲስሉ ፈቀደችላቸው የለምለም ስዕልም ከክፍሉ አንደኛ ስዕል ሆነ።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

1. "ለምለም ምን ትወድ ነበር?፣ ለምለም መጸዳጃ ቤት መሄድ ስትፈልግ ምን ብላ ታስፈቅድ ነበር?" በማለት ይጠይቋቸው።

ሳምንት አስራ ስምንት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ፦

- ስሜታቸውን በመቆጣጠር የሌሎችን ስሜት ያከብራሉ
- የሰሙት ድምጽ የምን እንደሆነ ይናገራሉ
- የሰሙትንየድምጽቃናደግመውያሰማሉ
- ራሳቸውንና አካባቢያቸውን መንከባከብ ይጀምራሉ
- የጊዜን ጽን ስህሳብ ይረዳሉ
- ማህበራዊግንኙነትንያዳብራሉ
- ቁሶችን እንደ ባህሪያቸው ለይተው ይደረድራሉ
- የሰሙትን ታሪክ ደግመው ይናገራሉ
- እስከ 15 ቁጥሮችን ይጽፋሉሰ
- ትናንሽ ጡንቻዎቻቸውን ይቆጣጠራሉ
- የተለያዩ መዝሙሮችን በመዘመር ይጨፍራሉ

ንዑስ ይዘቶች፦

- ራስንመግዛት
- የድምጾችን ተመሳሳይነትና ልዩነት መለየት
- ራስንና አካባቢን መንከባከብ
- ማህበራዊ ግንዛቤ
- የፈጠራ አገላለጽ
- የጥቃቅን ጡንቻዎች መዳበር
- ጊዜ
- መደርደርና መመደብ
- ማንበብ
- ቁጥሮችን መጻፍ

ተግባር 1፡- መዝሙር

ሀ. ጨረቃ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ጊዜ፣ ግንኙነት፣ መጨፈር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የፀሃይና የጨረቃ ምስል፣
* የሰዓት ሞዴል፣
* ስለቀንና ለሌት የሚያሳይ ስዕልና ወዘተ

መዝሙር 1፡- ጨረቃ

ጠዋት በማለዳ ከእንቅልፌ ስነቃ፤
ፀሀይዋ ብቅ አለች ብርሃን ፈንጥቃ፤
ልጆች በአንድነት በጋራ ሁላችን፤
እንጨፍር እንዝለል በውብ ባህላችን፤
ፀሃይዋ ስትገባ መሽቶ ከጓዳዋ፣
ጨረቃ ተተካች ምሽት በተራዋ፡፡
የጨለማን ግዝፈት በብርሃን ስብራ
ድምቅ አለችልን ብርሃንዋ በራ፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ፀሀይ መቼ ትወጣለች?፣ ጨረቃ መቼ ትወጣለች?

ለ. ወፊቷ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ጊዜ፣ ድምፅ፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዘዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መዝሙር የአዘማመር ስርዓቱን ጠብቀው ያዘምሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፀሃይና የጨረቃ ምስል፣ የሰዓት ሞዴል፣ ሰለቀንና ለሌት የሚያሳይ ሰዕልንአ ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። ለምሳሌ፡- ወፊቷ መቼ ጮኸች?፣ እስኪ የወፍ ድምጽ አሰሙኝ?

ተግባር 2፡- በሥራ መማር

ሀ. ቁጥር መቅረጽ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መደርደር፣ ጡንቻ መዳበር፣ አከባቢ

የማስተማሪያ ዘዴ:- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

• ቁጥሮችን በወረቀት ላይ መንደፍና የተነደፈውን ቁጥር ቅርፃቸውን ጠብቀው እንዲያወጡት ማድረግ፤

• ቆርጠው ካወጡት በኃላ ቁጥሩን በቅደም ተከተል እየደረደሩ ለክፍሉ ህጻናት እንዲያሳዩ ማድረግ፤

• የሰሩበትን የተቆራረጡ ወረቀቶች በጋራ በመሆን በማጽዳት ቆሻሻውን በቆሻሻ መጣያ ውስጥ መክተት፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ወረቀት፣ መቀስ፣ በፕላስቲክ ተፅፎ የተዘጋጀ ቁጥር፣ የፅዳት ዕቃዎች፣ ጠረጴዛና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* “ስንት ቁጥሮችን ቀረጻችሁ?፣ ስርተን ስንጨርስ አከባቢያችንን ምን ማድረግ አለብን?፣ የመጀመሪያው ቁጥር ማነው?” እና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ወቅት በትክክል ተሳታፊ መሆናቸውን ዞረው በመመልከት ያረጋግጡ።

ለ. ቁሶችን መለየትና መመደብ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መደርደር፣ ድምጽ፣ ቁጥር፣ ጡንቻዎች

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

• ለህጻናቱ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመቀላቀል ይስጧቸው። ለምሳሌ፡- ቆርኪ፣ የሀይላንድ ክዳን፣ የእንስሳት ምስል፣ የመኪና ምስል፣ የአውሮፕላን ምስል፣ የስማይ ቁሳቁስ ምስልና ወዘተ

• የተሰጣቸውን ቁሶች በዓይነታቸው በመለየት እንዲደረድሩ ያድርጉ፤

• ከዚያም ከደረደሩት መካከል ድምፅ ያላቸውን በማንሳት ምስሉን ሲያሳዩ እርስዎ በመቅረፀ ድምጽ ያዘጋጁትን ድምፅ ያሰማቸውና እነሱም የሰሙትን ድምጽ በማሰመሰል እንዲሉ ያድርጉ፤

• ድምጽ በሌላቸው በሀይላንድ ክዳንና በቆርኪ በመጠቀም ጠረጴዛቸው ላይ በመደርደር ከ1-15 ካሉት ቁጥሮች ውስጥ የፈለጉትን ቅርፁን ጠብቀው እንዲሰሩ ያድርጉ፤ የሰራትን ቁጥር እንዲናገሩም ያድርጉ።

• በደብተራቸው ገፅ ---- ላይ ያለውን ከ1-5 ቁጥሮችን ደግመው እንዲጽፉ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቁጥር ካርድ፣ ቆርኪ፣ የሀይላንድ ክዳን፣ የእንስሳት ምስል፣ የመኪና ምስል፣ የአውሮፕላንና የስማይ ቁሳቁስ ምስልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ስንት ቁጥሮችን ቀረጻችሁ?፣ የመኪና ድምጽ አሰሙኝ?፣ ይህ ድምፅ የምን ድምጽ ነው? እና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናቱ ተግባሩን በሚያከናውኑበት ወቅት በትክክል ተሳታፊ መሆናቸውን ዞረው በመመልከት ያረጋግጡ።

ተግባር 3፡- ተረት

ሀ. ብልኋ ሜላት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መለየት፣ አካባቢ፣ ስሜት፣ ንግግር

የማስተማሪያ ዜዴ:- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ስሜትን የሚገልፁ ምስል፣ ምሰር፣ ባቄላና ወዘተ

ብልኋ ሜላት

ከእለታት አንድ ቀን ሜላት የምትባል የሰባት ዓመት ልጅ ነበረች፡፡ እናትና አባቷን በጣም ትወዳለች፡፡ እናቷን በምትችለው ሁሉ በሰራ ታግዛታለች፡፡ አንድ ቀን እናቷ ወጥ ለመሰራት ምሰር ስትለቅም ምሰሩ ከእጇ አመለጣትና ከሰር ተቀምጦ ከነበረው ባቄላ ከያዘው ሰሀን ውስጥ ገብቶ ተደባለቀ፡፡ የሜላት እናት በጣም ተናደደች፡፡ ሜላትም ወደ እናቷ በመቅረብ “አይዞሽ እናቴ! እኔ አግዝሽና እንለቅመዋለን በማለት እናቷን አረጋጋቻት፡፡” ከዚያም ከእናቷ ጋር በመሆን ባቄላውን ለቅመው ጨረሱ፡፡ “የኔ ልጅ ስላገሽኝና ስላረጋጋሽኝ አመሰግናለው”! አለቻት፡፡ ሜላትም “እናቴ አንቺ እንድትናደጂ አልፈልግም እሺ!” አለቻት እና ሳመቻት፡፡ ከዚያ እንቷ ሽንኩርት ስልጡና ምሰር ሲለቅሙ የወደቀውን ትንሽ መጥረጊያ በማምጣት ቦታውን በማጽዳት እናቷ አገዘቻት፡፡ ሲጨርሱ “ጎበዝ የኔ ልጅ! ጡንቻዎችሽ በጣም ስለዳበሩ ስትሰሪ በጣም በጥንቃቄ ነው” አዎን እማዬ! ትምህርት ቤት የተለያዩ ቁሶችን እያነሳን እየደረደርን ስለምንጫወት እኮ ነው” በማለት አሁን እጅሽን በሳሙና ታጠቢ በማለት ውሃ ስጠቻት፡፡ ሜላትም እጇን ታጥባ የተሰራውን ምሰር ከወላጆቿ ጋር ትእመገቡ፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* “የሜላት እናት ስትናደድ ምን አደረገች?፣ ሜላት እናቷንን በምን አገዘቻት?” በማለት ይጠይቋቸው፡፡

ለ. አሰተዋዩ አብዲ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ግንኙነት፣ አካባቢ፣ ጊዜ፣ ንግግር፣ ማህበራዊ ግንኙነት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ልጆች በጋራ ጽዳት ሲያጸዱ የሚያሳይ ምሰል፣ ቡና ሲጠጡ የሚያሳይ ምሰልና ወዘተ

አስተዋዩ አብዲ

ከረጅም ጊዜ በፊት በአንድ መንደር የተወለዱ አብዲ እና ሮዛ የሚባሉ ልጆች ነበሩ። አብዲ ሰኔ 2/2012 ዓ.ም ጠዋት ተወለደ፤ ሮዛ ደግሞ ሰኔ 20/2012 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ተወለደች። ሁለቱም እኩዮች ሲሆኑ አምስት አመታቸው ነው። አብረው ይጫወታሉ፤ አንድ ትምህርት ቤት ይማራሉ። ቤተሰቦቻቸውም በጣም የሚከባበሩና የሚቀራረቡ ናቸው። ከእለታት አንድ ቀን የአብዲ እናት ቡና አፍልታ አብዲን ሄዶ የሮዛን እናት እንዲጠራ ላከችው። እሱም የእናቱን መልዕክት ለማድረስ በፍጥነት ሄዶ የነሮዛን በር ሲያንኳኳ ተከፍቶለት ወደውስጥ እንደገባ በግቢው የተቆራረጠ ቅጠልና ወረቀት ተመለከተ። ሮዛም ሌላ ቅጠል እንጀራ እያለች ስትቆራርጥ አያት። አብዲም ጓደኛው ሮዛን ሰላም ካላት በኃላ “ምነው ሮዛ ግቢያችሁን በቅጠልና በወረቀት አበላሸሽው? አሁን ተጫውተሽ ከጨረሽ በይ ላግዝሽና ግቢውን እናፀዳው” አላት። እሷም “እሺ! እናጽዳው” አለችውና የያዘችውን ቅጠል ወደቆሻሻ መጣያ ውስጥ ጣለችውና መጥረጊያ ልታመጣ ስትሄድ አብዲም ለሮዛ እናት “እናቴ ቡና ጠጡ ብላለች፤ እኔ ሮዛን ግቢውን በማጽዳት ላግዛትና እመጣለሁ” አለ። የሮዛ እናትም “ተባረክ የኔ ልጅ! ሁሌ ስትጫዎት እንደዚህ ነው የምታደርገው አለችው?” ሮዛም “ይቅርታ እናቴ ከዚህ በኋላ አንድ ቦታ ሆኜ እጫወታለሁ” በማለት ከአብዲ ጋር ተጋግዘው ግቢውን አጸዱ ይባላል።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ከተረቱ ምን እንማራለንና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 4፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ድምጽ ማስመሰል (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ማህበራዊ፣ ጊዜ፣ ድምፅ፣ አካባቢ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ህጻናት የተለያዩ እንስሳት ድምጽ እያስመሰሉ እንዲጫወቱ ለማድረግ ይሞክሩ።

* በቅድሚያ እርስዎ የተወሰኑ እንስሳት ድምጽ አስመስለው ያስሟቸው።

* በመቀጠል ህጻናት የመረጡት እንስሳ ድምጽ እንዲያስመስሉ ያድርጓቸው።

* ሁሉም ህጻናት የጨዋታው ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የድመት፣ ዶሮ፣ ውሻ፣ ጅብ፣ አህያ፣ ፍየል፣ ላምና በግ ምስልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* የምን የምን ድምጽ ሰማችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለ. እንቆቅልሽ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- አካባቢ፣ ጊዜ፣ ድምፅ፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ይህንን ጨዋታ የእንቆቅልሽ አጨዋወት ሥርዓትን ጠብቀው ያጫውቷቸው፡፡

* በቅድሚያ የተለያዩ ሰዕሎችን ያስመልክቷቸው፡፡

* ቀጥለው ሰለውሻ፣ አንበሳ፣ ጨረቃ፣ ወፍ፣ ጠዋትና ማታ፣ ሌሊት፣ ቁጥርና ንቦች እንቆቅልሽ ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፦ ዝንብ እመስላለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ አእባ ላይ እኖራለሁ፡፡ ለሰዎች ማር እሰጣለሁኝ፡ እኔ ማን ነኝ?

መልሱ፦ ንብ

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የውሻ፣ ጨረቃ፣ ወፍ፣ ጠዋትና ማታ፣ አንበሳ፣ ሌሊት፣ ቁጥርና ንቦች ሰዕልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* አንበሳ ለምግብ ፍለጋ መች መች ይወጣልና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 5፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. የሰሙትን መልዕክት ማስተላለፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሰሜት፣ ድምፅ፣ ጊዜ፣ አካባቢ፣ ንግግር፣ ቁጥር ፣ መዝሙር እና ዳንሰ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

• ህፃናቱን ወደደጅ በማሰወጣት አምሰት አምሰት አድርገው ይመድባቸው፡፡

• ከየቡድኑ መጀመሪያ ለተሰለፉት ህጻናት የሚከተለውን መልዕክት በጆሮቸው መልዕክት መንገር ለምሳሌ (ጠዋት መንገድ ላይ መኪናዎቹ ጺጺጺ ሲሉሰማሁ፣ ጓደኛችን ሰለተናደደ እኛ እንታገሰ፣ ምግቤን በሰርአት መመገብ ችያለሁ፣ የኛ ሰፈር ሰዎች ቅዳሜ ቅዳሜ ጽዳት ያጸዳሉ…) እና ሌሎችን ለየቡድኑ እየቀያየሩ ማሰራት፤

• የቡድኑ አባላት በተወሰነ ርቀት አሰልፈው ካቆሙ በኋላ ይህንን መልዕክት የመጀመሪያው ልጅ ለቀጣዩ እንዲነግር እንዲህ እያሉ መጨረሻ ላይ የተነገረው ህጻን ከየቡድኑ ለእርሰዎ እንዲነግርዎት ያድርጉ፤

• በመጨረሻም መልዕክቱን በትክክል ላሰተላለፈው ቡድን ያሰጨብጨቡና መልዕክቱን በጋራ ይንገራቸውና የአሸዋሳጥን በመጠቀም እሰከ አሰራ አምሰት ቁጥር ድረሰ በአሸዋው ላይ እንጽፉ እድል ይሰጣቸው፡፡

• ሁሉም ሲጨርሱ በሚያውቁት መዝሙር እየዘመሩ የተለያዩ እንቅሰቃሴዎችን እንዲያደርጉ ያድርጓቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የአሸዋ ሳጥን፣ መዝሙር፣ ቴፕ፣ ሞንታርቦ/ጂፓስ/ስልክ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* የተነገራችሁ መልዕክት ምን ነበር?፣ ስንት ቁጥርን ፃፋችሁ? እና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት የጨዋታው ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 6፡- ውይይት

ሀ. ስለአከባቢ እንክብካቤ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ማህበራዊ፣ ስሜት፣ አካባቢ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* በቅድሚያ አንድ የሚያውቁትን ታሪክ ያውሩላቸው።

* በመቀጠል በእርስዎ አከባቢ ሰዎች ዙሪያቸውን የምንከባከቡበትን ሁኔታ ይንገሯቸው።

* ህጻናት ተራ በተራ እጅ እያነሱ ከዚህ በፊት ስለሰሟቸው ታሪኮች እንዲያወሩና በአከባቢያቸው ሰዎች ዙሪያቸውን የምንከባከቡበትን ሁኔታ እንዲናገሩ ያድርጓቸው።

* ሁሉም ህጻናት ሀሳባቸውን በትክክ መግለጽ እንኪችሉ ድረስ ውይይቱን በጥያቄና መልስ ያስቀጥሉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከውይይቱ ርዕስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስዕሎችና ሌሎች ቁሳቁሶች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* የሚከተሉትን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

1. እናንተ አካባቢያችሁን እንዴት ታፀዳላችሁ?
2. በጽዳት ጊዜ ምን በማድረግ ታግዛላችሁ?
3. ምን አይነት ታሪክ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?

* ሁሉም ህጻናት የውይይቱ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ሳምንት አስራ ዘጠኝ

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- በተግባራቶቻቸው ሀላፊነት ያሳያሉ
- ከ4-6 የሚደርሱ እንቅስቃሴያዊ ተግባራትን ያሳያሉ
- ከ5-7 የሚደርሱ ጤና ማምግቦችንና መጠጦችን ይለያሉ
- የጎጂ ሁኔታዎችን መነሻ ይለያሉ
- የቁሶችን አቀማመጥ ይናገራሉ
- ቁሶችን ያቀልማሉ፤ ይለጣጥፋሉ
- የራሳቸውን ደህንነት ይጠብቃሉ
- እስከ 15 ያሉቁጥሮችን ወደ ፊትና ወደ ኋላ ይቆጥራሉ
- የተሰጡ ፊደላትን ደጋግመው ይጽፋሉ
- የባህላዊ አልባሳት ጥለት አቀማመጥ ይለያሉ፤ ያቀልማሉ

ንዑስ ይዘቶች:-

o ሀላፊነትና የራስ ምርጫ

o የትልልቅ ጡንቻዎች መዳበርና ዕድገት

o አመጋገብ

o ደህንነትና ጥበቃ

o የቃላት እውቀት

o ውበትን መገንዘብ

o ቁጥርና ቆጠራ

o ፊደላትን ደጋግመው መጻፍ

o ቀለማት

ተግባር 1፡- መዝሙር

ሀ. ጨረቃ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - የቁስ አቀማመጥ፣ ደህንነት፣ መጠጥ፣ ምግብ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የምግብና የመጠጥ ምስል፣ ቪድዮ፣ የቁሶችን አቀማመጥ የሚያሳይ ምስልንእ ወዘተ

መዝሙር 1፡- እኔ ጠንካራ ልጅ ነኝ

እኔ ጠንካራ ልጅ ነኝ ሁሉም ሰው የሚወደኝ
ጤናማ ምግብ መመገብ ጤና ነው የሚሰጠኝ
አንድ - ሙዝ ሁለት - ፓፓያ ተቀምጧል ጠረጴዘው ጋ
ሶስት- እተር አራት ስጋ ወደምግቡ ልበል ጠጋ
አምስት- ውሃ ስድስት- ወተት እየጠጣሁ ልደሰት
ሰባት ጁስ አለ ፍርጅ ውስጥ እስንም ላድርገው ጥጥት
እኔ ራሴን እጠብቃለው
የተመጣጠነ ምግብ በላለሁ
ስለዚህ አድጊያለሁ
ጠንካረ ልጅም ሆኘለሁ፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ለማደግ ምን ማድረግ አለብን?፣ እኛን የሚመግበን ማነው?

ለ. ኑ በጋራ እንጨፍር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - አቀማመጥ፣ ቆጠራ፣ ደህንነት፣ እንቅስቃሴ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መዝሙር የአዘማመር ስርዓቱን ጠብቀው ያዘምሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

የቁጥር ካርድ፣ የከዋክብት፣ የፀሀይ ምስል/ሞዴልና ወዘተ



ምዘና:- የቃል ጥያቄ

ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። ለምሳሌ:- ምን ምን አቅጣጫዎችን አሳየን?

ተግባር 2:- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ምግብና መጠጥ መምረጥ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት:- ሀላፊነት፣ ደህንነት፣ ምግብ፣ መጠጥ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱን ቀጥሎ የቀረበውን ጨዋታ ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ ያጫውታቸው፡፡፡

• የጨዋታው አካሄድ ህጻናትን ታላቅ እህት እና ታናሽ ወንድም ወይም ታላቅ ወንድምና ታናሽ እህት በማድረግ መሰየምና ታላቅ ታናሽን ምግብ እንዲመግብ የሚያደርግ የመሰሎ ጨዋታ ማጨዎት ነው፡፡

• ታላቅ የሆነው/ችው ልጅ የታናሹን ህጻን የምግብና የሚጠጣ ነገር ምርጫ መጠየቅና ያንን ምግብ አስመሰሎ መሰራትና ማቅረብ፤

ምሳሌ፡-

ልጅ፡- ምግብ ስጪኝ እህቴ!

እህት፡- እሺ ምን ልስጥህ ምን ትበላለህ?

ልጅ፡- ፓስታ መብላት እፈልጋለው፡፡

እህት፡- የሚጠጣስ?

ልጅ፡- ውሃ እፈልጋለሁ፡፡

እህት፡- እሺ! አሁን እሰራለሁ አንተም/አንቺም ነይ እያገዝሽኝ አብረን እንሰራለን፡፡

ልጅ፡- እሺ እህቴ/ወንድሜ! እኔም መለማመድ እፈልጋለሁ፡፡

እህትን ወንድም ፡- ምግቡን ይሰራሉ፡፡

እህት‹- ይሄው ወንድሜ/እህቴ! በሹካ ብላ/ብይ፡፡ ነገር ግን ሹካው አፍህን/ሽን እንዳይወጋህ/ሽ እና ምግቡ እንዳያንቅህ/ሽ ተጠንቅቀህ/ሽ ብላ፡፡

ልጅ፡- እሺ እህቴ/ወንድሜ! ስለምክርሽ አመሰግናለው፡፡ ልክ እንዳልሽኝ/ከኝ እኔ ራሴን ከአደጋ እጠብቃለሁ፡፡

• ይህንን ሁለት ሁለት በመሆን እርስ በእርስ እንዲሰሩ ያድርጉ፡ ህፃናቱ የሴትና ወንድ ቦታን እየተቀያየሩ ይሰሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የሰሃን፣ የሹካ፣ የምግብ/ቅጠል/፣ የሚጠጣ የሚመስል፣ ቆርኪ፣ የሀይልንድ ክዳን ምስል/ሞዴልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ምግብ ስንመገብ ምን ማድረግ አለብንና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለ. ሎቶ ማዛመድ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፊደል፣ አቀማመጥ፣ ምግብ፣ መጠጥ፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

• የምግብ አይነት፣ የመጠጥ አይነቶች፣ በምግብና በመጠጥ መጠሪያ ስም የሚጀምሩ ፊደላትን የያዘ ፍላሽ ካርድ፣ (በካርቶን ላይ ያሉ ምስሎችን) ያዘጋጁ፤

• ሌላ ደግሞ ካርቶኑ ላይ ያሉትን ምስሎችና ፊደላት በትንንሹ በመቅረጽ ያዘጋጁ፤

• ከዚያም ከሰር ያሉትን ምስሎች በመመልከት ተመሳሳያቸውን ከተቆራረጡት ውስጥ በመፈለግ እንዲያዛምዱ ማድረግ፤

• ያዛመዱትን ብዛት በመቁጠር እንዲናገሩ ማድረግ፤

• ያዛመዳቸውን በማንሳት ከሰር ከላይ በማለት አቀማመጣቸውን እንዲያሳዩና የምግብና የመጠጥ አይነቶችን ምስል በማየት ስያሜያቸውን እንዲናገሩ ማድረግ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የምግብና የመጠጥ አይነቶች ምስል፣ የምግብ ዓይነቶችንና ፊደሎችን የያዘ ሎቶ፣ የቁጥር ቻርት/ፍላሽ ካርድ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ፊደል አዛመዳችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ፡፡

ሐ. እንቆቅልሽ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - አቀማመጥ፣ መጠጥ፣ ፊደል፣ ቁጥር፣ ምግብ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

• የተለያዩ ምስሎችን በመጠቀም እንቆቅሉሹን ከመጠየቅዎ በፊት ስለ እንቆቅልሹ ጥቆማ ይስጧቸው፡፡

• በመቀጠል እንቆቅልሹን የእንቆቅልሽ ሰርዓትን በመከተል ይጠያቃቸው፤ ካልመለሱ ሀገር ሰጡኝ በማለት ምላሹን ይንገራቸው፡፡

• የመጀመሪውን ክፍለ ጊዜ እርሶ ከጠየቁ ቀጣዮቹን ክፍለ ጊዜያት እንሱ ሁለት ሁለት እየሆኑ ጠያቂ እና መላሽ በመሆን እንዲያጠናክሩት ያድርጉ፡፡

ለምሳሌ፦ በበ ፊደል፣ ስጋ፣ እንቁላል፣ ኮርኒስ፣ ቦርሳ፣ 7 ቁጥር፣ 10ና 4 ቁጥሮችና ወዘተ ርዕሶች ላይ ይጠይቋቸው፡፡

ደብተር ያድርጉብኛል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ልብሰም ያደርጉብኛል፡፡ እኔ ማን ነኝ? መልሱ፦ ቦርሳ

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የፊደል ፍላሽ ካርዶች፣ የቁጥር ካርዶች፣ የቁሳቁስ ሰዕሎችና ሌሎች

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* በእንቆቅልሹ ላይ የተጠየቁትንና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ሁሉም ህጻናት በጨዋታው ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 3፦ በሥራ መማር

ሀ. መለጣጠፍና መቅረጽ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ደህንነት፣ መለጠፍ፣ መቀባት፣ አቀማመጥ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

• አስቀድመው በደብተራቸው የተለያዩ ምስሎች ተከታታይ አድርገው ሶስት የተለያዩ ቁሶች ስለው ያዘጋጁ (ፖም/ አፕል፣ ሳህን፣ መቀስ)...

• ከዚያም ከምስሉ አቀማመጥ በመነሳት የተለያዩ ባለቀለም እርሳሶች በማዘጋጀት መጀመሪያ ያለውን ምስል ቀይ ቀለም አቅልሙ፤ መሀከል ያለውን ደግሞ ሰማያዊ አቅልሙ፤ ከኃላ ያለውን ደግሞ ቢጫ አቅልሙ፡ በማለት ከቀቡ በኃላ በትክክል አቀማመጣቸውን ተረድተው መቀባታቸውን ያረጋግጡ፡፡

• ከዚያም ሌላ ነጭ ወረቀት በመስጠት ከምግበና ከመጠጥ አይነቶች ውስጥ የፈለጉትን በመሳል ውስጡን የተለያዩ ቀለም ያላቸውን ወረቀቶች በመቆራረጥ እንዲለጣጥፉ ያድርጉ፡፡

• ሲቆራርጡ እጃቸውን እንዳይቆርጡ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይንገሯቸው፣ ለመቁረጥ የፕላስቲክ መቀስ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

• ለጥፈው ሲጨርሱ የሰሩትን ለጓደኞቻቸው በማሳየት ምን እንደሰሩ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

በወረቀት የተዘጋጁ ስዕሎች፣ የምግብና የመጠጥ ምስል፤ እርሳስ፣ ባቀለም እርሳስ፣ ባለቀለም ወረቀትና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ወረቀት ቆራርጣችሁ ምን ሰራችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ፡፡

ለ. ስዕል ማንበብ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ምግብ፣ መጠጥ፣ ማቅለም፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ ሰእርቶ ማሳየት፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

• በቻርት ወረቀት ላይ የምግብና የመጠጥ አይነቶችንና ጥለቶችን የያዘ ምስል ያዘጋጁ፡፡

• ህጻናቱን በተራ በማሰወጣትና ምስሉን በማመልከት ስያሜያቸውን እንዲናገሩና እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡

• በቻርት ወረቀት ላይ የምግብና የመጠጥ አይነቶችንና ጥለቶችን የያዘ ምስል ያዘጋጁ።
• ህጻናቱ በተራ በማስወጣትና ምስሉን በማመልከት ስያሜያቸውን እንዲናገሩና እንዲያሳዩ ያድርጉ።
• የጥለቱንም አቀማመጥ እንዲናገሩ ያድርጉ።
• ስንት ምስሎች እንደሆኑ ወደ ፊትና ወደ ኃላ እንዲቆጥሩና ብዛቱን እንዲናገሩ፣ (በተለይ ወደ ኃላ መቁጠር ስለሚቸግራቸው እርሰዎ ስሌዳ ላይ ወይም ቻርት ወረቀት ላይ ከአንድ እስከ 15 ያሉትን ቁጥሮች በመፃፍ ወደፊትና ወደኋላ) ...

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

በቻርት ወረቀት ላይ የተሳለ የምግብና የመጠጥ አይነቶች፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ፊደል ደጋግማችሁ ጻፋችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።
* ሁሉም ህጻናት በተግባሩ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ሐ. የባህል አልባሳት ጥለት ስዕል ማቅለም (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - አቀማመጥ፣ ጥለት፣ ማቅለም፣ ሀላፊነት፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ ስርቶ ማሳየት፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

• አስቀድመው ጠንካራና ባለቀለም ወረቀቶችን በቀጫጭኑ በመቆራረጥ ከህጻናቱ ጋር ያዘጋጁ፣
• በመቀጠል ያዘጋጁትን ወረቀት በተለያየ አይነት ቀለም ለሁሉም መስጠት እርሰዎ አስቀድመው ወረቀቶቹን በማቆላለፍ እንዴት እንደሚሰራ ያሳዩአቸው (ለምሳሌ፡- ልክ እንደጸጉር ሹሩባ፣ ልክ እንደዘንቢል ስራ...)
• በሸመና ጥለት እንደሚሰራና አቀማመጡን በማየት የትኛው ቀለም ከስር/ከላይ እንደሆነ እንዲናገሩ ያድርጉ።
• የሰሩትን ለጓደኞቻቸው በማሳየት ስንት ባለቀለም ወረቀት እንደተጠቀሙ እንዲናገሩና እንዲቆጥሩያ ድርጉ።
• በመቀጠል የተለያዩ የባህል ኣልባሳት ዲዛይን በወረቀት በመሳል በተለያዩ የቀለም አይነቶች ያቅልሙ፤ ቀለሙ ግን ተከታታይነት ያለው ቅጥ/ፓተርን/ መሆን ይኖርበታል።
• በመለማመጃ መፅሀፋቸው ገፅ ______ ላይ ያለውን ምስልና ባህላዊ አልባሳት እንዲያቀልሙ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ባለቀለም ወረቀት፣ መቀስ፣ ሽማ እንዴት እንደሚሰራ የሚሳይ ምስል/ቪድዮ፣ የቁጥር ካርድና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ስንት ባለቀለም ወረቀት ተጠቅማችሁ ጥለቱን ሰራችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።
* ሁሉም ህጻናት በተግባሩ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 4፦ የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. ጨረቃና ጸሃይ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ጥንቃቄ፣ እንቅስቃሴ፣ አቀማመጥ፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

- ህፃናቱን በቡድን ይከፋፍሏቸው፡፡
- አንደኛውን ቡድን የጨረቃ ቡድን በማለት ስያሜ ይስጡት፡፡
- ሁለተኛውን ደግሞ የፀሀይ ቡድን በማለት ስያሜ ይስጡት፡፡
- ለሁለቱም ቡድን የፀሃይና የጨረቃ ቤት ይሰሩ፡፡
- የቡድኑን ስም በፊደልና በምስል አዘጋጅተው አንገታቸው ላይ ይሰሩላቸው/ደረታቸው ላይ ያጣብቁላቸው (ጨ - ጨረቃ፣ ፀ - ፀሀይ)፡፡
- ህፃናቱ የጨረቃና ፀሀይን ቡድን ወክለው በሚሮጡበትና በሚጓተቱበት ግዜ እንዳይገፋፉና እንዳይወድቁ እራሳቸውን እንዲጠብቁ መንገርና ያስፈልጋል፡፡

ምሳሌ፡-እና ማሙቅ (በማለትይህንእንቅስቃሴይሰራሉ)

1- ቁጭ፣ 2- ብድግ፣ 3- ዱብዱብ፣ 4- እንዝለል፣ 5-እናጨብጭብ በማለት ይሰሩና ፀሀይ ተባራሪ ጨረቃ አባራሪ ሆነው እንዲህ በማለት ይሮጣሉ፡፡

1ኛ ቡድን፡- ጨረቃን ሆኜ ስጫዎት መሸ -- መጣሁብሽ ጸሃይዬ

2ኛ ቡድን፡- ፀሃይን ሆኜ እየተጫዎትኩኝ --አትምጭብኝ ቀኑን አትውሰጂብኝ ጨረቃሂጅልኝ

1ኛ ቡድን፡- መጣሁ እኮ አንችን ላባርርሽ---- ከያዝኩሽ ደግሞ ልማርክሽ

2ኛ ቡድን፡- አትድከሚ እኔን ለመማረክ----- አመልጥሻለሁ ብዬ ፈትለክ ፈትለክ

እያሉ ይጫወቱና አንድ ህጻን ሲያዝ ወደ ቤት ውስጥ በማስገባት ያስሯቸዋል ከዚያ ያልተጫወተው የፀሃይና የጨረቃ ቡድን እንደገና ጨዋታ ከመጀመራቸው በፊት እናማሙቅ 1- ቁጭ፣ 2- ብድግ፣ 3- ዱብዱብ፣ 4- እንዝለል፣ 5- እና ጨብጭብ በማለት ይሰሩና እንደገና ጨዋታው ይቀጥላል ያልተያዘ ቡድን አሸናፊ ይሆናል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ስለፀሀይና ጨረቃ ምስል/ሞዴል፣ ስለእንቅስቃሴ የሚያሳይ ቪድዮ/ምስል፣ የቁሶችን አቀማመጥ የሚያሳይ ምስል

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከጨዋታው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡
* ሁሉም ህጻናት በጨዋታው ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 5፡- ተረት

ሀ. መሪማና እናቷ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሀላፊነት፣ ምግብ፣ መጠጥ፣ ደህንነት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የምግብና መጠጥ ምስል፣ የፀሀይ ምስል፣ የሀኪም ምስልና ሌሎች ተረቱን ገላጭ ሊያደርጉ የሚችሉ ምስሎች

መሪማና እናቷ

መሪማ እና ቤተሰቦቿ በአንድ መንደር ይኖሩ ነበር ከእለታትት አንድ ቀን መሪማ ከጓደኞቿ ጋር ተጫውታ ወደቤት ስትመለስ ከአፍንጫዋ ደም መውረድ ጀመረ፡፡ እናቷም ደንግጣ ወደ ሀኪም ቤት ወሰደቻት፡፡ ሀኪሙም መረመራት እና መድሃኒት ሲሰጣት አፍንጫዋ መድማቱን አቆመ ለቤተሰቦቿም ተረጋጉ አሁን ይሻላታልት አላቸው፡፡ የመሪማ ቤተሰቦች ችግሯን ጠየቁ፡፡ በልጃቸው ህመም በጣም አዝነው ነበር፡፡ ሀኪሙም መሪማ ጤነኛ ነች ነገር ግን ፀሀይ በጣም ስለመታት ነው የነሰራት አሁን ስለተሸላት ወደቤት መሄድ ትችላላችሁ በማለት አሰናበታቸው፡፡ መሪማም ወደቤት ከተመለሱ በኃላ እናትና አባቷ እግራቸው ስር በመውደቅ ይቅርታ አድርጊልኝ ሁለተኛ አይለመደኝም ሪሴን ከአደጋ እጠብቃለሁ በማለት ቃል ገባች፡፡ እሺ የኔልጅ ይቅር ብዬሻለሁ በይ እጅሽን ታጠቢና መክሰስ ብዬ በማለት ቆንጆ አተር ወጥ በእንጀራና ወተት አመጡላት፡፡ መሪማም ምግቧን በልታ ወተቷን ጠጥታ ስትጨርስ እናቴ እኔን ስለምትንከባከቢኝ አመሰግናለሁ በማለት ጉንጫቸውን ሳመች እናቷም በይ አሁን የተሠጠሽን ሳይመሽ እኔና አባትሽእናስራሽ አለቻት መሪማም በደስታ ከቤተሰቦቿ ጋር ደብተሯን አምጥታ መስራት ጀመረች፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* "መሪማ የነሰራት ለምንድን ነው? መሪማ ምን ለማድረግ ቃል ገባች?" በማለት ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 6፡- ውይይት

ሀ. ጉዳት የሚያስከትሉ ነገሮች (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሀላፊነት፣ ሁኔታዎች፣ ደህንነት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ጉደት ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ነገሮች መነሻ የሚሆኑ ሃሳቦችን በማንሳት እንዲወያዩና ራሳቸውን እንዴት ከአደጋ መጠበቅ እንዳለባቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

ለምሳሌ፡- (አይተው የሚያውቁት አደጋ ካለ እስከ ምክንያቱ ጭምር እንዲያነሱ) እንዲሁም አደጋው እንዳይደርስ የእነሱ ሀላፊነት ምን እንደሆነ እንዲወያዩ ማድረግ፤

• በውይይቱ ወቅት ሁሉም ተሳታፉ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡ እንዲሁም የውይይቱን ርዕስ በምስል አስደግፈው በትልቁ ይጻፉላቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ስለተለያዩ የዐደጋ አይነቶች መነሻና መከላከያ የሚገልጽ ምስል/ቪድዮና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* የአደጋ መነሻ ምን ሊሆን ይችላል?፣ አደጋን እንዴት መከላከል ይቻላል? የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 7፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ፊደላትን ደጋግሞ መጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፊደል መፃፍ፣ ቁጥር፣ ሀላፊነት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

 በቅድሚያ የሳምንቱን ፊደል (ዠ-ዡ-ዢ-ዣ-ዤ-ዥ-ዦ) በፍላሽ ካርድ በጠረጴዛቸው ላይ መስጠት፤ እንዲሁም እርሳስ፣ ወረቀት መጽሀፍ ይስጧቸው፡፡

 የፊደሎቹን በተሰብ በጋራ በማንበብ ቀጥሎ ፊደሉን በመቅደም ተከተል በጠረጴዛቸው ላይ ከፊት ለፊታቸው እንዲደረድሩ ማድረግ፤

 ቀጥሎ በተሰጣቸው ወረቀት ሃላፊነት በተሞላበት መልኩ ፊደሎቹን በአግባቡ ማሰመር ጠብቀው ሁለት ሁለት ጊዜ ደግመው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

 የፃፉትን ፊደል እንዲያነቡ እና ስንት ፊደል እንደጻፉ ቆጥረው እንዲናገሩ ይፍቀዱላቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ደብተር፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ የፊደል ፍላሽ ካርድ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ፊደላትን ሲጽፉ ቀርበው መመልከትና ምን ምን ፊደሎችን እንደጻፉ በቃል መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

ሳምንት ሃያ

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- በአከባቢያቸው የሚገኙ ቁሶች ስም ይናገራሉ
- የቃላትን ድምጽ በመስማት ከፊደላ ትጋር ያዛምዳሉ
- ተረቶችን በቃል ይናገራሉ
- ቁሶችን በተመሳሳይነታቸው ያዛምዳሉ
- ቀላል የትንፋሽ ዳንስ ረዘም ላለ ጊዜ ይደንሳሉ
- ተደራቢ ንድፎችን ይሰራሉ
- ቀላል ምታዊ አካሄድን በመከተል በተመሳሳይ አቅጣጫ መንቀሳቀስ ይችላሉ
- ፊደላትን ይጽፍሉ
- ከሌሎች ጋር ምናባዊ ጨዋታ ይጫወታሉ
- የተመሳሳይ ቁሶችን ገጽታዎች ይገልጻሉ
- በማህበራዊ እሴቶች መሰረት ይተገብራሉ
- የተለያዩ ብሮችንና ሳንቲሞችን በዓይነታቸው ይመድባሉ

ንዑስ ይዘቶች:-

- የቃላት እውቀት
- የፊደላት ድምጾች ግንዛቤ
- ግንኙነትና ቅርበት
- የአካል ብቃት
- ቅጥ/ንድፍ
- ምታዊ እንቅስቃሴዎች
- ፊደላትን መጻፍ
- ከሌሎች ጋር የመግባባት ክህሎት
- የቅርብ አከባቢ
- ሞራላዊ እሴቶቻችን
- ገንዘብ

ተግባር 1፦ መዝሙር

ሀ. ነኝ ጠፈርተኛ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ሰሞ፣ ቃላት፣ ፊደል፣ ሞት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

የቁጥር ካርድ፣ የከዋክብትና የፀሀይ ምስል፣ መንኮራኩርን የሚያሳይ ምስል/ቪድዮና ወዘተ

መዝሙር 1:- ነኝ ጠፈርተኛ

ነኝ ጠፈርተኛ መጣቂ ወደ ህዋ 2x
በመንኮራኩሯ ወደላይ አመጥቃለዋ 2x
ፀ.... ፀሐይን እያለሁ
ጨ.... ጨረቃን እነካለሁ
ከ.... ከከዋክብት ጋራ ሰደንሰ
እ...እያለኝ ደሰደሰ
እሰክሰ እሰክሰ
ቸብ ቸብ
ዘለል ዘለል
ዳንሰ ዳንሰ።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ:- ምን ምን አየን?

ወደ ህዋ በምን እንሄዳለን?

ተግባር 2፦ በሥራ መማር

ሀ. ቁሶችን ማዛመድ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፤ ቁስ፣ ቃላት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

- የሰማይ ነገሮች ፍላሽ ካርድ (የጨረቃ፣ የኮከብ፣ የዳመና፣ የሰማይ)፣ የፊደላት ፍላሽ ካርድ (የጨ፣ የደ፣ የኮ፣ የሰ ፍደላት) እና ወዘተ ያቅርቡ።
- የቀረቡ ፍላሽ ካርዶችን በሁለት ምድብ ያሰቀምጧቸው።
- አንድ የሰዕልና አንድ ፍላሽ ካርድ በማንሳት እያሳዩ የሰዕሉን ሰም የመጀመሪያ ፊደል በመጥራት ፊደሉን የያዘውን ፍላሽ ካርድ ፈልገው ማንሳትና የፊደሉን ድምጽ ጠርተው በማሰማት ከቁሱ ጋር ያዛምዳሉ።
- ቀጥሎ ሁሉም ህፃናት የሰማይ ቁሶች የተፃፏበት የቃላት ካርድ (ለምሳሌ፡- ኮከብ፣ ጨረቃ፣ ፀሃይ፣ ደመና ...) ቃላቱን ጠርተው ከፊደሉ ጋር ያዛምዱ::
- በመጨረሻ በመለማመጃ መፅሀፋቸው ገፅ _____ ላይ ያለውን ባለድርብ ፊደላትን በማቅለም ደግመው እንዲጽፉ ማድረግ ያሰፈልጋል።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የፊደል ካርድ፣ እርሳስ፣ ባቀለም እርሳስ፣ ከፊደል ካርዱ ጋር የሚመሳሰሉ የተለያዩ ቁሶች ሰዕል (ለምሳሌ፡- የጨረቃ፣ የተማሪ፣ የቸኮሌት፣ የገመድ፣ የነብር) ለህጻናቱ መያዝ እንዲችሉ ተደርጎ የተዘጋጁ የቃላት ካርድ...

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ፊደላትን ከምን ጋር አዛመዳችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ።

ለ. የሙዚቃ ምት ተከትለው መደንስ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፊደል፤ ቃላት፣ ምት፣ ዳንስ፣ መግባባት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ ሰእርቶ ማሳየት፣ ምሰሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምሰል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

- ህጻናቱን በተቀመጡበት በተለያየ ቡድን ይክፈላቸው (የጨረቃ፣ የኮከብ፣ የፀሀይ)፤
- ከዚያ እርሰ በእርሳቸው ቃላት በመመሰረት ቡድናቸው እንዲወዳደር ያድርጉ።

- ባህላዊ ሙዚቃ በመክፈት ከየቡድኑ አንድ አንድ ህጻን በማስነሳት ሞቱን ተከትለው ይወዛወዙ።
- እርሰዎ ሙዚቃውን ሲያቋርጡ ከተቀመጠው ፍላሽ ካርድ አንድ አንድ በማንሳት ምስሉን በማየት በምስሉ የመጀመሪያ ፊደልቃላት እንዲናገሩ ያድርጉ፤
- የተሳሳተ ህጻን ካለ የቡድኑ አባላት እንዲያግዙት ያድርጉ፤
- እንዲህ እያለ ተግባራቱን ለሁሉም ህጻናት ያሰራቸው።
- በመለማመጃ መፅሀፋቸው በገጽ ___ ላይ ያሉትን ፊደላትና እና ቃላትን ደግመው ይጻፉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ካርድ፣ እርሳስ፣ የጨረቃ፣ የኮከብና የፀሀይ ምስል፣ ከፊደል ካርዱ ጋር የሚመሳሰሉ የተለያዩ ቁሶች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የምስሉ የመጀመሪያ ፊደል ማነውና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ።

ተግባር 3፡- ተረት

ሀ. የሩት ህልም (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቃላት፣ ጭፈራ፣ ቁስ፣ ፊደል፣ ንግግር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የምግብና መጠጥ ምስል፣ የፀሀይ ምስል፣ የሀኪም ምስልና ሌሎች ተረቱን ገላጭ ሊያደርጉ የሚችሉ ምስሎች

መሪማና እናቷ

ታችኛው ሰፈር የሚኖሩ አቶ ተሰፋዬ እና ወ/ሮ ሮማን የሚባሉ ቤተሰቦች ነበሩ። ሩት የምትባል ልጅ ነበረቻቸው። ሩት በትምህርቷ በጣም ጎበዝና ቤተሰቦቿን አክባሪነች። ከእለታት አንድ ቀን እቤት ውስጥ የመጽሃፍ መደርደሪያ ላይ የነበሩ የወላጆቿን መጽሄቶችና ጋዜጦች እያነሳች ስዕሎቹን በአድናቆት ስታይ ወላጆቿ በመገረም ያዩአትት ነበር። ሩት ቀና ስትል ወላጆቿ ቆመው እያዩዋት ነው። ከዚይ “እማዬ አባዬ ይሄ እኮ መምህራችን የነገሩን መንኮራኩር ነው። የኔ ህልም ሳድግ ጠፈርተኛ መሆን ነው” በማለት መናገር ጀመረች። አባቷም “አንቺ ጎበዝ ተማሪ ስለሆንሽ ትሆኛለሽ ግን ለምን ጠፈርተኛ መሆን ፈለግሽ?” አላት። እሷም “ወደ ሰማይ በመውጣት እዛ ያሉትን በሙሉ ማወቅና መመራመር እፈልጋለውሁ” አለችው። አባቷም “ትሆኛለሽ እኛን ቤተሰቦችሽን ታኮሪናለሽ!” አሏት።

እሷም “አዎ! አኮራህለው” በማለት መጽሀፉን ገልጣም ስሎችን በማየት ጮክ ብላ “መ-መንኮራኮር፣ መ-መሬት፣ ረ-ረዥም፣ ቀ-ቀለም፣ ተ-ተማሪ” በማለት አነበበች፡፡ ቤተሰቦቿም አጨበጨበላት፡፡ ሩት በጣም ደስ አላት፡፡ ከአሁኑ ወደጠፈር የሄደች ያህል ደስ አላት፡፡ ቤተሰቦቿም “በይ ሩት እስካሁን ብዙ ስላጠናሽ ደክሞሻል ነይ፡፡ አሁን ደግሞ በሀገራችን ባህላዊ ዘፈን ትንሽ ተወዛወዢ” በማለት ባህላዊ ሙዚቃ ከፈቱላት፡፡ አብረውም ጨፈሩ ይባላል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ካርድ (መ፣ ረ፣ ቀ፣ ተ)፣ የመንኮራኩር ምስል፣ቃላት (መሬት፣ ረዥም፣ ቀለም፣ ተማሪ፣ ሙዚቃ)

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ምን መሆን ትፈልጋላችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለ. ተረት በድራማ መልክ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቃላት፣ ጭፈራ፣ ቁስ፣ ፊደል፣ ንግግር፣ ግብረገብ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ያለፈውን ተረት በድራማ መልክ ለማቅረብ የሚከተሉትን አካሄዶች ይከተሉ፡፡

- በቅድሚያ ተዋናዮችን መምረጥ እናት ፣አባት፣ ሴት ልጅ
- ወንበር ጠረጴዛ ፣መጽሀፍ መደርደሪያ መፅሃፍ ያለበት (በከፍል ውስጥ ያለውን የደብተር መደርደሪያ መጠቀም ይቻላል)፣ የመንኮራኮር ስዕል፣ የጠፈርተኛ ስዕልመደርደሪያው ላይ ማስቀመጥ፤
- ሴት ልጅ ቁጭ ብላ መጽሄት ላይ ያሉት ስዕሎች ተመስጣ ታያለች፤
- ትንሽ ቆይተው እናትና አባት ቆመው ያዩታል፤
- ልጅቷ ቀና ብላ ለወላጆቿ ጥምህርት ቤት ያተማረችውን የጠፈርተኛና የመንኮራኩር ስዕል እያየች እንደሆነ እሷም ስታድግ ጠፈርተኛ መሆን እንደምትፈልግ ትነግራቸዋለች፤
- እነሱም ጎበዝ ልጅ ስለሆነች ካሁኑ ጠንክራ ከተማረች መሆን እንደምትችል ነግረው ነይ ብለው የቤት ሥራዋን አብረው ይሰራሉ፡፡ ከዚያም አሁን ቡዙ ስላጠናሽ ባህላዊ ሙዚቃ እንክፈትና ትንሽ ተንቀሳቀሺ ይሏታል፤
- ሩትም እንትና አባቷን በአክብሮት የቤት ስራዬን ሰላሰራቹኝና ስለምታግዙኝ አመሰግናለሁ ብላ ጉልበታቸውን ትስማላች፤ ባህላዊ ሙዚቃ ተከፍቶ አብረው ይጨፍራሉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ካርድ (መ፣ ረ፣ ቀ፣ ተ)፣ የመንኮራኩር ምስል፣ቃላት (መሬት፣ ረዥም፣ ቀለም፣ ተማሪ፣ ሙዚቃ)

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ድራማውን በትክክል ማቅረባቸውን መከታተልና የተረቱን ይዘት በቃል መጠየቅ፡፡

ሐ. እትዬ ትርንጎ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁስ፣ ገንዘብ፣ እሴቶቻችን

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ፡፡

እትዬ ትርንጎ

ከረጅም ጊዜ በፊት በአንድ ትንሽዬ መንደር የሚኖሩ እትዬ ትርንጎ የሚባሉ በእድሜቸው ጠና ያሉ በጣም ደግ ሴት ነበሩ፡፡ ልጅ ስላልነበራቸው የሰፈሩ ልጆች በሙሉ ይታዘዛቸው ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን የሰፈሩ ልጆች ትምህርት ቤት ስለሄዱ የሚልኩት ልጅ ማግኘት ባለመቻላቸው ቅር አላቸውና እበራፋቸው ላይ ቁጭ አሉ፡ ፡ በዚህ ጊዜ ድንገት ትንሹ ከድር ብቅ አለ፡፡ ከዚያም እሮጦ ሄዶ ጉልበታቸውን ሳመ፡፡ “ምነው በጣም ያዘኑ ይመስላሉ?” አላቸውው፡፡ “ልጄ ከየት መጣህ?” አሉት፡፡ እሱም “ዛሬ ከእናቴ ጋር ሃኪም ቤት ሄደን መተን ነው” አላቸው፡፡ እማማ ትርንጎ “ምን አተው ነው?” አላቸው፡፡ እሳቸውም “እባክህን ሂድና ክርቢት ግዛልኝ” አሉት፡፡ እሱም “እሺ!” በማለት አስር ብር ተቀብላቸው፡፡ እየሮጠ ሄዶ ክርቢት ገዝቶ መልስ ይዞ በመምጣት ሰጣቸው፡፡ እሳቸውም “ተባረክ!” ብለው መረቁት፡፡ ከድርም “አሜን!” በማለት እየሮጠ ወደቤቱ ሄደ፡፡ እናቱም “የት ሄደህ ነበር?” ስትለው “ትልቋ እማማ ክርቢት ግዛ ብለውኝ ገዝቼላቸው ነው” አላት፡፡ እሷም “በጣም ጎበዝ የኔ ልጅ! ከኛ ድጋፍ ለሚፈልጉ ሁሉ መታዘዝ መልካምነት ነው፡፡ ሲያዙህ እሺ ብለህ መታዘዝህ ጥሩ ነው፡፡ በል አሁን! ግባና ትምህርትህን አጥና” አለችውና ወደ ቤት ገባ ይባላል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የገንዘብ ሞዴል፣ ክርቢት ሞዴልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የተረቱን ፍሬ ሀሳብ በቃል ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 4፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ምናባዊ ጉዞ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ ቃላት፣ ዳንስ፣ ምት፣ መግባባት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

አስቀድመው ህጻናት እምናባዊ ጉብኝት ወደውጭ እንደሚወጡ ይንገሯቸው፡፡

• ልጆች ዛሬ ማታ ወደውጭ ወሰጄ ላሰጎበኛችሁ ነው ከኔ ጋር ትሄዳላችሁ፣
• ጥሩ ልጆች አሁን አይናችንን ጨፍነን እዛው ባለንበት ነው የምንጓዘው፣
• እስኪ አይናችሁን ጨፍኑና ወደሰማይ ቀናበሉ፣
• አያችሁ ልጆች ወደ ሰማይ እየበረርን ነው መንኮራኩሩ ከእኛ ጋር ፊደላት ይዞ
• ወደ ሰማይ ወጣ ፀሀዩዋ ደምቃለች፣ አቤት ስታሰደስት ደግሞም ስትሞቅ ሙቀቷ ደስ ይላል፣ ከመንኮራኩሩ ፊደላቱ እየወጡ ወደ እኛ እየመጡ ነው፣ ቸ-ቸኮሌት መጣች፣ ቀጥሎ ደግሞ ተ-ተማሪመጣች ና ቸኮሌቷን ልጣ በላቻት፣ መ-መነፅር ደግሞ መጣች እሷን ተከትሎ ቀ-ቀለም መጣ እንዴ አያችሁ ተ-ተማሪ ተመልሳ መጣች ና በቀለሙ መነፅሯን አቀለመቻት፡፡ ቀለሙ አቤት ሲያምር እንዴ ዘፈኑ ጀመረ (የባህላዊ ጭፈራ ይክፈቱ) ፊደላቱ መደነስ ጀመሩ እስኪ አይናችሁን በመግለጥ ተመልከቷቸው (እዚህ ጋር ፊደላቱን ያዘጋጁት ጅ የፊደል ካርድ ደርድረው ያዘጋጁና ሙዚቃውን በመክፈት ፊደላቱ እንደሚደንሱ እያንቀሳቀሱ በማስመሰል አብረው እንዲጨፍሩ ያድርጉ):: ሰላዩት ነገር እንዲናገሩ እድል ይሰጣቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ካርድ (ተ፣ ቸ፣ መ፣ ቀ)፣ ቴፕ፣ ፍላሽ፣ የፀሐይ ምሰልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ዬት ተጓዛችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለ. መመደብ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፣ ቃላት፣ ቁስ፣ መመደብ፣ ገንዘብ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልሰ

የመምህር ሚና፡-

• ህጻናቱ በተቀመጡበት ወንበር የተለያዩ ቁሱችን፣ ፊደላትንና ገንዘቦችን ቀላቅለው ያሰቀምጡ፡፡
• ካሰቀመጡት የተቀላቀሉ ነገሮች ውሰጥ ፊደላትን ብቻ ለይተው እንዲያወጡና ፊደላቱን ጮክ ብለው እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡
• ቀጥሎ ደግሞ ገንዘቦቹን እንዲያወጡና ባለ ሰንት ብር እንደሆኑ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
• በመጨረሻም የቀሩትን ቁሶች እያነሱ በማሳየት ሰማቸውን እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ቁሶች፣ የፊደል ፍላሽ ካርዶችና ሌሎች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን ቁሶችን መደባችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡
* ህጻናት ቁሶቹን በትክክል መመደባቸውን ቀርበው ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 5፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. መስሎ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ገንዘብ፣ ቃላት፣ እሴቶች፣ ቁሶች

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

- ህጻናቱን ወደ ውጪ አስልፈው ያሰወጧቸው፣
- ከዚያም የተወሰነውን ህጻናት ገዥ የተወሰኑትን ደግሞ ሻጭ በማድግ ይመድባቸው፣
- ለሻጮቹ የሚሸጡ የቁሶች ሞዴል ለምሳሌ፡- ከረሜላ፣ ቸኮሌት፣ ጨው፣ ስኳር፣ ሳሙና የመሳሰሉትን
- ለገዢዎች ደግሞ የወረቀት የብር ኖቶችና ናሳንቲሞች/ሞዴል ይስጣቸው፣
- ገዢዎቹ የሚፈልጉትን ነገር እባክዎን በማለት እየጠየቁ እንዲገዙና ዋጋውን በመጠየቅ እንዲከፍሉ መልስ እንዲቀበሉና አመሰግናለው በማለት እንዲሄዱ ያበረታቷቸው፣
- ሻጮችም ሊገዙ ሲመጡ በትህትና እንዲያናግራቸውና ሲገዛቸው አመሰግናለው በማለት እጅ ነሰተው ገንዘቡን እንዲቀበሉ፣
- በቀጣዩ ቀን ሻጭ የነበሩ ገዥ፤ ገዥ የነበሩ ደግሞ ሻጭ ሆነው እንዲጫወቱ ያድርጉ፣
- በመለማመጃ ደብተራቸው ገጽ _____ ላይ ያለውን የግብረገብ ቃላት ደግመው ይጻፉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ሳንቲሞ፣ በወረቀት የተዘጋጀ የገንዘብ ኖት፣ የሚሸጡ ቁሳቁሶችና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከጨዋታው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት በጨዋታው ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 6፡- ውይይት

ሀ. መልካም እሴቶች (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ገንዘብ፣ ቃላት፣ እሴቶች፣ ቁሶች

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናቱ ከዚህ ቀጥለው በቀረቡ አጀንዳዎች ላይ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

* በቅድሚያ የመወያያ ርዕሰ ጉዳዮችን አስተዋውቀው የተወሰነ ሃሳብ ያካፍሏቸው።

* በመቀጠል ስለማህበረሰባችን ሞራላዊ እሴቶች (ሰው ማክበር፣ አለመዋሸት፣ የተቸገረን ሰው መርዳት፣ ተፈጥሮን መውደድና ወዘተ) እንዲያወሩ ያድርጓቸው።

• በአከባቢያቸው ስለሚገኙ ቁሳቁሶች ተመሳሳይነታቸው (ከእንጨት፣ ከብረትና ከሸክላ የተሰሩ፣ ከጨርቅ የተሰሩና ወዘተ)

• የገንዘብ ጥቅምና አጠቃቀምን በተመለከተ በእነርሱ ደረጃ የሚያውቁትን እንዲያወሩ ማበረታታት

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የግብረገብነት እሴቶችን የሚያሳይ በቪድዮ/ስዕል፣ ቁሶችን የሚያሳይ ምስል፣ ራሱ ቁሱ፣ ገንዘብና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከውይይቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የቃል ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት በውይይቱ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 7፦ የተግባር ሥራ

ሀ. ፊደል መጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - መፃፍ፣ ቃላት፣ ቁሶች

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፦

* ጊዜው የተግባር ሥራ መሆኑን ይንገሯቸው።

* በቅድሚያ የዕለቱን የፊደል ቻርት ያዘጋጁ (ደ-ዱ-ዲ-ዳ-ዴ-ድ-ዶ) ለህፃናቱ በመስጠት በጋራ አንብቡ፤

* የተወሰኑ ፊደላትን እርሶ ደጋግመው ጽፈው ያሳዩአቸው።

* ቀጥሎ በያዙት ፊደል የሚጀምር ስም ወይም ቃል ያለውን ቁሰ በማሳየት እንዲያነቡ ያድርጉ። ለምሳሌ፦ ደ-ደውል፣ ዱ-ዱላ፣ ዳ-ዳቦ፣ ድ-ድፎ፣ ዶ-ዶሮ)

* በመቀጠል ወረቀት፣ እርሳስ፣ ደብተር፣ መለማመጃ መፅሃፍ ላይ የእላቱን ፊደል ዝርያ ደጋግመው እንዲጽፉ ያርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

እርሳስ ፣ ደብተር፣ የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ የቃላት ካርድና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ፊደላትን ሲጽፉ ቀርበው መመልከትና ምን ምን ፊደሎችን እንደጻፋ በቃል መጠየቅ ያስፈልጋል።

ሳምንት ሃያ አንድ

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- ቁሶችን በመለካትያወዳድራሉ
- የነገሮችን እንቅስቃሴ አቅጣጫ ይመርምራሉ
- ሰውነታቸውን ወደ ተለያየ ቦታ ያንቀሳቅሳሉ
- ለማኅበረሰባቸው አክብሮት ያሳያሉ
- የጂኦሜትሪ ቅርጾችን ይሰላሉ
- ፊደሎችን ይጽፋሉ
- እስከ 15 የሚደርሱ ቁጥሮችን ይቆጥራሉ
- ከመዝሙሮች ጋር መንቀሳቀስ መጨፈርይችላሉ

ንዑስ ይዘቶች፡-

- ልኬት
- የዲጂታል ንባብና ጽህፈት
- የሀገር ፍቅር
- የቦታ ግንዛቤ
- ቅርጽ
- ፊደላትን መጻፍ
- ቁጥሮችን መቁጠር
- የፈጠራ አገላለጽ

ተግባር 1፦ መዝሙር

ሀ. እገዛ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - መጠን፣ አክብሮት፣ ቅርጽ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ህጻናት እናትና አባትን ሲያግዙ የሚያሳዩ ምስሎችና ወዘተ

መዝሙር 1:- እገዛ

ተንከባለለ አንድ ትልቅ ድንጋይ
እየፈጠነ ወደቀ ከላይ
እኔም አንስቼ ተመለከትኩት
በትልቁ ድንጋይ ፈረካከስኩት
እናቴ መጣች ገበያ ሄዳ
እኔም ሮጥኩኝ እሷን ልረዳ
የገዛችውን ተመለከትኩኝ
ላግዛት እንደ አቅሜ ፌስታል ወሰድኩኝ
እይታኝ እናቴም ተደሰተች
ከቤት ስንደርስ ዳቦ ሸለመች
ዳቦው ክብ ነው ነጭ ነው መልኩ
በላሁኝ በሻይ እያወራረድኩ፡፡

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ:- ልጁ ምን ሰርቶ ተሸለመ?

ለ. ልጆች ተነሱ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - መመርመር፣ እንቅስቃሴ፣ ቅርጽ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ልዩ ልዩ ቅርፆችን የያዘ ምስል፣ የፀሐይና የኮከብ ምስልና ወዘተ

መዝሙር 2:- ልጆች ተነሱ

ኑ ልጆች ተነሱ እንመራመር
ዞር ዞር እያልን ማየት እንጀምር 2x
ወፎቹ ሲንጫጩ ከእንቅልፌ ነቅቼ
የንጋትን ኮከብ አየሁ ተደስቼ
ኮከቧ ተጉዛ ወደ ሰማይ ገባች
ሙቀቷን እየሰጠች ፀሀዪዋ ብቅ አለች
ፀሀዪ ክብናት ዜሮ ትመስላለች
መልኳ እሳታማ ትለበልባለች
እስኪ ተመልከቷት ፀሀዪን በአድናቆት
እናጨብጭብላት ሁላችን በአንድነት
ከወገባችን ጎንበስ ዘለል ከእግራችን
ከአንገታችን ሰበር ዝቅ ከትከሻችን፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ጠዋት ሰማይ ላይ ምን ምን ይታያል?

ሐ. ደብተሬ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ልኬት፣ ቅርፅ፣ አካላት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

ልዩ ልዩ ቅርፆችን የያዘ ምስል፣ የፀሐይና የኮከብ ምስልና ወዘተ

መዝሙር 3:- ደብተሬ

በግራ እጄ መጽሃፌን ይዣለሁ
በቀኝ እጄ እርሳሴን ይዣለሁ
ፊደል እጽፋለው
ደብተሬ ጎነ አራት ነው
እርሳሴ ደግሞ ቀጥ ያለ ነው
የከበደኝ መጽሃፌ ነው
የቀለለኝ እርሳሴ ነው
በቀኝ እጀ ከለሬን ይዣለሁ
በግራ እጀ ደብተሬን ይዣለሁ
የከበደኝ ደብተሬ ነው
የቀለለኝ ከለሬ ነው፡፡

ምዘና:- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ:- ከደብተርና ከእርሳስ የቱ ይከብዳል?

ደብተር ምን ዓይነት ቅርጽ አለው?

ተግባር 2፦ ተረት

ሀ. አራቱ ጓደኛሞች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ቅርጽ፣ ማወዳደር፣ እንቅስቃሴ

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፦

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

አራት ማዕዘን፣ ካሬ፣ ጎነ ሦስት፣ ክብ፣ ሞላላ ቅርፆችን የያዘ ምስል/ሞዴል፣ የጎጆ ቤት ምስልና ወዘተ

አራቱ ጓደኛሞች

በአንድ አከባቢ የሚኖሩ አራት ማዕዘን፣ ካሬ፣ ጎነ ሦስት፣ ክብ እና ሞላላ የሚባሉ ጓደኛሞች ነበሩ። ከእለታት አንድ ቀን ድብብቆሽ እየተጫዎቱ እያሉ ካሬ ጠፋችባቸው። ቢፈልጉ ቢፈልጉ አጧትና ደክሟቸው አዝነው ወደቤታቸው ሊመለሱ ሲሉ ከትልቁ ዛፍ ስር አኩርፋ ቁጭ ብላለች። “ምነው ካሬ ለምን አኮረፍሽ?” እያሉ ተራ በተራ ጠየቋት። “እኔ ጎጆቤት መስራት ፈልጌ ነበር፤ ግን አልቻልኩም” አለች እንዳኮረፈች። “በቃ በጋራ ተጋግዘን እንሰራለን አይክፋሽ!” አሏትና ለመስራት ተዘጋጁ። ከዛም ከካሬ ላይ ክብን እንስተው ጨመሩ። ነገር ግን የጎጆቤት ቅርጽ ሊመስል አልቻለም። በሌላ ሙከራ ሞላላን አንስተው ካሬላ ጨመሩ። አሁንም ጎጆቤት አልመሰለም። በመቀጠል አራት መዓዘንን ጨመሩ፤ በዚህም አልተሳካም። ካሬ ተሰፋ ቆርጣ ማልቀስ ጀመረች። ጓደኞችዋም “ቆይ አታልቅሽ ሙከራችን እኮ አላለቀም” አሉና ጎነ ሦስትን ከካሬ ላይ ሲያስቀምጡት የጎጆቤት ቅርጽ መሰለ። ካሬም በደስታ ብዛት እጆቿን ወደላይ ወደግራ ወደቀኝ ወደፊት ወደኋላ እያወዛወዘች እየዘለለች ቦረቀች። ጓደኞችዋም አብረዋት በደስታ ፈነደቁ። አራት ማዕዘን፣ ክብና ሞላላም የተሰራው ቤት ውስጥ ገቡ።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፦ ከቅርጾቹ ውስጥ የጠፋው ምን ዓይነት ነበር?

ለ. አልማዝና ቴወድሮስ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ሀገር፣ ቅርፅ፣ እሴቶች

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ቅርፆች፣ ባንዲራ፣ የተለያዩ መጠን ያላቸው ጠርሙሶች ስዕልና ወዘተ

አልማዝና ቴወድሮስ

ከእለታት አንድ ቀን አልማዝ እና ቴድሮስ የሚባሉ እህትና ወንድም ነበሩ። አልማዝ ትልቅ ናት። ቴድሮስ ደግሞ ገና 5 አመቱ ነው። አንድ ቀን አልማዝ ወጥ እየሰራች ቴድሮስን "ሂድና የጨው እቃ አምጣ" አለቸው። እሱም ይዞላት መጣና ሰጣት። እሷም ወጡ ውስጥ ጨምራ ስታስቀምጥ አንስቶ ከቅመም ዕቃው ጋር ማወዳደር ጀመረ። "ይህ ትልቅ ነው፤ ይህ ደግሞ ትንሽ ነው" ሲል አልማዝ ሰማችና "ጎበዝ! ይሄስ" በማለት ሌላ ትልቅ ድስት አንስታ ጠየቀችው። እሱም "ይሄማ በጣም ትልቅ ነው። ቅርጹም ይለያል። እነዚህ ጎነ አራት ናቸው። ይሄ ግን ክብ ነው" በማለት መለሰላት። እህቱም "ወደፊት ተምረህ ምን መሆን ትፈልጋህ?" አለችው። እሱም "እግር ኳስ ተጫዋች መሆን ነው የምፈልገው" አላት። "ለምን?" ስትለው "ወደፊት ታላቅ እግር ኳስ ተጫዋች በመሆን የሀገሬን ስም ማስጠራት እፈልጋለሁ"። "ጥሩ! ሀገርህን ለማስጠራት ጎበዝ ልጅ መሆን ብቻ ሳይሆን ሀገርህን መውደድ እናትና አባታችንን እንዲሁም ሌሎችን ሰዎች አክባሪ መሆን ያስፈልጋል" አለችው። ቴድሮስም "እኔ ሀገሬን እወዳለሁ! ቤተሰቤን አከብራለው እህቴ" በማለት እቤታቸው ውስጥ የነበረውን ባንዲራ አንስቶ ቀጥ ብሎ በመቆም መዘመር ጀመረ። እህቱም በጣም ተገርማ ከሱ ጋር ዘመረች ይባላል።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡- ሀገሩን የሚወድ ሰው ምን ምን ያደርጋል?

ተግባር 3፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ቅርጾችን መሳልና ማድመቅ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቅርጽ፣ ማወዳደር፣ ቆጠራ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

* ለህጻናቱ ወረቀት ይሰጣቸው፤ ከዚያም ወረቀቱ ላይ ትንሽ ክብ ትልቅ ክብ፣ ትንሽ ጎነ ሶስት፣ ትልቅ ጎነ ሶስት፣ ትልቅ ጎነ አራት፣ ትንሽ ጎነ አራት እንዲስሉ ያድርጉ፤
* የሳሉትን ቅርፆች የፈለጉትን ቀለም እንዲያቀልሙ ያድርጉ፤
* አቅልመው ከጨረሱ በኃላ ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩና የቅርፆቹን መጠሪያ ስም እንዲናገሩ ያድርጉ፤
* የሰሯቸውን ቅርፆች ብዛት እንዲቆጥሩና ብዛቱን እንዲናገሩ ያድርጉ፤ ከምስሎቹ ስር እንዲፅፉ ያድርጋቸው።

* ትንሹን ቅርፆች ለይተው እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡
* በድጋሚ ተግባሩን ሲያከናውኑ ቅርጾቹን በመቀየር ያሰሯቸው፡፡
* በመለማመጃ መጽሀፋቸው ገጽ _____ ላይ ያሉትን የጂኦሜትሪ ቅርፃችን ያስሏቸው፡፡

ዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

፣ ደብተር፣ ቅእለም፣ የተለያዩ ቅርጾችን የያዘ ቻርትና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ቅርጾችን ሲስሉ ቀርበው መመልከትና ምን ምን ቅርጾችን እንደሳሉ በቃል መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

ለ. ፊደል መጻፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፊደል፣ መንቀሳቀስ፣ መጨፈር

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

* ለህፃናቱ ስለዕለቱ ትምህርት ገለፃ ካደረጉ በኋላ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በማቅረብ ተግባሩን ያከናውኑ፡፡ የእለቱን የፊደል ቤተሰብ (ጀ-ጁ-ጂ-ጃ-ጄ-ጅ-ጆ) በፍላሽ ካርድ አዘጋጅተው እየነኩ ያስነብቡ፡፡ በመቀጠል ፍላሽ ካርዱን በየጠረጴዛቸው ላይ በማስቀመጥ ፊደሉን በተገቢ የአፃፃፍ ስርአት በመለማመጃ ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ እና የፃፉትን ደግሞ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ሲጨርሱ ከዚህ በፊት የሚያውቁጥን መዝሙር በመክፈት እየዘመሩ ወደተለያየ አቅጣጫ እተንቀሳቀሱ እንዲደንሱ ማድረግ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እርሳስ፣ ወረቀት፣ የመለማመጃ መጽሐፍ፣ የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ ቴፕ/ጂፓሰንአ ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ፊደላትን ሲጽፉ ቀርበው መመልከትና ምን ምን ፊደላትን እንደጻፉ በቃል መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 4፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. መጠን መለየት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቅርጽ፣ ማወዳደር፣ እንቅስቃሴ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

• ህፃናቱን በማሰለፍ ወደ ውጪ ያሰወጧቸው፤

• መሬት ላይ በትልልቁ ትንሽ ቤት ትልቅ ቤት፣ ትልቅ ኳስ ትንሽ ኳስ፣ ትልቅ አራት ማዕዘን ትንሽ አራት ማዕዘን፣ ትልቅ ጎነ ሶስት ትንሽ ጎነሶስት፣ ያስምሩ

• ህጻናቱን በአራት ቡድን ይክፈላቸውና አንዱን ቡድን በኳሱ መደዳ፣ አንዱን ቡድን በጎነ ሶስት መደዳ፣ አንዱን ቡድን በአራት ማዕዘኑ መደዳ፣ የመጨረሻውን ቡድን በክቡ መደዳ ይመድቡ፣

• ህፃናቱ በቆሙት ቅደም ተከተል መሰረት ትንሽ ሲባል ትንንሽ ምስሎች ውስጥ መግባት፣ ትልቅ ሲባል ትልልቅ ምስሎቹ ውስጥ እንዲገቡ፣ ይንገሯቸው

• የኳስ ቡድን አባላት ትልቅ ሲባል ትልቅን መምታት ትንሽ ሲባል ትንሹን ኳስ የመምታት ድሪጊት ያሳያሉ።

• ኳስ ሲባል ተሳስቶ የገባ ህጻን ከጨዋታ ውጪ ይሆናል ሌላ ከኃላ ያለ ህጻን ይቀጥላል

• ጨዋታው እንዲህ እያለ ይቀጥላል እስከ መጨረሻው ሳይሳሳቱ የሰሩ ህጻናት የጨዋታው አሸናፊ ይሆናሉ።

• በሌላኛው ቀን ተግባራቱን ሲደግሙ ቦታ ያቀያይሯቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ቅርፆችን የያዘ ምስል፣ ኳስ፣ ማርከርና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ሲጫወቱ ቀርበው መመልከትና ምን ምን ቅርጾችን እንደሳሉ በቃል መጠየቅ ያስፈልጋል።

ለ. ቁስ ማወዳደር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ ቅርጽ፣ ማወዳደር፣ እንቅስቃሴ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ስርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

• ህጻናትን ወጭ አውጥቶ አከባቢያቸው ላይ ያሉ የተለያዩ ቅርፆችን በመፈለግ ቅርጻቸውን እንዲናገሩ ማድረግ፣

• ያገኟቸውን ቅርፆች ተመሳሳይነት ያላቸውን አንድ ላይ እንዲያስቀምጡ ማድረግ፣

• የትኛው ከየትኛው ቁስ እንደሚበልጥ በማወዳደር እንዲናገሩ ማበረታታት፣

• የለቀሟቸውን ቁሶች በእጃቸው እያነሱ እስከ አስራ አምስት ድረስ እንዲቆጥሩ ማድረግ፣

• የያዙት ቁስ አስራ አምስት ካልሞላ እንዲጨምሩና እንዲቆጥሩ ማድረግ፣

• በትክክል አስራ አምስት መሆኑን አብሮ በመቁጠር ማረጋገጥ፣

• የቆጠሩትን ቁስ በግምት ሁለት ቦታ በመክፈል ለየብቻ እንዲቆጥሩና የቱ እንደሚበልጥ እንዲያወዳድሩ ማድረግ፣ ቁሶቹን እርስ በርስ እንዲያለካኩ ማድረግ ፣እኩል የሆኑትን በአንድ እንዲመድቡ ያድርጉ

• ሰርተው ሲጨርሱ ለቅመው ያመጣቸውን ቁሶች ወደ ቦታቸው እንዲመልሱና እጃቸውን እንዲታጠቡ ማድረግ፣

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚኖሩ ልዩ ልዩ ቁሶች (ቆርኪ፣ ጠጠር፣ ቅጠልና ወዘተ)

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ሲጫወቱ ቀርበው መመልከትና ምን ምን ቁሶችን እንደተመለከቱ በቃል መጠየቅ ያስፈልጋል።

ተግባር 5፡- ውይይት

ሀ. ሀገር (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሀገር፣ እክብሮት፣ ቦታ፣ ቁስ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

- በቅድሚያ ውብ ሁገሬ የሚለው መዝሙር የታወቀ መዝሙር ያስደምጧቸው፡፡
- ቀጥሎ ህፃናቱ የሚከተሉት ነጥችን እያነሳችሁ ሁሉም በየተራ ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- ልጆች ስለሃገር ፍቅር ስሜት እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡

(ለምሳሌ፡- ሀገራችሁን እንዴት ነው የምትወዱት፣ መውደዳችሁን ምን በማድረግ ትገልፃላችሁ…) በማለት መጠየቅና ሃሳባቸውን መሰብሰብ፤

- ቀጥሎ ለሀገራቸውና ለወገናቸው ለማበርከት ስለሚያልሙት ነገር እንዲያወሩ ያድርጓቸው፡፡
  (ለምሳሌ፡- ህዝቡን ምን እንዲኖረው ይፈልጋሉ ለዚያ ደግሞ ምን ማድረግ ይፈልጋሉ…)
- በኢትዮጵያ በተለያዩ አቅጣጫ የሚገኙ ታሪካዊ ፒታዎችን እንዲናገሩ ያድርጉዋቸው (ሰሜን አክሱም፣ ዳሸን ተራራ፣ ባሌ ፓርክ፣ ሶፍ ኡመር ዋሻ፣ ላሊባ ውቅር አቢያተ ክርሲቲያናት፣ ጎንደር ቤተመንግሰት፣ የኮንሶ ቤቶችና መልከዓ ምድር፣ የጂማ ቤት መንግሰት፣ የሀረር ግንብ፣ የአፋር ዳሎል፣ የሲዳማ ቤት አሰራር…
- ስለ አንድነትና ትብብር እንዲያወሩ ያድርጓቸው፡፡
- ስለሰዎችና ስለመከባበር እንዲያወሩ ያድርጓቸው፡፡
- ውይይቱን በተለያዩ ምሰሎች አሰደግፈው ማቅረብ በጣም አሰፈላጊ ነው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

- የኢትዮጵያ ካርታ ምስል፣
- የተለያዩ ታሪካዊ ቦታዎችና ቁሶች ስዕል፣
- ለሀገራቸው የተለያዩ መልካም ሰራዎችን የሰሩ ሰዎች ፎቶና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ሲወያዩ ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ መሆናቸውን ማየት
* እንድሁም ልዩ ልዩ የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ ያስፈልጋል።

ተግባር 6፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. እንቆቅልሽ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- አቅጣጫ፣ ቅርፆች፣ ልኬት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ይህንን ጨዋታ የእንቆቅልሽ አጨዋወት ሥርዓትን ጠብቀው ያጫውቷቸው፡፡

* በቅድሚያ የተለያዩ ስዕሎችን ያስመልክቷቸው፡፡

* ቀጥለው ስለየተለያዩ ቅርጾች፣ መኪና፣ ዓይን፣ ጸሀይና የኢትዮጵያ ባንዲራ እንቆቅልሽ ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡-

አርንጓዴ፣ ቀይ ብጫ ቀለማት አሉብኝ፡፡ ብዙ ጊዜ ት/ቤት ውስጥ አልጠፋም፡፡ የሀገር ፍቅር መገለጫ ነኝ፡፡ እኔ ማን ነኝ?

መልሱ፡- የኢትዮጵያ ባንዲራ

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

- የኢትዮጵያ ባንዲራ፣
- ቅርፆች፣ መኪናና አውሮፕላን ምስል፣
- ከእንቆቅልሹ ጋር ተያያዥነት ያለቸውን ሌሎች ቁሶች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ከእንቆቅልሹ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

የአውድ 4 ማጠቃለያ መመዘኛ ቼክ-ሊሰት

የህጻኑ/ኗ ስም፡______________________________ **ጾታ፡** ________ **ዕድሜ**______

ተ.ቁ	የሚጠበቀው የመማር ውጤት	ዝቅተኛ	መካከለኛ	ጥሩ	በጣም ጥሩ
1	ሆሄያት/ፊደላት እና የድምፃቸውን ቅላፄ መረዳት				
2	የሆያት ቤተሰብ ድምጽ እና ቅርፅ መለየት፣				
3	ሰዕሎች፣ሆሄያት እና ቀላል ቃላቶችን ማነበብ፣				
4	ከሌላ አቅጣጫ በመዞር አቅጣጫ መያዝ፣				
5	ከሁለት አማራጮጭን መለየትና ምርጫ ማድረግ፣				
6	እሰከ 20 ድረሰ ያሉትን ቁጥሮች ወደፊት እና ወደኋላ መቁጠር፣				
7	ቀላል ንድፍ (ነጠላ ንድፎች) መረዳትና መፍጠር፣				
8	የጎደሉ ቁጥሮችን መለየት፣				
9	ከ5-7 የሚደርሱ የተለመዱ ጤናማ ምግቦች እና መጠጦች መለየት፣				
10	በመንቀሳቀስ እና ሳይንቀሳቀሱ ትክክለኛ አፈጻጸም ክሎታቸውን ማሳየት፣				
11	በድምፅ ፍጥነት መሰረት እንቅሰቃሴዎችን በመምረጥ ተግባራትን ማከናወን፣				
12	በአካባቢያቸው ያሉ ነገሮችን፣ ቁሳቁሶችን፣እንሰሳትን፣ዕፅዋትን እና የታወቁ ህዝቦችን መመርመር እና መረዳት መቻል፣				
13	ቀላል ባህላዊ ጭፈራዎችን ማከናወን፣ ቀላል ዘፈኖችን መዘመር እና በግጥም መንቀሳቀሰ				
14	የተለመዱ ተረቶችን፣ በመዝሙር፣ በዳንሰና በድራማ መልክ ማከናወን				

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፡- ____

____

____

____

አውድ አምስት፦ ውሃ

ለአውዱ የተሰጠ ጊዜ፦ 6 ሳምንት/180 ክ/ጊዜ

መግቢያ

በዚህ አውድ ሰድስቱ የመማሪያ መስኮች ላይ ባሉት አበይት ይዘቶች ውስጥ በማቀናጀት በሚሰጣቸው ትምህርቶች ህፃናቶች የውሀን መገኛ፣ አስፈላጊነትና አጠቃቀም እንዲረዱ ታስቧል። በዚህ አውድም በሌሎች አውዶች ይቀናጁ የነበሩ የትምህርት ይዘቶች የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ባማከለ መልኩ እንዲደራጁ ታስበው ቀርዋል። አውዱ ህጻናት በአከባቢያቸው ስለሚያዩአቸው ውሃዎች መገኛ፣ አስፈላጊነትና፣ አጠቃቀም እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል። የተቀናጀ ትምህርት የሚቀርበው በአንድ ተግባር ውስጥ ቢያንስ ከሶስት በላይ ይዘቶች ተቀናጅተው መቅረብ ሲችሉ ነው። በዚህ አውድ ስር የተቀናጁ ይዘቶች (ቅድመ ስሌት፣ የቋንቋ እድገት፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ የአካል መዳበር፣ የማህበራዊና ስሜት መዳበር እንዲሁም የስነ-ጥበባት ግንዛቤ) ከውሃ ጋር ተቆራኝተው እንዲቀርቡ የታሰቡ ናቸው።

የእድገትና የመማር ውጤቶች

ህጻናት ከዚህ አውድ ትምህርት በኋላ፦

- በአካባቢያቸው የሚገኙ የቁሳቁሶችን እናየዕቃዎችን ስም መለየት
- የፊደላትን ድምፅ ከተባለው የፊደላት ቅርጾች ጋር በማያያዝ መለየት
- የፊትን ገፅታ ከመልእክት ዓላማ ጋር በማጣመር መለየት
- የተሰጡትን ፊደላት በመጥራት ማንበብ መቻል
- ሌሎችን የመርዳት ሃላፊነትን መጋራት፣ መለገስ፣ በጎፈቃደኝነት፣ የመተባበር ወዘተ መረዳት
- በተመሳሳይ እድሜ ካሉ ልጆች ጋር መጫወትና መግባባት
- ከ0 እስከ 10 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በግጥም እና በጨዋታ መዝሙር መደመርና መቀነስ መቻል
- የኢትዮጲያ ሳንቲሞችን እና የብርኖቶችን በመጠቀም መግዛት እና መሸጥን እንደጨዋታ መለማመድ
- የተለያዩ ቅርጾችን፣ ትሪያንግል፣ ክብ፣ ካሬ፣ አራት ማዕዘን፣ ግማሽ ክብ፣ ሞላላ፣ ኮከብ መለየት፤
- ዕቃዎችን፣ ግንባታዎችን፣ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ቁሳቁሶችን ደህንነት መጠበቅና ቁጥጥርን መለየት፤
- የሰውነትን አቀማመጥ ላይ ያለለውጥን ማስመሰል፣ መለየት እና ማሳየት መቻል፤
- በመሬት ላይ ስለሚገኙ ቁስአካል፣ በአየር ላይ ያሉ ቁስ አካል፣ ስለቀን እናማታ፣ ስለ የሳምንቱ ቀናት፣ የመጓጓዣ ዓይነቶች እና የመሳሰሉትን መለየት እና ለጓደኛቸው ማጋራት።
- ድራማን መተረክ እና በኪነጥበብ/እንቅስቃሴ በሰራ መከወን፤
- የተለያዩ የመጫወቻ ቁሳቁሶችን በጭቃ፣ በወረቀት፣ በቁርጥራጭ ልብስ እና በበትር ወዘተ መስራት፤

አበይት ይዘቶች

- ድምፆችን መለየት
- የፊደላት ድምፅና ቅርፅ ግንዛቤ
- ቁሶችን በአይነት መደርደርና መመደብ
- የመወሰን ችሎታ
- ለውበት ዋጋ መሰጠት
- የትላልቅ ጡንቻ መዳበር
- ደህንነትና ጥበቃ
- ቁጥር መደመር
- የቃላት እውቀት
- ቅርጾች
- ግንኙነት፣ ዝምድናና ትግበራ
- ማንበብና መፃፍ
- ንድፍ
- የድምፅን ምት ተከትሎ መንቀሳቀስ
- ሁለገብ ችሎታ
- ተክሎች
- ልኬት
- ዲጂታል ማንበብና መፃፍ
- የቦታ ግንዛቤ
- ጥበባዊ ግንዛቤ
- ፊደላትን ማንበብ
- የቁጥር ካረዲናሊቲ
- እራሰን መቻል
- የሀገር ፍቅር ሰሜት
- የተፈጥሮ እና ሰውሰራሽ አካባቢ
- ሞራል
- ቁጥሮችና ቁሶችን ማዛመድ
- ባህላዊ ቅርሶች
- ጤናማ አመጋገብ

ሳምንት ሃያ ሁለት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- ሰላምታን መለዋወጥ
- የፊት መግለጫዎችን ከመልእክት ዓላማ ጋር መረዳት
- የጾታ ልዩነት ሳይኖር ተግባራትን ማከናወን
- በአካባቢያቸው ያሉትን ነገሮች መለየት
- የግል ንፅህና መጠበቅ
- ፊደላትን ከስእል ጋር ማዛመድ
- እስከ 15 ቁጥሮችን መለየትና መፃፍ
- የቁሶችን ሰዕሎች በኮላጅ መሰራት
- የመግዛትና የመሸጥ ሂደትን መለየት

ንዑስ ይዘቶች:-

- ራስን ማስተዋወቅ
- ራስን መግለጽ
- ራስን ማወቅ/መረዳት
- አካባን መረዳት
- ጤና መጠበቅ
- ፊደላትን መጻፍ
- ቁጥሮች መጻፍ
- ጥበባዊ ግንዛቤ
- በገንዘብ መገበያየት

ተግባር 1፡- ተረት

ሀ. አቤልና የውሃ ኮዳው (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሰላምታ፣ ንፅህና፣ ፆታ፣ ስራ፣ ስሜት፣ ግብይት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የውሃ መጠጫ ኮዳ፣ የገንዘብ ኖት ሞዴል፣ የተለያዩ ስሜቶችን የሚያሳይ ሰዕል፣ ሲገበያዩ የሚያሳይ ሰዕል ወዘተ

አቤልና የውሃ ኮዳው

አቤል የሚባል ልጅ ነበር ሁልጊዜ ከእንቅልፉ ሲነቃ ፊቱን ታጥቦ ልብሱን ቀይሮ የውሀ መጠጫ ኮዳውን አጥቦ ውሀ ይሞላና ይይዘዋል። ምክንያቱም ውሃ መጠጣት ለጤና አስፈላጊ መሆኑን ስለተረዳ ቀኑን ሙሉ አቤል ኮዳውን አይለቃትም። ከእለታት አንድ ቀን አቤል ከእንቅልፉ ሲነሳ በጣም እርቦት ነበር። "እማየ!... እማዬ!" በማለት ተጣራና ቁርስ ደርሶ ከሆነ ጠየቃት። እናቱም አታክልቶች ውሃ እያጠጣች እንደሆነና አባቱን ጓዳ ገብቶ እንዲጠይቅ ነገረችው። አቤልም አባቱን ገብቶ ሲጠይቅ ሻይ እያፈላ እንደሆነና ዳቦ ገዝቶ እንዲመጣ አዘዘው። አቤልም ገና ልገዛ "እንዴ እርቦኛል እኮ" ብሎ ክፍት እርጎት ቀና ሲል አባቱን ሲመለከት አባቱ በቁጣ እንደተኮሳተረ አስተዋለ። ከዚያም "እሺ አባቴ" በማለት ገንዘብ ተቀብሎ ሄደ። ሱቅ እንደደረሰም "ደህና አደርሽ ስሚራ! 3 ዳቦ ስጪኝ" አለና ብር ሰጣት። ስሚራም "ፈጣሪ ይመስገን አቤል!" አለችውና ዳቦና መልስ ሰጠችው። አቤልም "አመሰግናለሁ! ሰላም ዋይ" ብሎ ወደ ቤቱ ሄደ። እቤቱ ሲደርስም ዳቦውንና መልሱን ለአባቱ ከሰጠ በኋላ እጁን በሳሙና ታጥቦ ቁርሱን ለመመገብ ተቀመጠ። ድንገት አቤል ከተቀመጠበት ተነሳና ወደ እቃ ቤት ገባ። ከዚያም ያቺን ከአንገቱ የማትጠፋውን የውሀ ኮዳውን በአንገቱ ላይ አንጠልጥሏት ተመልሶ ቁርሱ ጋር ቁጭ አለ። ቤተሰቦቹም በስራው ፈገግ ካሉ በኋላ እስኪበላ ከጎኑ ጠረጴዛው ላይ እንዲያስቀምጠው ነገሩት።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡- አቤል ምን ዓይነት ልጅ ነበር?

የአቤል ቤተሰቦች ምን ምን ይሰሩ ነበር?

አቤል ስሚራን ምን አላት?

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ከ1-15 ያሉ ቁጥሮችን ደጋግሞ መፃፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁጥር፣ ሰላምታ፣ በአካባቢ የሚገኝ ቁስ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

* ከ1-15 ያሉ ቁጥሮችን በመከፋፈል በአከባቢያቸው ካሉ ቁሶች (የቁስ ስዕል) መስጠት እና ቁስና ቁጥር እንዲቆጥሩ ማድረግ፤

* በመቀጠል ህፃናቱ ቁጥሩን ደግመው እንዲፅፉ የመለማመጃ ደብተራቸውን እንዲሁም ተጨማሪ ወረቀቶችን በመጠቀም በመጀመሪያ በክፍል ውስጥ ያሰሯቸው፡

* እንዲሁም እቤታቸው ደግመው እንዲሰሩ ያድርጉ።

* ህፃናቱ የሚሰሩትን ስራ ለመከታተል በሚዞሩበት ጊዜ ከህፃናቱ ጋር ሰላምታ እየተለዋወጡ ይሁን።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቁጥር ካርድ፣ የቁጥር ቻርት እና ሞዴል፣ በአከባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶች ስዕል/ሞዴል፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣ መለማመጃ መጽሃፍ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ስንት ቁጥር ጻፋችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* የህጻናትን ሥራ ዞረው በመመልከት ያበረታቷቸው።

ለ. ፊደላትን ከስዕል ጋር ማዛመድ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ስሜት፣ ፊደላት፣ ንፅህና፣ ግብይት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

* ቀድሞ የተማሩዋቸውን ፊደላት ከንፅህና ቁሰቁስ፣ ስሜት ከሚገልፁ ስእሎች እና ግብይትን ከሚገልፁ ስእሎች ጋር በፍላሽ ካርድ ተዘጋጅቶ እንዲያዛምዱ በክፍል ውስጥ ያሰሯቸው።

* በመቀጠል እቤታቸው (ምሳሌ፡- ደ-ደስታን የሚያሳይ ስዕል፣ ብ_ የብር ኖት የሚያሳይ ስዕልና ወዘተ) ቦታ በመቀያየር ያዛምዱ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደልና የስእል ካርድ፣ ሞዴል የተቀረጹ ፊደላት ፣የገንዘብ ስእል፣ ሴሜት የሚገልፁ ስዕሎች፣ ንፅህና መጠበቂያ ቁስ ሞዴል፣ እርሳስ፣ ደብተር

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምንን ከምን ጋር እንዳዛመዱና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* የህጻናትን ሥራ ዞረው በመመልከት ያበረታቷቸው፡፡

ሐ. የተለያዩ ቁሶችን በኮላጅ መስራት (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - በአካባቢ የሚገኙቁሶች፣ ኮላጅ ስራ፣ ስላምታ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ስርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

* ህፃናቱን በቡድን በመክፈል በአካባቢ ያሉ ቁሶችን ኮላጅ አሰራርን በመጠቀም በክፍል ውስጥ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል የሰሩትን በየቡድናቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ ሲያቀርቡ ለክፍሉ ህፃናትና ለተማሪዎች እና ለእርሶ ስላምታ ከተለዋወጡ በኋላ የሰሩትን ኮላጅ እያሳዩ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠልም እቤታቸው ከወለጆቻቸው ጋር ሰርተው እንዲያመጡ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ወረቀት፣ ኮላ፣ የተለያዩ በካባቢ ያሉ ቁሳቁሶች ስእሎች/ሞዴል ለኮላጅ ማዘጋጃ የሚሆን እቃና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን እነደሰሩና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* የህጻናትን ሥራ ዞረው በመመልከት ያበረታቷቸው፡፡

ተግባር 3፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ትዕዛዝ አዳምጦ ምላሽ መስጠት (5 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- በአካባቢ ያሉ ቁሶች፣ ቁጥር፣ ፊደላት፣ ስላምታ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ስርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

የጨዋታውሂደት፡-ሕፃናቱን ክብ ማሰራትና ማስቀመጥ በመቀጠልም በመሀከላቸው ተረጴዛ ላይ የተለያዩ ህፃናቱ በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን ቁሶች ፊደላትና ቁጥሮች ማስቀመጥ በመቀጠልም የተወሰኑ ልጆችን እንዲቆሙ ማድረግና ቆመው ለተቀመጡት ህፃናት ሰላምታ ያቀርቡ ቀጥሎ እርዎ መልእክት ያስተላልፉላቸው እና እንዲያዳምጡ ማድረግ ለምሳሌ ከተቀመጡት ቁስ ፊደልና ቁጥር (5 ቁጥር፣ እርሳስ፣ ፊደል ‹ቺ›) እንዱን በመጥራት ፈልገው እንዲያነሱ ማድረግ ቀድመው ያነሱ ጨዋታውን ይቀጥላሉ ያላነሱ ይቀመጡና ሌሎች ልጆች ይተካሉበዝህ መሰረት ሁሉንም ህጻናት ደጋግመው ማሰራት፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የተለያዩ ቁሶች ሞዴል፣ የቁጥርና ፊደል ሞዴልና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን እንዳደረጉና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* የህጻናትን ሥራ ዘረው በመመልከት ያበረታቷቸው፡፡

ተግባር 4፦ ውይይት

ሀ. ስዕል እያዩ መወያየት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ሰላምታ፣ ስሜት፣ ተግባራትን እኩል ማከናወን፣ ጾታ

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

* ህፃናቱን በቡድን ከፍለው ያስቀምጧቸው፡፡ ቀጥሎ በየቡድናቸው ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ የተለያ ስሜትን የሚገልፁ ምስሎችን እና ወንድና ሴት የተለያዩ ስራዎችን ያለ ፆታ ልዩነት ሲሰሩ የሚያሳዩ ስዕሎችን እየተመለከቱ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በውይይታቸው መሀልም ሀሳባቸውን እንዲናገሩ በየቡድኑ በመገኘት ይጠይቋቸው፡፡ በመጨረሻም እቤት ሄደው ከወላጆቻቸው ጋር ተወያይተው በመምጣት እንዲያቀርቡ እድል ይስጧቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

-የተለያየ ስሜትን የሚገልፁ ምስሎች፣ ወንድና ሴት የተለያዩ ስራዎችን ሲሰሩ የሚያሳይ ስዕል/ንቀሳቃሽ ምስል

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የደስታ ስሜት፣ የሃዘን፣ የንዴት... ስሜት እንዴት ይገለፃልና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 5፦ መዝሙር

ሀ. ጓደኞቼ ሆይ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ስሜት፣ ጤና፣ በአካባቢ ያሉ ነገሮች፣ ስራ

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፦

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የተደሰተ ሰው ስዕል፣ በዛፍና በአበባ የተከበበ ሰፈር ስዕል፣ ሴቶችና ወንዶች ስራ ሲሰሩ የሚያሳይ ስዕል፣ የንፅህና አጠባበቅ የሚያሳይ ስዕል፣ጂፓስ፣ ሞንታርቦ፣ ሰልክ

መዝሙር 1:- ጓደኞች ሆይ

ጓደኞቼ ሆይ ሰላም ልበላችሁ
በፊታቹ ላይ ይታያል ደስታቹ
አካባቢያችን እንዴት ያምራል
ዛፎች አበቦች ከበውታል
ሴቶች ተነሱ ዛሬ በጠዋት
ተክሎችን ዉሃ ለማጠጣት
ወንዶች ተነሱ ዛሬ በጠዋት
ቤትና ግቢን ለማፀዳዳት
ልጆች እንጠብቅ ጤናችንን
ሁሌ እንታጠብ እጃችንን።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 6፦ የመስክ ጉብኝት

ሀ. አካባቢን መጎብኘትና ቁሶችን ማወቅ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- አካባቢ፣ የተለያዩቁሶች፣ ሰላምታ፣ ንጽህና

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኘት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ህጻናትን ወደውጭ በመውሰድ በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን እንዲጎበኙ ያድርጓቸው። የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ጉብኝቱን ተሳታፊ ያድርጉ። ህጻናት በጉብኝቱ ወቅት ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን እንደተመለቱና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። ሁሉም ህጻናት ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ሳምንት ሃያ ሶስት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- አስጨናቂ ስሜትን እና ግፊቶችን መቆጣጠር
- የግልን ፅህናን መጠበቅ
- የሽንት ቤት አጠቃቀምን እና ቆሻሻ በአግባቡ ማስወገድን መገንዘብ
- በሰዎች መካከል ያሉ የጋራ የሆኑና ያልሆኑ ልዩነቶችን መገንዘብና ማክበር
- የታወቁ ታሪኮችን በመዝሙርና በድራማ አስመስሎ መተግበር
- ለተለያዩ ትዕዛዝና መልዕክት ምላሽ መስጠት
- እስከ 15 ቁጥሮችንመፃፍ
- የተለያዩ መጫዎቻዎችን መሰራት

ንዑስ ይዘቶች:-

- ራስን መቆጣጠር
- ጤናን መጠበቅ
- የራስ አከባቢ እንክብካቤ
- ማህበራዊ ግንዛቤ
- የፈጠራ አገላለጽ
- ርትመት መገንዘብ
- ቁጥሮች መጻፍ
- ቅድመ ምህንድስና ክህሎት

ተግባር 1፡- ተረት

ሀ.ሀጎስና ጎረቤቶቹ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ንፅህና፣ የሰዎች ልዩነት፣ ስሜት መቆጣጠር፣ አካባቢ እንክብካቤ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መስረት ያውሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፅዳት እቃዎች ምስል/ሞዴል (መጥረጊያና መወልወያ)፣ ፅዱ እና ቆሻሻ አካባቢን የሚገልፅ ስዕልና ወዘተ

ሀጎስና ጎረቤቶቹ

በድሮ ጊዜ በአንዲት መንደር የሚኖር ሀጎስ የሚባል በጣም ንፅህና የሚወድና ጤናውን የሚጠብቅ ሰው ነበር፡፡ እሁል ጊዜ ቤቱንና ግቢውን በአግባቡ ካፀዳ በኋላ ከግቢ ውጪ ያለውን አካባቢ ያፀዳል፡፡ ነገር ግን ስፊ በመሆኑ በጋራ መፀዳት እንዳለበት ያምንና ከእለታት አንድ ቀን ጎረቤቶቹን በመጥራት በጋራ ማፅዳት እንዳለባቸው ይነግራቸዋል፡፡ ነገር ግን የተወሰኑት ሲሰማሙ የተወሰኑት ደግሞ አልተሰማሙም፡፡ ሀጎስም ባልተሰማሙት ሰዎች በጣም ተናደደ፡፡ ሊጣላቸው ፈለገና እራሱን በመቆጣጠር ምክንያታቸውን ጠየቃቸው፡፡ እነሱም ያላቸው ጊዜ በቂ ስላልሆነ በፕሮግራም እና በተመቻቸው ቀን ማፅዳት እንደሚችሉ አስረዱት፡፡ በመጨረሻም ምክንያታቸውን ተረድቶ በሀሳቡ ተሰማምተው በሚመቻቸው ቀናት ለማፅዳት ፕሮግራም አወጡ፡፡ የሀጎስ ጎረቤቶችም በሀሳቡ በጣም ተደስተው አመሰገኑት፡፡ ሀጎስም “ከዚህ በኋላ ሰፈራችን ንጹህ ሰለሚሆን ልጆቹም በጥንቃቄ ቆሻሻ ሳይጥሉ እንዲጫወቱ መንገር አለብን” አላቸው፡፡ ሁሉም ልጆቹን ለመምከር ተሰማምተው የእለቱ ተረኞች ሰፈራቸውን አፀዱ ይባላል፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ሀጎስ ምን አደረገ?

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ከ1-15 ያሉ ቁጥሮችን በቃል መፃፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ትዛዛት፣ ምላሽ መስጠት፣ ቁጥር፣ ስሜት መቆጣጠር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

- በቅድሚያ ወረቀት፣ ደብተርና እረሳስ ያዘጋጁ እና ለሁሉም ህፃናት ይስጡ፡፡
- ሁሉም ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ እና የእለቱን ተግባር ማስተዋወቅ ማለትም ከ1-15 ያሉ ቁጥሮችን ለሶስት በመከፋፈል (ከ1 እስከ 5፣ ከ6 እስከ 10 እና ከ 11 እስከ 15) ህፃናቱ ቁጥሩ ሲነገራቸው በአግባቡ በማዳመጥ ተገቢ የአፃፃፍ ስርአትን ተከትሎ መጻፍ መቻል ነው፡፡
- በሚሰሩበት ሰዓትም አስጨናቂ ስሜት ሲገጥማቸው መቆጣጠር እንዲችሉ ይንገሩዋቸው ምሳሌ የተነገራቸውን ቁጥር ሳይሰሙ ቢቀሩ ወይንም መፃፍ ሲያቅታቸው ተረጋግተው ከጓደኞቻቸው የመመልከት፣ በትህትና መምህራቸው እንዴ ድገሙልኝ የመሳሰሉ አመረጮችን እንዲወስዱ መንገር፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እርሳሰና የመለማመጃ ደብተር

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ስንት ቁጥር ጻፋችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* የህጻናትን ሥራ ዞረው በመመልከት ያበረታቷቸው፡፡

ለ. የግል ንጽህና አጠባበቅ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ንጽህና፣ ቁጥር፣ ትእዛዝ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

- አሻንጉሊት የወንድና ሴት ማዘጋጀት፣ የጥርስ ቡሩሽ እና ሳሙና፣ ሻንፖ፣ ሳሙና፣ ውሃ፣ መዘፍዘፊያ፣ የውሃ መያዣ ባልዲ/ሳፋ/ጀግ፣ መቅጃ ኩባያ/ትንንሽ የፕላስቲክ ኩባያዎች፣ ፎጣ፣ የጸጉር ማበጠሪያ፣ ቅባት... ማዘጋጀት (ሁሉም ቁሶች በአንድ ጊዜ ሁለት ህፃናትን ማሰራት የሚችል መሆን አለበት)
- በቅድሚያ እርሶ የአሻንጉሊቶቹን ጥርስ ማጽዳት፣ ገላ ማጠብ፣ ጸጉር ማጠብ፣ በፎጣ ማድረቅ፣ ቅባት መቀባት፣ ልብስ መቀየር፣ የወለቀውን ልብስ ቆሻሻ ማስቀመጫ ውስጥ ማስቀመጥን ያሳዩአቸው፡፡
- ቀጥሎ ህፃናቱ ትእዛዙን ተከትለው ሁለት ሁለት እየሆኑ በእርሶ መሰረት እንዲያከናውኑ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ወንድና ሴት አሻትንጉሊ፣ የጥርስ ብሩሽ እና ሳሙና ፣ ሻንፖ፣ ሳሙና፣ ውሃ፣ መዘፍዘፊያ፣ የውሃ መያዣ ባልዲ/ ሳፋ/ጀግ፣ ውሃ መቅጃ ኩባያ/ትንንሽ የፕላስቲክ ኩባያዎች፣ ፎጣ፣ የጸጉር ማበጠሪያ፣ ቅባትና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ተግባር ፈጸማችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* የህጻናትን ሥራ ዞረው በመመልከት ያበረታቷቸው፡፡

ተግባር 3፦ በሥራ መማር

ሀ. የግል ንጽህና መጠበቅና የቆሸሹ ቁሶችን ማጽዳት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፊደል፤ ቁስ፣ ቃላት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

 በቅድሚያ በክፍላችን ውስጥ ያሉ ቁሶችን እንዴት እንደምናፀዳ መንገር

 ቀጥሎ ቁሶችን ለማጽዳት የሚያገለግሉ ፎጣ፣ ውሃ፣ እስፖንጅ ያዘጋጁ

 ቀጥሎ ህጻናቱን በቡድን ይክፈሉ ከዚያም በክፍሉ ውስጥ ያሉትን የደብተር መደርደሪያ ፣ የምሳ እቃ መደርደሪያ፣ የመጫወቻ ማእዘናት እንዴት ማጽዳት እንደሚችሉ አሳይተው እነሱም ተራ በተራ የተሰጣቸውን እንዲያጸዱ ያድርጉ

 ተግባሩን በአግባቡ ማከናወናቸውን ለማየት በአንድ ጊዜ አንድ ቡድን ብቻ የሚሰራ ይሆናል

 የጽዳት ቅደም ተከተል በጀመሪያ ቁሶቹ ከነበሩበት ማንሳት ያስፈልጋል (ምሳሌ ደብተሮቹን ወደሌላ ጠረጴዛ መውሰድ ቀጥሎ በእስፖንጅ ውሃ ነክረው ከጨመቁ በኋላ አዋራውን ማንሳት ቀጥሎ በሌላ ውሃ ተነክሮ በተጨመቀ ጨርቅ መወልወል፣ በመጨረሻ በደረቅ ፎጣ/ጨርቅ ማድረቅ

 ቁሶቹን በደረቅ ጨርቅ/ፎጣ እያወለወሉ ቦታው ላይ መመለስ ሲጨርሱ አከባቢውን በመጥረጊያ አጽድተው ቆሻሻውን መጣልና የተጠቀሙበትን እስፖንጅና ጨርቅ/ፎጣ አጣጥበው እና እጃቸውን በውሃና በሳሙና አጽድተው ለቀጣይ ተረኛ ስረክባሉ፤

 ሲሰሩ ያጨነቃቸው ነገር ኖሮ የመበሳጨት ስሜት ካዩባቸው ቀረብ በማለት የሚሰሩትን ተቀብለው እያሳዩ ዘና የሚያደርግ ነገር መንገረ ለምሳሌ አሁን ከጓደኞቻቸው ጋር እየተዝናኑ በመቁጠር ተግባራትን እንዲያከናውኑ አድርገው እኔዴት ስሜታቸውን ተቆጣትረው ነገሮችን መከናወን እንደሚቻል አሳይተው ተግባሩን እንዲቀጥሉ ማድረግ

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

- ፎጣ/ጨርቅ፣
- እስፖንጅ፣
- ውሃ ማቅረቢያ እቃ፣ መጥረጊያ፣ የቆሻሻ ቅርጫት፣ ሳሙናና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የግል ንጽህናችንን እንዴት እንጠብቃለንና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ።

ለ. ከጭቃና የወዳደቁ ቁሶች መጫዎቻ መስራት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ንጽህና፣ መጫወቻ፣ ታሪክ፣ አስጨናቂ ስሜት

የማስተማሪያ ዘዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

በወዳደቁ ቁሳቁስ ማለትም ከሃይላድ የፕላስቲክ ጠርሙሶች፣ የፒላስቲክ ኩባያዎች ጭቃ፣ በተቦካ ወረቀት… በክፍል ውስጥ የተለያዪ መጫወቻዎችን (ቤት፣ አሻንጉሊት፣ መኪና፣ አልጋ፣ወንበር…) እና ታሪክን የሚገልፁ ግንባታዎችን ሰርቶ በማሳየት (አክሱም ሃውልት ፣ ተራራ፣ ዋሻ፣ የሙዚቃ መሳሪያ…) እንዲሞክሩ ማድረግ፤ በመቀጠል እቤታቸው ሰርተው እንዲያመጡ መንገር፤ በሚሰሩበት ወቅትም አስቸጋሪ ሁኔታ ሲገጥማቸው መረጋጋትና ከወላጆቻቸው እርዳታ በመጠየቅ ሰርተው እንዲያመጡ ይንገሯቸው፡፡

ትምህርት ቤትም ሆነ እቤታቸው ሰርተው ሲጨርሱ የሰሩበትን እቃዎች አጽድተው እቦታው መመለስ፤ የሰሩበትን ሰፍራ ማጽዳት እና የራሳቸውን ንጽህና መጠበቅ እንዳለባቸው መንገር አስፈላጊ ነው፡፡ እቤት ውስጥም ተመሳሳይ ነገር ማድረገቻውን ከወላጆቻቸው በመጠየቅ ያረጋግጡ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ወረቀት፣ ኮላ፣ እጥሚት/እብሲት፣ በአካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ቁሳቁስ፣ ጭቃ፣ የተቦካ ወረቀት፣ የሃይለድ ጠርሙስ ፕላስቲክ፣ ጄሶ እና የተለያዩ መጠጦች ታሽገው የሚሠጡባቸው ቁሶች/ኩባያዎችና ወዘተ…

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምንና እንዴት ሰራችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡
* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 4፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ምን ልታዘዝ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ ፊደል፣ ትዛዝ፣ ፅዳት፣ ታሪክ

የማስተማሪያ ዘዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

እንደንግስት መቀመጥና ህፃናቱን ተራ በተራ እየመጡ ትእዛዛትን እንዲተገብሩ ማዘዝ (በርከክ ብለው ንግስት ወይ ምን ልታዘዝ ለልጆቼ ከአንድ እስከ አምስት ቁጥር ጽፈህ/ሽ/ አስተምርልኝ፣ ፊደላትን እንዲፅፉ፣ ለህዝቤ ማስታወሻ ሃውልት ሰሩ፤ የፅዳት እቃዎችን እንዲያመጡና የጽዳት ቅደም ተከተልን ተከትለው እንዲያጸዱ፣ ከዚህ በፊት የሰሙትን ታሪክ ለህዝቡ እንዲናገሩ በማዘዝ የጫወታውን ሂደት ካሳዩ በኋላ ከህፃናቱ መካከል ንግስትና ንጉስ የሚሆኑ ተማሪዎችን በየተራ በመምረጥ በተመለከቱት መሰረት እንዲጫወቱ ማድረግ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ከትዕዛዛቱ ጋር የሚሄዱ ነገሮች (ለምሳሌ - የፅዳት እቃዎች ሞዴል፣ የቁጥርና ፊደል ሞዴል (በአሸዋ የተቀረፀ)፣ ማርከር፣ ቾክ፣ እርሳስ፣ ወረቀት…

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

* ንግስቲቱ ምን ብላ አዘዘቻችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 5፦ ውይይት

ሀ. የግል ንፅህና፣ የቆሸሹ ቁሶችን ማጽዳት እና አስጨናቂ ስሜትን መቆጣጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ የግል ንጽህና፣ አስጨናቂ ሰሜት፣ ቁሶችን ማጽዳት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ስለግል ንጽህና አጠባበቅ ልምዶች ሶስት ቡድን፣ የቆሸሹ ቁሶችን እንዴት እናጸዳለን፣ እና አስጨናቂ ስሜትና ግፊቶችን እንዴት መቆጣጠር አለብን፣ በሚሉ ርዕሶች ላይ የራሰዎን ሀሳብ ያጋሯቸው፡፡

* በመቀጠል ሁሉም ህጻናት በርዕሱ ላይ ሀሳብ እንዲሰጡ ይጋብዟቸው፡፡

* የህጻናትን ሀሳብ እርሰዎ በሚሰጡት መጠናከሪያ ሀሳብ ይሰብስቡ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የተለያየ ከውይይቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰዕላዊ መገለጫዎችና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የደስታና አስጨናቂ ሰሜቶችን እንዴት መቆጣጠር ይቻላልና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ሀ. ትዛዝ፣ ታሪክ፣ የሰዎች ልዩነትና አንድነት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ የግል ንጽህና፣ አስጨናቂ ሰሜት፣ ቁሶችን ማጽዳት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ በፊት ሰለሰሙት የተለያዩ ታሪኮች እና በሰዎች መካከል ያሉ የጋራ የሆኑና ያልሆኑ ልዩነቶችን ለምሳሌ የድሮ ሰዎች ትዕዛዝ የአሁን ሰዎችትዕዛዝ፣ ሰለ ሀገራቸው የተለያዩ አካባቢዎች የሚያውቁት ታሪክ፣ አንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚደረግ ነገር እና ሌላ ቤተሰ ቤት የሚደረግ ነገሮች ለምሳሌ (በዓል አከባበር፣ አመጋገብ …) በመሳሰሉት አንድነት እና ልዩነት ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በውይይታቸው መሀልም ሀሳባቸውን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

በተለያየ ቦታ የሚገኙ የሀገራቸው ታሪኮች፣ በማህበረሰብ መካከል ያሉ ልዩነቶችና አንድነትን የሚገልጹ ምስሎች

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* በታሪኮቹ መካከል ስላለው ልዩነትና አንድነትና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡



ተግባር 6፦ መዝሙር

ሀ. አድዋ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ታሪክ፣ ስሜት፣ ትዛዝ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

አድዋን የሚገልፁ የተለያዩ ስእሎችና ተንቀሳቃሽ ምስሎችና ሌሎች

መዝሙር 1፦ አድዋ

ኢትዮጲያ ሀገሬ የኛ ኩራት
የቆየችልን ባባቶች ጀግንነት
ያልተበገሩ ለውጪ ሀገራት
ከፍለዋልኮ ብዙ መስዋዕት
ስጠ ንጉሱ አጭር ትዛዝ
ግድ ነውና መተጋገዝ
አስጨናቂ ስሜት ግፊት ቢገጥማቸው
ሂወታቸውን ለኛ ሰጡ ላገራቸው
የአድዋ ድል ሁሌም ይወሳል
ታላቅ ጀግንነት እንዴት ይረሳል፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- አድዋ ለሀገራችን ምኗ ነው?

ለ. እኛ አንድ ነን (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ታሪክ፣ የጋራ ነገሮች፣ ልዩ ነገሮች፣ ትእዛዝ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የብሄር ብሄረሰቦች አለባበስ፣ አነጋገር የሚገልፁ የተለያዩ ሰእሎችና ተንቀሳቃሽ ምስሎችና ሌሎች

መዝሙር 2:- እኛ አንድ ነን

ምንም ብንለያይ በአለባበሳችን
ምንም ብንለያይ በአነጋገራችን
ብዙ ነገር አለን የሚያመሳስለን
በፍቅር በሰላም በጋራ የሚያኖረን
ጀግንነትም አለን በጋራ የሰራነው
ታሪክ አለን እኮ በጋራ ያቆየነው
የአባቶቻችንን ትዕዛዝንን ትዕዛዝ ተቀብለን
ሀገርን ወደፊት እናሻግራለን
ለነገው ትውልድም ታሪክ እናኖራለን
መለያችን ትንሽ እኛኮ አንድ ነን፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ሰእዎችን አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድ ነው?

ተግባር 7፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. የመጸዳጃ ቤት አጠቃቀም (1 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ስሜት መቆጣጠር፣ ትዛዝ፣ በሰዎች መካከል ልዩነት፣ ንፅህና

የማስተማሪያ ዜዴ:- ስርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

 በቅድሚያ ህፃናቱን ከክፍል ውጪ ይዞ በመውጣት ሁሉም ነጣ እና የፈለጉትን ጨዋታ መጫወት እንደሚችሉ መንገር፤

 ቀጥሎ ሲጫወቱ በመካከላቸው አለመግባባት ቢፈጠር እራሳቸውን በመቆጣጠር ችግሩን መፍታት ካልቻሉ ደግሞ በቅርባቸው ለላው ትልቅ ሰው መንገር እንደሚገባ እንጂ መጣላት ተገቢ አለመሆኑን አስረግጠው ይንገሩ፤

 ሲጫወቱ የሰዎችን ልዩነት አክብረው መጫወት እንዳለባቸው ይንገሯቸው፡፡ በፍጥነት ሊለያዩ ይችላሉ፣ ጨዋታ በማወቅ ሊለያዩ ይችላሉ፤ ስለዚህ ያንን አክብረው እንዲጫወቱ ትእዛዝ በመስጠት እንዲጫወቱ ማድረግ፤

 እርሶ በአግባቡ ይከታተሉ፤ የጨዋታው ክፍለ ጊዜ ሲያበቃ የሴትና የወንድ መጸዳጃ ቤት ህፃናቱን በቡድን እያረጉ በመውሰድ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ያሳዩአቸው፡፡ የተወሰኑ ህፃናትም በተነገረው መሰረት እየሚከሩ እንዲያሳዩ ያድርጉ ከመጸዳጃ ቤት መልሰ ሁል ገዜም እጆቻቸውን በሳሙና ታጥበው እንዲገቡ ማድረግ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ተለያዩ የውጪ መጫዎቻዎች፣ ሳሙና፣ አመድና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የመጸዳጃ ቤት ስንጠቀም ምን ማድረግ አለብንና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ሁሉም ህጻናት የጨዋታው ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ቀርበው ያረጋግጡ፡፡

ሳምንት ሃያ አራት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ:- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- ድምፆችን ከድምፅ ምንጭ ስእሎችጋርማዛመድ
- የፊደላትን ድምፅና ቅርፅ መለየት
- ከ 6-8 ቁሶችን በቅርፅ በመለየት መመደብ
- የተሰጣቸውን ፊደላት መፃፍ
- ከተሰጣቸው ሁለት አማራጮች መካከል አንዱን መምረጥ
- ዘፈንና ውዝዋዜን መዳኘት ይለማመዳሉ
- ከጓደኞቻቸው ጋር ከ4-6 ፈታኝ እንቅስቃሴዎችን መስራት
- የጥንቃቄናየ ደህንነት ምልክቶችን መግለፅ
- እስከ 5 ቁሶችን በመጠቀም መደመር

ንዑስ ይዘቶች:-

- ድምፆችን መለየት
- የፊደላት ድምፅ
- ነገሮችን በአይነት መለየትና መመደብ
- ፊደላትን መፃፍ
- ውሳኔ የመወሰን ክህሎት
- ለውበት ዋጋ መስጠት
- የጥላልቅ ጡንቻ መዳበር
- ደህንነትና ጥበቃ
- ቁጥሮችን መደመር

ተግባር 1፦ ተረት

ሀ. በቀለና አማረች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ድምፅ፣ መምረጥ፣ ጥንቃቄ

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፦

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ልጆች ስፖርት ሲሰሩ፣ ሰዎች ወንዝ ዳር ልብስ ሲያጥቡ፣የመኪና መንገድ፣ ምልክቶች … የሚያሳይ ምስል

በቀለና አማረች

በአንድ መንደር የሚኖሩ በቀለና አማረች የሚባሉ ጓደኛማቾች ነበሩ ሁልጊዜ ስፖርት ይሰራሉ ይሮጣሉ፣ ገመድይዘላሉ፣ ይጎትታሉ፣ ተራራ ይወጣሉ ይወርዳሉ፣ ጎማ በማሽከርከር ይሮጣሉ፡፡ ነገር ግን አማረች ጥንቃቄ ማድረግና እራሷን ከአደጋ መጠበቅ ትረሳለች፡፡ በቀለም “እባክሽ ጓደኛዬ ማንኛውንም እንቅስቃሴ ስናደርግ እራሳችንን ከአደጋ መጠበቅ አለብን እኮ” በማለት ይመክራታል፡፡ ከእለታት አንድ ቀን በመኪና መንገድ አጠገብ በመሮጥ ላይ እያሉ አስፓልቱን እሩጠን እንሻገር በማለት ልትሮጥ ስትል በቀለ አስቆማትና “መኪኖች እኮ እያለፉ ነው፤ የመንገደኞች መብራት አረንጓዴ በርቷል” በማለት ምልክቱን አሳያት፡፡ በመቀጠልም “መንገዱን ለመሻገር ሁለት አማራጭ አለን እኮ፤ ወይ ቀዩ መብራት ሲበራ በዜብራው መሻገር ወይንም በላይ በኩል በድልድዩ ላይ መውጣት እንችላለን” በማለት እንዲትመርጥ ነገራት፡፡ አማረችም በድልድዩ ላይ ደረጃውን በመውጣት እንሻገር በማለት መረጠች፡፡ ከዚያም በድልድዩ በኩል መንገዱን ተሻገሩና ወደመንደሩ ውስጥ ገቡ፡፡ ከዚያም መንገዳቸውን ቀጠሉ፤ ነገር ግን ትንሽ ዛፎቹ ጋር እንረፍ ብለው አረፍ እንዳሉ አማረች የሆነ ድምጽ እየሰማሁ ነው አንተስ ይሰማሃል አለችው፡፡ ይሄማ የወንዙ ድምፅ ነው እኮ ባለፈው ከወንድሜ ጋር መጥቼ እየሰማሁት ነበር፡፡ ሲወርድ የሚያወጣው ድምጽ ነው አላት፡፡ እረ ሌላም ድምፅ አለ ስትለው እንስሳቶች ናቸው፤ ስንጠጋ እናያቸዋለን አላት፡፡ እንደ ደረሱም ወንዙ አጠገብ ዳር ላይ ሰዎች ልብሳቸውን ሲያጥቡ እንስሳቶችም ውሀውን ሲጠጡ ተመለከቱ፡፡ አየሽ የሰማነው ድምፅ የላሞቹን የበሬዎቹንና የበጎቹን ነው በማለት አሳያት፡፡ አማረችም ወደወንዙ ገብታ መጫወት ፈለገችና በቀለ እራሳችንን ከአደጋ መጠበቅ አለብን ያላትን በማስታወስ እና ወንዙ ሊወስዳቸው እንደሚችል በማሰብ ተወችው፡፡ በመጨረሻም ወደየቤታቸው ተመለሱ፡፡

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፦ በቀለ አማረችን ምን ብሎ መከራት?

ለ. ፋጡማና እያሱ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ድምፅ፣ መምረጥ፣ መደመር፣ ደህንነት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

_ ልጆች ስፖርት ሲሰሩ፣ ሰዎች ወንዝ ዳር ልብስ ሲያጥቡ፣

_ የመኪና መንገድ፣ ምልክቶች ... የሚያሳይ ምስል

ፋጡማና እያሱ

በአንድ ሰፈር የሚኖሩ ፋጡማና እያሱ የሚባሉ ጓደኛማቾች ነበሩ። ሁል ጊዜ አብረው ይጫወታሉ። ከእለታት አንድ ቀን ደመናማ በሆነ አየር በጫወታ ላይ እያሉ የመብረቅ ድምፅ ሰሙ። ፋጡማም ሰማከው ከሰማይ ላይ የመብረቁን ድምፅ ዝናብ ሊዘንብ ስለሚችል ወደ ቤታችን እንግባ አለችው። እያሱም ለምን እኛ ቤት ገብተን እንጫወትም አላትና ወደ እነሱ ቤት መሄድ ጀመሩ። እቤት እንደ ደረሱም ዝናቡ ዘነበ። እያሱም እናቱን ተጣራና ሰላምታ አቀረቡ። የእያሱ እናትም ሰላም ልጆች አለቻቸውና እስቲ ቁጭ በሉ እና ጨጨብሳና ሽሮ አለ ላምጣላቹ ብሉ አሏቸው። እያሱም እኔ ጨጨብሳ ነው ምፈልገው ሲል ፋጡማ እኔ እንጀራ በሽሮ ይሻለኛል አለች። ከዚያም እጃቸውን በሳሙና ታጥበው የቀረበላቸውን ምግብ ተመገቡ። ሲጨርሱ የተመገቡበትን እንስተው ለምግቡ አመሰገኑ። ከዚያም እያሱ የተለያየ መጫወቻዎቹን አውጥቶ ተመሳሳይ ቅርፅ ያላቸውን መጫወቻዎች በመደዳ በመደርደር መጫወት ጀመሩ። በመቀጠል ፋጡማ ዝናቡ ሰላባራ ውጪ ወጥተን እንጫወት አለችው። እያሱም እሺ ጫማ ልቀይር አላትና ወደጫማ ማስቀመጫ አብረው ሄዱ። ፋጡማም ስንት ጫማ ነው ያለክ አለችው ጫማዎቹን እየተመለከተች። እያሱም 3 ሽፍንና 2 ክፍት ጫማዎች አንድላይ 5 ነው ያሉኝ አላት። ፋጡማም እኔ ደግሞ 2 ክፍትና 2 ሽፍን አንድላይ 4 ጫማዎች ነው ያሉኝ አለችውና እያሱም ሽፍን ጫማ አድርጎ ተያይዘው ወጡ። ነገር ግን ውጪ ሲወጡ የሚጫወቱበት ሜዳ በጎርፍ ስለተሞላ አደጋ ሊያጋጥመን ይችላል በማለት ወደ ቤታችን እንግባ ተባብለው ተስነባበቱ።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡- ፋጡማ ምን ዓይነት ጫማዎች አሏት?

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ከ1-5 ያሉ ቁጥሮችን በቁስ መደመር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ደህንነት፣ ጥንቃቄ፣ ቁጥር፣ ቅርጾች

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

- በቅድሚያ ከ1-5 ያሉቁጥሮችን የሚወክል የደህንነት ምልክቶችን እና የጂኦሜትሪ ቅርፃችን ስእል በመስጠት፤
- ቀጥሎ ቁሶቹን እንዲደምሩ ያድርጉ፡፡
- ቁሶችን ሲቆጥሩ ለደህንነታቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይንገሯቸው፤ ህፃናት በየተራ እንዲሰሩ ያበረታቱ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቁጥር ካርድ፣ የቁጥር ቻርት፣ የደህንነት ምልክቶችን፣ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን ስእል፣ የተለያዩ ቁሳቁሶችና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ስንት ቁስ ደመራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡
* ህጻናት ተግባሩን በተገቢው ማከናወናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ለ. የፊደላት ቅርጽና ድምጽ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፊደላት፣ መወሰን፣ መፃፍ፣ ድምጽ፣ ማዛመድ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

የሳምንቱን ፊደላት (ሠ-ሡ-ሢ-ሣ-ሤ-ሥ-ሦ) ድምፅና ቅርፅ በመለየት ደግመው እንዲፅፉ በክፍል ውስጥ ያስሯቸውና በመቀጠልም እቤታቸው ደግመው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ቀጥሎ በዕቱ ፊደሎችና ከዚህ በፊት በተዋወቋቸው ፊደላት የተመሰረቱ ቃላትን የሚወክሉ ስዕሎች በየጠረጴዛቸው መስጠት፤ ከዚያ ድምፅና ስእልን ማዛመድ (ለምስሌ፡- ው - ውሻ ሠ- ሠንሠለት...በዘህ መልኩ ስእሎችን በመስጠት እርስዎ ቃሉን ሲጠሩ እነሱ ስዕሉን ያሳያሉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ካርድ/ሞዴል፣ የተለያዩ ስእሎች፣ እርሳስ፣ ወረቀትና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ምን ምን ፊደላትን ጻፋችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡
* ህጻናት ተግባሩን በተገቢው ማከናወናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ሐ. ፊደላትን በቅርጽ መመደብ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቅርፆች፣ መለየት፣ ፊደላት፣ ቅርጽ ድምጽ፣ ማዛመድ

የማስተማሪያ ዘዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱን በቡድን በመመደብ ቀጥሎ የተለያዩ የፊደል ቤተሰቦችን ቀላቅሎ መስጠት፡ በጠረጴዛቸው ላይ እየተረዳዱ ተመሳሳይ ቤተሰብ የሆኑትን እንዲለዩ ማድረግ፤ የለዩትን ፊደሎች ጮክ ብለው እንዲያነቡ ማድረግ፤ ከዚያ ከድምጹ ጋር የተገኛኘ ስዕል ከክፍሉ ውስጥ ፈልገው እንዲያዛምዱ መዳረግ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያየ ቅርፅ እና ድምጽ ያላቸው ፊደላት፣ ስዕሎች ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ምን ምን ፊደላትን መደባችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት ተግባሩን በተገቢው ማከናወናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 3፡- በፕሮጀክት መማር

ሀ. የሙዚቃ መሳሪያ መስራት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ውሳኔ፣ ድምፅ፣ ቅርፆች

የማስተማሪያ ዘዴ፡- በገለፃ፣ ሰርቶ ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

* የተለያዩ የድምፅ መሳሪያ (የሙዚቃ መሳሪያ ምሳሌ ክራር፣ ዋሽንት፣ ከበሮ፣ መሰንቆ...) መርጠው ከወላጆቻቸው ጋር ሰርተው እንዲያመጡ ያድርጉ፡፡

* ሲጨርሱ ይዘው በመምጣት የተሰረውን ለክፍሉ ህፃናት ይንገሩ፡፡

* በመጨረሻም የሰሩበትን መንገድ ከማን ጋር እንደሰሩ፣ ከየትኛው ፊደል ጋር እንደሚመሳሰል እንዲናገሩ ያርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከሚያቀርቡት ፕሮጀክት ሰራ ጋር የሚሄዱ ስዕሎች እና ቁሶችና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ስለፕሮጀክታቸው አጠቃላይ ነገር ከሚያቀርቡት ተነስተው መጠየቅ

ተግባር 4፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. መስሎ ጨዋታ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ውዝዋዜ፣ ዳኝነት፣ ውሳኔ፣ ድምፅ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

በቅድሚያ ከህጻናቱ መሀከል ሶስት ዳኛ ይምረጡ። ዳኞች ተግባራቸው የዳንሰና የዘፈን እና የሙዚቃ መሳሪያ መጫወት ውድድርን መዳኘት ነው። ቀጥሎ የውዝዋዜ ተወዳዳሪ ለብቻ፣ የሙዚቃ ተጫዋች ለብቻ እንዲሁም በውዝዋዜ የሚወዳደሩ ለብቻ ይለዩ፤ ቀጥሎ በየተራ ከዘፋኞች ሶስት ሶስት ተወዳዳሪ በማድረግ ይወዳደሩ። ከዚያ ከተወዛዋዥ እንዲሁ ሶስት ሶስት ተወዳዳሪ ያደርጋሉ። እንዲሁ ደግሞ ከሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋች ሶስት ህፃናት ያወደደራሉ። ሲወዳደሩ እራሳቸውን እና የሚያቀርቡትን ነገር ምንነት ማስተዋወቅ መቻል አለባቸው።እርሶ ዳኞችን በማገዝ ውጤት እንዲያሳውቁ ያደርጋሉ። በዚህ ክፍለ ጊዜ ካልበቃ እንዲሁ እየቀላቀሉ (ዘፋኞች፣ ተወዛዋዦች፣ እና ሙዚቃ መሳሪያ ተጫወች) እያደረጉ ሁሉም ህፃናት እንዲወዳደሩ ያደርጋሉ። ህፃናቱ ዳኞች የመወሰን አቅማቸውን መጠቀም አለባቸው እንዲሁ ደግሞ ተወዳዳሪዎች ውጤታቸውን በበጎ ጎን የመቀበል ልምድ ማዳበር አላቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ አልባሳት፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች (ከበሮ፣ ጀሪካን፣ ጽናፅል፣ ዋሽንት)፣ ጠረጴዛ፣ ወረቀት፣ የዳኞች ዱላ፣

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ምን ምን የሙዚቃ መሳሪያዎችን ተጫወታችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ተግባሩን በተገቢው ማከናወናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 5፡- ውይይት

ሀ. አደጋ የሚያደርሱ ነገሮች (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ደህንነት፣ ድምፆች፣ ውሳኔ፣ የአደገኛ ነገሮች

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* አደጋ ስለሚያስከትሉ ነገሮች በቃል ይንገሯቸው። ህጻናት ተራ በተራ እጅ እያነሱ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ያድርጓቸው። ሁሉም ህጻናት ሀሳባቸውን በትክክል መግለጻቸውን ያረጋግጡ።

የመጫዎቻና መግሪያ ቁሳቁስ፦

አደገኛ አጥር፣ መሻገሪያ መንገድ፣ የእሳት አደጋ፣ የእሳት አደጋ መኪና፣ የአንቡላንስ መኪና ስዕልና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

የውይይቱን ፍሬ ሀሳብ መነሻ ያደረጉ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለ. ፊደላትና ድምጾቻቸው (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ፊደላት፣ ድምፆች፣ ሙዚቃ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* የተለያዩ ፊደላት ፍላሽ ካርድ ያቅርቡላቸውና እያንዳንዱን ካርድ እያነሱ ልጆች የፊደሉን ስም እንዲጠሩ ያድርጓቸው። ሁሉም ህጻናት የውይይቱ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

የመጫዎቻና መግሪያ ቁሳቁስ፦

የፊደላት ፍላሽ ካርድ፣ የባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያ ስዕልና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

የምን ምን ፊደላት ድምጽ እንዳሰሙ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 6፦ የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. ጎማ መግፋትና ገመድ ጉተታ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ደህንነት፣ ምርጫ፣ እንቅስቃሴ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

* በክፍል ውስጥ ያሉ ህፃናት ጉዳት ካለባቸው ተመጣጣኝ የሆነ ጨዋታ እንዲጫወቱ ማድረግ ይኖርቦታል።

* በመሆኑም ህፃናቱን ወደውጭ ይዘው በመውጣት የአጨዋወት ህግን መንገር፣ የደህንነት ማስጠንቀቂያዎችን ማሳወቅና ጨዋተውን ማጫወት፤

ለምሳሌ፦ ሲጎትቱ እንዳይወድቁ እራሳቸውን መጠበቅ፣ ጎማ ሲገፉ እንቅፋት እንዳይጥላቸው እያዩ መሮጥ...)።

* በቅድሚያ የህፃናቱን እጅ የማይጎዳ ወፍራም ገመድ ማዘጋጀት፤

* ሁለት ቡድን ስድስት ስድስት ሴትና ወንድ አድርገው ቡድን ይመስርቱ፤

* የገመድ መጎተት ውድድር በአንድ በኩል ሶስት ሴት እና ሶስት ወንድ ፣በሌላኛውም ሶስት ወንድ ሶስት ሴት ህፃናት ተወዳዳሪ ይሆናሉ፤

* አሸናፊ ገመዱን ጎትቶ ተቃራኒውን ቡድን ወደራሱ ያስገባ ቡድን ነው፤

ጨዋታ ሁለት፡-

- ከእድሜያቸው ጋር የሚመጣጠን ሽቦ የሌለው ጎማ ማዘጋጀት፤
- መነሻ እና መድረሻ በመስመር አስምር መወሰን፤
- በአንድ ጊዜ ሶስት ተወዳዳሪ ማድርግ፤
- ጎማውን በሩጫ ሳያቋርጡ እየገፉ ፊሽካ ሲነፋ እኩል ይጀምራሉ፤ መድረሻው ጋር ደርሰው ይመለሳሉ።
- መጨረሻ ላይ የአሸናፊዎች አሸናፊ ውድድር ይደረግ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ገመድ፣ ጎማ፣ ፊሽካና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ጎማ ስትገፉና ገመድ ስትጎትቱ ምን አጋጠማችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለ. ገመድ ጉተታ፣ መሰላል ላይ መውጣትና መውረድ (1 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ *ቃላት*፡- ደህንነት፣ ምርጫ፣ እንቅስቃሴ

***የማስተማሪያ ዜዴ*፡-** ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

***የመምህር ሚና*፡-**

ህፃናቱን ወደውጭ ይዘው በመውጣት የአጨዋወት ህግን መንገር፣ የደህንነት ማስጠንቀቂያዎችን ማሰወቅና ጨዋተውን ማጫወት።

- ቢያንስ አሰር የሚሆን መያዣ ያለቻውን የአስፖርት እንቅስቃሴ መሰሪያ የሚሆኑ የመዝለያ ገመድ ማዘጋጀት
- ህፃናቱ በጨዋታ ወቅት ሊያጋጥናቸው ከምችሉ ድንገተኛ አደጋዎች እየተጠነቀቁ አደጋ የማያስከትል አጨዋወትን በመምረጥ እንዲጫወቱ ያድርጉ፤
- አሰር ህፃናት በአንድ ጊዜ ይዘላሉ የሚዘሉት አሰራ አምስት ጊዜ ነው፤
- ሳያቋርጡ እስከመጨረሻ የቆዩት አሸናፊ ይሆናሉ፤
- ቀጥሎ መሰላል መውጣት በጊያቸው ላይ የመጫወቻ መሰላል ላይ በጥንቃቄ ወቶ የመውረድ ውድድር ለመጀመር ፊሽካ ይነፋል።
- ፊሽካ ሲነፋ ወቶ ቀድሞ የወረደ አሸናፊ ይሆናል።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ገመድ፣ ምእሰላል፣ ፊሽካና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ስትጫወቱ ምን አጋጠማችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 7፡- መዝሙር

ሀ. ራሳችንን እንጠብቅ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - አደጋ፣ ጥንቃቄ፣ ምርጫ፣ ውሰኔ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የአደገኛ አጥር ምስል፣ የእሳት አደጋ መኪናና ወዘተ

መዝሙር 1፡- ራሳችንን እንጠብቅ

የአደጋ ምንጭን ለይቶ ማወቅ
አደጋው ሳይደርስ ራስን መረበቅ
ጡሩንባውን በጣም ከነፋ መኪናው
መንገዱ የኛ አይደለም የሱ ነው የሱ ነው
አላርሙን ካሰጪኸ መኪነው ትልቁ
እሳት አደጋ አለ መንገዱን ልቀቁ
ከሰማይ መጪኸ የመብረቁ ድምጽ
ዝናብ ሊዘንብ ነው ቶሎ እናምልጥ
አጥንቱን አድርቆት ከየን ከአጥሩ
ኤልክትሪክ አለ በደንብ ጠርጥሩ
እራስን ለመጠበቅ ከብዙ አደጋ 2x
ውሳኜ ያስፈልጋል እንዳንዘናጋ 2x

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ሳምንት ሃያ አምስት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- የቀላል ቃላት ትርጎሞችን መረዳት
- የፊደላትን ድምፅና ቅርፅ መለየት
- ቅርፆችን መሳል
- ቅርፆችን አካባቢያቸው ካሉ ነገሮች ጋር ማዛመድ
- የሰዎችን ስሜት የሚገልፁ ስእሎችን በመመልከት ስሜቶችን መረዳት
- ንድፍ ሰርተው ማብራራት
- ባለ ሁለት ድግግሞሽ ንድፎችን መስራት
- የተለያ እንቅስቃሴዎችን ምትን በመከተል መስራት
- ግጭቶችን ያለፀብ መፍታት
- እስከ 10 ቁሶችንበመጠቀምመደመር
- ለተክሎች እድገት አስፈላጊ ነገሮችን መለየት

ንዑስ ይዘቶች:-

- የቃላት እውቀት
- የፊደላት የድምፅ ግዛቤ
- ቅርፆች
- ግንኙነት ዝምድናናትግበራ
- ማንበብ
- መፃፍ
- ንድፍ
- የድምፅ ምት ያላቸው እንቅስቃሴዎች
- ሁለገብ ችሎታ
- ቁጥሮችን መደመር
- እፅዋት

ተግባር 1፦ ተረት

ሀ.የተክል ቀን (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ንድፍ፣ ተክል

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ውሃ፣ መትከያ እቃ፣ መኮትኮቻ፣ አፈር፣ ፍግኝና ወዘተ

የተክል ቀን

ከእለታታት አንድ ቀን በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የደረጃ ሁለት ተማሪዎች ተክሎች ለመትከል ፈለጉና ለተክል ለመትከል አስፈላጊውን ነገር መዘጋጀት ጀመሩ፡፡ የመትከያ እቃ፣ አፈር፣ ውሃ፣ መኮትኮቻ እና ችግኝ አድርገው በቅደም ተከተል ደረደሩ፡፡ እንዲሁም ችግኞቹን ሁለት ቀይ አበባ ቀጥሎ ሁለት ነጭ አበባ፣ ሁለት ቀይ፣ ሁለት ነጭ እያደረጉ መትከል እንዳሰቡ እስካሁን የሰሩትን ለመምህራቸው ማስረዳት ጀመሩ፡፡ በመካከልም አንድ ልጅ ለመምህሯ ለማሳየት ሲል የተደረደረውን ቅደም ተከተል በታተነው፡፡ ልጆቹም በጣም ተናደዱና ገፈተሩት፡፡ መምህርቷም ለምን ትገፈትሩታላችሁ ብላ ጠየቀቻቸው፡፡ እነሱም የደረደርነውን በተነው እኮ አሏት፡፡ በተናደደ ስሜት እያችሁ ልጆች እሱ እኮ አውቆ አይደለም ቅደም ተከተሉን ያበላሸው፤ ለእኔ ለማሳየት ሲል ነው፡፡ ይቅርታ አድረጉለት እናንተም ስለገፈተራችሁት ይቅርታ ጠይቁ፡፡ ምን ጊዜም አለመግባባት ሲገጥም ከፀብ ይልቅ በንግግር ለመፍታት ሞክሩ አለቻቸው፡፡ ተማሪዎቹም ጓደኛቸውንም መምህራቸውንም ይቅረታ ጠየቁ፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ተማሪዎቹ ለምን ተጣሉ?

ተግባር 2፦ የተግባር ሥራ

ሀ. ከ1-10 ያሉ ቁጥሮችን በቁስ መደመር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁጥር፣ መደመር፣ አካባቢ፣ ቁሶች፣ ቅርጾች

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱን ከ 1-10 ያሉ ቁጥሮችን የሚወክል የተለያየ ቅርፅ ያለው ቁሶች በመስጠት ቁሶችን በመቀላቀል እንዲደምሩ ያሳዩዋቸው:: ለሁሉም እድል በመስጠት ተራ በተራ እየደመሩ ያሰዩ:: በቅድሚያ ሁለት አይነት ቅርጽ ይሰጧቸው:: የተሰጣቸውን ቅርጽ የሚመስሉ ቅርጾችን ከክፍሉ ውስጥ ፈልገው ያመሳስላሉ:: ቀጥሎ ሁለቱን ቅርጾች ቀላቅለው በመደመር ውጤቱን ይነገሩ በዚህ መረት ሁሉንም ያሳትፉ::

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ተቆጣሪ ቁሶችና ሌሎች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ስንት ቁሰ ደመራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ተግባሩን በተገቢው ማከናወናቸውን ያረጋግጡ።

ለ. ፊደላትን ደጋግም በመፃፍ ባለሁለት ንድፍ መስራት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ንድፍ፣ ፊደላት፣ ቅርፅ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

* በዚህ ሳምንት የደረሱበትን ፊደላት ቅርፅ መሰመር ጠብቀው በተገቢ አጻጻፍ ደግመው እንዲፅፉ እና እንዲያነቡ ያድርጉ። በቅድሚያ የፊደል ንድፍ እርሶ ሰርተው ያሳዩአቸው። ቀጥሎ እነሱ እንዲሰሩ ማድረግ፤

* የፊደል ድግግሞሹ ባለሁለት ንድፍ መሆን ይኖርበታል (ለምሳሌ፡- የ-የ-ዩ-ዩ-ዪዪ-ያ-ያ-ዬ-ዬ-ይ-ይ-ዮ-ዮ)... እያለ የሚደጋገም መሆን አለበት። ሲጨርሱ የሰሩትን የፊደል ንድፍ ለክፍሉ ህጻናት ይገልጻሉ፤ ቀጥሎ እቤታቸው ከቤተሰብ ጋር በመሆን ሰርተው እንዲመጡ ማድረግም አስፈላጊ ነው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ካርድ/ሞዴል፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ደብተር

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ስንት ፊደላትን ደጋግማችሁ ጻፋችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* የህጻናትን ሥራ ቀርበው በትኩረት መመልከት ያስፈልጋል።

ሐ. ባለሁለት ድግሞሽ ቅርፆችን መሳል (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቅርፆች፣ አካባቢ፣ ንድፍ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

በቅድሚያ ለህፃናቱ ተግባሩን ለመስራት የሚያስችል ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡፡ የሚሰሩት የተለያዩ ቅርጾችን መሳልና መቀባት፣ የሳሉትን አከባቢያቸው ላይ ከሚገኙ ነገሮች ጋር ያዛምዳሉ፡፡ (ለምሳሌ የተክል ቅርጽ፣ የኳስ ቅርጽ፣ የበር ቅርጽ፣ የጠረጴዛ ...) ቅርፆችን በመጠቀም እንዲስሉ ማድረግ፤ ቅርጹን ሲስሩ በባለሁለት ንድፍ እንዲሆንም ይንገሯቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ሁለት ቅጠል፣ ሁለት ኳስ....

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ቅርፅ ያላቸው ስዕሎች እና ሞዴሎች፣ እርሳስ፣ወረቀት፣ ደብተር፣ ቀለምና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* የምን ምን ቅርጽ ሰራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* የህጻናትን ሥራ ቀርበው በትኩረት መመልከት ያስፈልጋል፡፡

መ . ንድፎችን መስራት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቃላት፣ ንድፍ፣ ቅርጽ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

* ለህፃናቱ ቀላል ትርጉም ያላቸውን ቃላቶች እንዲለዋወጡ ያደርጉ፡፡

(ለምሳሌ፡- ቀለም ማለት የተለያዩ አይነት የሆነ በልብሳችንና በቤታችን ላይ ተውቦ የሚታይ ነው፡፡ ውሃ ማለት ፈሳሽ የሆነ ለመጠጥ ለንጽህና መጠበቂያ ለተክሎች ማሳደጊያ ... የሚሆን ማለት ነው) በማለት እንዲወያዩ ማድረግ፤

* በመቀጠል የተለያዩ ቅርፆችን በመጠቀም ባለሁለት ንድፎችን ሰርተው ያሳዩዋቸውና፡፡

* ህፃናቱ እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

* ሲጨርሱ የሰሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲነግሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ቅርፅ ያላቸው ስዕሎች/ሞዴል፣ የቃላት ካርድ፣ ከቃላት ጋር የሚገናኙ የተለያዩ ስዕላዊ መገለጫዎች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ስንት ንድፍ ሰራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* የህጻናትን ሥራ ቀርበው በትኩረት መመልከት ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 3፦ በፕሮጀክት መማር

ሀ. በተለያዩ ቅርጾች ንድፍ መስራት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ባለሁለት ድግግሞሽ ንድፍ፣ ቅርጽ፣ ቃላት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ ሰርቶ ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

* እቤት ውስጥ ከወላጆቻቸው ጋር በመሆን የተለያዩ ቅርጾችን ተጠቅመው ባለሁለት ድግግሞሽ ንድፍ ስርተው እንዲያመጡ እንዲሁም ትርጉማቸውን የሚያውቁትን ቀላል ቃላት ይዘው በመመጥጣት ለክፋሉ ህፃናት እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የተለያዩ ቅርጾች፣ የቃላትት ካርድና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ስለፕሮጀክታቸው አጠቃላይ ነገር ከሚያቀርቡት ተነስተው መጠየቅ

ተግባር 4፦ የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. አዳምጦ መመለስ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ድምፅ፣ ግጭት መፍታት፣ ሰላም፣ ቃላት፣ ፊደላት

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፦

ጨዋታውን ለማጫዎት የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ይከተሉ።

 በቅድሚያ የተለያዩ ፊደላት በሳህን/በካርቶን የዘጋጁ መሃል ለመሮጥ በሚመች ቦታ ጠረጴዛ ላይ ያሰቀምጡ፣ በአንድ ዙር ቢያንስ ሶስት ተወዳዳሪዎች በአንዴ ማወዳደር ይችላሉ።

 ጨዋታው በጭብጨባና በዜማ እሩጫ እሩጫ ማለት ህፃናቱም የድምፅ ሞቱን ተከትለው መሮጥ ከዛም አንድ ቃል እርሶ ሲጠሩ አድምጠው ልክ ቃሉ ሲጠራ ከፊደሉ ውስጥ የተጠራውን ቃል የመጀመሪያ ፊደል ተሽምቶ ፈልጎ ማግኘትና ፊደሉን እና ቃሉን ደግሞ በመናገር ትርጉሙን መናገር፤

 ቀድሚ ፊደል ለመገኘት ሲባል የሚፈጠር እኔ ቀድሞ እኔ ቀድሞ ግፊያ እና ሽሚያ ወቅት የሚገጥማቸውን ግጭት/ጸብ በመረጋጋት በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ማድረግ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፍደላት ካርድ፣ ካርቶን፣ ጎድጓዳ/ዝርግ ሳህን፣ ጠረጴዛና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከጨዋታው ምን ተማርንና ሌሎች ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡
* ህጻናት ጨዋታውን በንቃት መጫዎታቸውን ይከታተሉ፡፡

ተግባር 5፡- ውይይት

ሀ. ስሜት የሚገልጹ ስዕሎችን መረዳት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ስሜት፣ አካባቢ፣ ቃላት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* የተለያዩ (የደስታ፣ የሀዘን፣ የለቅሶ፣ የድንጋጤ፣ የህመም፣ የመረበሽና ሌሎች) ስሜቶችን የያዘ ስዕል ያሳዩአቸው፡፡
* ስዕሉን በማየት ሴቱን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
* ስሜቱን በትክክል የሚገልጹ ህጻናት ስለስሜቱ ምክንያትም እንዲያወሩ ይደረግ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ (የደስታ፣ የሀዘን፣ የለቅሶ፣ የድንጋጤ፣ የህመም፣ የመረበሽና ሌሎች) ስሜቶችን የያዘ ስዕል

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የውይይቱን ፍሬ ሀሳብ መነሻ ያደረጉ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለ. ግጭት አፈታት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ግጭት፣ መፍታት፣ ቃላት፣ ስሜት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥረዓትን የሚያሳዩ ስዕሎችን ያሳዩአቸው፡፡
* የተወሰኑ ህጻናትን ተጠቅመው ስለግጭት አፈታት በምሳሌ ያስረዷቸው፡፡
* በመቀጠል ህጻናት በአከባቢያቸው ሰዎች ሰጋጩ የሚታረቁበትን መንገድ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
* ሁሉም ህጻናት ሀሳባቸውን በትክክል ማካፈል መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥረዓትን የሚያሳዩ ስዕሎችና ሌሎች

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ግጭት ለመፍታት ምን እናደርጋለንና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 6፦ መዝሙር

ሀ. ሠላም (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ሰላም፣ ድምፅ፣ ቃላት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

እርቅ የሚያወርዱ ሰዎች ስዕል፣ የእርግብ ምስልና ወዘተ

መዝሙር 1:- ሠላም

ልጆች ስንጫወት አንድ ላይ
ዜማ እየሰማን መዝለል ወደ ላይ
ደግሞ ወደ ግራ ደግሞ ወደ ቀኝ
በጨዋታው መሃል ብንጋጭ ድንገት
በሰላም እንፈታለን በመወያየት
በሰላም በሰላም በሰላም እንፍታ 2x
በ - በሰላም ሰ- ሰንጫወት
ላ- ላይመለሰ ግጭት
ም- ምርጥ እንዲሆን ጊዜያችን
ፀ- ፀብ እንዳይኖር መሃላችን
ላላ ላላላ ላላላ 2x

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 7፦ የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. የድምጽ ምቶችን ተከትሎ መንቀሳቀስ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሙዚቃ፣ እንቅስቃሴ፣ ሰላም

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

* ህፃናቱን በስርዓት ሳይገፋፉ ወደውጭ ይዘው ይውጡ።

* ለጨዋተው ማድመቂያ ደግሞ ሞንታርቦ/ጂፓስ/ስልክ/ቴፕ ማስሚያ እና የተዘጋጀ መዝሙር አብረው ይዘው ይውጡ።

* በመቀጠል ህፃናቱ ለማየት በሚመች መልኩ ተራ በተራ በቡድን እየከፋፈሉ እና የተለያዩ መዝሙሮችን እየከፈቱ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ፤

* እንቅስቃሴው ገደብ የሌለው ሆነው ጉዳት ግን የማያደርስ መሆን አለበት።

* ህፃናቱ እንደፈለጉ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ መገፋፋትና መጣላት ቢያጋጥም እራሳቸውን እየተቆጣጠሩ እና ይቅርታ እየተጠያየቁ መንቀሳቀሳቸውን ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ልምምድ እያደረጉ መሆኑን ይመልከቱ፤ በየመሃሉም ያስታውሷቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ቴፕ፣ ጂፓስ፣ ሞባይል፣ ሞንታርቦና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ስትንቀሳቀሱ ምን ተሰማችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት የአካል እንቅስቃሴ በሚያደርጉበት ወቅት ተገቢውን ክትትልና እንክብካቤ ያድርጉላቸው።

ሳምንት ሃያ ሰድሰት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- ስለራሳቸው ፍላጎት ማውራት
- የአራት ቁሶችን ክብደት ማነፃፀር
- በቴክኖሎጂ ቀላል ሙከራዎችን መለማመድ
- ከሰዎች ጋር ማህበራዊ ግንኙነትን መለማመድ
- የግልና አጠቃላይ የቦታ ግንዛቤን መለየት
- ቀላል ባህላዊ ጭፈራዎችን መጨፈር
- እስከ 10 ቁሶችንመደመር
- ከተሰጣቸው ቃላት ውስጥ ፊዳላትን ማንበብ
- ቁጥሮችን በቁስ መወከል
- ቀላል ተግባራትን በራሳቸው ያደርጋሉ

ንዑስ ይዘቶች:-

- እራስን ማስተዋወቅ
- ልኬት
- የማንበብና መፃፍ ችሎታ
- ማህበራዊ ግንዣቤ
- የመገኛ ቦታ ግንዛቤ
- ጥበባዊ ግንዛቤ
- ቁጥሮችን መደመር
- ፊደላትን ማንበብ
- የቁጥሮች ካርዲናል
- እራስን መቻል

ተግባር 1፦ ተረት

ሀ. ደጉ አበበ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ ፍላጎት፣ ቀላልተግባር፣ ጓደኝነት/ማህበራዊ ግንኙነት

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፦

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስዕሎች ወዘተ

ደጉ አበበ

አበበ የሚባል አንድ ልጅ ነበር። ልብሱን እያጠፈ ማስቀመጥ በጣም ይወዳል። ለዚያም ቤተሰቦቹ የገዙለት የራሱ ሻንጣ አለው። ልብሶቹ ከታጠቡለት በኋላ እያጣጠፈ በሻንጣው ውስጥ ያስቀምጣል። ካልሲና ፓንቱን ከእናቱ ጋር በመሆን ለማጠብ ይሞክራል። ሌሎችም ቀላል ተግባራትን ከወላጆቹ ጋር ይሰራል። ሁል ጊዜ ሲያጥብ እማዬ ውሃ ባይኖር ኖሮ ምን እንሆን ነበር? ያለውሀ መኖር እኮ ይከብዳል አይደል? በማለት ይጠይቃታል፡፡ እናቱም አዎ የውሀ ጥቅም ብዙ ነው እንጠጣለን፤ ምግብ እንሰራበታለን፤ ንጽህናችንን እንጠብቅበታለን፤ ተክሎችን እናሳድግበታለን... በማለት ታብራራለታለች። ከእለታት አንድ ቀን አበበ ከሰፈሩ ልጆች ጋር ሲጫወት ልጅ የያዙ ሰዎች ሲለምኑ ተመለከተ። ልጆቹም የለበሱት ልብስ መቀዳደዱን ስላስተዋለ ለጓደኞቹ እቤት ያለኝን ልብስ አካፍዬ መስጠት እፈልጋለሁ ለልጆቹ ብሎ ነገራቸው። እቤት ሲደርስ እናቱን አስፈቀዳት። የአበበ እናትም እሺ ፍላጎትክ ከሆነ ጥሩ ነው። የቱን መስጠት ፈለክ አለችው። አበበም መረጠና እነዚን አልፈልጋቸውም ልስጣቸው ሲላት ጎበዝ ልጅ ነገር ግን መስጠት ያለብክ የማትፈልገውን ሳይሆን ሁለት ካለክ አንዱን ማካፈል ነው በማለት አስረዳችው። አበበም እሺ እናቴ በማለት የሚለበሱ ልብሶችን መርጦ ወስዶ ሰጣቸው ሰዎቹም አመሰግነውት ሄዱ ይባላል።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፦ አበበ ምን ጥሩ ነገር አደረገ?

ተግባር 2፦ የተግባር ሥራ

ሀ. ከ1-10 ያሉ ቁጥሮችን በቁስ መደመር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁጥር፣ መደመር፣ ቀላልተግባራት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና:-

ህፃናቱን ከ1-10 ያሉ ቁጥሮችን የሚወክል የተለያየ ቅርፅ ያለው ቁሶች በመሰጠት ቁሶችን በመቀላቀል እንዲደምሩ ያሳዩዋቸው:: ለሁሉም እድል በመሰጠት ተራ በተራ እየደመሩ ያሰዩ:: በቅድሚያ ሁለት አይነት ቅርጽ ይሰጧቸው:: የተሰጣቸውን ቅርጽ የሚመስሉ ቅርጾችን ከክፍሉ ውስጥ ፈልገው ያመሳሰላሉ:: ቀጥሎ ሁለቱን ቅርጾች ቀላቅለው በመደመር ውጤቱን ይነገሩ በዚህ መረት ሁሉንም ያሳትፉ::

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

የተለያዩ ተቆጣሪ ቁሶችና ሌሎች

ምዘና:- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ሁለት ቁጥርና ሁለት ቁስ አሳዩኝና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት በተግባሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ለ. ቁሶችን በክብደት ማነፃፀር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁስ፣ ክብደት፣ ማነፃፀር፣ መወከል፣ ቀላል ተግባር

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

የተለያዩ ቁሶችን በቁጥር በመወከል ትልቁ ቁጥር በብዙ ቁስ ሲወከል እና ትንሹ ቁጥር በትንሽ ቁስ ሲወከል ያለውን የክብደት ልዩነት ህፃናቱ ክብደቱን በእጃቸው በማንሳት አመዛዝነው እንዲናገሩ ያድርጉ። በተጨማሪም በክፍል ውስጥ ካሉት ቁሶች አራት የተለያዩ መጠን ያላቸውን በማምጣት በየተራ እንዲያወዳድሩ ያድርጉ ትልቅ ነው፣ ትንሽ ነው፣ ከባድ ነው፣ ቀላል ነው... በማለት ይናገሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣ የተለያየ ክብደት ያላቸው ቁሶች (ድንጋይ፣ ውሃ የተሞላ ኮዳ)

ምዘና:- የቃል ጥያቄ

* ክብደትን በየትኞቹ ቃላት እንገልጻለንና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ሐ. ከቃላት ውስጥ ፊደላትን ማንበብ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፍላጎት፣ ቃላት፣ ቀላል ተግባር፣ ፊደል

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

በቅድሚያ የተለያዩ የቃላት ካርድ ህፃናቱ በራሳቸው ካለበት እንዲያመጡ ያድርጉ።

ከቃላቱ ውስጥ ፈልገው የሚፈልጉትን ቃላት መርጠው በማንሳት ከቃላቱ ውስጥ ፊደላቱን እንዲያነቡ ያድርጓቸው። ሲጨርሱ እራሳቸው እቃውን እንዲመልሱ ያድርጉ። ቀጥሎ ቃላቱን በወረቀት፣በደብተር፣ እንዲጽፉ ያድርጉ።

የመጪዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቃላት ፍላሽ ካርድና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ምን ምን ፊደላትን አነበባችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 3፡- በሥራ መማር

ሀ. የውሃ ላይ ቀላል ሙከራዎች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቀላል ተግባር፤ ፍላጎት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ስርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

 በዚህ ሙከራ ህፃናቱ ከባድና ቀላል (የሚሰጥሙና የሚንሳፈፉ) ነገሮችን ይለዩበታል። ለዚህ ተግባር፣

 በመዘፍዘፊያ ውሃ በመሙላት ያዘጋጁ ቀጥሎ ድንጋይ እና ትንሽ የፕላስቲክ ኮዳ ውሃ ውስጥ ጨምረው የትኛው እንደተንሳፈፈ እና የትኛው እንደሰመጠ እንዲለዩ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

 ቀጥሎ እነሱ በራሳቸው ፍላጎት የተለያዩ ቁሶችን እያመጡ እንዲሞክሩ ማድረግ ለምሳሌ የተለያየ መጠን ያላቸው አሻንጉሊቶች፣ ትንንሽ እና ትልልቅ ኳሶች…

የመጪዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ውሃ፣ መዘፍዘፊያ/ባልዲ፣ አሻንጉሊቶች፣ትንንሽ እና ትልልቅ ኳሶች፣ ድንጋይ፣ የፕላስቲክ ኮዳ…

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ቁስ ለምን ተንሳፈፈና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ።

ለ. የውሃ መምጠጥ ሙከራ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቀላል ተግባራትን፣ የግል ግንዛቤ፣ ፍላጎት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ስርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

* ህፃናቱ ስለሚያከናውኑት ተግባር ይንገሯቸው እና እነሱ ለተግባሩ ምን እንደሚያስፈልጋቸው አስበው ለእርሶ ይንገሩ።

* ህፃናቱ ስለሚያከናውኑት ተግባር ይንገሯቸው እና እነሱ ለተግባሩ ምን እንደሚያስፈልጋቸው አስበው ለእርሶ ይንገሩ፡፡
* እርሶም ነገሩን አስተካክለው እንዲያቀርቡ ያደርጋሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ህፃናቱ ስለራሳቸው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡
* እንዲሁም የትኛው እቃ የት እንደሚገኝ ለመለየት ያስቸላቸዋል፡፡ በዚህም የቦታን ግንዛቤ ያዳብራሉ ስለዚህ አስፈላጊውን ቁሳቁስ እራሳቸው ከየቦታው እንዲያመጡ ያድርጉ፡፡
* በእቃ ውስጥ ውሃ በማዘጋጀት በእስፖንጅ/በጥጥ፣ በጨርቅ ውሃውን መምጠጥ፤
* በባልዲ ውሃ በማዘጋጀት ቤት መወልወል ውሃው እየቀነሰ እንዲያዩ/እንዲገነዘቡ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ባልዲ፣ ውሃ፣ ጨርቅ፣ ፎጣ፣ እስፖንጅ፣ ጥጥና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* በስፖንጅ ውሃ ስትመጡ ምን ሆነና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡
* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 4፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. መስሎ ጨዋታ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ማህበራዊ ግንኙነት፣ ቀላል ተግባር፣ የቦታ ግንዛቤ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ጨዋታውን ለማጫዎት የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ይከተሉ፡፡

- የሚጫወቱት እንደ ጎረቤታሞች ነው፡፡ ስለዚህ ልጆች እና ወላጆች ያሉበት ሁለት ቤተሰብ ያዘጋጁ፡፡
- አንደኛው ቤተሰብ ከግቢ ውጭ ለአትክልት ሰፋራ ማጠር ፈልገዋል፡፡ ስለዚህ እንጨት፣ ማሰሪያ፣ ገመድ፣ መቆፈሪያ፣ የሚተከል ችግኝና ውሃ ማጠጫ ይዘው ተክሎቹን ተክለው አጥሩን ለማጠር ይወጣሉ፤
- ለህፃናቱም በአቅማቸው ልክ መኮትኮቻ ሰተው እንዲሰሩ ያደርጋሉ
- የሌላኛው ቤት ልጆች ደጅ ላይ እየተጫወቱ ሳሉ ያንን ያያሉ ከዚያም ሄደው ለወላጆቻቸው ነግራሉ የእነሱ ወላጆችም ይወጡና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ አብረው በመተጋገዝ አጥሩን ያጥራሉ የጎረቤቶቹም ህፃናት አትክልቱን ውሃ ያጠጣሉ፤
- ሁሉም በጣም ይደሰታሉ፡፡ በቀጣይ የእረፍት ቀን ደግሞ የጎረቤታቸውን ደጅ እንደሚሰሩ ተነጋግረው አብረው ሻይና ዳቦ ይበላሉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እንጨት፣ ማሰሪያ፣ ገመድ፣ መቆፈሪያ፣ የሚተከል ችግኝና ውሃ ማጠጫና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የመጀመሪያው ቤተሰብ ምን ማድረግ ፈለገና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 5፡- ውይይት

ሀ. የራስ ፍላጎት እና የግል ግንዛቤ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የራስ ፍላጎት፣ ቀላል ተግባራት፣ ማህበራዊ ግንኙነት፣ ግንዛቤ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* አስቀድመው ስለራስዎ ፍላጎትና ግንዛቤ አሳጥረው ይንገሯቸው፡፡

* ህጻናት እጃቸውን ተራ በተራ እያነሱ ስለፍላጎቶቻቸውና ግንዛቤያቸው እንዲያወሩ ዕድል ይስጧቸው፡፡

* ሁሉም ህጻናት ሀሳባቸውን በትክክል መግለጽ እንዲችሉ ድረስ ማወያየቱን አይርሱ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የሰው ስራሽ ቁሳቁሶች ምስልና ሌሎች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የውይይቱን ፍሬ ሀሳብ መነሻ ያደረጉ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ሁሉም ህጻናት የውይይቱ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 6፡- መዝሙር

ሀ. ልደቴ ነው ዛሬ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁጥር፣ እንቅስቃሴ፣ ኀረቤት፣ ማገዝ፣ መደመር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ልደት ሲከበር የሚያሳይ ስዕል፣ 10 ከረሜላዎች፣ የኬክ ሞዴል፣ ልደት ሲከበር የሚቀርቡ ነገሮች/ሞዴልና ወዘተ

መዝሙር 1:- ልደቴ ነው ዛሬ

ጎረቤቶቼ ኑ እንደሰት
ቀኑ ዛሬ እኮ ነው የተወለድኩበት
እስቲ እኔም ልሂድ ላግዛት እናቴን
ድግሱ እንዲያምር በመስራት ያቅሜን
10 ከረሜላ እዚ ጋር አለ
ሌላ የጎደለ አረ የቀረ ምን አለ
ኬኩንም ልቁረሰው እኔም በደስታ
አጨብጭቡልኝ እስኪ እልልታ 2×

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 7፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. ቀላል ተግባራትን ማከናወን (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቀላል ተግባር፣ ቁጥር፣ ማነፃፀር፣ ግንዛቤ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

አንደንድ በእነሱ ልክ የሆኑ ቁሶችን ያምጡና አንድ ቦታ ያስቀምጡ፡፡ እኩል የሆኑትን ከነሱ ጋር እየተነጋገራቹ በአንድ መደብ አስቀምጡ፡፡ ከአራት አይነት ውስጥ በጣም ትልቁን አሳዩኝ፣ መከካለኛውን፣ ትንሹን እያሉ ህፃናቱን በየተራ እንዲጫወቱ ያድርጉ፡፡ በመሬት ላይ ቀጥ ያለ መሰመር በቾክ ያስምሩ፡፡ ከዚያ አምስት አምስት ቡድን ያለውን ያደራጁና ከተሰመረው መሰመር ሳይወጡ በእርምጃ አስር እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡ ከአምስቱ ውስጥ አንድ ሰው ከመሰመሩ ከወጣ ቡድኑ ይሸነፋል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

በአካባቢው የሚገኙ የተለያዩ መጠን ያላቸው ቁሶች፣ ቾክ፣ ማርከር፣ አመድ፣ ከሰል...

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

በእርምጃ ጊዜ ስውነታችሁ ላይ ምን ተሰማችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ሳምንት ሃያ ሰባት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- ሀገራዊ በጎነትን ይለያሉ
- የመጓጓዣ አይነቶችን ይለያሉ
- ለማህበራዊ እሴቶች አክብሮት ያሳያሉ
- የጂኦሜትሪ ቅርፆችን ይሰላሉ
- ቀላል ተግባራትን በራሳቸው ያከናውናሉ
- ፊደላትን ደግመው ይፅፋሉ
- እስከ 20 ቁጥሮችን ያዛምዳሉ
- ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎችን ይጫወታሉ
- ጤናማ የሆኑ አመጋገቦችን ይመርጣሉ
- ፊደላትን ከቃላት ውስጥ ያነባሉ

ንዑስ ይዘቶች፡-

- የሀገር ፍቅር
- የተፈጥሮና ሰው ስራሽ አካባቢ
- ስነ-ምግባር
- ቅርፅ
- እራስን መቻል
- ፊደላትን ማንበብና መፃፍ
- ቁጥርና ተቆጣሪ
- ባህላዊ ቅርሶች
- የተመጣጠነ ምግብ
- ማንበብ

ተግባር 1፡- ተረት

ሀ.በጎነት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- በጎነት፣ ባህል፣ ሙዚቃ፣ መረዳዳት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስዕሎች ወዘተ

በጎነት

በአንድ የህፃናት ትምህርት ቤት የምትማር ሳራ የምትባል ልጅ ነበረች። ከእለታት አንድ ቀን በትምህርት ቤታቸው የበጎ አድራጎት ቀን እንደሚከበር ሰማች። እቤቷም በመሄድ እናቷን ስለበጎ አድራጎት ጠየቀቻት፡ ፡ እናቷም በጎ አድራጎት ማለት እርስ በርስ መተሳሰብና መረዳዳት ነው። እኛ ስንረዳዳ ሀገር ታድጋለች። ይሄ ደግሞ ሀገራዊ በጎነት ይባላል። ለምሳሌ ሜቄዶኒያ የሚባል ለአእምሮ ህሙማንና አረጋዊያን ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርግ ሀገራዊ በጎነትን እየሰራ ያለማህበር አለ። በግለሰብ በጎፍቃድ የተመሰረተ ነው። ስለዚህ ልጄ አንቺም እንደ አቅምሽ የሀገርሽን ባህልና ስርዓት በማወቅ ሀገራዊ በጎነትን መለማመድ ይኖርብሻል በማለት አብራራችላት። በማግስቱ ትምህርት ቤት ስትደርስም መምህራኖች እለቱን ለማክበር ተሰብስበው ብዙ ባህላዊ ሙዚቃ በመዝፈንና በማዘፈን ማህበራዊ እሴታችን ከሆነው አንዱ እርስ በርስ መረዳዳታችን ነው ሙዚቃችንም አንዱ መገለጫ ነው እያሉ የእለቱን የበጎሰራ ብዙ የተቸገሩ ሰዎችን በመርዳት እና በባህላዊ ሙዚቃዎች በመዝናናት አከበሩ።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ከ1-20 ያሉ ቁጥሮችን ማዛመድ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁጥር፣ በጓጓዣ፣ የጂኦሜትሪ ቅርፅ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና:-

ህፃናቱን ዝግጁ በማድረግ እና አስፈላጊ ቁሶችን በማዘጋጀት ተግባሩን ያሰሯቸው፡፡ ከ1-20 ያሉ ቁጥሮችን ለተለያዩ ክፍለ ጊዜ በመከፋፈል ከተቆጣሪ መጓጓዣአይነቶች እና የጂኦሜትሪ ቅርፆች ጋር በማድረግ እንዲያዛምዱ ማድረግ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

እርሳስ፣ ወረቀት/መለማመጃ መጽሀፍ፣ የመጓጓዣ አይነቶችና የጂኦሜትሪ ቅርጾችን የሚያሳይ ምስልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ተግባራት አከናወናችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት በተግባሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ለ. ፊደላትን መጻፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፊደላት፣ ቁጥር፣ ተግባራትን ማከናወን፣ ማህበራዊ እሴት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

የእለቱን ፊደል ቤተሰብ (ፀ-ፁ-ፂ-ፃ-ፄ-ፅ-ፆ፣ ወ-ዉ-ዊ-ዋ-ዌ-ዎ) ለህፃናቱ ያስተዋውቁ፣ እነ ማን እንደሆኑ በጋራ አንብቡ፤ ቀጥሎ ለመፃፍ የሚያስፈልጉ ቁሶችን ህፃናቱ በየተራ (በተቀመጡበት መደዳ) እየተነሱ ወደ ጠረጴዛቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ የእለቱን ፊደል ፍላሽ ካርድ/ቻርት በሚታይ ቦታ/ጠረጴዛቸው ላይ ማስቀመጥ፤ ከዚያም የእለቱን የፊደል ቤሰብ ተገቢ አጻጻፍን ተከትለው ይፃፉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

እርሳስ፣ ቀረቀት፣ ደብተር፣ የመለማመጃ መጽሃፍ፣ መቅረጫ፣ ላጲስና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ምን ፊደል ጻፋችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት ተግባሩን በተገቢው ማከናወናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ሐ. የጂኦሜትሪ ቅርፆችን መሳልና ማቅለም (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቅርፅ፣ ቀላል ተግባር፣ ማህበራዊ እሴት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

ስለሚሰሩት ተግባር ማለትም የጂኦሜትሪ ቅርጽ መሳልና መቀባት እንደሆነ ገለፃ ያርጉላቸው፡፡ ለማስታወስ ይረዳ ዘንድ የጆኦሜትሪ ቅርጾችን እየነኩ እንዲያስታውሱ ያድርጉ፡፡

ቀጥሎ ለመሳልና ለመቀባት የሚረዷቸውን መሳሪያዎች እንደተለመደው በራሳቸው ያዘጋጁ። እርሶ ሁሉንም ማቅረባቸውን ያረጋግጡ።

 ቀጥሎ ሁሉም በሚያዩበት ቦታ ቅርጾቹን ያስቀምጡላቸው፤ እርሶም በስሌዳ ላይ ስለው እና ከለር ቾክ ቀብተው ያሳዩ ቀጥሎ ሁሉም ሰርተው እንዲያቀልሙ ይንገሯቸው።

 በሚሰሩበት ጊዜ ላጲስ ፣ቀለም /እርሳስ መዋዋስ ቢፈልጉ እርስ በእርስ በመከባበር መጠያየቅ እንዳለባቸው ያስታውሱ (እባክሽ/እባክህ፣ ይቅርታ ... እርሳስ ስጭኝ/ስጠኝ ውሰኝ/እውሸኝ፣ ልትሰጠኝ ትችላለህ/ያለሽ...)

 ሲጨርሱ እርማት ይሰጡ ምን እንደሰሩ እንዲገልጹ አድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

እርሳስ፣ ደብተር፣ ወረቀት፣ የመለማመጃ መጽሃፍ፣ላጲስ፣ ቀለም፣ የጂኦሜትሪ ቅርጾችና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

* ምን ቅርጽ ጻፋችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ተግባሩን በተገቢው ማከናወናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 3፦ በሥራ መማር

ሀ. የጂኦሜትሪ ቅርጾች ተጠቅመው መኪና መስራት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፦ መጓጓዣ፣ ቅርፅ፣ በራስ አቅም ነገሮችን ማከናወን፣ ማህበራዊ እሴት

የማስተማሪያ ዜዴ፦ በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፦

የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾችን ገጣጥመው መኪና የመስራት ልምምድ በራሳቸው ይሰሩ። ለዚህ እንዲረዳ፦

 የጂኦሜትሪ ቅርጽ በርከት ያለ ከወረቀት/ከካርቶን ... ያዘጋጁ፤ ቀጥሎ ህፃናቱን በቡድን ከፍለው በክብ ያስቀምጧቸው እና በየጠረጴዛቸው ቅርጾችን ይስጧቸው።

 እነሱም እየተረዳዱ ቅርጾቹን እየገጣጠሙ መኪና እንዲሰሩ ይንገሯቸው።

 በጋራ ሲሰሩ የመከባበር እሴቶች ላይ ትኩረት ማድረጋቸውን ያስታውሱ፤ በሰነስርአት እየተረዳዱ ሀሳብ እየተለዋወጡ እንዲሰሩ ያድርጉ።

 እርሶም እየተዘዋወሩ ይመልከቱና ሲጨርሱ እየተነሱ ስለሰሩት መኪና ተራ በተራ እንዲገልጹ ያድርጉ።

 እቤት ውስጥ ከወላጆቻቸው ጋር ከተለያዩ የወደቁ ቁሳቁሶች መጓጓዣ ሰርተው እንዲመጡ ያድርጉ እና የሰሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዴት እንደሰሩና ከማን ጋር እንደሰሩ ይግለጹ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾች (ከወረቀት፣ ከካርቶን፣ ከእንጨት የተዘጋጁ) እና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ዓይነት መኪና ሰራችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ፡፡

ለ. የሙዚቃ መሳሪያ መስራት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ባህላዊ መሳሪያ፣ ሙዚቃ፣ መጫወት፣ ማህበራዊ እሴት፣ ተግባራትን ማከናወን

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

 በቅድሚ ስለ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ምስል/ስዕል/ሞዴል እያሳዩ ስለድምፃቸው እና ስለተሰሩበት ቁስ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡ በእጃቸውም እንዲዳስሱት ያድርጉ፡፡

 ሁሉም የግሉን የሚሰራ ሲሆን (ክራራ፣ መሰንቆ፣ ዋሽንት፣ ከበሮ፣ ጽናጽል) የሚሰሩትን አስመርጡና መዝግበወው ይያዙ፡፡ እቤት ከወላጆቻቸው ጋር ሆነው ሰርተው እንዲመጡ ያድርጉ፤ ሲያመጡ የመዘገቡትን መሰራታቸውን ያረጋግጡ፡፡ ከመረጡት ውጭ ለውጠው የሰሩ ህፃናት ካሉ ምክንያታቸውን በግልጽነት እንዲያሰረዱ ይፍቀዱላቸው፡፡

 ባመጡት የሙዚቃ መሳሪ እየተጫወቱ የተለያዩ የህብረተሰቡን ዳንሶች በአክብሮት እንዲደንሱ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ክር፣ ሲባጎ፣ ጅማት፣ እንጨት፣ ጣውላ፣ ጣሳ፣ ቆዳ፣ጨርቅ፣ ሸንበቆ፣ ቆርኪ፣ ሽቦንአ ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ዓይነት የሙዚቃ መሳሪያ ከምን ቁስ ሰራችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 4፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ቃላት ማንበብ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቃላት፣ ባህል፣ ሙዚቃ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ለህፃናቱ ከቃላት ውስጥ ፊደሎቹን አንቦ ቃሉን ሙሉ የማለት ጨዋታ እንደሚጫወቱ ያስተዋውቁ፡፡ ለዚህም፡-

 በቅድሚያ የመጓጓዣ፣ የጂኦሜትሪ ቅርጾች እና ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ፍላሽ ካርድ ስማቸው አብሮ ተጻፈበት በሳህን ጠረጴዛ ላይ ያዘጋጁ፡፡ አንድ ባዶ ሳጥን/ሳህን ያዘጋጁ፤ ለአሻናፊም ኮከብ ያዘጋጁ፡፡

 ሶስት ዳኞች እንዲኖሩ ያድርጉ፤ ውድድሩን ይዳኙ። በሰማቸው ትክክል የመለሱትን ነጥብ ይይዛሉ።

 ሶስት ተወዳዳሪ ይወጣሉ፤ ተራ በተራ ከተቀመጠው የቃላት ሳህን ውስጥ በመውሰድ ፊደሉን ካነበቡ በኋላ ቃሉን ሙሉ ያነባሉ (ምሳሌ ከ - ራ - ር ... ክራር...) በማለት ያነባሉ። በብዛት ያነበበ አሸናፊ ይሆንና ኮከቡን ይወስዳል።

 በዚህ መሰረት ሁሉም ህጻናት ተራ በተራ ያነባሉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የጂኦሜትሪ፣ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ፣ የመጓጓዣ ስዕል፣ ጠረጴዛ፣ ሳህን፣ ከወረቀት የተዘጋጁ ኮከቦች...

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን ፊደሎችን አነበባችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ።

ተግባር 5፡- ውይይት

ሀ. ጤናማ አመጋገብና የማህበረሰብ ዕሴቶች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ጤናማ አመጋገብ፣ መልካም ዕሴቶች

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* አስቀድመው ስለጤናማ አመጋገብና መልካም ዕሴቶች ይንገሯቸው።

* ህጻናት እጃቸውን ተራ በተራ እያነሱ ህእሳብ እንዲሰጡ ዕድል ይስጧቸው።

* ሁሉም ህጻናት ሀሳባቸውን በትክክል መግለጽ እንዲችሉ ድረስ ማወያየቱን አይርሱ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ምግብ የሚመገቡ ሰዎች ምስልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የውይይቱን ፍሬ ሀሳብ መነሻ ያደረጉ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት የውይይቱ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 6፡- መዝሙር

ሀ. እንሂድ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - መጓጓዣ፣ ባህል፣ የሙዚቃ መሳሪያ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች ስዕል፣
* የተለያዩ በጎ ስራ የሚሰሩ ሰዎች ፎቶ፣
* ጂፓስ፣
* ስልክ፣
* ሞንታርቦና ወዘተ

መዝሙር 1:- እንሂድ

እንሂድ በጋሪ እንሂድ በባቡር
ከቦታ ወደ ቦታ ለመዘዋወር
ከቦታ ወደቦታ በመዘዋወር
ማህበራዊ እሴትን እንወቅ እንማር
ሰዎችን ማክበርና መታዘዝ አለብን
ለሀገር በጎነትን ማሳየት አለብን
ባህል ጠብቀን ሰንዝናና
አለልን ክራር ደግሞም በገና
አለልን ከበሮ አለልን ዋሽንት 2x
የሚያስከብሩ የሀገርን እሴት 2×

ሞዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 7፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. ቀላል እንቅስቃሴ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መከባበር፣ ቀላልተግባር፣ መጓጓዣ፣ ጨዋታ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱን በተለመደው የጨዋነት ደንብ መሰረት ወደውጭ ይዘው በመውጣት ጨዋታውን በማስተዋወቅ እንዲጨዋቱ ያድርጉ።

- ከዚህ በፊት የሰሩትን የሙዚቃ መሳሪያ እና መኪና ይዘው ይውጡ።
- በመቀጠል ክራር የሰሩ አንድ ቡድን፣ መሰንቆ የሰሩ አንድ ቡድን፣ ዋሽንት የሰሩ አንድ ቡድን ሌላም የሰሩ ካሉ በአንድ ቡድን በመሆን የተለያዩ ባህላዊ እሴቶችን የሚወክሉ ቸዋታዎችን መርጠው ያሳዩ።
- ለምሳሌ ክራር የያዙት ትግረኛ፣ ዋሽንት የያዙት አማርኛ፣ ከበሮ የያዙት ጉራጊኛ … የመሳሰሉትን መርጠው ተራ በተራ ያሳዩ።
- ቀጥሎ ከዚህ በፊት በሰሩት መኪና የመኪና ውድድር ያድርጉ። ሶስት ሶስት ህፃናት ያወዳድሩ።
- መነሻ እና መድረሻ ወሰኑ ከዚያም መነሻ ጋር ሶስት ህፃናት መድረሻጋር ሶስት ይቆሙ። የመጫወቻውን መኪና በጥንቃቄ ሳይሰበር ፊሽካ ሲነፋ ይጀምሩ እና በእርምጃ እየነዱ ደርሰው እዚያ ለሚቆሙት ይሰጣሉ፤ የተቀበሉት ደግሞ በእርምጃ ወደመነሻ ይመልሳሉ።
- ቀድሞ የደረሰ አሸናፊ ይሆናል፤ ያሸነፉት ሁለቱም ኮከብ ይወስዳሉ። በዚህ መሰረት ሁሉም በየተራ ይወዳደራሉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያና የመኪና ሰዕል/ሞዴልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን ጨዋታዎችን ተጫዎታችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ጨዋታውን በትክክል መጫዎታቸውን ይከታተሉ።

የአውድ 5 ማጠቃለያ መመዘኛ ቼክ-ሊስት

የህጻኑ/ኗ ስም፡______________________________ ጾታ፡ _______ ዕድሜ______

ተ.ቁ	የሚጠበቀው የመማር ውጤት	ጥሩ	በጣም ጥሩ	እ. በ. ጥሩ
1	ሀገራዊ በጎነትን መለየት			
2	የመጓጓዣ አይነቶችን መለየት			
3	ለማህበራዊ እሴቶች እክብሮት ማሳየት			
4	የጅኦሜትሪ ቅርጾችን መለየት			
5	ቀላል ተግባራትን በራሳቸው ማከናወን			
6	ፊደላትን ደግመው መጻፍ			
7	እስከ 20 ቁጥሮችን ማዛመድ			
8	ባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎችን መምርጥ			
9	ጤናማ የሆኑ አመጋገቦችን መምረጥ			
10	ፊደላትን ከቃላት ውስጥ ማንበብ			

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፡- ____

____

____

____

አውድ ስድስት፡- ወቅቶች

ለአውዱ የተሰጠ ጊዜ፡- 5 ሳምንት/150 ክ/ጊዜ

መግቢያ

አውዱ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን አቀናጅተን ለማቅረብ የምንጠቀመው አቃፊያችን ነው። ይህ ማለት ህጻናት የሚማሩት በአውዱ መሰረት የተቀናጁ ይዘቶችን እንጂ ቀጥታ አውዱን አይደለም። ይህ የመማር አውድ የህጻናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ለማዳበር የሚያስችሉ ስድስት የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን በተቀናጀ የማስተማር ዘዴ ለማቅረብ የተዘጋጀ ነው። በዚህ አውድ እንዲቀናጁ የታሰቡት ስድስቱም የትምህርት ይዘቶች (የቋንቋ እድገት፣ የቅድመሰሌት፣ የአካላዊ መዳበር፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ዕድገት፣ ክዋና ስነ-ጥበባትና ሳይንስ) ሲሆኑህጻናት እነዚህን ይዘቶች በተቀናጀ መልኩ እንዲገነዘቧቸው ለማስቻል በህጻን ተኮር የማስተማር ዘዴ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ተግባራትን ማዘጋጀትተችሏል። በዚህ አውድ የሚዳሰሱ ስድስቱም የትምህርት ይዘቶች ከህጻናቱ መማር ደርጃና እድገት ጋር ተቆራኝተው በዝርዝር ተቀምጠዋል። በመሆኑም በአውዱ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ቅደምተከተላቸውን ጠብቀው ለአምስት ሳምንታት ተዳራጅተዋል።

የእድገትና የመማር ውጤቶች

ህጻናት ከዚህ አውድ ትምህርት በኋላ፦

- የነገሮችን አቀማመጥ (ታች፣ ከጎን፣ ከላይ ወ ዘ ተ) ይናገራሉ።
- ነገሮችን (ሻካራ/ለስላሳ) ይለያሉ።
- ህትመት ትርጉም እንዳለው በመረዳት ከግራ ወደ ቀኝ እና ከላይ ወደታች ያነባሉ።
- በቃላት ውስጥ ፊደላትን ለይተው ያነባሉ።
- የጀግኖቻቸውን ሀገራዊ በጎነትና ሚና ይረዳሉ፡
- ከሌሎች ጋር በአዎንታዊ መልኩ ለመግባባት ሞራላዊ እሴቶችን ይጠብቃሉ።
- ነገሮችን (ረጅም፣ አጭር፣ ከባድ፣ ቀላል፣ ሩቅ፣ ቅርብ ወ.ዘ.ተ) ያወዳድራሉ
- መሰረታዊ ቀለማትንና ውህድቀ ለማትን ለያሉ።
- በንግግር ውስጥ ጊዜ ነክ ቃላትን ይጠቀማሉ።
- የጡንቻና አጥንት እንቅስቃሴዎችን በትክክልና በድግግሞሽ ያከናውናሉ።
- በመደበኛ ምት እንቅስቃሴዎችን ከጓደኞቻቸው ጋር ያሳያሉ።
- በአካባቢያቸው ስለሚገኙ የተለያዩ ተቋማት ግንዛቤ ይፈጥራሉ።
- በሙዚቃና ጭፈራ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ።

አበይት ይዘቶች

* ራስን መግለጽና ማስተዋዋቅ
* የሰውነት ክፍሎች
* ትንንሽና ትልልቅ ጡንቻዎች መዳበር
* ድምጾችን መለየት
* ቁጥርና ቆጠራ
* ገንዘን
* ቀለማት
* ጥበባዊ ግንዛቤ
* ራስን መቆጣጠር
* ራስንና የቅርብ አከባቢን መንከባከብ
* መለካትና ማወዳደር
* ቁጥር መጻፍ
* መለየትና መመደብ
* ውሳኔ ሰጭነት
* የፈጠራ አገላለጽ
* ምግብ፣ ደህንነትና ጥንቃቄ
* የቃላት ዕውቀት
* ቁጥር መቀነስና መደመር
* ፊደላትና ድምጾቻቸው
* ከሌሎች ጋር የመግባባት ክህሎት
* ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አከባቢ
* ዲጂታል ሊቲሬሲ
* ምት ያላቸው እንቅስቃሴዎች

ሳምንት ሃያ ሰምንት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- በአካላዊ ባህሪያት ሰውን መለየት
- በመሳል ስሜታቸውን ይገልፃሉ
- የታወቁ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት ያውቃሉ
- እስከ 12 የሚደርሱ የሎኮሞትር እንቅስቃሴዎችን ያሳያሉ
- የተለያዩ ድምፆችን ይለያሉ
- እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ይቆጥራሉ
- የወቅቶችን ስዕሎች ይለጥፋሉ
- ገዢና ሻጭ መስለው ይጫወታሉ

ንዑስ ይዘቶች፦

- ራስን መገንዘብ
- ራስን መግለጽ
- የሰውነት ክፍሎች
- የትላልቅ ጡንቻዎች እድገት
- ድምጽን መለየት
- ቁጥርና መቁጠሪያ ቁጥሮች
- ጥበባዊ መረዳት
- ገንዘብ

ተግባር 1፡- ተረት

ሀ. ወቅቶች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- አካላዊ ባህርያት፣ ስሜትን መግለጽ፣ መንቀሳቀስ፣ ድምጽ፣ ወቅት፣ ገንዘብ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስዕሎች ወዘተ

ወቅቶች

ብርሃኑና አብዱ ማይወይኒ በሚባል ትምህርት ቤት ይማራሉ። አንድ ቀን በሠፈራቸው ሜዳ ላይ ቁጭ ብለው እየተጫወቱ ከፍተኛ ቅዝቃዜ ስለነበረ በጣም በረዳቸው። ዝናብ ሊመጣ ነው መሰለኝ መቀዝቀዝ ጀመረ አለ አብዱ። ብርሃኑ ደግሞ አሁን እኮ ሰለመሸ ነው የበረደህ አለው። ግን ዝናብ በጣም የሚበዛው መቼ ነው ብሎ አብዱ ብርሃኑን ጠየቀው። ይህንን እኔ አላውቅም እስኪ ነገ ጠዋት መምህራችን ቀመርያን እንጠይቃታለን ተባብለው ወደ የቤታቸው ሄዱ። በማግስቱ ጠዋት ትምህርት ቤት እንደደረሱ መምህርት ቀመርያን አገኟትና 3 ጥያቄዎችን ጠየቋት። እሷም እንዲህ በማለት ነገረቻቸው። ፀሃያማ ወራት በጋ በመባል ይጠራል። ዝናባማ ወራት ደግሞ ክረምት በመባል ይጠራል። ክረምት በጣም ይበርዳል። በጋ ደግሞ በጣም ይሞቃል በማለት መምህርት ቀመሪያ ለብርሃኑና ለአብዱ ነገረቻቸው። እነሱም ባገኙት መልስ ተደስተው መምህራቸውን አመሰግነው ወደ ክፍል ገቡ ይባላል።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡- ብርሃኑና አብዱ ሜዳ ላይ ቁጭ ብለው ሰለምን ተጨዋወቱ?

ሀ. አሊ የሚወዳት አበባ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ገጽታ፣ የነገሮች አቀማመጥ፣ መሰረታዊ ቀለማት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መግሪያ ቁሳቁስ፦

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስዕሎች ወዘተ

አሊ የሚዳት አበባ

አሊ ጎበዝ ልጅ ነው፡፡ በየቀኑ ጠዋት ጠዋት እየተነሳ አትክልቶቹን ውሃ ያጠጣል፡፡ በአትክልት ቦታውም ለምግብነት የሚጠቅሙ ቲማቲሞች፤ ጎመኖችና ካሮቶች ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም ቀይ፣ ቢጫና ሰማያዊ ቀለም ያሏቸው የሚያማምሩ አበቦች ይገኙበታል፡፡ አበቦቹ አተካከላቸው በቅደም ተከተል ነው ቀዩዋ አበባ በላይ በኩል፣ ቢጫዋ ሰማያዊ አበባ ካለችበት ከታች ስትሆን ከአበቦቹ መሃል አሊ የሚወዷት አንዲት ቢጫ ነጠብጣብ ያላት ሰማያዊ አበባ አለች፡፡ እሷ ደግሞ ከሌሎቹ አበቦች በጎን በኩል ትገኛለች፡፡ እሱ ራሱ የተከላት ናት፡፡ በደንብም ስለሚንከባከባት ቶሎ ነበር ያደገችለት፡፡ ገጽታቸው ደግሞ በጣሙን ያምር ነበር፡፡

ከእለታት አንድ ቀን አሊ እንደተለመደው ውሃ ሊያጠጣ በጠዋት ተነሰቶ ወደ አትክልቶቹ ሄደ፡፡ የሚወዷት አበባው ቀለሟ ቡናማ ሆኖና ጠውልጋ ተመለከታት፡፡ ተጨማሪ ውሃ ቢያጠጣትም ከመጠውለግ ሊያድናት ባለመቻሉ በጣም አዘነ፤ ወደ አትክልት ሰፍራው መሄድም አቆመ፡፡ ይህንን ያስተዋሉት ያሉት አባቱም "ልጄ ያቺን አበባ እንደምትወዳት አውቃለሁ ነገር ግን አበባዋ ብዙ ውሀ ስለማትወድ ለማቆጥቆጥ የክረምቱ ንዝናብ ማለፍ አለበት፤ አንተም ተሰፋ ሳትቆርጥ መከታትልና መንከባከብ አለብህ" አሉት፡፡ እናም አንድ ቀን ጠዋት የአሊ አባት አትክልት ሰፍራው ሆነው "አሊ ቶሎ ብለህ ና ፍጠን" አሉት፡፡ አሊ ሮጦ እንደ ደረሰ ልክ አበባው በነበረችበት ቦታ መሬቱ ላይ ወዲለችው አረንጓዴ ቅጠል አመለከቱት፤ የኔ አበባነች? አለ አሊ ተገረሞ፡፡ በጣም ተደሰቶ እንደገና አትክልቶቹን ውሀ ማጠጣትና መንከባከብ ጀመረ፡፡ አባቱም የመጀመሪያ ቀለማትን እስኪ ከአበቦቹ ውስጥ ንገረኝ አሉት እሱም ደስ እያለው ቢጫ፣ አረንጓዴ፣ ሳማያዊ፣ ቡናማ ቀይ እየለ አበባው ሰፋራ የሚያየውን ቀለም ሁሉ ጠራ አባቱም ቆይ ቆይ አሊ ጥሩ ነው ቀለማትን አውቀሃል ግን እነዝህ በተፈጥሮ ስለሚገኙ ነው ነገር ግን ቀለም ማዘጋጀት ብንፈልግ ሌሎችን ቀለማት ለመፍጠር የሚጠቅሙ ሶሰት መሰረታዊ ቀለማት አሉ እነሱም ቀይ፣ ሳማያዊ እና ቢጫ ናቸው ሌሎቹን ቀለም ለማግኘት እነሱን መቀላቀል አለብን አሉት አሊም እንዴ አባዬ እንዴት ይቀላቀላሉ በማለት ጠየቀ ና ላሳይህ አሉትና ከቤት ውሰጥ ቀለማት አምጥተው ትንሽ ሰማያዊ እና ትንሽ ቢጫ ሲቀላቅሉ አረንጓዴ ቀለም አገኙ አሊ በጣም ተደነቀ እንደገና ቀይና ቢጫ ሲቀላቅሉ ብርቱካናማ ቀለም አገኙ አሊ በነገሩ በጣም ተደሰተና አባቱን እንደገና እንዲያሳዩት በመጠየቅ አብረው ቀለማትን እየቀለቀሉ ብዙ ቀለማትን መግኘት ቻሉ፡፡

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፦ አሊ ማነው፤ ምን አደረገ?

ተግባር 2፦ መዝሙር

ሀ. ጸሃይ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - የጡንቻ እና አጥንት እንቅስቃሴ፣ ስሜት፣ መውደድ፣ ድምጽ፣ ወቅቶች

የማስተማሪያ ዘዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የጸሃይ ምስልና ወዘተ

መዝሙር 1፦ ጸሃይ

ፀሀይ ዉጭ ዉጭ እኛ እንወድሻለን
በጠዋት ተነስተን እንጠብቅሻለን
ገና በጠዋቱ ደስ ደስ ብሎኛል
የወፎቹ ዜማ ከሩቅ ይሰማኛል
እንዴ እጆቼን እንዴ ደግሞ እግሮቼን
ያወዛውዘኛል መላ ሰውነቴን
እስቲ ልንቀሳቀስ እግዜኝ ልበርታ
ሰውነቴ ሁሉ ጡንቻዬ ይፍታታ
አጥንቴም ይጠንክር ጉልበቴም ይበርታ
ዝናቡ ሲያካፋ ፀሀይዋ ጠፍታለች
ክረምት ሲገባ ትናፍቀናለች።

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለ. እንቀሳቀሳለሁ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ግብረገብ፣ አዎንታዊ ግንኙነት፣ ከጓደኛ ጋር መንቀሳቀስ፣ ማህበራዊ በጎነት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

በጎ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች ምስል፣ የጓደኛማቾች ሰዕልና ወዘተ

መዝሙር 2፦ እንቀሳቀሳለሁ

ከጓደኞቼ ጋር በደስታ እዘላለሁ
በሀገሬ ባህሎች እንቀሳቀሳለሁ
በሁለት እጆቼ _ አጨበጭባለሁ 2x
እራስ ትከሻዬን ላርገው መታ መታ
ከጓደኞቼ ጋራ ጠዋትና ማታ
ወገቤን ጨምሬ ጎነበስ ቀና እላለሁ
ከጓደኞቼጋር ጋራ ስፖርት እሰራለሁ
እግሮቼን እጆቼን አወዛውዛለሁ
ታላላቆቼንም እኔ እታዘዛለሁ
የሚሉኝን ሁሉ በደምብ እሰማለሁ
የጀግኖቻችንን በጎነት አውቃለሁ
እንደነሱ መሆን እኔም እፈልጋለሁ
ከጓደኞቼ ጋር በደስታ እዘላለሁ፡፡

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለ. ጀግኖቻችን (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ጀግኖች ፣ ሚና፣ መከባበር፣ ቀለማት፣ መደሰት፣ እሴት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይዘምሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ቀለም፣ የጀግኖች ስዕልና ወዘተ

መዝሙር 3፡- ጀግኖቻችን

የሀገሬን ጅግኖች ሚና አደንቃለሁ
እኔም እንደነሱ ታሪክ እሰራለሁ
የሰሩልን ስራ መቼ ይረሳል
ታሪካቸው እኮ ዛሬም ይታወሳል
ሰዕሎችን መሳል በጣም እወዳለሁ
የሀገሬን ጅግኖች ደግሞ እሰላለሁ
ቀለም ቀላቅዬ ልብሳቸውን እቀባለሁ
ሰማዊ ቀዩን ቢጫ እቀባለሁ
በፍትሃዊነት ከሰው ጋር ኖራለሁ
እሴቶቻችንን በደንብ እከብራለሁ።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 3፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ወቅቶችን በስዕል መግለጽ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቀለማት፣ ከላይ፣ ከታች፣ ከጎን፣ የጡንቻ ጥንካሬ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

ለዚህ ሳምንት ሁለት የተለይዩ የግል ተግባራት ቀርበዋል። ህጻናት ሁለቱንም ተግባራት በተቀመጡ መመሪያዎች መሰረት እንዲሞክሯቸው ያድርጓቸው።

- በቅድሚያ ለስእል የሚሆኑ መሳሪያዎችን አዘጋጅቶ ለሁሉም መስጠት (ወረቀት/ደብተር፣ እርሳስ፣ የተለያዩ ቀለማት)
- መሰረታዊ ቀለማት የተቀቡና በቻርት ላይ ተስሎ የተዘጋጀ የፀሃይ፣ የዳመና እና የዝናብ ሰዕል ማዘጋጀት እና ለሁለም በሚታይ ቦታ በማስቀመጥ፤ ስለወቅቶችና ስለቀለማት መንገር፤ ስዕሉ ፀሃይ ከላይ፣ ደመና ከታች እና ዝናብ ከደመና ጎን ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል። ይህም ህፃናቱ የነገሮችን አቅጣጫ አቀማመጣቸውን እየተው መናገር እንዲችሉ ይረዳል።
- ቀጥሎ ያንን እያዩ እነሱም ስለው እንዲቀቡ ያርጉ (ፀሃይ ቢጫና ቀይ፣ ደመና ሳማያዊ፣ ዝናብ ደግሞ በግራጫ ቀለም) እንዲቀቡ ያድርጉ በሚሰሉበት ጊዜ የእጆቻቸው ጡንቻዎች እና አጥንቶች ይጠነክራሉ።
- ሲጨርሱ የተጠቀሙበትን እቃ ቦታው መልሰው የሰሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

እርሳስ፣ ቀለም፣ ወረቀት፣ መቅረጫ፣ ላጲስ፣ የሰማይ ሰዕልና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ጸሃይ ከዳመና በምን አቅጣጫ ላይ ትገኛለችና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት በተግባሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ለ. ከግራ ወደቀኝና ከቀኝ ወደግራ ማንበብ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - የህትመት ትርጉም፣ ከግራ ወቀደቀኝ ማንበብ፣ ፊደል መለየት፣ ማወዳደር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ሰርቶ ማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ይህ ተግባር ህፃናቱ ህትመቶች ትርጉም እንዳላቸው ይእሚገነዘቡበት ነው።

 በቅድሚያ የተለያዩ በተዋወቋቸውን ፊደላት የተመሰረቱ ቃላት ያለባቸው የተለያዩ ፍልሽ ካርዶችን ለህፃናቱ መሰጠት (በሰለ፣ ሰው፣ ውሻ፣ ክራር፣ ቀለም፣ ፀሀይ...)፤

 በየጠረጴዛቸው ላይ በመስጠት ለተወሰነ ጊዜ በእጃቸው ይዘው ድምጽ ሳያወጡ በለሆሳስ ለራሳቸው ብቻ ከቃላቱ ውሰጥ ፊደላቱን እንዲያነቡ፣ ቃላቱን ደግሞ ከግራ ወደቀኝ ፣ከኋላ ወደፊት የማንበብ ልምምድ ያድርጉ (ምሳሌ ለሰበ፣ ውሰ፣ሻው.....)

 የተሰጣቸውን ቃል ያላወቁ ከሆነ በቅድሚያ እርሶ በማስታወስ ይርዷቸው፤

 ቀጥሎ በየተራ እየተነሱ የያዙትን ካርድ ተጠቅመው ቃሉን በተሰጠው መመሪያ መሰረት እንዲያነቡ ማድረግ እያንዳንዱ ቃል የያዘውን የፊደል ብዛት በመቁጠር ያወዳድሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ቃላትን የያዙ ፍላሽ ካርዶችና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

* ምን ፊደል አነበባችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ተግባሩን በተገቢው ማከናወናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 4፡- የክፍል ውሰጥ ጨዋታ

ሀ. ማወዳደርና መለየት (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መዳሰሰ፣ ማወዳደር፣ ቀለማት፣ መለየት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናት ይህንን ጨዋታ እየተጫዋቱ እንዲማሩ ለማስቻል የሚከተሉትን የድርጊት ቅደም ተከተሎች መከተል ያስፈልጋል።

 በቅድሚያ ለዚህ ጨዋታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ ሻካራና ለሰላሳን ለመለይት የሚያስችሉ (ከደቃቅ እና ከወፋፍራም አሻዋ በተቆራረጡ ጣውላዎች ላይ ተለጥፎ የተዘጋጀ፣ ሶፍት፣ ጨርቅ...)፣ ቁሶችን በቁመታቸው፣ በውፍረታቸው/በክብደታቸው ለማወዳደር የሚሆኑ የተለያዩ ቁሶች (የተለያዩ ቁመት ያላቸው ዘንጎች፣ ተለያዩ መጠን ያላቸው አሻንጉሊቶች፣ መፅሃፍ ደብተር...)፣ መሰረታዊ እና ውህድ ቀለማት ለመለየት የሚያችሉ ቁሶች (ከወረቀት፣ በሰዕል፣ የውሃ ቀለም ...) ማዘጋጀት፤

 ቀጥሎ ህፃናቱን በቡድን በመክፈል የተለያዩ ቁሶችን ይሰጡ እና በቡድናቸው የትኛው እንደሚሻክር፣ የቱ እንደሚለሰልስ፣ የቱ ረጅም ነው፣ የቱ አጭር ነው፣ የትኛው ቀለም መሰረታዊ ነው የቱ ቀለም ተቀላቅሎ ወይንጠጅ ቀለም እንደሚፈጥር... እንዲወያዩ ያድርጉ፤

- በተመደበው ክፍል ጊዜ ከፋፍለው ሁሉንም ተግባር ደጋግመው ሁሉም ህፃናት እንዲሰሩ ያድርጉ፤
- ሲጨርሱ በየቡድናቸው ፊት ለፊት እየወጡ እንዲያሳዩ ያድርጉ።
- እቤት ውስጥ የተለያዩ ወቅቶችን ስለው የተለያዩ ቀለማትን ቀብተው እንዲመጡ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ሻካራና ለሰላሳን የሚያሳዩ ነገሮች፣ የተለያዩ መጠንን ለማወዳደር የሚያገለግሉ ነገሮች እና የውሃ ቀለም

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን አወዳደራችሁና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ተግባሩን በሚያከናውኑበት ጊዜ በትክክል መሳተፋቸውን ቀርበው ያረጋግጡ።

ተግባር 5፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. ቅርብ እና ሩቅ (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ማወዳደር፣ የነገሮች አቀማመጥ፣ ከሌሎች ጋር በአዎንታዊ መልኩ መግባባት፣ ቀለማት

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱ በዚህ ጨዋታ ቁሶች የተቀመጡበትን እርቀትና ቅርበት እንዲለዩ፣ መጠናቸውን ከቀለማቸው ጋር አጣምረው እንዲለዩ የማድረግ ጨዋታ ማቸወትን የሚፈለገው ብቃት ላይ ማድረስ ነው።

- ህፃናቱን ስርኣት ባለው መንገድ ከክፍል ወደመጫወቻ ስፍራ ይዘው መውጣት፣
- ለመጫወቻ የሚያስፈልጉ የተለያየ መጠን ያላቸው በለቀለም ኳሶች፣ የተለያዩ ቀለም እና መጠን ያላቸው የህፃናቱ ወንበሮች፣ ...ለመጫወቻ የሚሆኑ ቁሶችን ማዘጋጀት
- ገለፃማድረግ ለምሳሌ ወንበሩን፣ ኳሱን በተለያየ ርቀት አስቀምጠው ቀዩ ወነበር ከነጩ ይርቃል ቡኒው ወንበር ከቀዩ ቅርብ ነው፣ ትልቁ ኳስ ከወንበሩ ስር ነው፣ ቢጫዋና ትንሽ ኳስ ከወንበሩ ላይ ነች... በማለት ቀለምን፣ አቀማመጥን፣ ሩቅ እና ቅርብን ገለፃ ያድርጉ፤
- ቀጥሎ ሶስት ሶስት ህፃናት እያደረጉ እንዲጫወቱ ያድርጉ፤
- ትዕዛዝ መስጠት ፊሽካ መንፋት (ለምሳሌ ፊሽካ ነፍተው እሩቅ ያለውን ቀይ ወንበር እንዲያመጡ ማዘዝና ህፃናቱ በሩጫ ሁደው ማምጣት፣ ኳሶችን አንድ ቦታ ሰብሰበው ሶስቱን ህፃናት ክብ ሰርተው ይቆሙና ትልቁን ኳስ በመውሰድ እሩቅ ያለው ወንበር ስር ማስቀመጥ) ብለው ማዘዝ ቀድሞ ድርጊቱን የጨረሰ የዙሩ አሸናፊ ይሆናል.... በዚህ መሰረት ህፃናቱን እየቀያየሩ ያጫውቱ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ መጠን ያላቸው ባለቀለም ኳሶች፣ የተለያዩ ቀለም ያላቸው የፒላስቲክ ወንበሮች፣ ፊሽካና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን ጨዋታዎችን ተጫዎታችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት ጨዋታውን በትክክል መጫዎታቸውን ይከታተሉ።

ተግባር 6፡- ውይይት

ሀ. አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- የተቋማት ግንዛቤ፣ ፍትሃዊነት፣ ታማኝነት፣ ጊዜ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

***የመምህር ሚና*፡-**

* ህፃናቱ ከዚህ ውይይት ስለተቋማት ግንዛቤ እንዲኖራቸው፣ በተቋማት ውስጥ መኖር ስለሚገባው ታማኝነት እንዲሁም ተቋማቱ አገልግሎት ሲሰጡ በፍትሃዊነት መገልገል እንዲቻል ስለማድረግ ግንዛቤ ይገነዘባሉ።

* የተለያዩ ተቋማትን በስዕል/በፎቶ ማዘጋጀትና እነሱ ስለእነዚህ ተቋማት የሚያውቁትን መጠየቅ፣ (ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል፣ ክፍለ ከተማ፣ መብራት ሀይል…) የመሳሰሉትን ማዘጋጀት፤

* ህፃናቱ በተቋማቱ ስለሚሰጡ አገልግሎት አይነት ይወያዩ አገልግሎት ስለሚሰጥባቸው ጊዜት ይነጋገሩ

* በቀጣይ አገልግሎትን በታማኝነት እና በፍትሃዊነት ስለመስጠት ይወያዩ።

* ቀጥሎ እነሱ ወደፊት የትኛው ተቋም ውስጥ መስራት እንደሚፈልጉ ያወያዩአቸው።

***የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ*፡-**

የተለያዩ ተቋማትን የሚያሳዩ ስእሎች/ፎቶዎችና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የውይይቱን ፍሬ ሀሳብ መነሻ ያደረጉ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት የውይይቱ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ሳምንት ሃያ ዘጠኝ

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- በተለየዩ ሁኔታዎች ውስጥ እራሳቸውን መቆጣጠር ይችላሉ
- ንፅህናን የመጠበቅ ልምዶችን ያዳብራሉ
- የሰዎችን ሃላፊነት እውቅና ይሰጣሉ
- የአካል ብቃትና ቅልጥፍናን ያዳብራሉ
- ቀጥታ ህትመትን ይለማመዳሉ
- እቃዎችን በመጠንና በዓይነት ይደረድራሉ
- እስከ 15 ያሉቁጥሮችን ይፅፋሉ
- በተሰጣቸው ቃላት ውስጥ ፊደላትን ያነባሉ
- የነገሮችን መጠን ክብደትና ቅለት ያወዳድራሉ
- መሰረታዊ ቀለሞችንና ውህድ ቀለሞችን ይለያሉ፡፡

ንዑሰ ይዘቶች:-

- ራስን መግዛት
- የግልና የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ
- ማህበራዊ ግንዛቤ
- የአካል ብቃት
- ፈጠራን መግለጽ
- መምረጥና መመደብ
- ቁጥሮችን መጻፍ
- ማንበብ
- ልኬት
- ቀለማት

ተግባር 1፡- መዝሙር

ሀ. ተክሎችና ወቅቶች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ፊደል፣ ቁጥር፣ የአካል ብቃት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ ወቅቶችን የሚያሳዩ ሰዕሎች/ተንቀሳቃሽ ምስሎችና ወዘተ

መዝሙር 1፡- ተክሎችና ወቅቶች

በ - በልጅነት
አ - አረንጓዴ
ለ- ለሰላሳ ቅጠል እየቀጠፍን ሰንጫወትውለን
ጭቃ እያቦካን ሰንጫወትውለን
በዝናብ ውሃ እንጫወታለን
በዝናቡ ውሃ እንጫወታለን
የበጋ ወቅት ሲደርስ በጣም እጓጓለሁ
ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ እሻለሁ
መምህራኖቼን ማየት እናፍቃለሁ
ቁጥርን መቁጠር እወዳለሁ
እንቅስቃሴ ማድረግ ደስ ይለኛል
በጋ ወቅት ሲደርስ በጣምይሞቀኛል
ከዛፎች ጥላ ስር መቀመጥ ያምረኛል፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለ. ገበሬው (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ድምጽ፣ ቀለም፣ እንቅስቃሴ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቅርብ አካባቢን የሚያሳዩ (እትክልቶች፣ የቤቶች፣የበጎች፣ የፍየሎች፣ እና የእርሻ መሳሪያዎች) እና ወዘተ

መዝሙር 2፡- ገበሬው

በበጋ በክረምት ገበሬውን እዩት
እርሻው ላይ በመዋል ሲያርም ሲኮተኩት
ጎመኑ አረንጋዴ ቀይ ስሩ ቀይ ነው
ገበሬው ጎበዝ ነው
ፀሀይ አይመልሰው
ዝናቡን አይፈራ
ዘወትር ይጓዛል
ሜዳና ተራራ
ሙቀት እና ብርዱ መች ያሸንፈዋል
ማለዳ ተነስቶ ከብቶችን ይነዳል
እንቅስቃሴንም ይወዳል ይወዳል፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ተግባር 2፡- ውይይት

ሀ. ሀላፊነት መውሰድ፣ የክረምትና በጋ አለባበስ (5 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሀላፊነት፣ ቅልጥፍና፣ እውቅና መስጠት፣ ክረምት፣ በጋ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* በቅድሚያ ሀላፊነት የምንወሰድባቸው ሁኔታዎችና ወቆችን ታሳቢ ስላደረገ አለባበስ አጭር ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡

* በመቀጠል ህጻናት ተራ በተራ እጅ እያነሱ ሀሳብ እንዲሰጡ ይጋብዟቸው፡፡

* ሁሉም ህጻናት ሀሳባቸውን በትክክል መስጠት እስከሚችሉ ድረስ ውይይቱን በጥያቄና መልስ ያስቀጥሉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ባህላዊ መንደርን የሚያሳይ፣ የግል ንፅህና አጠባበቅን የሚያሳይ እና አካላዊ መገለጫን የሚያሳይ ስዕል ወይም ወቅቶችን የሚያሳዩ ስዕሎችና አልባሳት ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የውይይቱን ፍሬ ሀሳብ መነሻ ያደረጉ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ሁሉም ህጻናት የውይይቱ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 3፡- የመስክ ጉብኝት

ሀ. ቁስ መፈለግ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መጠን፣ ንፅህናን መጠበቅ፣ የአካል ብቃት፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ለሚከተለው የመስክ ጉብኝት ህጻናቱን ከክፍል ውጪ ይዘው ይውጡና የተለያዩ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ያርጓቸው፡፡ በመቀጠል አከባቢያቸውን ከጎበኙ በኋላ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች ውስጥ 15 የሚደርሱ ቁሶችን ቆጥረው እንዲያመጡ ማድረግ፤ ለምሳሌ (ጠጠር፣ ቁርጥራጭ እንጨት፣ ቅጠሎች...) ሁሉም በጉብኝት ወቅት ያመጡትን ተራ በተራ እንዲቆጥሩ እና ያመጢትንም በመጠን እንዲደረድሩ ማድረግ፤

በቀጣይ ደግሞ ሰለጉብኝታቸው እንዲሁም ከየት አከባቢ ቁሱን እንዳገኑ በቀጣይ ክፍል ጊዜ እንዲያብራሩ ማድረግ፤ አሁን ግን ያመጡትን ቁስ ቆጥረው ያገኙበት ቦታ እንዲመልሱ እና በመቀጠል የእጃቻቸዉን ንጽህና እንዲጠብቁ ያድርጓቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

በአካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ቁሶችና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን ቁሶችን ተመለከታችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት የተግባሩ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 4፡- የተግባር ሥራ

ሀ. መሳልና ማንበብ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ህላፊነት፣ ፊደል፤ ቀለም፣ ማንበብ፣ መቀባት፣ ህትመት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

- የተለያዩ አበባዎችና ቅጠሎችን መሰራታዊ እና ውህድ የውሃ ቀለም ተጠቅም ቀጥታ ህትመት እንዲያትሙ ማድረግ ከሌሎች ጋር ሰለህትመታቸው እና ሰለቀለማቱ አይነት እንዲወያዩ እርሰ በርሰ አድናቆት እንዲሰጣጡ፣ እንዲተራረሙ እድል ይሰጧቸው፤
- ቀጥሎ በተዋወቋቸው ፊደላት የተመሰረቱ ቃላትን በፍላሽ ካርድ በመሰጠት ከቃላቱ ውሰጥ ፊደላቱን እንዲያነቡ ማድረግ ምሳሌ (ገመድ - ገ- መ- ድ፣ ቀለበት ቀ-ለ-በ-ት..)፤
- ህፃናቱ የተሰጣችውን ተግባራት ሲያከናውኑ ሃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ይንገሯቸው፤
- ፍላሽ ካርዶችና ሰዕሎችን ቀላቅሎ በመሰጠት ቁሶችን በባህሪያቸው እንዲመድቡና እንዲከፋፈሉ ያድርጉ፤
- ቀጥሎ እቤት ውሰጥ ከወላጆቻቸው ጋር በመሆን በውህድ ቀለማት የተለያዩ ህትመት በወረቀት ሰርተው እንዲመጡ ማድረግ አሰፈላጊ ነው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

በአካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ቁሶች፣ እርሳስ፣ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳስ፣ የውሃ ቀለም፣ የቃላት ፍላሽ ካርድ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን ሳላችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት በተግባሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 5፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. አትክልት ውሃ ማጠጣት (2 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሀላፊነት፣ መጠንና ክብደት፣ ንጽህና፣ ራስን መቆጣጠር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ ያለውን ጨዋታ ሲጫወቱ እርስ በርስ መከባበር፣ እራሳቸውን ተቆጣጥረው እና አንድን ተግባር ሲያከናውኑ የግል ንጽህናቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው በመንገር በስርአት ወደውጭ ይዘው መውጣትና ጨዋተውን እንዲጫወቱ ማድረግ፤ ጨዋታውም ትዕዛዝን በአግባቡ መወጣት ነው። አትክልቶችን ውሃ ማጠጣት፣ በፀሀይ የረጋገፉትን ቅጠሎች መልቀም፣ መኮትኮት፣ አከባቢውን ማጽዳት ነው። በአንድ ጊዜ አምስት አምስት ህፃናት ማሳተፍ ትዕዛዙን በቅደም ተከተል ያከናወነ አሸናፊ ይሆናሉ። ህፃናቱ ውሃ በሚያጠጡበት ጊዜ እንደመጠናቸው ለትንንሾቹ ትንንሽ ሀይላንድ፣ ለትልልቆቹ ደግሞ ተለቅ ተለቅ ያሉ ሀይላንድ በመጠቀም እንዲያጠጡ ማገዝ፤ ድርጊቱን በሚያከናውኑበት ጊዜ ልብሳቸውና ጫማቸው እንዳይቆሸሽ ማድረግ፤ ከጨዋታው በኋላ በውሃ እና በሳሙና እንዲታጠቡ ማድረግ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ውሀ ማጠጫ ሀይላንድ፣ መኮትኮቻ፣ ውሃ፣ የቆሻሻ ቅርጫትና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን እንደሰሩና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት የተግባሩ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 6፡- ተረት

ሀ. ጎበዙ ያዕቆብና አስቸጋሪዋ ሀና (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ መጠን፤ ራሳቸዉን መቆጣጠር፣ ማወዳደር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስዕሎች ወዘተ

ያዕቆብና ሀና

ከዕለታት አንድ ቀን በአንድ ሰፈር ውስጥ የሚኖሩ ያቆብና ሀና የሚባሉ ልጆች ነበሩ፡፡ ሁል ጊዜ ሲጫወቱ ሀና የያቆብን መጫወቻ በመውሰድ አልመልሰም ትለዋለች፡፡ ያቆብም እኔ መጫወቻ እሰጥሻለው አንቺ ግን ወሰደሽ ትከለክይኛለሽ፤ በዚህ ምክንያት ካንቺ ጋር መጣላት ሰልችቶኛል እባክሽ እንግባባ የሰጠውሽን መጫወቻ ስትጨርሺ በአግባቡ መልሺልኝ በማለት ጠየቃት፡፡ ፋጡማም በተናገራት ንግግር ተሰምቷት ይቅርታ ጠየቀችውና አሁን እኔ ማሳየውን እንቅስቃሴ አንተ በመድገም እንጫወት፤ ካልቻልክ ትሸነፋለክ አለችው፡፡ መጫወትም ጀመሩ፤ ሲጨርሱም ወደ ቤታቸው ለመሄድ ተስማምተው እየሄዱ እያለ ሀና እየካቸው እነዚ ዛፎች እያደጉ ነው፡፡ አንዱ ግን በጣም እረዥም ነው፤ አንደኛው አጭር አለችው፡፡ ያዕቆብም አዎ እኔ ደግሞ እኮ ያኛውን ድንጋይ እያየሁ ነበር፡፡ ስንጫወት ምንቀመጥበት አንዳኛው ትልቅ ነው፤ አንዱ ግን ትንሽ ነው አላት፡፡ ሀናም አከባቢያችን ላይ ግን ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ እየከው ያንን ቤት ሁለት በር አለው፡፡ አንዱ ሰፊ አንዱ ደግሞ ጠባብ አለችው፡፡ ያዕቆብም ሰፊው ለመኪና መግቢያ ጠባብ ለሰው ነው አላትና ወደ ቤታቸው እንደደረሱ ሲመለከት በእጁ ከያዘው 5 መጫወቻ ውስጥ 2 ቀንሶ ሰጣት ሀናም አመሰገነችውና ተሰነባብተው ወደ የቤታቸው ሄዱ፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ያዕቆብና ሀና ለምን ይጣሉ ነበር?

ተግባር 7፡- በፕሮጀክት መማር

ሀ. የቤተሰብ አባላት ሀላፊነት (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቀጥታ ህትመት፣ ንጽህና፣ ቀለም፣ ኃላፊነት

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ ሰርቶ ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

* ህጻናት በአከባቢያቸው ያሉ ሰዎችና የቤተሰቦቻቸው አባላት ሀላፊነት ጠይቀው በመምጣት ክፍል ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡ ሁሉም ህጻናት የእያንዳንዱን ቤተሰብ አባል የሥራ ድርሻና ልዩ ሀላፊነት ብበሚገባ ተረድተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቤተሰብ አባላት ልዩ ልዩ ሥራዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች/ፎቶዎችና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ስለፕሮጀክታቸው አጠቃላይ ነገር ከሚያቀርቡት ተነስተው መጠየቅ

ሳምንት ሠላሳ

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- የቅርብ ዘመዶቻቸውን ስም በመጥቀስ ዝምድናቸዉን ይናገራሉ፣
- ቃላቶችን ድምፁ ከሚወክለው ስዕል ጋር ያዛምዳሉ፣
- ከሁለት አማራጭ መካከል ምርጫ ያደርጋሉ፣ የእቃዎችን አቅጣጫ ይናገራሉ፣
- ሙዚቃና ዳንስን በመለማመድ ሃሳብ ይሰጣሉ፣
- ካሉበት ቦታ ሳይንቀሳቀሱ ከ4 እስከ 7 ክህሎቶችን ያሳያሉ፣
- የጤናማ ምግብ አዘገጃጀት ችሎታን ያሳያሉ፣
- የአደገኛ አከባቢ መረጃን ያውቃሉ፣
- ቀላል ያሉ ቃላት ትርጉም ልምምድ ያደርጋሉ፣
- ማንሳትን በመጠቀም እስከ 10 ድረስ ቁጥሮችን ይቀንሳሉ፣
- እስከ 10 ድረስ ሁለት ቁጥሮችን ይደምራሉ፣ ይቀንሳሉ።

ንዑስ ይዘቶች፦

- ራስን ማስተዋዎቅ
- ድምፅ መለየት
- ውሳኔ የማድረግ ችሎታ
- ለውበት ዋጋ መስጠት
- የትላልቅ ጡንቻ እድገት
- አመጋገብ
- ደህንነት እና ጥበቃ
- ቃላት
- ቁጥር መቀነስ
- ቁጥር መደመር

ተግባር 1፡- መዝሙር

ሀ. ትንሿ ብሌን (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁጥር መቀነስ፣ ቁጥር መደመር፣ ራስን ማስተዋወቅ፣ ትላልቅ ጡንቻዎች፤ አመጋገብ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

መቅረጸ ድምጽ፣ ቴሌቪዢን፣ ፍላሽና ወዘተ

መዝሙር 1፡- ትንሿ ብሌን

ብሌን እባላለሁ ትምህርት እወዳለሁ
መዝሙር እችላለሁ ዳንስ እሞክራለሁ
ከአረት ሲቀነስ ሁለት ቀሪው ነው ሁለት
ሁለት ሲደመር ሁለት ይሆናል አራት
ደግሞ ልንገራችሁ ሌላም እችላለሁ
በመዝሙር እየዘመርኩኝ አቅጣጫ እነግራለሁ
እንቀሳቀሳልሁ ስፖርት እሰራልሁ
ትልልቅ ጡንቻዬን እጠነክራልሁ
ሁሌም ጤነኛ ነኝ ምግብ እበላለሁ 2x
ከምግብ አይነቱ አመጣጥናለሁ 2x

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለ. ትንሿ ክራሬ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ድምጽ፤ መንቀሳቀስ፤ ፊደላትን ማንበብ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

መቅረጸ ድምጽ ፣ቴሌቪዥን ፣ፍላሽና ወዘተ

መዝሙር 2:- ትንሿ ክራሬ

ትንሷ ክራሬ የድምጽሽ ማማሩ
ከሩቅይጠራኛል እያለ እሽሩሩ
እቤት ቁጭ ብዬ እጫወታል
ብዙ ጨዋታዎች በደንብ አውቃለሁ
ኳስ እቃቃ ቅብብሎሽ
ጠጠር እና ብይ እንቆቅልሽ
ስለዚህ እናንተም በደንብ ተማሩ
ቁጥሮችን በመፃፍ ቀንሱ ደምሩ

ምዘና:- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 2:- ተረት

ሀ. የአሊ ቤተሰቦች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት:- ቁጥር፣ ምግብ፣ ቀለማት፣ አክስት፣ አጎት፣ ክረምት፣ በጋ

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስዕሎችና ወዘተ

አሊ እና ቤተሰቦቹ

በአንዲት ትንሽ መንደር ውስጥ አሊ ከቤተሰቦቹ ጋር ይኖሩ ነበር። የአሊ ቤሰቦች 2 ሴት ልጆች፤ 2 ወንድ ልጆች፣ ባለቤቱ፣ እናቱእና አያቱናቸው። አሊ ልጆቹ በክረምት ብርድ ስላላ ወፋፍራም ልብሶች ሙኒ ሹራብ፣ ጥቁር ጃኬትና ካቦርቶች እንዲሁም የቦት ጫማዎችን በመግዛት አመጣላቸው። በሙቀት ግዜ ልጆቹ የሚለብሱት ለስላሳ ልብሶችና ክፍት ጫማዎች ለቅዝቃዜ ያጋልጣቸዋል ብሎ በማሰብ ለቅዝቃዜ የገዛላቸውን ልብስ እንዲለብሱ ሰጣቸው። የአሊ እናትና አያቱ በክረምት ወቅት ትኩስ መጠጦችንና ምግቦችን መመገብ ስለሚፈልጉ አሊም ለክረምት የሚሆኑ የሚቆረጠሙ ጥራጥሬዎች፣ ሻይቅጠል፣ ድንች፣ ለንፍሮና ገንፎ የሚሆኑ እህሎችን እና ማርን በመግዛት ትኩስ ምግቦችን እንዲመገቡና ትኩስ የሚጠጡ ነገሮችን በማፍላት እንዲጠጡ አዘጋጀላቸው አሊ እና ቤተሰቡ በእረፍት ቀን በጋራ የተለያዩ ጤናማ ምግቦችን ይሰራሉ ልጆቹም እንዴት እንደሚሰሩ ከነሱ ለመማር ይሞክራሉ ከእለታት አንድ ቀን አክስታቸው አንሻ እና አጎታቸው ከድር ከእነሱ ጋር ለማሳለፍ ስለመጡ አሊ እና ቤሰቡ በመተባበር የሚጣፍጡ ምግቦችን ሰርተው በማቅረብ አብረው በደስታ ተመገቡ።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡- አሊ ማነው፤ ምን አደረገ?

ተግባር 3፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. መስሎ ጨዋታ (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቀለም፣ የቅርብ ዘመድ፣ ምግብ፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱ ከላይ ያለውን የአሊና ቤተሰቡን ተረት በመስሎ ጨዋታ እንዲጫወቱ ለማድረግ ለህፃናቱ በተረቱ ውስጥ ያሉትን የአሊን እና የቤተሰቡን ስም እና የቤተሰብ ሓላፊነት እና የስራ ድርሻ ሚና በመስጠት በመስሎ ጨዋታ እንዲወጡ ያርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ አልባሳት፣ የቤት ቁሳቁስና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከጨዋታው ፍሬ ሀሳብ ተነስተው የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ....

ለ. ቀላል ስሌቶች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ስሌት፣ ምርጫ፣ ቁስ፤ ቁጠር፤ የትላልቅ ጡንቻዎች መዳብር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

• አስቀድመው ለጨዋታው የሚያስፈልጉትን መጫወቻዎች ያዘጋጁ። ለምሳሌ፡- ከአምስት የማይበልጡ ኳስና እሻንጉሊት...

• ከዚያም በክፍል ውስጥ ሁሉም ህፃናት ማየት በሚችሉበት ቦታ ላይ ያስቀምጡ፤

• ጨዋታው መደመር እና መቀነስ ነው። ሁለት ሁለት እየሆኑ በመውጣት የተሰጣቸውን ይደምራሉ፤ ይቀንሳሉ። ቀድሞ የጨረሰ አሸናፊ ይሆናል። ያልጨረሱት ከቀጣይ ተረኛ ጋር ደግመው ይወዳደራሉ።

• ጨዋታውን ለመጫወት ፈቃደኛ የሆኑ 2 ህፃናት ያስወጡና ያዘጋጁትን አስር ትንንሽ አሻንጉሊቶች ጠረጴዛ ላይ በማስቀመጥ በሌላ ጠረጴዛ ደግሞ አራት ማዕዘን ካርቶን ወይም ስፋ ያለ ሌላ ቅርጽ ያለው እቃ በጠረጴዛ ላይ ያዘጋጁ፤

• ቀድሞ የወጡትን ህጻናት ከአሻንጉሊትና ከኳስ እንዲመርጥ በማድረግ የመረጠውን ሁለት አንስቶ ወደ ሳጥኑ ውስጥ እንዲከት ያድርጉ። ቀጥሎ አንድ ይጨምሩ ስንት እንደከተቱ ሁለት እና አንድ ስንት እንደሆነ ይናገሩ።

• ከዚያም ቀጣዮቹ ህጻናት ሲጫወቱ ማእዘኑ ውስጥ ያለውን በመቁጠር እላዩ ላይ እንዲጨምሩበትና ስንት እንደሆነ እንዲናገሩ ያድርጉ፤

• የመጀመሪያውን ደምረው ከጨረሱ ቀጥሎ ደግሞ የመቀነስ ተግባርን እንዲያከናውኑ ያድርጉይህን ያህል ውሰድ በማለት እንዲቀንሱና ስንት እንደቀረ እንዲናገሩ ያበረታታቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የተለያዩ አልባሳት፣ የቤት ቁሳቁስና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከጨዋታው ፍሬ ሀሳብ ተነስተው የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ....

ተግባር 4፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. አቅጣጫ ማወቅ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ድምፅ፣ ቁጥሮችን መቁጠር፣ ትልልቅ ጡንቻዎች፣ ውሳኔ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ስርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

“አቅጣጫን የማወቅ ጨዋታ” የሚለውን ጨዋታ ለማጫወት የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች በመከተል ህፃናትን ያጫውቷቸው። • ለጨዋታው የሚመች ቦታ መፈለግ፣ ህፃናት በሰልፍ በመስመር እንዲሰለፉ በማድረግ የአቅጣጫ ጨዋታ እንደሚጫወቱ መናገር፣ ለህፃናቱ ወደ ግራ፣ ወደ ሃላ፣ ወደ ቀኝ፣ወደፊት፣ ወደ ላይ እና ወደታች ሲባሉ እየዞሩ፣ ጎንበስና ቀና በማለት አቀጣጫን እንዲያመለክቱ ንገሯቸው።

• በቀጣይ የአቅጣጫን ጨዋታ በክፍል ውስጥ ሆነው እንዲጫወቱ በማድረግ የበር፣ የመስኮት፣ የብላክ ቦርድ፣ የወለል፣ የጣሪያ፣ የተለያዩ የተሰቀሉ ስእሎችን በመጥራት ህፃናት አቅጣጫውን እንዲያመለክቱ በማድረግ አጫውታቸው። በክፍል ውስጥ አንድ ጠረጴዛ በማዘጋጀት በጠረጴዛው ስር፣ ጎን፣ ፊት፣ ኋላ እና በላዩ ላይ የተለያዩ እቃዎችን በማስቀመጥ ህፃናትን እቃው የሚገኝበትን አቅጣጫ እንዲናገሩ በመጠየቅ አቅጣጫዎችን ማስያዝ በዚያ አቅጣጫ የተቀመጡ ቁሶች ካሉ እንዲቆጥሩ ያድርጉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

አቅጣጫ ጠቋሚ ስእሎችና ሌሎች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን አቅጣጫዎችን አወቃችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት የተግባሩ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 5፡- ውይይት

ሀ. ራስን ከአደጋ ክስተት መከላከል (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ራስን ማስተዋወቅ፣ ደህንነት፤ ጥበቃ፣ አደጋ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* በቅድሚያ ራሳችንን ከአደጋ እንዴት እንደሚንጠብቅ አጭር ማብራሪያ ይስጧቸው።

* በመቀጠል ህጻናት ተራ በተራ እጅ እያነሱ ሀሳብ እንዲሰጡ ይጋብዟቸው።

* ሁሉም ህጻናት ሀሳባቸውን በትክክል መስጠት እስከሚችሉ ድረስ ውይይቱን በጥያቄና መልስ ያስቀጥሉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከውይይቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስእሎችና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የውይይቱን ፍሬ ሀሳብ መነሻ ያደረጉ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት የውይይቱ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ለ. ወቅቶችና ቃላት ከምስሎች ጋር ያላቸው ዝምድና (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ዝምድና፣ ቃላቶች፣ ምግብ፣ ሰላምታ አለዋወጥ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* በቅድሚያ ከወቅቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስዕሎች አቅርበው አጭር ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡

* በመቀጠል ህጻናት ተራ በተራ እጅ እያነሱ ሀሳብ እንዲሰጡ ይጋብዟቸው፡፡

* ሁሉም ህጻናት ሀሳባቸውን በትክክል መስጠት እስከሚችሉ ድረስ ውይይቱን በጥያቄና መልስ ያስቀጥሉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከውይይቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስእሎችና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የውይይቱን ፍሬ ሀሳብ መነሻ ያደረጉ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ሳምንት ሠላሳ አንድ

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፡- 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፡-

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

- ከሌሎች ጋር ያለግንኙነት
- ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ አካባቢዎች
- በአካባቢያቸውያሉቁሶችን ሰያሜይጠቅሳሉ
- የፊደላትን ድምፅና ቅርፅ
- ሙዚቃዊ ምት ያላቸው እንቅሰቃሴዎች
- ከጓደኞቻቸው የሰውነት አቀማመጥ ላይ ለውጦችን መኮረጅ
- ቁሶችን በመጠቀም መቀነሰና
- እስከ 10 ቁጥሮችን መደመርና መቀነሰ
- ዕቃዎችንበተለመዱባህሪዎች

ንዑሰ ይዘቶች፡-

- የቃላት እውቀት
- የፊደላት ድምፅ
- ግንኙነት ዝምድናና ትግበራ
- የቦታ ግንዛቤ
- ቁጥሮችን መቀነሰ
- ቁትሮችን መደመር
- ፊደላትን መፃፍ
- ልኬት

ተግባር 1፡- ተረት

ሀ.ሁለቱ ወንድማማቾች (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ግንኙነትን ማጠንከር፤ ቁጥር፣ የቦታ ገንዛቤ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መስረት ያውሩ፡፡ ለምሳሌ፡- ሳር፤ ፍየል፤ ቻርት

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስዕሎች ወዘተ

ሁለቱ ወንድማማቾች

ፍየልና በግ በአንድ ቤት ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ ከእለታት በአንዱ ቀን አብረዉ መንገድ እየተጓዙ ሳሉ ኃይለኛ የክረምት ዝናብ ዘንቦባቸዉ ጎርፍ ያዛቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ፍየሉ በብርድና በቅዝቃዜ እየተንቀጠቀጠ ለበጉ ‘’ፈራሁ፤ ጎረፉ ሊወስደኝ ነው’’ አለዉ፡፡ በዚህ ጊዜ በጉ ትንሽ አሰበና ‘’እኔ ብርድና ዉኃ አልፈራም ና ጀርባዬ ላይ ዉጣ’’ ብሎት ተሸክሞት ወደ ደረቅ ቦታ ወሰደው፡፡ ፍየሉም‘’በጣም አመስግናለሁ፤ እኔም አንድ ቀን እረደሃለሁ’’ ብሎት ደስ እያላቸዉ ወደ ቤታቸዉ ገቡ፡፡ ታዲያ የክረምትና የመከር ወቅት አልፎ የበጋ ወቅት ሲመጣ ኃይለኛ ፀሀይ ስለነበር መሬት ላይ ያለ ሳር ሁሉ ደርቆ በጉና ፍየሉ የሚበሉትን አጥተው ተራቡ፡፡ በጉ ፍየሉን‘’ የሚበላ ሳር አጥቼ በራብ መሞቴ ነዉ’’ አለው፡፡ በዚህ ጊዜ ፍየሉም‘’ አሁን በጋ ስለሆነ ሳሮች ሁሉ ደርቀዉ ጠፍተዉ መረቱ አፈር ብቻ ነዉ፡፡ ዛፎች ላይ ግን ቅጠሎች ይታዩኛል፡፡ ስለዚህ እኔ በኋላ እግሬ መሬት ላይ ቆሜ የፊት እግሮቼን አንስቼ ቅጠሉን ወደ ታች ስቤ አቀርብልሃለሁ፤ ከዚያም አብረን እንብላ’’ አለዉ፡፡ ፍየሉ ሁለቱን ፊት እግሮቹን ወደላይ ከፍ በማድረግ የዛፉን ቅርንጫፍ ወደጣች በመጎተት ለበጉ አቀረበለት በጉም ጓደኛው ፍያልበደረገው ነገር በእጅጉ አመሰግኖ ሁለቱም ቅጠሉን በልተዉ ጠግበው ወደ ቤታቸዉ ተመለሱ ይባላል፡፡

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ለምሳሌ፡- ሁለቱ ወንድማማቾች የተባሉት እነማን ነበር?

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ. የፊደል ቅርጽ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቅርጽ፣ መጸፍ፣ ማንበብ፣ ቁስ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ስርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

በመጀመሪያ የእለቱን ፊደል (ቸ-ቹ-ቺ-ቻ-ቼ-ች-ቾ እና ኘ-ኙ-ኚ-ኛ-ኘየ-ኝ-ኞ) በፍላሽ ካርድ/በነጭ/በጥቁር ሰሌዳ ጽፈው ያሳዩአቸው እና በጋራ እንብቡ ቀጥሎ ሁሉም ህፃናት በየተራ ያንብቡ ፤

በመቀጠል ፊደላቱን ለመፃፍ የሚያገለግሉ ቁሶችን ስም በስም እንዲናገሩ ማድረግ (እርሳስ፣ ደብተር፣ መጽሀፍ፣ ጠረጴዛ….) ከዚያ ለመጽህፈት የሚያገለግላቸውን ቁሳቁስ በራሳቸው በየተራ ወስደው ካዘጋጁ በኋላ ፊደላቱን ደግመው ይፃፉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደላት ፍላሽ ካርድ/ሞዴል፣ ደብተር፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ መቅረጫ፣ ጥቁር እና ነጭ ሰሌዳ፣ ማርከር

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን ፊደላትን ተዋወቃችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት በተግባሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ለ. ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ግንኙነት፣ ቁሶች ሰው ሰራሽ፣ ተፈጥሮ፣ አካባቢ፣ ሙዚቃዊ እንቅስቃሴ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

* በመጀመሪያ በስዕል እና በመሰል አሰደግፈው የተፈጥሮ እና ሰውሰራሽ አከባቢን ያሳዩአቸው፡፡

* በመቀጠል ከቅርባቸው ከሚገኙ ቁሶች ጠፈጥሮአዊ እና ሰውሰራሽ የሆኑትን በሰም ለይተው እንዲጠሩ ማድረግ፤

* ቀጥሎ ለሰዕል መሳያነት የሚያገለግሉ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ደብተር፣ የተለያዩ ቀለማት የቁሶችን ሰም እየጠሩ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፤

* ከዚያም በተፈጥሮ የሚገኙና ሰው የሰራቸውን ነገሮች ውሰጥ እነሱ የፈለጉትን ሰለው እንዲቀቡ ማድረግ፤

*ሲሰሩ እና ሲናገሩ ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር መከባበር እና መረዳዳት መከባበር አሰፈላጊ ሰለሆነ ግንኙነታቸው ጥሩ እንዲሆን ክትትል ያድርጉ፡፡

* እቃ ሲዋዋሱ ፍቃድ መጠየቅ፣ ሲያጠፉ ይቅርታ መጠየቅ፣ ሌሎች ለሚያደርጉላቸው ነገሮች ምሰጋና ማቅረብ…

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደላት ፍላሽ ካርድ/ሞዴል፣ ደብተር፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ መቅረጫ፣ ጥቁር እና ነጭ ሰሌዳ፣ ማርከር

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የተባሉት ምን ምን ናቸውና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት በተግባሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 3፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. የሌሎችን የሰውነት እንቅስቃሴ አይቶ መናገር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- አካላዊ እንቅስቃሴ፣ ሙዘቃ፣ ከሌሎች ጋር ግንኙነት፣ የሰውነት ለውጥ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱን በሁለት ስያሜ ማታና ቀን በማለት ይሰይሙ በመቀጠልም ለህፃናቱ ማታንና ቀንን የሚወክሉ ነገሮችን ይስጧቸው። ለምሳሌ፡- ጨረቃ እና ፀሀይ በመቀጠል የያዙትን እየተቀባበሉ ለጓደኛቸው የተለያየ አካላዊ እንቅስቃሴ በማሳየት እንዲደግመው መጠየቅ፤ ጓደኛውም በትክክል ያየውን ተግባር አስመስሎ ለመተግበር መሞከርና ቀጥሎ ለሌላ ሰው ሌላ እንቅስቃሴ ማሳየት ... ያየውን ተግባር በትክክል ያላስመሰለ ተማሪ ህጻን ይሆናል። ከማታና ከቀን ማን ብዙ እንቅስቃሴ እንደለየ ለይታችሁ ማበረታቻ የሚሆን የሙዚቃ ምት ያለው ባህላዊ ዘፈን/መዝሙር በመክፈት እንዲደንሱ ያድርጉ። በሚሰሩበት ጊዜ ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ተገቢነት እና ተቀባይነት ያለው መሆን እንዳለበት ያሳውቁ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ቀን እና ማታን የሚያሳዩ ስእሎች፣ ቴፕ፣ ጂፓስ፣ ስልክና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ተግባራቱን ስትሰሩ ምን ተሰማችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።
* ሁሉም ህጻናት የተግባሩ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ተግባር 4፡- ውይይት

ሀ. ከሌሎች ጋር ያለን ግንኙነትና የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አካባቢ (5 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሰው ሰራሽ፣ ተፈጥሮ፣ ግንኙነት

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

* በቅድሚያ ከሌሎች ጋር ስለሚኖረን ግንኙነትና የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አከባቢ አጭር ማብራሪያ ይስጧቸው።
* በመቀጠል ህጻናት ተራ በተራ እጅ እያነሱ ሀሳብ እንዲሰጡ ይጋብዟቸው።
* ሁሉም ህጻናት ሀሳባቸውን በትክክል መስጠት እስከሚችሉ ድረስ ውይይቱን በጥያቄና መልስ ያስቀጥሉ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የሚነጋገሩ ሰዎች ስዕል፣ የተፈጥሮና ሰው ስራሽ አከባቢን የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* የውይይቱን ፍሬ ሀሳብ መነሻ ያደረጉ የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ሁሉም ህጻናት የውይይቱ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 5፦ መዝሙር

ሀ. ስንጫወት በጋራ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - እንቅስቃሴ፣ ተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የቁሶች ስዕል፣ የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣ የእንስሳትና የአእዋፋት ስዕል፣ ቀንና ማታን የሚያሳዩ ስዕሎች...

መዝሙር 1፡- እንጫወት በጋራ

ስንጫወት በጋራ ተግባብተን
እስቲ እንወዛወዝ ሙዚቃ እየሰማን
ቀንበስራ ውለን ማታ እየተኛን
በአካባቢያችን ብዙ ቁሶች አሉ
እፅዋት እንስሳት እንዲሁም አዋፈት
ብዙ ቁሳቁሶች ተዘርዝሮ ማያልቅ
1 2 3 4 ብለን እንቆጥራለን
እስቲ እንጥራቸው የተወሰኑትን፡፡

ምዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

ሀ. አበባዬ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - የቦታ ግንዛቤ፣ ግንኙነት፣ ተፈጥሮ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና:-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ:-

* የቁሶች ስዕል፣
* የቁጥር ፍላሽ ካርድ፣
* የእንስሳትና የአእዋፋት ስዕል፣
* ቀንና ማታን የሚያሳዩ ስዕሎች...

መዝሙር 2:- አበባዬ

አበባዬ አበባዬ አበባዬ እወድሻለሁ
ጠዋትም ማታ እንከባከብሻለሁ
ውሃም አጠጣሻለው እንድታምሪልኝ
እባክሽ አበባዬ እደግልኝ
ጓደኞቼ ተነሱ እንጫወት
የበጋ ወቅት አልፎ መቷል ክረምት
በጋራ ባንድነት በስምምነት
አይገኝም እና ሁልጊዜ ልጅነት
ከአበባዬ ጋራ ኑ እንደሰት 2x

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 6፦ የመስክ ጉብኝት

ሀ. የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቁሳቁሶች (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- እንቅስቃሴ፣ ተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ፣ ቁጥር

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጉብኝት፣ ጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ህፃናቱን ወደ ውጪ ይዞ በመውጣት በአካባቢያቸው ያሉ ቁሶችን እየተመለከቱ እርስ በርስ በመግባባትና በመደማመጥ ያዩትን ቁስ ስያሜ እንዲጠቅሱ እንዲሁም የተመለከቱትን ቁስ በተለመደ ባህሪ እንዲያወዳድሩ በማታና በቀን የሚገኙ በማለት እየቆጠሩ፣ እንዲመድቡ በማድረግ እንዲሁም ተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ቁሶችን ለይተው እንዲመድቡ በማድረግ ጉብኝቱን ያከናውኑ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

በአካባቢ የሚገኙ የተለያዩ ቁሶችና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን ምን ቁሶችን ተመለከታችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት የተግባሩ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ሳምንት ሠላሳ ሁለት

ለሳምንቱ የተሰጠ ጊዜ፦ 30 ክ/ጊዜ ወይም 750 ደቂቃ

አጥጋቢ የመማርና ዕድገት ብቃቶች፦

ህጻናት ከዚህ ሳምንት ትምህርት በኋላ:-

o ቁሶችን ለመለካት ባህላዊ መለኪያዎችን ይጠቀማሉ

o አካሎቻቸውን ወደተለያዩ አቅጣጫዎች ያንቀሳቅሳሉ

o በሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ቁሶች መሰረታዊ ቀለማትን ይደረድራሉ

o የቴክኖሎጂ ቁሶችን ይጠቀማሉ

o የገንዘብን ዋጋ ይረዳሉ

o በአከባቢያቸው ለእነሱ ሞዴል ሰው ይለያሉ

o እስከ አስር ያሉ ቁጥሮችን በማንሳት ስትራቴጂ ይቀንሳሉ

o እስከ አስር ያሉ ቁጥሮችን መደመር ይችላሉ

o የተሰጡ ፍደላትን ያነባሉ

o የተመረጡ ምታዊ እንቅስቃሴዎችን ያሳያሉ

ንዑስ ይዘቶች:-

o ማወዳደር

o ዓይቶ መገንዘብ

o ጥበብን መገንዘብ

o ድጂታል ሊትሬሲ ክህሎት

o ገንዘብ

o ሀገርን መውደድ

o ቁጥሮችን መቀነስ

o ቁጥሮችን መደመር

o ማንበብ

o ሞራላዊ ዕሴቶቻችን

o ምታዊ እንቅስቃሴዎ

ተግባር 1፡- ተረት

ሀ. ጀግኖቻችን (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ሀገር መውደድ፣ ቁጥር፣ ሞራላዊ እሴቶች

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በትረካ፣ በገለፃ፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን ተረት በተረት አቀራረብ መሰረት ያውሩ። ለምሳሌ፡- ሳር፤ ፍየል፤ ቻርት

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ከተረቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ለምሳሌ የተለያዩ ቤተብ፣ የተለያዩ ስራ ላይ ተሰማርተው ያሉ ሰዎች፣ የስፖርት ሜዳን ሲያፀዱ የሚያሳይ ሞዴሎች/ተንቀሳቀሽ ምስልና ወዘተ

ጀግኖቻችን

ሀገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ጀግኖች አሏት። ጀግኖቿ የተለያዩ ሥራዎችን በመስራት የሚታወቁ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ ቀዳሚው አበበ ቢቂላ ነበር። አበበ በባዶ እግሩ ሮጦ የሀገሩን ስም ከፍ አድርጓል። ሌላይኛው ሀይሌ ገ/ስላሴ ነው። ሀይሌም እንደ አበበ ሁሉ ሯጭ ነው። በሚያገኘው ገንዘብ ከሩጫው ጎን ለጎን ይነግዳል፡ ፡ ሀይሌ ከ10 በላይ ሆቴሎች ያሉት ሰሆንብዙ ስራተኞችን ቀጥሮ ያሰራል። ሀይሌ ክረምት ክረምት እርሻ ያርሳል። ዝናብ ከመጣ እሱ ሁሌም ወደ ጓሮ ነው የሚሮጠው። ሁለቱም ጅግኖች ሀገራቸውን በጣም ይወዳሉ፡ ፡ አበበ ሰው አክባሪ፣ የተቸገረን የሚረዳና ግጭቶች ሲፈጠሩ እንኳን በመነጋገር የሚፈታ ነበር። ሀይሌም እንደዚያው። ሁለቱም ጀግኖቻችን በሰሯቸው ሥራዎች እስካሁን ስማቸው ጎልቶ ይነሳል።

ምዘና፡- የቃል ጥያቄ

ከተረቱ ምን ተማራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ለምሳሌ፡- እነሀይሌ ገ/ሲላሴ ጀግኖቻችን የተባሉት ለምን ይመስላችኋል።

ተግባር 2፡- የተግባር ሥራ

ሀ. ቁሶችን መለካትና መደርደር (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁሳቁስ፣ ቁጥር፣ ሰው ሰራሽ፣ ባህላዊ መለኪያ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን የተግባር ሥራ በተቀመጡ ቅደም ተከተሎች መሰረት ያሰሯቸው።

• የተለያዩ የተፈጥሮ ቁሳቁሶች (ቅጠሎች, ድንጋዮች፣ እንጨቶች) እና ሰው ሠራሽ ቀለም ያላቸው ነገሮች (ብሎኮች፣ ክሬይኖች፣ ጨርቆች፣ የተለያዩ ጠንና ቁመት ያላቸው ዘንጎችን) ያቅርቡ፤

• ከጫማ ማሰሪያ፣ ጨርቅ ወይንም ገመድ የመለኪያ መሳሪያ ይስሩ።

• ከቀረቡ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቁሶች የተወሰኑትን በመለኪያ ገመዱ ለክተው ያሳዩአቸው።

• ህጻናት ቁሶቹን ተራ በተራ እየተነሱ እንድለኩና በቀለማቸው መሰረት ቆጥረው እንድደረድሩ ያበረታቷቸው።

• ህጻናት የለኳቸውና የደረደሯቸው ቁሶች የተፈጥሮ ወይንም ሰው ሰራሽ መሆናቸውን በቃል እንድያወሩ ያድርጓቸው።

• ህፃናቱ ከተሰጣቸው የተፈጥሮ እና የሰውሰራሽ ቁሶችን ተጠቅመው በመቁጠር መቀነስን ያሳዩአቸው።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

በአካባቢ የሚገኙ ቁሶች፣ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ቁሶች፣ገመድ፣ ብሎኮች፣ ጨርቆች፣ ዘንጎች/እንጨቶች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ተፈጥሯዊ ቁሶች የተባሉት ምን ምን ናቸውና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት በተግባሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ለ. ፊደላትን ከፍላሽ ካርድ ላይ ማንበብ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - አይቶ መገንዘብ፣ ማንበብ፣ ፊደል፣ እንቅስቃሴ፣ ሙዚቃ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በተግባር ሰርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን የተግባር ሥራ በተቀመጡ ቅደም ተከተሎች መሰረት ያሰሯቸው።

• ከሀ እስከ ፐ ካሉት የፊደል ቤተሰብ ቢያንስ አስር የሚሆኑ የፈለጉትን መርጠው ፍላሽ ካርድ በየጠረጴዛቸው መስጠትና በቡድን ሆነው ፊደሎቹን ተገንዝበው እንዲያነቡ ማድረግ፤

• ቀጥሎ ህጻናት ተራ በተራ እየተነሱ የሚያዩዋቸውን ፊደላት እንዲያነቡ እና በነጭ/በጥቁር ሰሌዳ ቢያንስ አንድ የፊደል ቤተሰብ እንዲጽፉና እንዲቆጥሩ ያበረታቷቸው።

• በመቀጠል የተለያዩ ሙዚቃዊ ምት ያላቸውን ምቱን እራሳቸው እየመቱ እንቅስቃሴውን ያሳያሉ፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የፊደል ፍላሽ ካርድ፣ ቾክ፣ ማርከር፣ የሙዚቃ ማጫወቻ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ዬትኞቹን ፊደላት አነበባችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ህጻናት በተግባሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

ሐ. የሙዚቃ ምት ተከትሎ እየተንቀሳቀሱ ቁስ መቀባበል (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁጥር፣ ቴክኖሎጂ፣ ምታዊ እንቅስቃሴ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር ስርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

ቀጥሎ የቀረበውን የተግባር ሥራ በተቀመጡ ቅደም ተከተሎች መስረት ያሰሯቸው፡፡

- ኳስ/ጨርቅ/ሀይላንድ ውይም ሌላ የተገኘ ቁስ ያቅርቡ፤
- በቴፕ/ጂፓስ/ሞባይል ስለወቅቶች የተዘፈነ ምት ያለውን ሙዚቃ ይክፈቱ፤
  (ለምሳሌ የአስራ ሶስት ወር ፀጋ) የሚለውን
- ለህጻናት ከአንድ እስከ አስር ቁጥር ስጥዋቸው በቁጥራቸው መሰረት እየተነሱ ክብ ስርተው እንድቆሙ ማድረግ፤
- የተሰጣቸውን ቁስ ከአጠገባቸው ላሉ ጓደኞቻቸው በአክብሮት ጎንበስ እያሉ ሰያቀብሉ የሙዚቃን ምት ተከትለው እንድንቀሳቀሱ ማበረታታት፤
- ተግባሩ ሲጠናቀቅ ልጆቹ አንድ በአንድ ቁጥራቸው እየተጠራ እንዲቀመጡ ቀጣይ ተረኛ ህጻናትን ማሰራት፤

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

ቴፕ፣ ሞባይል፣ ጂፓስ፣ ኳስ፣ ሀይላንድ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ምን የተክኖሎጂ ቁስ ተጠቀማችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት በተግባሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

መ. ቁስ ማንሳትና መጨመር (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ቁጥር፣ መቀነስ፣ መደመር፣ ተፈጥሮ፣ ሰው ስራሽ

የማስተማሪያ ዜዴ:- በገለፃ፣ በተግባር ስርተው ማሳየት

የመምህር ሚና፡-

o የዛፍ ፍሬ፣ ጠጠር፣ ቆርኪ፣ የሀይላንድ ክዳንና ሌሎች ተቆጣሪ ተፈጥሮአዊና ሰው ስራሽ ቁሶችን አስር አስር እያደረጉ በማቅረብ ልጆች በሰሃን አድርገው ማዞር፤ ልጆች የቻሉትን ያክል ቁስ እንድያነሱ ማድረግና ያነሱትን ቁስ መልሰው እንድጨምሩ ማበረታታት (ቁሱን በሚያነሱበትና በሚጨምሩበት ጊዜ ስንት እንደቀረና ስንት እንደሆነ እንዲያወሩ ይደረግ)፤

o ቀጥሎ ህፃናቱ ከተሰጣቸው ቁሶች ውስጥ መሰረታዊ ቀለም ያላቸውን እንዲለዩ ያድርጉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የዛፍ ፍሬ፣ ጠጠር፣ ቆርኪ፣ የሀይላንድ ክዳንና ሌሎች ተቆጣሪ ቁሶች

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ስንት ቁስ ጨመራችሁና ሌሎች ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፡፡

* ህጻናት በተግባሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 3፡- የክፍል ውስጥ ጨዋታ

ሀ. ትንሹ ባለሱቅና ደንበኛው (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ ሞራላዊ እሴቶች፣ ገንዘብ

የማስተማሪያ ዜዴ፡- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ለዚህ ሳምንት የቀረበው መስሎ ጨዋታ “ትንሹ ባለሱቅና ደንበኛው” የተሰኘ ነው፡፡ ይህንን ጨዋታ ለማጫዎት የሚከተሉት የድርጊት ቅደም ተከተሎችን ይከተሉ፡፡

• ትንሽዬ የእህል መሸጫ የእህል/የጥራጥሬ ሞዴል (በአሸዋ፣ በትንንሽ ጠጠሮችና ወዘተ የተሞላ) ሱቅ አስመስለው ያዘጋጁ፡

• የብር፣ የሳንቲም፣ የኪሎ ገራሞችና ሚዛን፣ ሊትር ሞዴል ያቅርቡ እንዲሁም የሂሳብ መስሪያ ካልኩሌተር ያዘጋጁ፤

• ቀጥሎ ህፃናትን በየተራ የገዥና ሻጭ ጨዋታ እንዲጫወቱማድረግ፡፡ ለምሳሌ፡- ገዥዎች ሳንቲም ወይንም ብር ይዘው ይመጡና የዘር በቆሎ… ጠይቀው እንድገዙ ማድረግ፤ ሻጩ በኪሎ ይመዝንና ሂሳቡን በካልኩሌተር አስልተው ይናገራል፡፡

• ህጻናት ሁለት ሁለት እየሆኑ በመነሳት የገዥና ሻጭ ሚና እንድጫወቱ ማበረታታት ሽያጭና ጊዢ ሲካሄድ በገዢኛ ሸማች መካከል አክብሮት፣ መልካም አገልጋይነት፣ትህትና፣ ምስጋና… እንዲኖር ጥቆማ ይስጡ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የእህል ሱቅ ሞዴል፣ የተለያዩ የእህል አይነቶች/ሞዴል፣ የገንዘብ ሞዴል

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከጨዋታው ፍሬ ሀሳብ ተነስተው የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ….

* ሁሉም ህጻናት በተባለው መስረት የጨዋታው ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ለ. አንድ ወደላይ. . . (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- መቁጠር፣ ማወዳደር፣ አቅጣጫ፣ እንቅስቃሴ፣ ቁጥር፣ መፃፍ፣ ማንበብ

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በጨዋታ፣ በገለፃ፣ በጥያቄና መልስ

የመምህር ሚና፡-

ህጻናትን

- ዝግጁ ማድረግ፣
- ስለጨዋታው ገለፃ ማድረግ፣
- አስፈላጊውን የትምህርት ቁሳቁስ ማዘጋጀትና
- ቀጥሎ ጨዋታውን በተሰጠው መመሪያና እና ቅደም ተከተል መሰረት ማጫወት ያስፈልጋል፡፡
- ሁለት ህፃናት በአንድ ጊዜ ይደረደራሉ፡፡

• ቀጥሎ ሁለት ሁለት እየሆኑ በመነሳት በተነገራቸው መሰረት የተሰጣቸውን ስዕሎች/ሞዴሎች አንድ በአንድ እያነሱ እላያቸው ላይ የተፃፈውን ቃል እየተናገሩ ስዕሉን ይቆጥራሉ፡፡

• የቆጠሩትን አስራ አምስት ቁጥር በወረቀት ይፅፋሉ፡ ቀድሞ የጨረሰ የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል፡፡

• በመቀጠል ‘አንድ ወደ ላይ...’ የተሰኘውን፡፡ ጨዋታውን በተፈለገው ልክ ለማጫዎት ከዚህ በታች የቀረቡ የድርጊት ቅደም ተከተሎችን ይከተሉ፡፡ ጨዋታውን የተለያዩ የሰውነት ክፍላቸን እያንቀሳቀሱ ይጫወታሉ፡፡

• አንድ ወደ ላይ... ውሸት አልወድም፣ ሁለት ወደ ፊት... ሰው አከብራለሁ፣ ሶስት ወደ ኋላ... ፈጽሞ አልዋሽም እያሉ እጅንና እግርዎን ወደ የተለያዩ አቅጣጫዎች ማንቀሳቀስ፤

• ሁሉም ህጻናት ተመሳሳይ እንቅስቃሴ እያደረጉ የሚደርጉትን እንቅስቃሴ እየተያዩ እንዲናገሩ ማድረግ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህጻናት አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ማድረግ ከሌሎች ጋር ሞራላዊ መግባባት ይፈጥራሉ፡፡

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

* የቁጥር ካርድ፣
* የፊደል ፍላሽ ካርድ፣
* እርሳስ፣
* ወረቀት፣
* ላጲስና ወዘተ

ምዘና፡- የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከጨዋታው ፍሬ ሀሳብ ተነስተው የተለያዩ የቃል ጥያቄዎችን መጠየቅ....
* ሁሉም ህጻናት በተባለው መሰረት የጨዋታው ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ፡፡

ተግባር 4፦ መዝሙር

ሀ. ወላጆቻችን (4 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት - ሀገር መዉደድ፣ ገንዘብ፣ ሞራላዊ እሴት፣ ጀግኖች

የማስተማሪያ ዜዴ፡- በገለፃ፣ በመዝሙር፣ ምስሎችን ማሳየት፣ ተንቀሳቃሽ ምስል በማሳየትና ወዘተ

የመምህር ሚና፡-

ከዚህ ቀጥለው የቀረበውን መዝሙር የመዝሙር አቀራረብ መመሪያዎችን ተከትለው ይአዘምሩ።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፡-

የቤተሰብ ስዕልና ወዘተ

መዝሙር 1፡- ወላጆቻችን

ወላጆቻችን ለእኛ ጀግኖቻችን ናቸው
ከዘመዶቻችን ማንም አይተካቸው
ልብስ ይገዙልናል ብራቸውን አውጥተው
እኛን አስቀድመው ሌላ ነገር ተትው
ያስተምሩናል ያሳድጉናል
ትልልቅ እንድንሆን ይጨነቁልናል
ሰው አክባርነትን የተቸገረን መርዳት
ስለምትነግረን ትለያለች እናት
ሰው አክባርነትን የተቸገረን መርዳት
ስልሚያስተምረን ደስ ይለናል አባት።

ሞዘና፦ የቃል ጥያቄ

ከመዝሙሩ ምን ተማራችሁና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

ተግባር 5፡- የክፍል ውጭ ጨዋታ

ሀ. 10 ዶሮዎች አሉኝ (3 ክፍለ ጊዜ)

ቁልፍ ቃላት፡- ቁጥር፣ መቀነስ፣ መደመር፣ ሞራላዊ እሴቶች

የማስተማሪያ ዜዴ:- ሰርቶ በማሳየት፣ በገለፃ፣ በጨዋታ

የመምህር ሚና፡-

ለዚህ ሳምንት የቀረበውን '10 ዶሮዎች አሉኝ' የተሰኘ የክፍል ውጭ ጨዋታ ለማጫዎት ከተለመደው የውጭ ጨዋታ ሥርዓት በተጨማሪ የሚከተሉትን የድርጊት ቅደም ተከተሎችን ይከተሉ።

 አስር ህፃናትን ሴትና ወንድ ቀላቅለው መጥራት እና በትልልቁ ቁጥር በመፃፍ ልብሳቸው ላይ ከፊትለፊት መለጠፍ፤

 አንድ እናት ዶሮ ለብቻ አጫዋች በመሆን 10 ዶሮዎች አሉኝ እስቲ ልቁጠራቸው.... 1... 2.... 3.... 4..... 5.... 6..... 7..... 8.... 9..... 10......አንዷ በራ ሄዴች 9 ብቻ ቀሩኝ ሲባል አንድ ቁጥር ህፃን እየበረሩ ይሄዳሉ ቀጥሎ ዘጠኝ ዶሮች አሉኝ አንዷም በራ ሄዴች አሁንም ከህፃናቱ ሁለት ቁጥር ትበራለች አሁን 8 ቀሩኝ.... እያለች መጨረሻ ላይ "ምንም አልቀረኝም" ትልና "ስማቸውን ልጥራና ሮጠው ይመጣሉ፤ 1.... እቿትና መጣች። 2...." እያሉ የተቀነሱትን በመደመር ጨዋታውን ለቀጣይ ተረኛ ያስረክባሉ ።

 ይህንን ጨዋታ ሁሉም ህጻናት መጫዎት እንድችሉ አንድ ጊዜ በዶሮዎች ሌላ ጊዜ ደግሞ በሌሎች ነገሮች ማስመሰል ያስፈልጋል።

የመጫዎቻና መማሪያ ቁሳቁስ፦

የ10 ዶሮዎች ሰዕልና ወዘተ

ምዘና፦ የቃል ጥያቄና ምልከታ

* ከ10 ዶሮዎች ሁለቱ ቢበሩ ስንት ይቀራሉና ሌሎች የቃል ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው።

* ሁሉም ህጻናት የተግባሩ ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

የአውድ 6 ማጠቃለያ መመዘኛ ቼክ-ሊስት

የህጻኑ/ኗ ስም፡________________________ **ጾታ፡** ________ **ዕድሜ**______

ተ.ቁ	የሚጠበቅ ተፈላጊ የመማርና የዕድገት ብቃት	ጥሩ	በ. ጥሩ	እ..በ.ጥሩ
1	መመሪያዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ማብራሪያዎችን ማዳመጥ እና ተግባራዊ ማድረግ			
2	ስለ ፍላጎታቸው፣ ስለ ወዳጆቻቸው፣ ስለታወቁ ህዝቦች፣ በአካባቢያቸው ስላሉት ነገሮች እና ስለ አካላዊ ባህሪያት መነጋገር			
3	የተለያዩ ድምፆችን፣ አመጣጡን ለይተው ማወቅ እና ከሰዕሎች ጋር ማጣጣም			
4	አንድ ሰው የራሱ ድርጊት በሌሎች ሰዎች ስሜት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር መረዳት			
5	በተገቢው መንገድ ፍላጎቶችን፣ ምርጫዎች፣ ችሎታዎችን እና ስሜቶችን መግለጽ			
6	የመጫወቻ ደንቦችን ማወቅና እና መከተል			
7	እቃዎችን በመጠን፣ ርዝመት፣ ቅርጽ፣ እና ዓይነት መመደብ			
8	ዜሮ ምንም እንደሆነች ማወቅ			
9	እስከ 15 ቁጥሮችን በቃል መቁጠር ማንበብ፣ መጻፍ			
10	ራሳቸውን መረዳ መቻል			
11	ቁሶችን በመያዝ፣ በመቅለብ፣ በመግፋትና በመወርወር መቆጣጠር መቻል			
12	የታወቁ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መለየት እና ማብራራት መቻል			
13	የቅርብ አካባቢንና ደህንነት እንክብካቤ ተረድተው መንከባከብ			
14	የቤተሰብ አባላትና የሙዚቃ መሳሪያ ድምጽ መለየትና ማወቅ			
15	የቤትና የትምህርት ቤት አከባቢያቸውን ማድነቅ			

የህጻኑ/ኗ አጠቃላይ አፈጻጸም፡- ______________________________________

____

____

____

የሳምንታዊ ተባራት መዘርዝር ናሙና

አውድ፡-1 ሳምንት፡- 1

ተግባራት ስም	የሳምንቱ ቀናት				
	ሰኞ	**ማክሰኞ**	**ረቡዕ**	**ሐሙስ**	**እርብ**
መዝሙር	መዝ 1	መዝ 2	መዝ 1	መዝ 2	መዝ 1
	መዝ 2				
ተረት		ተረ 1	ተረ1	ተረ1	
ውይይት	ውይ 1			ውይ 1	ውይ 1
የተግባር ሥራ	ተሥ 1		ተሥ 1	ተሥ 1	
		ተሥ 2	ተሥ 2		ተሥ 2
	ተሥ 3	ተሥ 3			ተሥ 3
የክፍል ጨዋታ	ክጨ 1		ክጨ 1	ክጨ 1	
የመሰክ ጉብኝት			መጉ 1	መጉ 1	
የውጭ ጨዋታ		ውጭ 1			ውጭ 1
ድምር	6	5	6	6	5

ማሳሰቢያ፡- ማክሰኞና እርብ 5 ተግባራት ብቻ የተቀመጡት የክፍል ውጭ ጨዋታ ክ/ጊዜ ያለባቸው ዕለታት በመሆናቸው እንደሰድሰት ክ/ጊዜ ይወሰዳል፡፡

አባሪ 1

የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት የዕለት ዕቅድ ናሙና

የት/ቤቱ ስም፡ አዳማ ቅድመ-አንደኛ ደረጃ
የመ/ር ስም፡ ሳዲያ አማን
ደረጃ፡ 2
አውድ፡ ማህበረሰብ
ሳምንት፡ 1
የህጻናት ብዛት፡ ወ፡ 17 ሴ፡ 23 ድ፡ 40
የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ፡ 25 ደቂቃ

ዓላማዎች፦ ህጻናት ከዕለቱ ተግባራት በኋላ
- ሠላምታ ይለዋወጣሉ፤
- ራሳቸውንና ችሎታቸውን በትህትና ይገልጻሉ፤
- በአካላዊ ገጽታቸው እራሳቸውን ይገልፃሉ፤
- በአከባቢያቸው የሚሰሙ ድምጾችን ይለያሉ፤
- የግል ንጽህናቸውን ይጠብቃሉ፤
- የስሜት ህዋሳትን ስም ይጠራሉ።

ጊዜ	የተግባራት ርዕስ	የመምህር ሚና	የህጻናት ሚና	የትምህርት አቀራረብ ዜደ	መጫዎቻ ቁሳቁስ	ምዘና
2:00-2:30	የመቀበያ ጊዜ	ህጻናትን ጤንነታቸውንና ስሜታቸውን እያዩ ከመግቢያ በር አቀባበል ማድረግ፤ የህዝብ መዝሙር እየዘመሩ የባንዲራ ሥነ-ሥርዓት እንዲያከብሩ ማድረግ፤ ነጻ ጨዋታ እንዲጫወቱ ማበረታታትና ወደ መማሪያ ክፍል ማስገባት	ነጻ ጨዋታዎችን መጫዎት፣ የህዝብ መዝሙር መዘመርና ባንዲራ መስቀል፣ ወደ ክፍል መግባት			
2:30-2:55	**ክፍለ ጊዜ 1፡ መዝሙር** ርዕስ፦ ልጆች እንተዋዎቅ	ህጻናትን ለመዝሙር ማነሳሳት፣ የመዝሙሩን አቀራረብ ዜደን ተከትለው ማዘመር፣ የመዝሙሩን ፍሬ ነገር መንገር	ለመዝሙር ዝግጁ መሆን፣ መዝሙሩን መስማት፣ ተከትለው መዘመር፣ ለብቻ መዘመር፣	-መንገር -ማሳየት -መዘመር	- የሰው ስዕል - ቴፕ/ሞባይል/ጂፓስ	- የቃል ጥያቄ

			የመዝሙሩን ፍሬ ሀሳብ ስጠየቁ መንገር			
3:00-3:25	**ክፍለ ጊዜ 2: ተረት** ርዕስ፦ ጎበዟ መሰረት	ህጻናትን ለተረቱ ማዘጋጀት፣ ተረቱን ባህላዊ የአቀራረብ ስልት ጠብቀው ማቅረብ፣ ከተረቱ ላይ ጥያቄዎን መጠየቅና የተረቱን ፍሬ ሀሳብ በቃል መንገር	ተረቱን ለመስማት መዘጋጀት፣ ተረቱን ተቀባይ ሆነው መስማት፣ ጥያቄዎችን መመልስና የተረቱን ፍሬ ሀሳብ መከታተል	- መተረክ - ማብራራት - ውይይት	-ውሃ -ሳሙና/አመድ/እንዶድ -የሴት ልጅ ስዕል	- የቃል ጥያቄ
3:30-3:55	**ክፍለ ጊዜ 3: የተግባር ሥራ** ርዕስ: የራስ ስዕል መሳል	ቁሳቁስ ማቅረብ፣ የዕለቱን ተግባር ማስተዋወቅ፣ የራስ ስዕል ስለው ማሳየት፣ ህጻናት ራሳቸውን እንዲስሉ ማበረታታት	ቁሳቁሱን መቀበል፣ ትዕዛዝ መከተል፣ የመምህን ሥራ በትኩረት መከታተል፣ የራስ ስዕል መሳል	- መንገር - ማሳየት - መሳል	- እርሳስ - ወረቀት - ላጲስ	- ምልከታ - የቃል ጥያቄ - ገለ-ማህደር ማደራጀት
4:00-4:15	**የእረፍት ሰዓት**	ህጻናት አየር እንዲወስዱ ማድረግ	ወደውጭ ወጥተው ተንፈስ ብለው መመለስ			
4:15-4:40	**ክፍለ ጊዜ 4: የተግባር ሥራ** ርዕስ: የስሜት ህዋሳትን መቁጠር	የስሜት ህዋሳት ስዕል ማቅረብ፣ የዕለቱን ተግባር ርዕስ ማስተዋዎቅ፣ የተወሰኑ የስሜት ህዋሳትን ከስዕሉ ላይ መጥራት፣ ህጻናት ተራ በተራ እየተነሱ ከስዕሉ	የሚቀርበውን ስዕል መመልከት፣ የዕለቱን ተግባር ርዕስ መተዋዎቅ፣ መመሪያዎችን መከተል፣ እየተነሱ የስሜት ህዋሳትን	- ገለጻ - ማሳየት - ውይይት	- የስሜት ህዋሳት ስዕል/ቻርት - የእጅ ጣቶች	- ምልከታ - የቃል ጥያቄ

		ላይ የስሜት ህዋሳትን በስም እየጠሩ እንዲጠሩ ማድረግ	ስም መጥራትና መቁጠር			
4:45-5:10 5:15-5:40	**ክፍለ ጊዜ 5፡ የክፍል ውጭ ጨዋታ** ርዕስ፡ ድምጽ ማውጣት					
5:45-6:00	የመሸኛ ጊዜ	ህጻናት ቁሳቁሳቸውን መያዛቸውን ማረጋገጥ፣ ተጠባብቀው ከክፍል እንዲወጡ ማድረግ፣ እንስከበር ድረስ መውሰድና ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር ማገናኘት	ቁሳቁሳቸውን መሰብሰብ፣ በሥርዓት ከክፍል መውጣት፣ ከወላጅ ጋር መገናኘትና መምህራቸውን መሰናበት			

የር/መ/ር አስተያየት:______________________________

ስም: ________________ ፊርማ: ________________ ቀን: ________________

የራስ ግምገማ:

ጠንካራ ጎኖቼ: ______________________________

____

ማሻሻል ያለብኝ: ______________________________

____